የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት


Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Wubet Getachew

www.ehrc.org

## ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተላከ

ከሰኔ 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# የኢትዮጵያ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት

## ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም.

ማውጫ

ምኅጻረ ቃላት ..... 5
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የከተማ ጽሕፈት ቤቶች (ካርታ) ..... 7
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኮሚሽነሮች ..... 8
የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር መልዕክት ..... 9
ክፍል 1 ..... 12
አንኳር ጉዳዮች ..... 13
በሕይወት የመኖር መብት ..... 13
ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 6/2015 አተገባበር ጋር የተያያዘ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ . 14
የነጻነትና ሌሎች የፖለቲካ መብቶች ..... 15
በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሰሩ) ሰዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ..... 17
የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች ..... 19
ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ..... 20
የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ..... 21
የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን መብቶች ..... 23
የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና የፍልሰተኞች መብቶች ..... 23
አሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችን ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ..... 26
ምክረ ሐሳቦች ..... 27
መልካም እመርታዎች ..... 28
ክፍል 2 ..... 30
በሕይወት የመኖር መብት ..... 32
የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 አተገባበር ጋር የተያያዘ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ... 40
የነጻነት እና የፖለቲካ መብቶች ..... 46
በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች አያያዝ ..... 53
አጠቃላይ ምልከታ ..... 53
ከፋይናንስ እና አስተዳደር ጋር የተያያዘ ..... 55
የተጠርጣሪዎች እና የታራሚዎች መብቶች ..... 58
ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች ..... 62
አጠቃላይ ምልከታ ..... 62
ሌሎች መብቶችን የተመለከቱ ..... 65
ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ..... 68
አጠቃላይ ምልከታ ..... 68
የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ..... 76
የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ..... 81

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች.......... 86
የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች.......... 86
ስደተኞች እና ጥገኝነት ፈላጊዎች.......... 93
ፍልሰተኞች.......... 95
ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ.......... 99
የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ከማጽደቅ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ 99
የሰብአዊ መብቶችን ሪፖርት ከማቅረብ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ.......... 102
ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ ከማካተት (Domestication) አንጻር ያለችበት ሁኔታ.......... 108
ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ከመፈጸም አንጻር ያለችበት ሁኔታ.......... 109
ምክረ ሐሳቦች እና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች.......... 115
ክፍል 3.......... 120
አባሪ 1፡ የሕግ ማዕቀፍ እና አጠቃላይ ማብራሪያ.......... 120
የሕግ ማዕቀፍ.......... 121
ሥነ-ዘዴ.......... 122
የመረጃ አሰባሰብ ሥነ-ዘዴ ውስንነቶች.......... 123
አባሪ 2 ፡.......... 124
ኢሰመኮ ከ 2012 እስከ 2016 ዓ.ም. ያስመዘገባቸው ውጤቶች አጭር ገለጻ.......... 124
አባሪ 3፦ የምስል ምንጮች.......... 132


# ምኅጻረ ቃላት

| | |
|---|---|
| ዓ.ም. | ዓመተ ምሕረት |
| ጽ/ቤት | ጽሕፈት ቤት |
| ቅ/ጽ/ቤት | ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት |
| ፍ/ቤት | ፍርድ ቤት |
| ም/ቤት | ምክር ቤት |
| ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ |
| ኢሰመኮ | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን |
| ተ.መ.ድ. | የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት |
| እ.ኤ.አ. | እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር |
| ሕወሓት | ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ |
| አብን | የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ |
| ኢዜማ | የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ |
| ቤህነን | የቤኒሻንጉል ህዝቦች ነጻነት ንቅናቄ |
| መኢአድ | የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትን |
| ኦነግ | የኦሮሞ ነጻነት ግንባር |
| ብ/ብ/ሕ | ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች |
| ፖ/ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ |
| SDG | Sustainable Development Goal (ዘላቂ የልማት ግቦች) |
| CCPR-OP1-IC | Optional Protocol to the International Covenant on Civil and Political Rights (የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አማራጭ ፕሮቶኮል) |

| | |
|---|---|
| CRC-OP-IC | Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child (የሕፃናት መብቶች ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል) |
| OAU | Organization of African Unity (የአፍሪካ አንድነት ድርጅት) |
| CEDAW | Convention on the Elimination of All forms of Discrimination against Women (በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት) |
| CRC | Convention on the Rights of the Child (የሕፃናት መብቶች ስምምነት) |
| ICCPR | International Covenant on Civil and Political Rights (የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን |
| ICESCR | International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights (የኢኮኖሚ ፣የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን) |
| CAT | Convention against Torture (የፀረ ኢሰብአዊ አያያዝ ስምምነት) |
| CERD | Convention on the Elimination of Racial Discrimination (አድሎአዊ የዘር ልዩነቶች ለማስቀረት የተቋቋመ ስምምነት) |
| CRPD | Convention on the Rights of Persons with Disabilities (ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት) |
| UPR | Universal Periodic Review) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሁሉ-አቀፍ የግምገማ መድረክ |
| UNFPA | United Nations Population Fund |

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የከተማ ጽሕፈት ቤቶች (ካርታ)




**መቐለ**
Female: - | Male: -
በመዋቀር ላይ | –

**ሰመራ**
Female: 5 | Male: 13
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 18

**ባሕር ዳር**
Female: 9 | Male: 21
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 30

**አሶሳ**
Female: 4 | Male: 15
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 19

**አዲስ አበባ**
Female: 106 | Male: 97
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 203

**ጅግጅጋ**
Female: 9 | Male: 12
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 21

**ጋምቤላ**
Female: 4 | Male: 16
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 20

**ጅማ**
Female: 9 | Male: 19
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 28

**ሃዋሳ**
Female: 9 | Male: 20
ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት | 29

## የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኮሚሽነሮች



**ዶክተር ዳንኤል በቀለ**
ዋና ኮሚሽነር



**ራኬብ መሰለ አበራ**
ምክትል ዋና ኮሚሽነር



**ዶክተር አብዲ ጅብሪል አሊ**
ሲቪል፣ፖለቲካዊ እና ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ መብቶች ኮሚሽነር



**ርግበ ገብረሐዋሪያ ሐጎስ**
የሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች
መብቶች ኮሚሽነር

# የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር መልዕክት

*ይህ ለሦስተኛ ተከታታይ ዓመት የቀረበው ዓመታዊ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት፣ ኢሰመኮ በተቋቋመበት አዋጅ መሠረት የዋና ኮሚሽነር የአንድ የሥራ ዘመን ማብቂያ ጋር የተገጣጠመ በመሆኑ፣ ይዘቱን በተወሰነ መልኩ ለየት በማድረግ ኢሰመኮ ባለፉት አምስት ዓመታት ያካሄዳቸውን ለውጦችና ያስመዘገባቸውን አንኳር ውጤቶች በተመለከተ አጭር ገለጻ በአባሪነት አካቷል። ከ2011 እስከ 2016 ዓ.ም. የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትንና ውጤቶቻቸውን የሚያሳየው አጭር ገለጻ የመቋቋምያ አዋጁን ከማሻሻል ጀምሮ ከጠንካራ የግምገማ ሂደት በኋላ የሚሰጠውን የዓለም አቀፉ የብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጥምረት (Global Alliance of National Human Rights Institutions (GANHRI)) የደረጃ "A" Status Accreditation (አንደኛ ደረጃ) ዕውቅና የማግኘቱ ሂደት ድረስ ያለፈበትን ሂደትና ተቋማዊ ነጻነትን እና ዐቅምን በማረጋገጥ ረገድ የተከናወኑ ሥራዎችን ያሳያል። በመቀጠልም ብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋም እንደመሆኑ የተጣለበትን የሰብአዊ መብቶችን ትምህርትና ማስፋፋት፣ የክትትል፣ የምርመራ፣ የውትወታ እና ከሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ተቋማትና ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን የመፍጠርና የማጠናከር ኃላፊነቶች አንጻር ቁልፍ የሆኑ ክንዋኔዎችን አካቷል።*



**ዶክተር ዳንኤል በቀለ**
ዋና ኮሚሽነር

*Daniel Bekele*

*ጠቅለል ባለ መልኩ የተመላከቱት እነዚህ ክንዋኔዎች አንድም ኢሰመኮ ውስጣዊ የሆኑ ወይም የሚንቀሳቀስበት የሕግ ማዕቀፍ፣ የተቋሙን መዋቅር፣ የሰው ኃይልና የሀብት ዐቅም እንዲሁም ሌሎች የተቋም ማሻሻያ ሥራዎች በሚያከናውንበት ወቅትም ጭምር ለወቅታዊው ሀገራዊ ዐውድና ክስተቶች ምላሽ ለመስጠት የተቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረጉን የሚያረጋግጡ ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ኢሰመኮ በአሁኑ ወቅት ያለውን አቋምና አቅም የኢሰመኮ የአምስት ዓመታት የተቋማዊና የሰብአዊ መብቶች ሥራዎች ድምር ውጤት መሆኑንና አንዱ ከሌላው ክንዋኔ ወይም ውጤት ሊነጣጠል ወይም ሊቀነስ ወይም ሊዘገይ እንደማይችል፤ ይልቁንም ኢሰመኮ የብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ሊያሟሏቸው የሚገባቸውን መስፈርቶችና ሊወጧቸው የሚገባቸውን ግዴታዎች በተሟላ መልኩ እንዲወጣ ሊያደርገው ያስቻለው አሠራር መሆኑን አመላካች ነው።*

*ኢሰመኮ እነዚህን ተግባራት ያከናወነባቸው ያለፉት አምስት ዓመታት የነበረው ሀገራዊ ዐውድ የጦርነት፣ የትጥቅ ግጭት፣ የተካረረ የፖለቲካና የአመለካከት ልዩነቶች፣ ከፍተኛ የሀገር ውስጥ መፈናቀልና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የደረሰበትና የሰብአዊ መብቶች ቀውስ ሊባል የሚችል ሁኔታ የነበረበት ነው። በዚህ ዐውድ ውስጥም ቢሆን ባለመዘናጋት ተቋሙ አሁን ላለበት ደረጃ እንዲበቃ ሰፊውን ድርሻ ለተወጡት ሁሉንም የኢሰመኮ ሥራ ባልደረቦቼና የሙያ አጋሮቼ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። በእርግጥም የኢሰመኮ የአምስት ዓመታት ጉዞም ሆነ ተቋሙ ወደፊት የሚያስገኛቸው ውጤቶችና መሻሻሎች መካከል ዋነኛው "ሰብአዊ መብቶች ባህል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት" የሚለውን ራዕይ አምነውበት፣ ተቀብለው፣ ይህንኑ ለማሳካት የበኩላቸውን ሁሉ አስተዋጽዖ ለማድረግ በማለት ኢሰመኮን የተቀላቀሉ ባለሞያዎቹ ናቸው።*

ሆኖም በዋነኛነት በፋይናንስ ዐቅም ማነስና ተያያዥ ምክንያቶች ሳቢያ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እና በሁሉም የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ተደራሽ ሊሆን ባለመቻሉ፣ እንዲሁም የተቋም ማጠናከር ሥራ የማያቋርጥና በተለያዩ ወቅቶች ያሉትን ሀገራዊና ዓለምአቀፍ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዐውድ የተከተለ ሊሆን የሚገባ በመሆኑ ኢሰመኮ በእነዚህ አምስት ዓመታት ማስገኘት የቻላቸውን ለውጦች እኔም ሆነ የኢሰመኮ ባልደረቦቼ በታላቅ ትህትና የምንመለከተው እንጂ፣ የተገባደደ ሂደት አድርገን የምንቆጥረው አይደለም።

ምንም እንኳን ባለፉት አምስት ዓመታት በሀገር አቀፍ ደረጃ በነበረው እጅግ አዳጋችና በተግዳሮት የተሞላ ወቅትም ቢሆን ነጻና ገለልተኛ እንዲሁም ዓለምአቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟላ ብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋም መመሥረት መቻል ለወቅታዊውም ሆነ ለረዥም ጊዜው ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ፋይዳ ያለው ቢሆንም፣ እንዲሁም ስለሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በርካታ አወንታዊ እመርታዎች እና አበረታች እርምጃዎች ቢኖሩም፤ በአንጻሩ በተለይ በፖለቲካ ቀውስና በግጭት ዐውድ በተከሰቱ መጠነ ሰፊ ችግሮች ምክንያት ከሰብአዊ መብቶች ቀውስ አዙሪት ለመውጣት አልተቻለም። የኢሰመኮን የ2011 እስከ 2016 ዓ.ም. ሂደትና ክንዋኔዎች የሚዳስሰው ገለጻ ዘላቂነትን በማረጋገጥ ረገድ የሚቀሩ ሥራዎችን መደምደሚያ ያደረገው በዚህ ምክንያት ነው።

ከዚህ አኳያ ኢሰመኮ ወቅታዊ ለሆኑ ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታዎችና ጉዳዮች ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ መስጠት የሚችልና አስፈላጊና (relevant) ተደራሽ (accessible) እንዲሆን ከማድረጉ የማያቋርጥ ሥራ ጎን ለጎን፣ የሰብአዊ መብቶች ሥራውን ማስፋፋትና ማጠናከር ይገባል። በተለይም በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ እና የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ቀጣይ ሂደቶች ለሚቀጥሉት ዓመታት የሚካሄዱ በመሆኑ፣ እንዲሁም አጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታውን በማሻሻል ረገድ ሊኖራቸው በሚችለው ከፍተኛ ፋይዳ እና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች ባሳተፈ መልኩ ሊካሄዱ የሚገቡ በመሆናቸው፣ ኢሰመኮ በተለይም በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ አስፈላጊነትና ፋይዳ በተመለከተ ምክረ ሐሳብ ከማቅረብ ጀምሮ እስከ ፖሊሲው መጽደቅ ድረስ ባለው ሂደት ባከናወናቸው በርካታ የውትወታና የድጋፍ ሥራዎችን የከወነበት ጉዳይ በመሆኑ፣ በሁሉም የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው አተገባበርና ተያያዥ ሂደቶች የሚያደርገውን የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ድጋፍ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

በእርግጥም ኢትዮጵያ ከምትገኝበት የግጭት አዙሪት ዐውድ ለመውጣትና በዚሁ ዐውድ ለደረሱ መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በዘላቂነት እልባት ለመስጠት ከሰላማዊ መንገድ፣ ከውይይት፣ ከምክክር እና ከሽግግር ፍትሕ ሂደት ውጪ በአህጉራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኝ ሌላ አማራጭ የለም። ይልቁንም በዓለም አቀፍ ደረጃ ልምድም ቢሆን የሽግግር ፍትሕ ሂደት ፍጹማዊና ለችግሮቻችን በሙሉ አስማታዊ ምላሽ ሊሰጥ የማይችል ሂደት ቢሆንም፣ ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ፣ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችንና የሰብአዊ መብቶች መርሖችን የተከተለ እርስ በርሳቸው የተያያዙና የሚደጋገፉ መሠረታዊ የሆኑ እውነትን ማፈላለግ፣ ተጠያቂነትን ማስፈን፣ ለተጎጂዎች ማካካሻ መስጠት፣ እና ጉዳቶች/ጥሰቶች እንዳይደገሙ ዋስትና ለመስጠት የሚወሰዱ ተቋማዊና ሌሎች ማሻሻያዎች ማድረግን የሚያስችል የሽግግር ፍትሕ ሂደት ጠቀሜታና ፋይዳ በተመለከተ ያለው አረዳድና እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል።

የሽግግር ፍትሕ ሂደት ተዓማኒና ቅቡልነት ባለው መንገድ ለመተግበር የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠርና ሰላምና ደኅንነት ለማረጋገጥ በዋነኛነት በመንግሥት በኩል መከናወን ካለባቸው ተግባራት ጎን ለጎን፣ ለሲቪክ ማኅበራት፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በሀገሪቱ በተለያዩ ክፍሎች በሚካሄዱ የትጥቅ ግጭቶች ተሳታፊ ለሆኑ ወገኖች፣ ለሚድያ አባላት እንዲሁም የሀገሪቱ

የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ይመለከተኛል ለሚሉ ሁሉም ወገኖች፣ ለሽግግር ፍትሕ ሂደቱ በቀና መንፈስ ዕድል እንዲሰጡ በትህትና ጥሪ የማቀርበው በዚሁ መንፈስ እና እምነት ነው።

በመጨረሻም ሀገራዊውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተመለከተ በዚህ ዝርዝር ዓመታዊ ሪፖርት ከተካተቱ በርካታ ጉዳዮች እና ለአስከፊው የትጥቅ ግጭት ሰላማዊ መፍትሄ ከመሻት በተጨማሪ ሁለት ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ብዬ የምላቸውን ጉዳዮች ለማንሳት እወዳለሁ።

የመጀመሪያው አሳሳቢነቱ እጅግ እየጨመረ የመጣውን የኢኮኖሚ ሁኔታ ይመለከታል። በተለይም በትጥቅ ግጭቶች ሳቢያ ከደረሱ የመተዳደሪያና የንብረት ማጣት፣ የምርታማ አካባቢዎች ምርት መቋረጥና መስተጓጎል፣ ከመሠረተ ልማቶች መውደምና ያልተጀመሩ ወይም የተጓተቱ የመልሶ መቋቋም ሂደቶች ሳቢያ በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብትና በሌሎች የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ በበርካታ ሰብአዊ መብቶችን ላይ አሳሳቢ አደጋ ጥሏል።

ሁለተኛው በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሕፃናት ከትምህርት ውጪ የሆኑበትን ማኅበራዊ ቀውስ አደጋ ይመለከታል። በትጥቅ ግጭት የተነሳና እንዲሁም በተለይ በዘንድሮ በጀት ዓመት ይበልጥ ጎልቶ በታየው የመንግሥት የፋይናንስና የበጀት እጥረት በትምህርት አገልግሎት ያስከተለው ጉዳትና በመቶዎች የሚቆጠሩ የትምህርት ተቋማት አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸው የሚታወቅ ነው። እነዚህ ተያያዥ የሆኑ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አሁን ከሚያስከትሉት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በተጨማሪም፣ መጪውን ትውልድና የሀገሪቱን የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ጭምር አሉታዊ ተጽዕኖና ጉዳት የሚያደርሱ፣ እንዲሁም ተደራራቢ የሆኑ እጅግ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቁ ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውሶችና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያስከትሉ ናቸው።

ስለሆነም ኢሰመኮ በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ዘርፍ የሚያካሂደውን ሥራ እንዲያጠናክርና እንዲያጎለብት፣ በተለይም የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በጤና እና በትምህርት መብቶች ረገድ ከፍተኛ ትኩረትና የችግሩን ደረጃ የሚመጥን እርምጃ እንዲወስዱ፣ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፉ የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቀርባለሁ።

WWW.EHRC.ORG

# ክፍል ፩



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Genechu Fikadu

# አንኳር ጉዳዮች

ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ያለውን ጊዜ የሚሸፍነውና ለሦስተኛ በጀት ዓመት በዚህ መልኩ ተጠናቅሮ ይፋ የተደረገው ይህ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ዓመታዊ ሪፖርት ኮሚሽኑ ባደራጃቸው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች እና የከተማ ጽሕፈት ቤቶች አማካኝነት በተሰበሰበ መረጃ መሠረት ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ጠቅለል ባለ መልኩ የሚዳስስ ነው። ሪፖርቱ ኢሰመኮ በለያቸውና በሚሠራባቸው የትኩረት ዘርፎች (Thematic Areas) ላይ መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ በሪፖርቱ ውስጥ በዝርዝር ከተተነተኑት አንኳር ጉዳዮች መካከል የተወሰኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በሪፖርት ዘመኑ ከተመዘገቡ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ማሻሻል የሚያስችሉ ቁልፍ ክስተቶች እና እመርታዎች መካከል በዋናነት በሰሜን ኢትዮጵያ ለሁለት ዓመታት ሲካሄድ የቆየው ጦርነት በደቡብ አፍሪካ በጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕዋሓት) መካከል የዘላቂ ተኩስ ማቆም ስምምነት መፈረሙ እና ይህን ተከትሎም በፌዴራል መንግሥት የፍትሕ ሚኒስቴር አማካኝነት በተደራጀው የባለሙያዎች ቡድን ተዘጋጅቶ በተለያየ ሂደቶች ያለፈው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. መጽደቁ በዋነኝነት ይጠቀሳል።

## በሕይወት የመኖር መብት

በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክልሎች የትጥቅ ግጭቶች፣ ጥቃቶች ወይም የጸጥታ መደፍረሶች ሁነቶች ከሐምሌ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ግንቦት ወር 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ድረስ የተመዘገቡ ሲሆን፣ በዚህ ሳቢያ እና በዚሁ ዐውድ ውስጥ በታጣቂ ኃይሎች እና በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በተወሰዱ እርምጃዎች በሲቪል ሰዎች ላይ የሚደርስ የሞት እና የአካል ጉዳት አሳሳቢነት ቀጥሏል።

ኢሰመኮ በተገባደደው በጀት ዓመት በትጥቅ ግጭት ውስጥ በቆዩ የአማራ ክልል እና በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ያካሄዳቸው ክትትሎች እና ምርመራዎች መሠረት በተለይም በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ በሲቪል ሰዎች ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንደቀጠሉ፣ ብሎም እየተስፋፉ መምጣታቸውን የሚያመላክቱ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው። በተለይም ግንቦት 20 ቀን 2016 ዓ.ም. ይፋ ባደረገው ሪፖርት ከሕግ ውጪ በተፈጸሙ ግድያዎች፣ ሲቪል ሰዎችን ያልለዩ ወይም በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች እና አሳሳቢነቱ እየጨመረ በመጣ እና በሲቪል ሰዎች ላይ በሚደርሱ እገታዎች ላይ በማተኮር፣ በአማራ ክልል በሰሜን፣ በምዕራብ እና በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ እንዲሁም በባሕር ዳር ከተማ እና አቅራቢያ አካባቢዎች፣ በደቡብ ጎንደር ዞን እና በሰሜን ሸዋ እና በኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሸዋ፣ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ በምዕራብ ጉጂ ዞን እና በምዕራብ አርሲ ዞን የትጥቅ ግጭት ከተካሄደባቸው አካባቢዎች መካከል መሆናቸው ተመላክቷል። በተለይም ከኅዳር ወር እስከ ሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በተከሰቱ ሁነቶች ላይ ያተኮሩት እነዚህ የምርመራ ግኝቶች በትጥቅ ግጭት ወቅት በሚደርሱ እና በግጭቶቹ ተሳታፊ በሆኑ ሁሉም ኃይሎች በሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አብዛኛዎቹ/ዋነኛ ተጎጂዎች ሲቪል ሰዎች የሆኑ የአካባቢዎቹ ነዋሪዎች መሆናቸውን የሚያመላክቱ ናቸው። በትጥቅ ግጭቱ ሳቢያ በሚከሰቱ እና ለተለያየ ጊዜያት በሚቆዩ የእንቅስቃሴ ገደቦች፣ ውጥረቶች እና ሌሎች ተዘዋዋሪ ችግሮች ሳቢያ በአካባቢው ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃዮች፣ ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ለምግብና ለመሠረታዊ ሰብአዊ ድጋፍ እጥረት፣ ለጤና እና ትምህርት አገልግሎቶች መስተጓጎል ወይም መቋረጥ እና ለሌሎች ተጨማሪ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ አድርጓል።

በትጥቅ ግጭቱ ወቅት ሲቪል ሰዎችን ባልለዩ እና በአየር እና በሌሎች ከባድ መሣሪያዎች በታገዙ ወታደራዊ ጥቃቶች (military actions) በነዋሪዎች ላይ የሞት እና የአካል ጉዳት የደረሰ ሲሆን፣ በአብዛኛው የመኖሪያ ቤቶች እና ከብቶች እና ሰብሎችን ጨምሮ የመተዳደሪያ ንብረቶች ወድመዋል፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ነዋሪዎች ለመፈናቀል እንዲገደዱ አድርጓል፡፡

በትጥቅ ግጭት ወቅት፣ በግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች ግጭት በሌለበት ወቅት ጭምር የሚፈጸሙ ከሕግ ውጪ የሆኑ የሲቪል ሰዎች ግድያዎችም አሳሳቢ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በትጥቅ ግጭት ውስጥ የሚሳተፉ የታጠቁ ኃይሎች በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችን እና በሲቪል ሰዎች ላይ ከሕግ ውጪ የሆኑ ግድያዎችን የሚፈጽሙ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ በሁለቱም ክልሎች በሲቪል ሰዎች ላይ በትጥቅ ግጭቱ እንዲሁም በግጭቱ ዐውድ ውስጥ ከሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በተጨማሪ ሲቪል ሰዎችን ዒላማ ያደረጉ እገታዎች አሳሳቢነት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑ በዝርዝር ሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

## ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 6/2015 አተገባበር ጋር የተያያዘ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ

በበጀት ዓመቱ በሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ካሳደሩ ሁነቶች መካከል ከሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ለአስር ወራት ተፈጻሚ ሆኖ የቆየው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ (ቁጥር 6/2015) ነው፡፡ ኢሰመኮ በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 6 (12) በተሰጠው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ሰብአዊ መብቶችን የመከታተል ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ አተገባበር ጋር ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታም ውስጥ ቢሆን የጸጥታ እና የፍትሕ አካላት በሰብአዊ መብቶች እና ሕገ መንግሥታዊ መርሖች እንዲመሩ፣ በማናቸውም ሁኔታ ሊገደቡ የማይችሉ መብቶች ሊከበሩ እንደሚገባ፤ እንዲሁም ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈጻጸም ጋር የሚወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች የጥብቅ አስፈላጊነትን፣ የተመጣጣኝነትን፣ ከአድሎ ነጻ የመሆንን እና የሕጋዊነትን መርሖች ጨምሮ በሰብአዊ መብቶች መርሖች እና ድንጋጌዎች ሊመሩ እንደሚገባ በማስታወስ ኢሰመኮ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካሎች በሰጠው ምክረ ሐሳብ፣ እንዲሁም ለሕዝብ ይፋ ባደረጋቸው ሰነዶች ማሳሰቡ የሚታወስ ነው፡፡ ኢሰመኮ በተለይም ለምክር ቤቱ በላከው የሰብአዊ መብቶች ትንታኔ እና ምክረ ሐሳብ ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታው ጥብቅ አስፈላጊነትና ተመጣጣኝነት በተጨማሪ የፓርላማው ክትትል አስፈላጊነትን፣ የዳኝነት ነጻነትና ዋስትና አስፈላጊነትና የኮሚሽኑን የሰብአዊ መብቶች ክትትል አስፈላጊነትን ሊያደናቅፉ የሚችሉ እርምጃዎች የሰብአዊ መብቶች መርሖችን የሚጥሱ መሆናቸውን አመልክቷል፡፡

ሆኖም ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ አተገባበር እና በዚሁ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ውስጥ በርካታ ሰዎች መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ማቆያ ቦታዎች ውስጥ ለተራዘመ እስር ተዳርገዋል፣ በርካቶች ለቀናት ወይንም ለሳምንታት ለቆየ ጊዜ ያሉበት ቦታ ሳይገለጽ/ሳይታወቅ በእስር ቆይተዋል፡፡ በተለይም ከአዲስ አበባ እና ከአማራ ክልል መደበኛ ባልሆኑ ቦታዎች ውስጥ በእስር የቆዩ ሰዎችን በተመለከተ ከቦታዎቹ የውሃ፣ የንጽሕና እና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ፣ እንዲሁም ለተለያዩ የጤና እክሎች መጋለጥ፣ ከእንግልት፣ ዘለፋ፣ ድብደባ እና ሌሎች ኢሰብአዊ አያያዝ በተመለከተ ኢሰመኮ በርካታ አቤቱታዎች ከተጎጂዎች እና ከተጎጂ ቤተሰቦች ደርሰውታል፡፡ በተለይም ሁሉንም መደበኛ ያልሆኑ ቦታዎችን በመጎብኘት ክትትል እና ምርመራ ለማድረግ ኢሰመኮ ያደረገው ጥረት በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳካ የቆየ ቢሆንም፣ የደረሱትን አቤቱታዎች እና ጥቆማዎች መሠረት በማድረግ ከሚመከለታቸው የክልል እና የፌዴራል የአስተዳደርና የጸጥታ አካላት ጋር

በመነጋገርና ውትወታ በማድረግ ሲከታተል ቆይቷል፤ ያሰባሰባቸውን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግም በተለያየ ወቅት መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል፡፡

ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ አተገባበር ጋር ተያይዞ በኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ከታሰሩ ሰዎች ውጪ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚድያ አባላት እና የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ያለ ኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ለእስር ተዳርገዋል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ተፈጻሚነት ማብቃቱን ተከትሎም ኢሰመኮ ግንቦት 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ በዚሁ አዋጅ አተገባበር ዐውድ ውስጥ በእስር ላይ የቆዩ ሰዎች እንዲለቀቁ ማድረግን ጨምሮ ወደ መደበኛው የሕግ አተገባበር ሂደት መመለስ፣ እንዲሁም በተለያዩ የክልል አካባቢዎች የተጣሉ የእንቅስቃሴ ገደቦች እንዲነሱ እና ሌሎች ማኅበረሰባዊ አገልግሎቶች እንዲመለሱ ጥሪ አቅርቧል፡፡

## የነጻነትና ሌሎች የፖለቲካ መብቶች

በቀጥታ ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ ጋር የተያያዙ ባይሆኑም በዚሁ ዐውድ ውስጥ በዚህ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ዘመን በአንድ ክስተትም ሆነ ረዘም ላለ ጊዜ በሚቆይ እና በተለምዶ ወቅታዊ ሁኔታ በመባል በሚታወቁ ምክንያቶች ሳቢያ ሰዎች ለዘፈቀደ እስር እንዲሁም ለአስገድዶ መሰወር የተዳረጉበት በርካታ ክስተቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተመዝግበዋል፡፡ አብዛኞቹ ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች ከአዲስ አበባ ሲሆኑ፣ በአማራ ክልል እና በኦሮሚያ ክልሎች ኢሰመኮ ተመሳሳይ አቤቱታዎች ደርሰውታል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ካለው የጸጥታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ፣ ‘ወቅታዊ ጉዳይ’ በሚል ምክንያት ሰዎችን በተለይ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እስር፤ በክልሉ ታጥቆ የሚንቀሳቀስ ቡድን ትረዳላችሁ በሚል ሰዎችን በጅምላ ማሰር፤ እንዲሁም የመንቀሳቀስ መብታቸውን ማገድ ይታያል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመነጋገር እና የውትወታ ሥራ በመሥራት እልባት ማስገኘት ችሏል፡፡ ለምሳሌ በአፋር ክልል፣ ሰመራ ከተማ ከነሃሴ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ አደገኛ ቦዘኔነትን ለመከላከል በሚል ከሰመራ፣ ከሎግያ ከዱብቲ እና ከሚሌ የተያዙ ቢያንስ 189 ወጣቶች እሰር ላይ የነበሩ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ ባደረገው ክትትል 93 ሰዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ተገቢውን ሂደት እንዲከታተሉ እና ቀሪዎቹ በዋስትና እንዲለቀቁ ተደርጓል፡፡ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን፣ ከ3 ወራት በላይ አሶሳ አቅራቢያ የሚገኝ የወንጀል ተጠርጣሪዎች ማቆያ የሆነ ካምፕ ውስጥ ተይዘው እንዲቆዩ የተደረጉ የትጥቅ ቡድን አባልነታቸውን የተው (በተለምዶ “የሰላም ተመላሽ” በመባል የሚጠሩ) 11 የጉሙዝ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጉሕዲን) ታጣቂ ቡድን የቀድሞ አባላት ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ባደረገው ንግግር ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው አካባቢ እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

ሆኖም በተለይም በክልሎች ውስጥ የመንግሥት ኃላፊዎችን ስም አጥፍተዋል፣ ግጭት ለማስነሳት ተንቀሳቅሰዋል በሚል የሚታሰሩ ሰዎች (በአብዛኛው በማኅበራዊ ሚድያ የሚጽፉ) አሉ፡፡ በአፋር ክልል በ2016 ዓ.ም. ለ6 ወራት ያክል በእስር ላይ የቆዩ እና በማኅበራዊ ሚድያ ላይ መንግሥትን የሚቃወም ሐሳብ አስተላልፋችኋል በሚል ምክንያት የተያዙ ሰዎች አሉ፡፡ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ከኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የክልሉ የጸጥታ እና የፍትሕ ተቋማት በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ዞኖች እና ወረዳዎች ( በዋናነት በቀቤና እና በጉራጌ፣ በምሥራቅ ጉራጌ ዞን እና በሀዲያ ዞን፣ ምሥራቅ ባደዋቾ ወረዳ) “ሕዝብን እርስ በእርስ ለማጋጨት በማሰብ፣ በክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት ስራ ኃላፊዎች ላይ ሀሰተኛ መረጃዎችን በተለያዩ ማሕበራዊ ሚዲያ ድረገጾች አማካይኝነት አሰራጭተዋል”፣ ወይም “በአከባቢዎቹ በተከሰቱ

ግጭቶች ላይም እጃቸው አለበት” በሚል ጥርጣሬ የተያዙ 244 ሰዎች በሆሳዕና ማረሚያ ተቋም እና በሌሎች የዞን እና ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች በእስር እንዲቆዩ ተደርጓል።

የመንቀሳቀስ መብትን በተመለከተ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ባለው የጸጥታ ሁኔታ ወይም በሌላ ምክንያት በሚጣሉ ገደቦች ምክንያት በተለይም በመንገድ የሚደረግን እንቅስቃሴ አዳጋች አድርጎታል። በአማራ ክልል በየኬላው በመንግሥት የጸጥታ አካላት፣ እንዲሁም በፋኖ ታጣቂ ኃይሎች አስገዳጅ ፍተሻ የሚደረግ ሲሆን፣ በሌላ በኩል በመንገድ ላይ ድንገት የተኩስ ልውውጥ ሊያጋጥም ይችላል። በዚህም ምክንያት አብዛኛው ማኅበረሰብ እጅግ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በመንገድ የሚጓዙ የትራንስፖርት አማራጮችን አይመርጥም። በትጥቅ ግጭቱ ሳቢያ በክልሉ የነዳጅ አቅርቦት ላይ የተፈጠረው እጥረት ተከትሎ፣ ነዳጅ በጥቁር ገበያ የሚሸጥ ሲሆን፣ የትራንስፖርት ክፍያን እጅግ እንዲንርና በሰዎች እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዲፈጠር አድርጓል።

በተጨማሪም በወንጀል መበራከት ምክንያት፣ እንዲሁም የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ወይም በታጣቂ ቡድኖች ለተከታታይ ቀናት ወይም ለአጭር ጊዜ የሚዘጉ መንገዶች ምክንያት የሚደርሱ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ችግሮች፣ በሸቀጦች ዋጋ እና በገቢ ላይ እንዲሁም በጤና እና ትምህርት አገልግሎቶች ተደራሽነት ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተጽዕኖዎች በዘንድሮ በጀት ዓመትም በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ እና በኦሮሚያ ክልሎችም ቀጥሏል።

ኢሰመኮ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. አስገድዶ መሰወርን እና ሰዎችን መደበኛ ባልሆኑ ማቆያ ቦታዎች መያዝን በተመለከተ [ይፋ ባደረገው ሪፖርት] እንዳሳሰበው “በመንግሥት ወኪሎች ወይም ከመንግሥት ፈቃድ ወይም ድጋፍ በተሰጣቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች ወይም በመንግሥት ስምምነት አንድን ሰው በማሰር፣ አፍኖ በመውሰድ፣ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ነጻነቱን በማጥፋትና፤ በቁጥጥር ሥር መዋሉን በመካድ፣ በመደበቅ፣ ያለበትን ቦታ ባለማሳወቅ ወይም ደብዛውን በማጥፋት ፈጽሞ ከሕግ ጥበቃ ውጪ እንዲሆን ማድረግ” አስገድዶ መሰወርን የሚያቋቁም ሲሆን፣ አስገድዶ መሰወር ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ነው።

በዚህ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ዘመን በፖለቲካ መብቶች ረገድ ዋነኛ ሁነቶች ከሆኑት መካከል ምርጫ ባልተካሄደባቸው እና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በተወሰኑባቸው የሀገሪቱ ክልሎች ምርጫ መካሄዱ ነው። ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. በ6ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ ወቅት ምርጫ ባልተካሄደባቸው የአፋር እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች፣ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግባቸው ውሳኔ በተሰጠባቸው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የመስቃን እና ማረቆ አካባቢዎች ውስጥ በሚገኙ 29 የምርጫ ክልሎች ውስጥ (ለ9 የተወካዮች ምክር ቤት እና ለ 26 የክልል ምክር ቤቶች) እና በሶማሊ ክልል የጅግጅጋ ከተማ የሚካሄዱትን የምርጫ ሂደቶች ኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች ክትትል አድርጓል።

በዚህ መሠረት ባካሄደው ክትትል ተመሥርቶ ይፋ ባደረጋቸው ግኝቶች፦

- በጸጥታ ችግር ምክንያት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫው እንዲሰረዝ ወይም እንዳይካሄድ ከወሰነበት የምርጫ ጣቢያዎች በስተቀር ምርጫው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች በተረጋጋ ሁኔታ እና አሳሳቢ የጸጥታ አደጋ እና ሥጋት ሳይደርስ መከናወኑ፤
- ምርጫ ቦርድ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመራጭነት በመሳተፍ ሂደት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ 7 ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን፣ ጉባ እና ድባጤ ወረዳዎች ያቋቋመ መሆኑ፤
- ምርጫ ቦርድ በተለይም በድምፅ መስጫው ዕለት ከኢሰመኮ ለተላኩለት አሳሳቢ ጉዳዮች ፈጣን ምላሽና የማስተካከያ እርምጃዎችን የወሰደ መሆኑን አመላክቷል።

በምርጫ ክትትል ሪፖርቱ ከተካተቱና በሂደቱ በተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ከታዩ ክፍተቶች መካከል:-

- በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ወይም በ500 ሜትር አቅራቢያ የደንብ ልብስ የለበሱ (አልፎ አልፎም የታጠቁ) የጸጥታ አካላት ታይተዋል። ምንም እንኳን የጸጥታ አካላቱ የምርጫ ጣቢያውን ጸጥታ በሚያደፈርሱ ሁኔታዎች ላይ የተሳተፉባቸው አሉታዊ አጋጣሚዎች በዕለቱ ባይመዘገቡም፤ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በግልጽ ካለተፈቀደላቸው በቀር በምርጫ ጣቢያው 500 ሜትር አቅራቢያ መገኘት አልነበረባቸውም።
- ክትትሉ በተከናወነባቸው የተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ በሕግ ከተፈቀደላቸው ሰዎች (ከመራጮች፣ ከምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ከእጩ ወኪሎች፣ ከታዛቢዎችና ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት) ውጪ የሆኑ በተለይም የቀበሌ/ወረዳ አመራሮች እና የብልጽግና ፓርቲ አባላት በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መራጮች ላይ ጫና ሊያሳድሩ በሚችሉ ድርጊቶች ላይ ሲሳተፉ መስተዋላቸው ተመላክቷል።

## በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሰሩ) ሰዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ

በ2016 በጀት ዓመት ኢሰመኮ በአጠቃላይ 306 ፖሊስ ጣብያዎችን እና 52 ማረሚያ ቤቶችን የጎበኘ ሲሆን፣ አዋሽ አርባን ጨምሮ 15 የሚሆኑ መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ቦታዎችን ጎብኝቷል። ሆኖም በተለይም በአማራ ክልል ከሚካሄደው የትጥቅ ግጭት እና ከሐምሌ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ከነበረው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ዐውድ ምክንያት በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎችን አያያዝ በተመለከተ ኮሚሽኑ የሚያደርገውን መደበኛ ክትትል ሥራ አዳጋች አድርጎት ቆይቷል።

በአማራ ክልል የአስቸኳይ ጊዜ መምሪያ ኮማንድ ፖስት ለሕዝብ ይፋ ካደረጋቸው እስሮችና ቦታዎች ውጪ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በአስቸኳይ ጊዜ ዐውድ ውስጥ በተለይም በባሕር ዳር፣ ደብረ ታቦር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ጎንደር፣ ላሊበላ፣ መካነሰላም፣ ቆቦ እና ሸዋ ሮቢት ከተሞች የተፈጸሙ የዘፈቀደ እስሮች ስለመኖራቸው ኮሚሽኑ ከታሳሪ ቤተሰቦች እና እማኞች በርካታ አቤቱታዎች ደርሰውታል። በመንግሥት የጸጥታ አካላት የሚታሰሩ ሰዎች በአብዛኛው "ለታጣቂ ቡድኑ ድጋፍ ታደርጋላችሁ" እና/ወይም «የጦር መሣሪያ ደብቃችኋል» በሚል ሲሆን፣ የተያዙ ሰዎች አያያዝ ሰብአዊነት የጎደለው መሆኑን ጠቅሰው የታሳሪ ቤተሰቦች በተደጋጋሚ ለኮሚሽኑ አቤቱታ አቅርበዋል። በሌላ በኩል በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች (በተለምዶ ፋኖ) በግጭት ዐውድ ውስጥ ወይም አካባቢዎቹን ተቆጣጥረው በቆዩበት ጊዜ ማረሚያ ቤቶችን እና ፖሊስ ጣቢያዎችን በማጥቃት ታራሚዎችንና ታሳሪዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማስለቀቃቸውንም የሚያመለክቱ በርካታ ጥቆማዎች ለኮሚሽኑ ደርሰዋል።

በሁሉም ክልሎች ለማለት በሚያስችል ሁኔታ የዘፈቀደ እስር፣ የጅምላ እስር ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ባለማክበር ሰዎችን ይዞ የማቆየት፣ መደበኛ ባልሆኑ ማቆያ ቦታዎች ሰዎችን የመያዝ ተግባራት የተፈጸመ ቢሆንም፣ በተለይ ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባ ባሉ ማቆያ ቦታዎች እና ከአዲስ አበባ ተይዘው ወደ አዋሽ አርባ መከላከያ ካምፕ እና ሌሎች መደበኛ ባልሆኑ ማቆያ ቦታዎች በሚወሰዱ ሰዎች ላይ ችግሩ ተባብሶ ተስተውሏል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ ፍርድ ቤት ቀርበው የዋስትና መብታቸው የተከበረላቸው ሰዎች "በኮማንድ ፖስት ይፈለጋል፣ የበላይ ትእዛዝ ይምጣ" በሚል ሳይፈቱ ለረዥም ጊዜ በእስር ቆይተው የነበረ መሆኑ፤ በተለይም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ ከኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ውጪ በርካታ ሰዎች በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ "በወቅታዊ ጉዳይ ነው" በሚል ለረዥም ጊዜ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ቆይተው እንደነበር ታውቋል።

በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ ዐውድ ያለ ኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ በገላን ከተማ፣ በገላን አዋሽ ሲዳ ተብሎ በሚጠራው መደበኛ ያልሆነ ማቆያ ቦታ ተይዘው ከነበሩ ሰዎች ውስጥ፤ በወቅቱ በነበረው የተጨናነቀና የንጽሕና ደረጃውን ያልጠበቀ የተጠርጣሪዎች አያያዝ ምክንያት በተከሰተ ወረርሽኝ የ3 ሰዎች ሕይወት ያለፈ ሲሆን 190 ሰዎች ለሕመም ተዳርገው ሕክምና ተደርጎላቸዋል:: በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ከተማ በደጃዝማች ወንድይራድ ፣ደራርቱ ቱሉ ትምህርት ቤቶች በርካታ ግለሰቦች ሰብአዊ ክብርን ባልጠበቀ መልኩ ተይዘው የቆዩ መሆኑ እና ኮሚሽኑ ይህንኑ በተመለከተ ባደረገው ክትትል እና የውትወታ ሥራ አብዛኛዎቹ ተለቀዋል፣ ሌሎች ወደ መደበኛ ማቆያ ቦታዎች ተዛውረዋል:: በአዋሽ አርባ የሚገኘው የተጠርጣሪዎች ማቆያ በአካባቢው ባለው ከፍተኛ ሙቀት ፣ አካባቢው ታሳሪዎቹ ከሚኖሩበት አካባቢ ባለው ርቀት ምክንያት ታሳሪዎቹ በቤተሰብ መጠየቅ የማይችሉና ከሕክምና እና ሌሎች አገልግሎቶች ካለው ርቀት አንጻር በካምፑ ተይዘው የሚቆዩ ሰዎች ለሕክምና አለማግኘት እና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተዳርገዋል:: የካቲት 7 ቀን 2016 ዓ.ም. በአካባቢው በተከሰተ አውሎ ንፋስ ምክንያት በቦታው የተያዙ ሰዎች ለጉዳት እና ሕመም የተዳረጉ መሆናቸውን ለኮሚሽኑ አቤቱታዎች እና ጥቆማዎች የደረሱት ቢሆንም በአካል ተገኝቶ ለመጎብኘት ያደረገው ጥረት አልተሳካም::

ኢሰመኮ በተለይም በ2014 እና በ2015 ዓ.ም. ክትትል ባደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች ያቀረባቸው ምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም ሲከታተል እና በክልል እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከፖሊስ ጣቢያዎቹ ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም የሲቪክ ማኅበረሰቦች አባላትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት የውትወታ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል:: ክትትል በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች በርካታ መሻሻሎች ተስተውለዋል:: ኢሰመኮ በተለይም የማቆያ ቦታዎችን በተመለከተ የሚያደርገው መደበኛ ክትትል እና ያለቅደመ ማስጠንቀቂያ የማቆያ ቦታዎችን የመጎብኘት ሥራና የኮሚሽኑን ኃላፊነትን በተመለከተ የተሟላ አረዳድ በመፍጠር እንዲሁም በጎ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል::

ለምሳሌ በ2015 ዓ.ም. በተደረጉ የፖሊስ ጣቢያ ክትትሎች የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች አፈጻጸም ክትትል መሠረት በአብዛኞቹ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ከቤተሰቦቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር እንዲገናኙ የሚፈቅድ መሆኑ ወይም ክልከላ አለመኖሩ፣ በፖሊስ ጣቢያዎች ላይ በሚደረግ ክትትል አማካኝነት ያለአግባብ እስር ላይ የነበሩ በርካታ ተጠርጣሪዎች መፈታታቸው፣ በአዲስ አበባ የተወሰኑ "ሞዴል" የማቆያ ቦታዎች ተገንበተው ሥራ መጀመራቸው እና በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች (ለምሳሌ በአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ) በሚገኙ የተጠርጣሪዎች ማቆያ ክፍሎች የተጠርጣሪዎች አያያዝን ለመቆጣጠር የደኅንነት ካሜራዎች አገልግሎት ላይ መዋላቸው ሊጠቀሱ የሚችሉ መልካም እመርታዎች ናቸው:: ለምሳሌ በሶማሊ ክልል የፖሊስ ጣቢያዎችን አያያዝ በተመለከተ ድብደባና ኢ-ሰብአዊ የሆኑ የተጠርጣሪዎች አያያዝ መቀነስ፣ ለተጠርጣሪዎች የተመደበ የምግብ በጀት ባይኖርም ለፖሊስ አባላት ከሚዘጋጀው ምግብ ላይ ቤተሰብ ምግብ ለማያቀርብላቸው ተጠርጣሪዎች በተወሰነ ደረጃ ምግብ መቅረቡ፣ የቤተሰብ ጉብኝትን በተመለከተ በጣቢያዎች ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር ጥሩ መሻሻሎች መታየታቸው፣ እንዲሁም ተጠርጣሪን በ48 ሰአት ፍርድ ቤት ማቅረብ ላይ መልካም የሚባል መሻሻል እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል::

ማረሚያ ቤቶችን በተመለከተ ኢሰመኮ በማረሚያ ቤቶች ለሚያካሄደው ክትትልና ምርመራ የፌዴራል እና የክልል የማራሚያ ቤቶች አስተዳደር የሚያደርጉት ትብብር እና ድጋፍ፣ ኢሰመኮ ከፌዴራል መንግሥት እና ከክልል መስተዳደር ጋር ባደረገው ተደጋጋሚ ምክክር እና ውትወታ መሠረት በአንዳንድ ክልሎች ለታራሚዎች የሚመደበው እለታዊ የምግብ በጀት ከፍ እንዲል መደረጉ፣ እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት እንዲሁም በተወሰኑ ክልሎች

ማረሚያ ቤቶች ውስጥ በታራሚዎች፣ በማረሚያ ቤቶች አመራሮች እና አባላት መካከል ያለው መልካም ግንኙነት ተጠቃሽ ናቸው።

በተጠርጣሪዎች አያያዝ እና የሰብአዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች መካከል በዋነኝነት ከበጀት ወይም የገንዘብ አቅም እጥረት ጋር የሚያያዙት ናቸው። ይህ ችግር በሁሉም ክልሎች በተጎበኙ የፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች የተስተዋለ ሲሆን፣ በኢሰመኮ የ2014 እና በ2015 በጀት ዓመት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታዊ ሪፖርት የተመላከተ እና ኮሚሽኑ በሚያከናውናቸው የምክክር እና የውትወታ ሥራዎች ሁሉ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጉዳይ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የበጀት እጥረቱ ችግር ተጠርጣሪዎችን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት የሚዳርግ ነው። ለምሳሌ በአፋር ክልል በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች ሕጻናት ልጆች ለአካለ መጠን ከደረሱ ተጠርጣሪዎች ወይም ታራሚዎች ጋር አብረው እንዲቆዩ የሚደረግ መሆኑ፣ በጋላፊ ንዑስ ፖሊስ ጣቢያ ምንም ዐይነት የማቆያ ክፍል ያልተሠራ በመሆኑ ተጠርጣሪዎች ክፍት ሜዳ ላይ እንዲቆዩ የሚደረግ ሲሆን፣ በአፋምቦ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ እና በአርጎባ ልዩ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ደግሞ ሴት ተጠርጣሪዎች የተለየ ማቆያ ክፍል ባለመኖሩ፣ እደጅ ወይም ከማደሪያ ክፍል ውጪ እንዲያድሩ ተደርጓል።

በ2016 በጀት ዓመት ኢሰመኮ በጎበኛቸው የፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች የተስተዋሉ ሌሎች ችግሮች መካከል ከተጠርጣሪዎች መብቶች ጥበቃ/መከበር ጋር የተያያዙና አፋጣኝ መፍትሔ ሊሰጣቸው የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ ተላላፊ ሕመም ያለባቸውን ተጠርጣሪዎችን እና ታራሚዎችን በአፋጣኝ የመለየት እና ከሌሎች ተጠርጣሪዎች በተለየ ቦታ ማቆየት፣ በተመሳሳይ መልኩ የማኅበረ ሥነልቦና ጉዳት ያለባቸውን ወይም በአካል ጉዳተኝነታቸው፣ በአረጋዊነታቸው ወይም በሌላ ምክንያት ልዩ ፍላጎት /እንክብካቤ/ (special needs) ለሚያስፈልጋቸው ተጠርጣሪዎች ከአቅርቦት ጀምሮ ሌሎች አፋጣኝ መፍትሔዎችን ማፈላለግ አንዱ ጉዳይ ነው። ታራሚዎች ወደ ማረሚያ ቤት ሲዛወሩ ከሌሎች ታራሚዎች ጋር ከመገናኘታቸው በፊት መሠረታዊ ምርመራ በማድረግ እንዲሁም በእራሳቸው ወጪ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ለሚፈልጉ ታራሚዎች ይህ የሚፈቀድበት አሠራር መዘርጋትን ጨምሮ በአሠራር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን መለየት እና አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት ይገባል።

## የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች

ኢሰመኮ አዲስ አበባ በሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት እና በከተማ ጽሕፈት ቤቶቹ አማካኝነት በአካል፣ በስልክ፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜይል ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ የቀረቡለትን 1450 አቤቱታዎችን በመቀበል አስተናግዷል። ለኢሰመኮ የቀረቡት አብዛኛዎቹ ቅሬታዎች ከነጻነት፣ ፍትሕን ከማግኘት መብት እና ሌሎች የተጠርጣሪዎችና የታሳሪዎች መብቶች ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፣ ኮሚሽኑ በመደበኛ የጥበቃ ሥር ባሉ ሰዎች ክትትሎች ሥራው የሚነሱ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ናቸው። በተጨማሪም በሕይወት የመኖር መብት፣ ከመሬትና ቤት ይዞታ ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች፣ ከመሬት ይዞታ ጋር የተያያዘ ካሳ የማግኘት መብት፣ ጡረታና ከሠራተኞች መብቶች ፣ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጉዳይ እና ተንቀሳቅሶ ከመሥራት መብት ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች ቀርበዋል።

በምርመራ ግኝቶች መሠረት በተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ተፈጻሚነት ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማካሄድ እና ውትወታ በማድረግ፣ ወይም የሕግ ምክር አገልግሎት በመስጠት ወደሚመለከተው አቤቱታ የሚያስተናግደው አካል በመምራት ከ80 እስከ 90% ለሚሆኑት አወንታዊ መፍትሔዎች አስገኝቷል። የመብት ጥሰቶችን የማጣራትና መፍትሔ የማስገኘት ሂደት ውስጥ አቤቱታ የቀረበባቸው አካላት ትብብር መሻሻል በዘንድሮ በጀት ዓመትም በመልካም እመርታነት ተመልክቷል።

## ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች

በርካታ የሀገሪቱ አካባቢዎች በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያሉ ወይም በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያለፉ መሆናቸው በ2016 በጀት ዓመት አጠቃላይ የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩን ቀጥሏል። በዋነኝነት በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያሉ አካባቢዎች፣ ወይም ግጭት በየጊዜው የሚያገረሽባቸው ወይም በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያለፉ አካባቢዎች፣ በአንዳንድ ሁኔታዎችም በተፈጥሮ አደጋ ወይም በድርቅ ምክንያት የምርታማነት ወይም የማምረት ተግባር መቀዛቀዝ ብሎም ማቆም በክልሎቹ ወይም በአካባቢዎቹ ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ መሠረታዊ የሆኑ የምግብ ፍጆታዎች ላይ የዋጋ ንረት ያስከተለ፣ እንዲሁም በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች አስቸኳይ የምግብ እና የሰብአዊ ድጋፍ እንዲፈልጉ አድርጓል።

በጥር 23 ቀን 2016 የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) የሰብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት (UNOCHA) በጣምራ ባወጡት መግለጫ እንደተመለከተው እስከሚቀጥለው 2017 በጀት ዓመት መባቻ ድረስ አጠቃላይ እጅግ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸው (critically food insecure) ሰዎች ቁጥር 10.8 ሚልየን ደርሷል። እነዚህም በተለይም በአፋር፣ በአማራ፣ በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚገኙ መሆናቸውንም በወቅቱ ገልጸው ነበር።

የትጥቅ ግጭቱ ሌላኛው ተጽዕኖ በጤና መብት ላይ ሲሆን ይህም የእንቅስቃሴ ገደቡ፣ የሰዎች መፈናቀል፣ የመሠረተ ልማት ውድመት ተደራራቢ ውጤት፣ እንዲሁም ከባለሞያዎች ወደ አንጻራዊ ሰላም አካባቢዎች መሄድ፣ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የመድኃኒት አቅርቦት ሁኔታ እና የመድኃኒት ዋጋ እንዲሁም በግጭት ባሉ አካባቢዎች በሚከሰተው የባለሞያዎች እጥረት ምክንያት የሚከሰት የጥራት እና አገልግሎት መቀነስ/ማሽቆልቆል ጋር የሚዳመር ነው። ይህ ሁኔታ በሁሉም በግጭት ውስጥ ያለፉ አካባቢዎች ያሉባቸው ክልሎች የሚታይ ሁኔታ ሲሆን፣ በተለይም በትጥቅ ግጭት ወቅት ሴቶችን፣ ሕፃናት እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በጤና አገልግሎት መቋረጥ ሳቢያ ተጋላጭነታቸው እንዲጨምር ያደርጋል።

በግጭቶች በቆዩ አካባቢዎች ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለው የጤና አገልግሎት እና አቅርቦት ደረጃ አፋጣኝ እና የተቀናጀ ትኩረት የሚሻ ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በጥር ወር 2016 ዓ.ም. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አምስት ወራት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የወባ በሽታ በምርመራ የተገኘባቸው ሰዎች ቁጥር፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር "ከፍተኛ" መሆኑን ማሳወቁ የሚታወስ ነው።

በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል በግጭት ያሉ እና በግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች የጸጥታ እና የኢኮኖሚያ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ ወይም መቆም በአዋሳኝ ክልሎች ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ለምሳሌ በአፋር እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የጤና እና የምግብ ሸቀጦች እጥረት እንዲሁም ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ አሳይቷል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ3 እስከ 4 ሚልየን የሚቆጠሩ ሕፃናት በተለያዩ ምክንያቶች ከትምህርት ውጪ እንደሆነ እንደሚገመት የትምህርት ሚኒስቴር በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለምአቀፉ የሕፃናት አስቸኳይ ፈንድ (UNICEF) ይፋ ያደረገው ሪፖርት ከትምህርት ውጪ የሆኑ ሕፃናት ቁጥር በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ 8 ሚልየን እንደሚጠጋ ያመለክታል። በአንጻራዊ ሰላም ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች የትምህርት አገልግሎትን ለማስጀመር ወይም መልሶ ለማቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎች ቢኖሩም በዋነኝነት በገንዘብ አቅም ማነስ አቅርቦቱ/አገልግሎቱ የተሟላ እንዳይሆን አድርጓል። ለምሳሌ በቤኑሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚታየው የመልሶ ማቋቋም ሥራ አበረታች

ቢሆንም ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ ባለመሆኑ በርካታ የወደሙ ትምህርት ቤቶች፤ ጤና ተቋማት አለመሥራታቸውና አግልግሎት ለመስጠት ዝግጁ አለመሆናቸው፤ እንዲሁም ጉዳት ያልደረሰባቸውና በወረዳ ማዕከላት የሚገኙ ትምህርት ቤቶች እና ጤና ተቋማት ከመንገድ መዘጋትና ከበጀት እጥረት ጋር ተያይዞ በቂ የመማሪያ መጽሐፍትና ቁሳቁስ፤ በቂ የሕክምና ቁሳቁስ እና መድኃኒት ማቅረብ አለመቻላቸው ለነዋሪዎች ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኗል።

በቂ የሆነ መኖርያ የማግኘት መብትን በተመለከተ በአዲስ አበባ እና በሸገር ከተሞች በ2016 በጀት ዓመት በተለያየ ወቅት ከተካሄዱት የቤት ፈረሳዎች ጋር ተያይዞ ከታዩት ችግሮች በተጨማሪ በግጭት ውስጥ ባሉ ወይም በቆዩ አካባቢዎች ጋር በወደሙ መኖርያ ቦታዎች ሳቢያ፣ እንዲሁም ከአቅርቦት ማነስ ጋር የተያያዙ ችግሮች ታይተዋል። ኢሰመኮ የቀረቡለትን አቤቱታዎች መሠረት በማድረግ የመኖርያም ሆነ የንግድ ቤቶችን “ለሕዝብ ጥቅም ወይም ለልማት ሥራዎች” ተግባር በማንኛውም ጊዜ ቢሆን በቅድመ ማስለቀቅ፣ በማስለቀቅ ወቅት እንዲሁም ድኅረ ማስለቀቅ ጊዜ መንግሥት ሊያሟላ የሚገባቸው የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ሊከተል እና በተገቢው የሕግ አግባብ ሊፈጸም የሚገባ መሆኑን በማሳሰብ ከሚመለከታቸው የከተማዋ አስተዳደሮችን ሲያነጋግር እና ለቀረቡ አቤቱታዎች መፍትሔ ለማስገኘት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

የሕገ ወጥ ይዞታዎችን በተመለከተም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉንም የሚመለከታቸውን የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ያቀናጀ ዘላቂ እልባት ሊሰጥ የሚችል ፖሊሲ ሊቀረጽ ይገባል።

ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ባሉባቸው በአዲስ አበባ እና በክልል ዋና ከተሞች ያለው የመኖሪያ ቤት እጥረትም ትኩረት የሚሻ ነው። ለምሳሌ በአፋር ክልል በተለይም በክልሉ በሚገኙ ትልልቅ ከተሞች ሰመራ፣ ሎግያ እና አዋሽ ሰባት ኪሎ በ2016 ከፍተኛ የሆነ የቤት ኪራይ ዋጋ ጭማሪ የታየ ሲሆን፣ በኦሮሚያ ክልል ከተሞችም እንዲሁ በተለይም በግጭት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢዎቻቸው ተፈናቅለው ወደ አንጻራዊ ሰላም ወዳለባቸው ከተሞች የሄዱ ሰዎች ብዛት ጋር ተዳምሮ፣ አልያም በአዲስ መልኩ በተደራጁ ክልሎች በዋና ከተማነት በተሰየሙ ከተሞች የሕዝብ ቁጥር ጭማሪ በመኖሩ ምክንያት የመኖሪያ ቤት እጥረት መከሰቱ እየታየ ነው።

ከበቂ የሆነ መኖሪያ የማግኘት መብት ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የሚታየው የመሠረተ ልማት አቅርቦትና በተለይም ንጹሕ ውሃ አቅርቦት ችግር ትኩረት የሚሻ ሲሆን፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ያለው የንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነው።

## የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች

በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ ባሉ አካባቢዎች በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ፣ በአማራ ክልል በትጥቅ ግጭት ውስጥ ባሉ አካባቢዎች በተለይም በመንግሥት የጸጥታ አካላት አባላት የሚፈጸሙ የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃትን ኢሰመኮ ከመንግሥት የጤና ተቋማት ጨምሮ የተገኙ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ መንግሥት በአፋጣኝ ይህ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በአፋጣኝ እንዲቆም እና የጥሰቱ ሰለባ ለሆኑ ሴቶችም ተገቢው አገልግሎቶች መቅረቡን እንዲያረጋግጥ ማሳሰቡ የሚታወስ ነው። በአማራ ክልልም ሆነ በትጥቅ ግጭት ውስጥ በቆዩ ሌሎች አካባቢዎች በግጭት ሳቢያ የደረሱ የጤና እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሰጪ ተቋማት መውደም ወይም አገልግሎት መቋረጥ እና መስተጓጎል የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች አስከፊ ሁኔታን የሚያባብስ ነው። ለተለያዩ ጊዜያት በግጭት ውስጥ በቆዩ ሌሎች ክልሎችና አካባቢዎችም የወደሙ የጤና

እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን መልሶ የማቋቋም እና አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረጉ ሥራ መዘግየት ምክንያትም የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኙ ከሚያደርጉ ምክንያቶች በመሆኑ የመልሶ ማቋቋሙ ሥራ ተገቢውን ትኩረት ሊያገኝ ይገባል፡፡

ኢሰመኮ በድኅረ ግጭት ዐውድ ባሉ በአፋር፤ በትግራይ እና በቤኒሻንጉል ክልሎች የእናቶች እና የጨቅላ ሕፃናት የጤና መብቶችን የተመለከተ ባደረገው ክትትል መንግሥት በያዘው እቅድ መሠረት የጤና ተቋማት መልሶ አለመገንባት፤ የመሠረተ ልማት ውድመት፣ የሰው ሀብት፣ የመድኃኒት፣ የክትባትና የምግብ አቅርቦት ውስንነት፣ የድጋፍና የበጀት የተገኝነት/የተደራሽነት ችግሮች ሳቢያ እናቶችና ጨቅላ ሕፃናት በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ፣ በድንገተኛ ወሊድ ወቅት ሊያገኙ የሚገባቸውን መሠረታዊ አገልግሎቶች እያገኙ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለጨቅላ ሕፃናትም በሕይወት የመኖር መብትን ተግባራዊ ለማድረግ መሠረታዊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶች በተሟላ መልኩ ተገኚ አይደሉም፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በትጥቅ ግጭት ሳቢያ የደረሱ የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሰጪ ተቋማት መውደም ወይም አገልግሎት መቋረጥ እና መስተጓጎል ወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች የደረሰባቸውን አስከፊ ጉዳትን የሚያባብስ ነው፡፡

በትጥቅ ግጭት ሳቢያ የደረሱ የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሰጪ ተቋማት መውደም ወይም አገልግሎት መቋረጥ እና መስተጓጎል ወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች የደረሰባቸውን አስከፊ ጉዳትን የሚያባብስ ነው፡፡ ለምሳሌ በ2016 ዓ.ም. ከአማራ ክልል 4 ሚልዮን የሚሆኑ ሕፃናት ከትምህርት ውጪ መሆናቸውን የአማራ ክልል መንግሥት በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. አስታውቋል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎችም የወደሙ የጤና እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን መልሶ የማቋቋም እና አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረጉ ሥራ መዘግየት ምክንያትም የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኙ ከሚያደርጉ ምክንያቶች በመሆኑ የመልሶ ማቋቋሙ ሥራ ተገቢውን ትኩረት ሊያገኝ ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ በሆኑ ምክያቶች በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሴቶች እና ሕፃናት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡

በአንጻራዊ ሰላም ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የሚያልፉ የወሲባዊ እና ጾታዊ እና ሌሎች ጥቃቶች ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን በተመለከተ ኢሰመኮ የክትትል ሪፖርት ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎችም ጭምር የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ከወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የሚያገኙት አገልግሎት የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችን እና መርሖችን በአብዛኛው ተግባራዊ ባደረገ መልኩ እንዳልሆነ አመላክቷል፡፡

በሀገር አቀፍ የጸጥታ ሁኔታውና በሌሎች ተጓዳኝ ምክንያቶች ቀደም ሲል ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚሠሩባቸው የሴቶች እና የሴት ሕፃናት ጉዳዮች ትኩረት እንዲነፈጋቸው ወይም እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት የሴቶች ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ሌሎች ጎጂ ልማዶች በብዙ ክልሎች መልሶ እያገረሸ ወይም እየተስፋፋ ስለመምጣቱ የሚያመላክቱ በርካታ መረጃዎች አሉ፡፡

በአፋር፣ በአማራ እና በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች በመንገድ ተጥለው የተገኙ አዲስ የተወለዱ ጨቅላ ሕፃናት ቁጥር ማሻቀቡን ከክልሎቹ የጸጥታ አካላት የሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይም በትጥቅ ግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች፣ እንዲሁም በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ያሉ እና ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናት እና ታዳጊዎች ብዛት በአግባቡ ለመሰነድ እና

አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ በቂ ጥረት ካለመደረጉ ጋር ተዳምሮ ይህ በመንገድ ዳር ተጥለው የሚገኙ ጨቅላ ሕፃናት ጉዳይ የሕፃናት ማሳደጊያዎችን ማቋቋም፣ ማስፋፋት እና ማጠናከርን ጨምሮ አፋጣኝ እና ተገቢውን ትኩረት የሚሻ ነው።

## የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን መብቶች

ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የጤና፣ የትምህርት፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን እና አካባቢዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከሕግ እና ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ ከሀብት ምደባ እንዲሁም ከሰው ኃይል የግንዛቤ አቅም አኳያ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰጠው ትኩረት የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶችን ድንጋጌዎችን እና መርሖችን ለማሟላት በርካታ ክፍተቶች ያሉበት ነው። ኢሰመኮ ባለፉት ሦስት ዓመታት በተለይም ቅድሚያ ሰጥቶ ክትትል ባደረገባቸው የፍትሕ፣ የትምህርት እና የትራንስፖርት ተደራሽነት እንዲሁም የአረጋውያን እንክብካቤ ማዕከላት ምቹነት ከታዩ ግኝቶች በመነሳት በሰጣቸው ምክረ ሐሳቦች የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ወጥ የሆነ እና የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ፣ እንዲሁም ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግ አስፈጻሚ መዋቅር ጨምሮ በተለይም የትምህርት፣ የፍትሕ እና የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት ከባቢያዊ፣ ተቋማዊ እና የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነትን የማረጋገጥ አስቸኳይነት እና አስፈላጊነትን በተመለከተ በተደጋጋሚ ውትወታ ሲያደርግ ቆይቷል። ከዚሁ ከተደራሽነት ጋር ተያይዞ በተለይም ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተደራሽ ለማድረግ በክልልም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን ብዛት በተመለከተ ያለው የመረጃ ክፍተት የችግሩን አሳሳቢነት ደረጃ በአግባቡ ለመረዳትም ሆነ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑን ኮሚሽኑ አመላክቷል።

በትጥቅ ግጭት ሳቢያ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች፣ እንዲሁም በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ በመሆናቸው አልያም የገቢ እና የድጋፍ ምንጫቸውን በማጣታቸው ምክንያት፣ እንዲሁም በተለይም ለተደራራቢ ተጋላጭነት የተዳረጉ ሴት አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቁጥር በሺዎች የሚቆጠር እንደሆነ የሚገመት ነው። በተጨማሪም የትጥቅ ግጭቶች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች እና መፈናቀል የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያንን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሁኔታ የሚያባብስ እና ለጥሰቱም ያላቸውን ተጋላጭነት የሚጨምር ነው። ለምሳሌ በአማራ ክልል፣ ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታና በትጥቅ ግጭቱ ሳቢያ በተወሰነው የሰዓት እላፊና የእንቅስቃሴ ገደቦች ምክንያት በተለይም በአነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ሥራ ዘርፍ የሚተዳደሩ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ለችግር መዳረጋቸው፤ በደቡብ ኦሞ ዞን፣ ዳሰነች ወረዳ፣ አካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን ጨምሮ ለተደራራቢ የመብቶች ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂ እና ፍላጎታቸውን ያማከለ ሰብአዊ ድጋፍ የማይቀርብ መሆኑ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል፣ በምሥራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የመመለስ ቅድመ ዝግጅት ሂደት አካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን ጨምሮ ለተደራራቢ የመብቶች ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ ተቀባይ ዞኖቹም ሆነ ወረዳው የተሰባጠረ መረጃ (disaggregated data) የሌላቸዉ በመሆኑ ተደራራቢ ተጋላጭነት ያለባቸውን ሰዎች ፍላጎት መሠረት ያደረገ ምላሽ ለመስጠት በቂ ቅድመ ዝግጅት አለመደረጉ ተጠቃሽ ናቸው።

## የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና የፍልሰተኞች መብቶች

የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ጨምሮ የስደት እና ፍልሰትን በተመለከተ ክትትል የሚያደርገው እና መረጃዎችን በየጊዜው ይፋ በሚያደርገው በዓለም አቀፉ የፍልሰት ጉዳዮች ድርጅት (International Organization for Migration) መረጃ መሠረት እስከ ታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ በኢትዮጵያ የሚገኙ ሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር ወደ 3.2 ሚልዮን የሚጠጋ

ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ቁጥር በአማራ ክልል በሚካሄደው የትጥቅ ግጭት ሳቢያ፣ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች በዘንድሮ በጀት ዓመት በተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች (ድርቅ እና ጎርፍ መጥለቅለቅ) እንዲሁም በበጀት ዓመቱ በተለያየ ወቅት በሚያገረሹ የትጥቅ ግጭቶች ሳቢያ በደረሱ መፈናቀሎች ምክንያት ይህ ቁጥር እንደጨመረ ወይም እንደሚጨምር የተለያዩ የሰብአዊ ድጋፍ የሚያቀርቡ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በበጀት ዓመቱ ይፋ ያደረጓቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የሀገሪቱ ሁሉም ክፍሎች በሚባል ደረጃ የተለያየ ብዛት ያላቸው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሚያስተናግዱ ሲሆን፣ እነዚህ ተፈናቃዮች በመጠለያዎች፣ በጊዜያዊ የሰፈራ ቦታዎች ወይም ከማኅበረሰቡ ተቀላቅለው የሚኖሩ ናቸው፡፡

ኢሰመኮ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ሰብአዊ መብቶች አያያዝን በተመለከተ የሚያደርገው ክትትል በዋነኝነት ትኩረት የሚያደርገው በመፈናቀል ውስጥ ባሉበት ወቅት የመንግሥት ግዴታዎች የሆኑትን የመመዝገብ፣ የግል ሰነድ የመስጠት፣ እንቅስቃሴን የማመቻቸት፣ የደኅንነት ጥበቃ፣ የመጠለያ እና ሌሎች የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት፣ እንዲሁም የማኅበራዊ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሏቸውን መብቶች የሚመለከት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ከመፈናቀል ሁኔታ ሊያወጧቸው የሚያስችላቸውን እና በዋነኝነት የመንግሥት ግዴታ የሆነውን የዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግ ተግባር አፈጻጸም ላይ ነው፡፡ ከዚህ የክትትል ሥራ ጎን ለጎን የሀገር ውስጥ መፈናቀል ሁኔታን ለመከላከል በመንግሥት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት፣ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተገቢውን ጥበቃ የሚያደርጉ የሕግ፣ የፖሊሲ፣ የመዋቅር እና የሀብት ምደባ ተግባራት አፈጻጸም ይከታተላል፣ እንዲፈጸሙም ወደ ሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ውትወታ ያደርጋል፡፡ ኢሰመኮ የተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ ዓመታዊ የዘርፍ ሪፖርት ይፋ ማጠናቀር ከጀመረበት ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ ባደረገው ክትትል እንዳመላከተው ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው ክልሎች በተቀባይ ማኅበረሰብ፣ በመንግሥት እንዲሁም መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሰብአዊ ድጋፍ በተለይ የምግብ ድጋፍ ለማቅረብ የሚደረገው ጥረት፤ በተወሰኑ የተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎች በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የተሰባጠረ የተፈናቃዮች የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መኖሩ፤ የኮሚሽኑን የክትትል ግኝቶችና ምክረ ሐሳብ ተቀብለው የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጡ የወረዳ፣ የክልል እንዲሁም የፌዴራል አመራርና ተቋማት መኖራቸው በ2016 በጀት ዓመትም ከታዩ መልካም እመርታዎች መካከል ናቸው፡፡

ሆኖም የተፈናቃዮች ምዝገባ እና ሰነድ የማግኘት መብት በተመለከተ በበጀት ዓመቱ የታዩ ጅማሮዎች ቢኖሩም በሀገር አቀፍ ደረጃ በምዝገባ እና በሰነድ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ያለው ክፍተት መቀጠሉ፤ ለተፈናቃዮች የሚደረገው ድጋፍ በአግባቡ እንዳይከናወን አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩ በተጨማሪ ተፈናቃዮች ሌሎች የመንቀሳቀስ እና የማኅበራዊ አገልግሎት የማግኘት መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዳይችሉ እንቅፋት መፍጠሩ እንደቀጠለ ነው፡፡ ወቅቱን የጠበቀ፣ በቂ፣ ያልተቆራረጠ እንዲሁም ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸውን ተፈናቃዮች መሠረት ያደረገ የሰብአዊ ድጋፍ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት አለመኖሩ፤ ተፈናቃዮች ይህንን ክፍተት ለመሙላት እና ያሉበትን ሁኔታ ለመቋቋም አሉታዊ ውጤት ያላቸው አማራጮችን (Negative Coping Mechanisms) እንዲወስዱ መገደዳቸው አሳሳቢ ሲሆን፤ በተጣበበ የመጠለያ ሸራ ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች ወይም የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ሰዎች በጋራ እንዲኖሩ መደረጉ ሴቶችን እና ሕፃናትን ለጾታዊ ጥቃት እና ለጉልበት ብዝበዛ ተጋላጭ የሚያደርግ ነው፡፡

ሆኖም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በአንዳንድ አካባቢዎች የተመዘገቡ መልካም እመርታዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ በሐረሪ ክልል በሐኪም ወረዳ በሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ እንዲሁም በሸንኮር ወረዳ፤ በሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ ኢሰመኮ ከየካቲት 17 እስከ 23 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ እና

ግንቦት 12 ቀን 2016 ዓ.ም. የክትትል ሥራ ካከናወነ በኋላ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሚደረገው የዘላቂ መፈትሔ አተገባበር ከሰብአዊ መብቶች አንፃር የተቃኘ እንዲሆን አድርጓል። ኢሰመኮ በክትትሉ ያቀረባቸውን ምክረ ሐሳቦች ለመፈፀም ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን፤ ይህንንም የክልሉ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በደብዳቤ ገልጿል። በተጨማሪ ኮሚሽኑ ካደረገው የክትትል ሥራ በኋላ ተፈናቃዮችን በዘላቂነት ለማቋቋም ለዘጠኝ ቤተሰቦች የተሰጡ ቤቶችን ግንቦት 13 እና 14 2016 ዓ.ም. ባከናወነው የዳግም ክትትል ተመልክቷል፤ ኮሚቴው ያዘጋጀውን እቅድ ለመፈፀም የሚያግዝ ዝርዝር እቅድ በኮሚሽኑ ተዘጋጅቶ ለኮሚቴው ቀርቧል። በሌላ በኩል ከክትትሉ በኋላ የተቋቋመው ኮሚቴ ያዘጋጀውን ዝርዝር ዕቅድ ተመልክቶ ግብአት የሰጠ ሲሆን፣ በዚህም ዝርዝር እቅዱ ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ ሲውል የዘላቂ መፍትሔው አተገባበር ከሰብአዊ መብቶች አንፃር የተቃኘ እንዲሆን ያስችላል።

የተ.መ.ድ. የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) የሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. መረጃ እንደሚያሳየው 1,051,022 የሚጠጉ እና በአብዛኛው ከደቡብ ሱዳን፣ ከሶማሊያ እና ከኤርትራ የተሰደዱ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በተለይም በጋምቤላ፣ በሶማሊ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ክልሎች የሚገኙ ሲሆን፣ የተወሰኑትም በአዲስ አበባ ይኖራሉ። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወንባ፤ ሸርቆሌ እና ጾሬ መጠለያ ጣቢያዎች ቁጥራቸው ከ72,650 በላይ ስደተኞች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የተመድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በሚያዝያ ወር 2016 ባወጣው መረጃ መሠረት 22305ቱ በጦርነት ምክንያት ከሱዳን ሸሽተው የመጡ እና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል። ከባለፈው ዓመት ጀምሮ በሱዳን በተቀሰቀሰው ግጭት ምክንያት ከለላ ፈልገው ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው በተለይ በመተማ አማራ ክልል እና በኩርሙክ ጋምቤላ ክልል የሚገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል።

ኢትዮጵያ የስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶችን በተመለከተ በዓለም እና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ያሉ የሕግ ማዕቀፎችን ያጸደቀች በመሆኑ፤ የስደተኞችን መብቶች በተሻለ ሁኔታ ለመጠበቅ እና ለስደተኞች ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማፈላለግ የሚያስችል አጠቃላይ የሕግ ማዕቀፍ መኖሩ ለሰብአዊ መብቶች ሁኔታው ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው። በተጨማሪ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ጥበቃ እና ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም ለማስተባበር የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ተቋም መኖሩ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር እንዲሁም የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ሀገር በቀል የተራድዖ ድርጅቶች መንግሥት ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚያደርገው ጥበቃ እና ድጋፍ የተሟላ እንዲሆን ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑ በመልካም እመርታነት የሚጠቀሱ ናቸው። ሀገሪቱ በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥም ቢሆን በዘንድሮ በጀት ዓመት በተለይም ከሱዳን የፈለሱ ስደተኞችን ተቀብላ ማስተናገድ መቻሏም ለጉዳዩ የምትሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ነው።

ሆኖም ኢሰመኮ በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. በጋምቤላ ክልል በተመረጡ የስደተኛ መጠለያ ካምፖች ባደረገው ክትትል የምግብ እና ምግብ ነክ ድጋፎች በመቋረጣቸው ስደተኞች ለሕይወት አደጋ ጭምር እየተዳረጉ መሆናቸውን እና አሉታዊ የመቋቋሚያ ዘዴዎችን (Negative coping mechanism) ለመጠቀም ከመጠለያ አካባቢያቸው በሚወጡበት ጊዜም ለጥቃት እየተጋለጡ የነበሩ መሆኑ ከአሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ይጠቀሳል።

በተለይም በጋምቤላ ክልል የሚገኙት ስደተኞች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር በተደጋጋሚ ጊዜ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ውስጥ መግባታቸው፤ በዚህም የተነሳ ለተለያዩ ጥቃቶች ተጋላጭ እየሆኑ መምጣቱ አሳሳቢ ሲሆን፣ እነዚህን አለመግባባቶች እና ግጭቶች ለመፍታት የክልሉ መንግሥት ከስደተኞች እና ከስደተኞች ተመላሽ አገልግሎት (RRS) እና ሌሎች አጋር አካላት ጋር በትብብር እየሠራ መሆኑ ተመልክቷል።

## አሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችን ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

በአሕጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችን ከመወጣት አንጻር በዘንድሮ በጀት ዓመት የተወሰኑ ለውጦች ታይተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን (African Commission on Human and Peoples' Rights) የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር (African Charter on Human and Peoples' Rights) ሪፖርት አቅርባለች፡፡ የአፍሪካ የሰብአዊና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን በኢትዮጵያ የቀረበውን ሪፖርት አስመልክቶ በሚቀጥሉት ጉባኤዎች ገምግሞ የመደምደሚያ ምልከታውን (concluding observations) ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በተጨማሪም የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (Maputo Protocol) አፈጻጸምን አስመልክቶ በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ሪፖርት አቅርባለች፡፡

በጥቅምት 23 ቀን 2016 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንና የተመድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤት (Office of the High Commissioner for Human Rights) አዘጋጅነት የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌን (Universal Declaration of Human Rights) 75ኛ አመትን ለመዘከር በተካሄደው ሀገር አቀፍ ኮንፍረንስ ላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፍትሕ ሚኒስቴር የሕግ ክፍተቶችን ለመሙላት አለም አቀፍ የሕግ ልማዶችን (Customary International Law) እና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ስራ ላይ እንዲያውሉ አስፈላጊ እርምጃዎችን እንደሚወስዱ ቃል ገብተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የ ፍትሕ ሚኒስቴር የሕግ ክፍተቶችን ለመሙላት ዓለም አቀፍ የሕግ ልማዶችን (Customary International Law) እና ኢትዮጵያ ተቀብላ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን በቀጥታ ስራ ላይ ለማዋል ቃል ገብቷል፡፡ በተጨማሪም የፌደራል ፖሊስ የሕግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን ክብርና ከዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሚመነጩ የሰብአዊ መብቶችን እንዲጠብቁና እንዲያከብሩ ተጨባጭ እርምጃ እንደሚወስድ ቃል ገብቷል፡፡ እነዚህ በይፋ የተገቡ ቃሎች ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን በሕጎች ውስጥ አካቶ ከመፈጸም አንጻር ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

ሆኖም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስምምነቶች ከሆኑት ዋነኞቹ 9 የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች መካከል 1) "ሁሉንም ሰው ከአስገድዶ መሰወር ለመጠበቅ የተደረገ ስምምነት" (Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) እና 2) የፍልሰተኛ ሠራተኞችን እና የቤተሰቦቻቸውን መብቶች ለመጠበቅ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (International Convention on the Protection of the Rights of All Migrant Workers and Members of Their Families) በዘንድሮ በጀት ዓመትም አልተፈረሙም/አልጸደቁም፡፡

ከአፍሪካ ህብረት 12 መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች መካከል፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Persons with Disabilities in Africa) ገና ተቀብላ አላጸደቀችም፡፡

## ምክረ ሐሳቦች

በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ዋነኛ ምክንያት የሆነውን ግጭቶችን የማስቆም እና ሰላማዊ መፍትሄ ጥረቶች ሊጠናከሩ ይገባል። በተለይም በአንዳንድ ክልሎች ከሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ኃይሎች ጋር የተጀመሩ ባህላዊ እና ሌሎች ሰላም የማምጣት እንቅስቃሴዎች አበረታች ቢሆኑም ዘላቂ እንዲሆኑ ሂደታቸው ተጎጂዎችን ጨምሮ ሁሉን ባለድርሻ አካላት ያካተቱ እና ግልጽ ሊሆኑ ይገባል።

ስለሆነም በዋነኝነት በፍትሕ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተጀመረው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አጠቃላይ ሂደት በተለይም ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ፣ ተዓማኒ እና ግልጽነት ያለው እንዲሆን፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ያሟላ እና የሰብአዊ መብቶች መርሖች የተከተለ እንዲሆን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

## መልካም እመርታዎች

በዚህ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ዘመን በተለያዩ ዘርፎች የታዩ መልካም ጅማሮዎችና እመርታዎች በእያንዳንዱ የሪፖርቱ ክፍል/ምዕራፍ የተካተቱ ቢሆንም ዋና ዋና ወይም በሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታው ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነጥቦች በዚህ የመጀመሪያ ክፍል ጠቅለል ባለ መልኩ ተዳሰዋል።

ከእነዚህም መልካም እመርታዎች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀሰው በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ነው። በፖሊሲ ሰነዱ መግቢያ እንደተመላከተው "በአገሪቱ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ እና የቀጠሉ ተደራራቢ እና ሰፊ የተጎጂና የአጥፊ ወሰን ያላቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ ያልጠሩ ትርክቶች እና በደሎችን ለመፍታት የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል ። ሆኖም እነዚህ አሠራሮች በእውነት፣ በዕርቅ፣ በምህረት እና በፍትሕ ላይ የተዋቀረ እና በግልፅ ፖሊሲ የሚመራ ሁለተናዊ የሽግግር ፍትሕ ስልትን አካታች፣ ሰብአዊ መብት–ተኮር በሆነ እና በተሰናሰለ መንገድ ባለመተግበራቸው የሚፈለገውን ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት አልቻሉም። ስለሆነም ለችግሮች እና አገራዊ ፈተናዎች ስር-ነቀል እልባት ከመስጠት አንፃር ከነበሩ አገራዊ ሙከራዎች እና የሌሎች አገራት መልካም ተሞክሮዎች በመማር፣ አግባብነት ያላቸው የዓለም-አቀፍ ሰነዶች ስለሽግግር ፍትሕ አካሄድ ያስቀመጧቸውን ደረጃዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ሂደትን በአገሪቱ በመተግበር በየጊዜው ከሚከሰቱ ችግሮች መውጣት እና ዘላቂ ሰላም እና ፍትሕን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በ2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ የፀደቀው የአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማዕቀፍ የሽግግር ፍትሕ ሀገራት የተለያዩ የፖሊሲ እርምጃዎችን እና ተቋማዊ አሠራሮችን በመጠቀም ያለፉ ጥሰቶችን፣ ክፍፍሎችን እና አለመመጣጠኖችን ለማስወገድ እና ለደኅንነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሥርዓት ግንባታ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚደረግ አስፈላጊ ሂደት እንደሆነ ይገልጻል።" ሆኖም በዚህ ዓመታዊ ሪፖርት ክፍል ምክረ ሐሳቦችና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ክፍል ዘርዘር ባለ መልኩ እንደተገለጸው፣ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው አጠቃላይ አተገባበርም ሆነ በፖሊሲው የታቀዱ የተለያዩ የሂደቱ ክፍሎች አብዛኛዎቹ ተጎጂዎች የሚስማሙበት/የሚጠይቁትን አተገባበር ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በተሟላ መልኩ ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ማድረግ፣ እውነትን መፈለግ፣ ለተጎጂዎች ካሳ መስጠትን እና ተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ዳግመኛ እንዳይከሰቱ ዋስትና መስጠትን የሚያጠቃልል ሁለንተናዊ አሠራር የተከተለ፣ ሁሉን አቀፍ የሽግግር ፍትሕ ሂደት መተግበርና ይህንን ማድረግ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር/ማመቻቸት ይገባል።

ኢሰመኮ በሚያከናውነው መደበኛ በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሠሩ) ሰዎች አያያዝ ክትትል ወቅትም ሆነ ለኢሰመኮ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ምርመራ ግኝቶች ተከትሎ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት የሚያገኘው በአብዛኛው አዎንታዊ የሆነ ምላሽና ትብብር ከዓመት ዓመት መሻሻል ማሳየቱ መፍትሔ የማፈላለጉን ሥራ የሚያቀላጥፍና የምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም የሚያፋጥን ነው። በዚህም አግባብነት ለምሳሌ በ2016 በጀት ዓመት ኢሰመኮ ተቀብሎ ካስተናገዳቸው 1400 ገደማ አቤቱታዎች አብዛኛዎቹ መፍትሔ ወይም እልባት አግኝተዋል፣ ኢሰመኮ በፖሊስ ጣቢያዎችና በማረሚያ ቤቶች ባደረገው ክትትል በ2015 በጀት ዓመት ያቀረባቸው በርካታ ምክረ ሐሳቦች ተፈጻሚ ሆነው በጣቢያዎቹና በማረሚያ ቤቶቹ ሁኔታና በተጠርጣሪዎችና በታራሚዎች አያያዝ ላይም የታዩ መሻሻሎች አሉ። በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶች ዘርፍና በአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች ዘርፍ፣ በክልል፣ በተቋም ወይም በአንድ አካባቢ ደረጃም ቢሆን የዘላቂ መፍትሔን በማፈላለግ ረገድ፣ የአሠራር ለውጥ በማድረግ፣ ሀብት ወይም የሰው ኃይል በመመደብ ረገድ በዚህ በጀት ዓመት የተመዘገቡና በኢሰመኮ ውትወታ ወይም የተሰጡ ምክረ ሐሳብ በመፈጸም የተገኙ ለውጦችና መሻሻሎች

አሉ፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም በትግራይ ክልል ውዝፍ የ18 ወራት ጡረታ ክፍያን ሲጠባበቁ የቆዩ አረጋውያን በተመለከተ የፌዴራል መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ለመክፈል መወሰኑ ሊጠቀሱ ከሚችሉ መልካም እመርታዎች መካከል ነው፡፡ ኢሰመኮ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ዘርፎች ላይ በወጡ የሕግ እና የፖሊሲ ማሻሻያዎች ላይ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የሰጣቸው ምክረ ሐሳቦችና አስተያየቶች መካከል የተፈጸሙና ተግባራዊ የሆኑ አሉ፡፡ ለምሳሌ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉን አቀፍ የንግድ እና የሰብአዊ መብቶች መርኃ ግብር መኖር አስፈላጊነትን በተመለከተ ከ2014 ዓ.ም. ሲያከናውናቸው የነበሩ ተግባራትና የውትወታ ሥራዎች ውጤታማ ሆነው በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. በፍትሕ ሚኒስቴር አስተባባሪነት በተዘጋጀ መድረክ ይህንኑ ሀገር አቀፍ መርኃ ግብር የመቅረጽና የማዘጋጀት ሂደት በይፋ ተጀምሯል፡፡

እነዚህን መሰል በተለያዩ ዘርፎች የተመዘገቡና በክልልም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የታዩ የተወሰኑ መሻሻሎች ወይም መልካም ጅማሮዎች ቢኖሩም፣ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተደጋጋሚ በሚያገረሹ የትጥቅ ግጭቶች፡፡ እንዲሁም በአማራ ክልል ሁሉም አካባቢዎች ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. የተስፋፋው የትጥቅ ግጭት፣ በበጀት ዓመቱ ለአስር ወራት ተፈጻሚ ሆኖ የቆየው አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ዐውድ ጋር ተያይዞና በሌሎች ምክንያቶች አሳሳቢ ሆነው የቀጠሉ ወይም አሳሳቢ ሆነው የጎሉ ጉዳዮች ጋር ሲነጻጸር የተመዘገቡት መሻሻሎች የሚያደበዝዝ ነው፡፡

WWW.EHRC.ORG



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Bereket Berhanu

# ክፍል ፪



# በሕይወት የመኖር መብት

Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Kidus Ermias

## በሕይወት የመኖር መብት

ከሐምሌ ወር 2015 እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ ከአማራ እና ከኦሮሚያ ክልሎች በተጨማሪ በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በማእከላዊ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና በሶማሊ ክልሎች የትጥቅ ግጭት ሁነቶች የተመዘገቡ ሲሆን፣ በትጥቅ ግጭት እና በግጭቶች ዐውድ ውስጥ በሚፈጠሩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሳቢያ ሰዎች ለሞት፣ ለአካል ጉዳት፣ ለመፈናቀል እና ለሌሎች ጉዳቶች ተዳርገዋል። በተለይም ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በበርካታ የአማራ ክልል አካባቢዎች የተስፋፋው የትጥቅ ግጭት እና በኦሮሚያ ክልል አብዛኛው አካባቢዎች በየጊዜው የሚከሰቱ የትጥቅ ግጭቶች በሲቪል ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በአካባቢዎቹ ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል። በአማራ ክልል በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች (የሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ የክልል እና የፌዴራል ፖሊስ እንዲሁም የአካባቢ ሚሊሻዎች) እና በተለምዶ “ፋኖ” ተብሎ በሚታወቁ የታጠቁ ኃይሎች መካከል የሚካሄደው የትጥቅ ግጭት በክልሉ ሁሉም ዞኖች ተስፋፍቷል።

በዚሁ የትጥቅ ግጭት በተኩስ ልውውጥ ወቅት፣ የመለየትን፣ የጥብቅ አስፈላጊነትን እና የተመጣጣኝነት መርሖችን ባልጠበቁ የከባድ መሣሪያ ድብደባዎች (heavy artilery shelling) እና በአየር ድብደባዎች (በአብዛኛው በሰው አልባ በራሪዎች ወይም ድሮን) ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሲቪል ሰዎች (ሴቶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ሕፃናትን ጨምሮ) በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል። ለምሳሌ ያህል በሰሜን ሸዋ ዞን ሸዋ ሮቢት፣ በረኸት፣ መራቤቴ፣ ምንጃር፣ ሚዳ ወረሞ፣ ሞጃና ወዳና፣ መንዝ ቀያ ወረዳዎች፤ በምዕራብ ጎጃም ዞን ፍኖተሰላም፣ ደጋዳሞት፣ ቋሪት፣ ሰከላ እና ደንበጫ፤ በምሥራቅ ጎጃም ዞን ባሶ ሊበን፣ ደብረማርቆስ እና አዋበል፤ ሰሜን ጎጃም ዞን አዴት እና መራዊ፤ በደቡብ ወሎ ዞን ከላላ፣ ጃማ ደጎሎ፣ ደላንታ፣ ለጋምቦ፣ ወረባቦ ወርዳዎች፤ በደቡብ ወሎ ዞን ሃርቡ፣ ሃብሩ፣ አምባሰል፣ ቆቦ፣ ላስታ፣ ግዳን፣ አይና ቡግና፣ ተኩለሽ እንዲሁም በሌሎች ግጭት በተካሄደባቸው የክልሉ አካባቢዎች (በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ በተደጋጋሚ) በተፈጸሙ የድሮንና የከባድ መሣሪያ ድብደባዎች የተነሳ በርካታ ሲቪል ሰዎች ላይ የሞትና የአካል ጉዳት ደርሷል።

ኢሰመኮ በግንቦት ወር 2016 ዓ.ም. በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ከተራዘሙ የትጥቅ ግጭቶች ጋር በተያያዘና ከግጭት ዐውድ ውጭ የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችንና ሥጋቶችን በተመለከተ በተለይም ከኅዳር ወር እስከ ሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በተከሰቱ ሁነቶች ላይ ያተኮረ የምርመራ ግኝቶች በትጥቅ ግጭት ወቅት በሚደርሱ እና በግጭቶቹ ተሳታፊ በሆኑ ሁሉም ኃይሎች በሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አብዛኛዎቹ/ዋነኛ ተጎጂዎች ሲቪል ሰዎች የሆኑ የአካባቢዎቹ ነዋሪዎች መሆናቸውን ማመላከቱ የሚታወስ ነው።

በአማራ ክልል በሚካሄደው የትጥቅ ግጭት ጋር በተያያዘ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች የሚፈጸሙ እና ሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ከሕግ/ከፍርድ ውጪ ግድያዎች በከፍተኛ ደረጃ አሳሳቢ ሆነው ቀጥለዋል። እነዚህ ግድያዎች “የጦር መሣሪያ ደብቃችኋል አምጡ”፣ “ፋኖን ትደግፋላችሁ”፣ “ለፋኖ መረጃ ትሰጣላችሁ” በሚሉ እና መሰል ምክንያቶች የሚፈጸሙ ሲሆን፣ ሴቶችን እና ሕፃናት ጭምር የዚሁ ጥሰት ሰለባ ሆነዋል። በተለይም በአንድ አካባቢ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀናት የሚካሄዱ የትጥቅ ግጭቶችን ተከትሎ በሚካሄድ የቤት ለቤት ፍተሻ የተያዙ ወይም መንገድ ላይ የተገኙ ሲቪል ሰዎች በተለያዩ አካባቢዎች ከሕግ ውጭ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል። ከዚህ አንጻር ባለፉት ስድስት ወራት በነበሩ የተለያዩ ወቅቶች በባሕር ዳር፣ አዴት፣ ደብረማረቆስ፣ በደብረ ታቦር፣ ጅጋ፣ ለሚ፣ ማጀቴ፣ መራዊ፣ ቢኮሎ፣ መርጦ ለማርያም፣ ሸዋ ሮቢት እና የዕድውኃ ከተሞች በመንግሥት የጸጥታ አባላት በሲቪል ሰዎች ላይ የደረሱ ከሕግ ውጭ ግድያዎችን መጥቀስ ይቻላል።በአማራ ክልል ትጥቅ ግጭት ወቅት ሲቪል ሰዎችን ባልለዩ እና በአየር እና በሌሎች ከባድ መሣሪያዎች በታገዙ ወታደራዊ ጥቃቶች

(military actions) በነዋሪዎች ላይ የሞት እና የአካል ጉዳት የደረሰ ሲሆን፣ በአብዛኛው የመኖሪያ ቤቶች፣ ከብቶች እና ሰብሎችን ጨምሮ የመተዳደሪያ ንብረቶች ወድመዋል፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ነዋሪዎች ለመፈናቀል እንዲገደዱ አድርጓል። በአላማጣ ከተማ አስተዳደር፣ ኮረም ከተማ አስተዳደር፣ ራያ አላማጣ፣ ዛታ እና ኦፍላ ወረዳዎች በተከሰተ የጸጥታ ሥጋት እና ውጥረት ከሚያዝያ 7 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በርካታ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች እንደተፈናቀሉ ለመረዳት ተችሏል። ነዋሪዎች በደኅንነት ሥጋት ሳቢያ መኖሪያቸውን ጥለው በመሸሻቸው አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በተለይም ገጠራማ ቀበሌዎች በታጠቁ ኃይሎች የንብረት ዘረፋ እና ውድመት መፈጸሙ ታውቋል።

በትጥቅ ግጭት ወቅት፣ በግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች ግጭት በሌለበት ወቅት የሚፈጸሙ ከሕግ ውጪ የሆኑ የሲቪል ሰዎች ግድያዎችም አሳሳቢ ሆነው ቀጥለዋል። የካቲት 20 ቀን 2016 ዓ.ም. በአማራ ክልል፣ ሰሜን ጎጃም ዞን፣ ሜጫ ወረዳ፣ ብራቃት ቀበሌ በሚገኘው የጋፊት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የአብነት ተማሪዎች የዕለቱን መርኃ ግብር ከምሽቱ 5:00 ሰዓት ገደማ አጠናቀው ወደ ማደሪያዎቻቸው ከተመለሱ በኋላ፣ የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች አባላት እኩለ ለሊት 6:30 ሰዓት ገደማ መጥተው ተማሪዎቹን ከቤታቸው ማስወጣታቸውን፣ ቀድመው በወጡ 11 ተማሪዎች ላይ ተኩሰው መግደላቸውን እና ሌሎች 8 ተማሪዎችን "ለምን ትሰድቡናላችሁ" በሚል በቁጥጥር ሥር ማዋላቸውን ምስክሮች አስረድተዋል። ታስረው ያደሩት ተማሪዎች በማግስቱ "ምንም ጥፋት የለባችሁም" ተብለው መለቀቃቸው ታውቋል። ይህ ክስተት በደረሰበት ወቅት በአካባቢው የሚንቀሳቀስ የታጠቀ ኃይል እንዳልነበር ምስክሮች ጨምረው አስረድተዋል። መጋቢት 6 ቀን 2016 ዓ.ም. በአማራ ክልል በባሕር ዳር ከተማ ዘንዘልማ አካባቢ አቶ ብርሃኑ ሽባባው አካል፣ አቶ በላይ አካል እና አቶ ተሾመ ይበልጣል የተባሉ ነዋሪዎች አንዳቸው ከሚሠሩበት ሱቅ እና ሁለቱ ነዋሪዎች ደግሞ ከመኖሪያ ቤታቸው "ለጥያቄ ትፈለጋላችሁ" በሚል በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ፣ መጋቢት 7 ቀን 2016 ዓ.ም. በባሕር ዳር ከተማ፣ ቀበሌ 14 በተለምዶ ጉዶ ባሕር ተብሎ በሚጠራ ሰፈር በጥይት ተገድለው መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ሚያዚያ 7 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ላይ በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን እስቴ ወረዳ አጎና በተባለች መለስተኛ ቀበሌ የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ከእስቴ ወረዳ ወደ ላይ ጋይንት ወረዳ በመጓዝ ላይ እያሉ በአካባቢው በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ኃይሎች (በተለምዶ ፋኖ) ድንገተኛ የደፈጣ ጥቃት መፈጸሙን ተከትሎ ታጣቂዎቹ አካባቢውን ጥለው እንደሸሹ የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ወደ ቦታው (አጎና ቀበሌ) በመግባት 7 (1 ሴት እና 6 ወንዶች) ሲቪል ሰዎች ላይ ግድያ መፈጸማቸውን፣ ከ15 በላይ የሚሆኑ የቆርቆሮ ክዳን ያላቸው መኖሪያ ቤቶች እና 3 የገለባ ቤቶችና ንብረት መቃጠላቸውን፣ እንዲሁም ከ100 በላይ የሚሆኑ የቀበሌው ነዋሪዎች ወደ ሌላ አካባቢ የተፈናቀሉ መሆኑን የቀበሌው ነዋሪዎችና ተጎጂዎች ገልጸዋል። በወቅቱም ግለሰቦቹ ቃጠሎውን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ጥይት በመተኮስ እንደከለከሏቸውና ሆን ተብሎ የግለሰቦቹ ቤት እና ንብረት እንዲቃጠል እንደተደረገም ጨምረው አስረድተዋል። በዚህም የተነሳ በመኖሪያ ቤቶቹ ውስጥ የነበሩ የቤት ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ እህል እንዲሁም የአንድ ግለሰብ 8 በጎች ሙሉ በሙሉ እንደተቃጠሉ ለመረዳት ተችሏል።

በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች በትጥቅ ግጭት ውስጥ የሚሳተፉ የታጠቁ ኃይሎች በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችን እና በሲቪል ሰዎች ላይ ከሕግ ውጪ የሆኑ ግድያዎችን የሚፈጽሙ መሆኑን አመላክተዋል። ጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ደራ ወረዳን የሀገር መከላከያ ሰራዊት ለሌላ ግዳጅ አካባቢውን ለቅቆ መውጣቱን ተከትሎ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች በማግስቱ ጥር 10 ቀን 2016 ዓ.ም. አካባቢውን ከተቆጣጠሩ በኋላ "ለመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ምግብ ስታቀርቡ ነበር" በሚል ምክንያት በወረዳው 01 ቀበሌ የሚገኘው ሳላይሽ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ጥበቃ

የነበሩት አቶ ስዩም ካሴን በጥይት በመምታት መግደላቸውን እንዲሁም ከበደ ዓለማየሁ የተባሉ ነዋሪን ከመኖሪያ ቤታቸው ከወሰዷቸው በኋላ በአካባቢው ጫካ ውስጥ አስከሬናቸው መገኘቱን ኢሰመኮ አረጋግጧል። ጥር 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋት 2 ሰዓት ጀምሮ ማንነታቸው ያልታወቀ ታጣቂዎች በኦሮሚያ ክልል፣ ምዕራብ ጉጂ ዞን፣ ገላና አባያ ወረዳ ኤርገንሳ ቀበሌ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የኩፍኝ በሽታ ክትባት ለመስጠት በመንዝ ላይ በነበሩ ሠራተኞች ላይ በፈጸሙት ጥቃት የገላና አባያ ወረዳ አስተዳደር ጤና ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊን ጨምሮ ሁለት ሲቪል ሰዎች መገደላቸውን፣ እንዲሁም 3 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን ከመንግሥት ኃላፊዎች እና ከአካባቢው ነዋሪዎች ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል። ጥቃቱን ተከትሎ በገላና አባያ ወረዳ ጤና ጽሕፈት ቤት ሲሰጥ የነበረው የሕክምና አገልግሎት እና የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ስርጭት መስተጓጎሉን ለማወቅ ተችሏል። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") በኦሮሚያ ክልል፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ አመያ ወረዳ "የመንግሥት ሠራተኞችና የመንግሥት ጸጥታ ኃይል አባላት ቤተሰቦች ናችሁ" በሚል ወይም "ለመንግሥት አካላት ትብብር አድርጋችኋል" በሚል ምክንያት በወረዳው በተለያዩ ቀበሌዎች በየካቲት እና ሚያዝያ ወራት በፈጸማቸው ተከታታይ ጥቃቶች በሲቪል ሰዎች ላይ ግድያ፣ አካል ጉዳት፣ እገታ፣ ንብረት ውድመት እና ዘረፋ ፈጽሟል። ለምሳሌ በአመያ ወረዳ፣ አቡዬ ጀብላል ቀበሌ የካቲት 7 ቀን 2016 ዓ.ም. በፈጸመው ጥቃት 11 ሲቪል ሰዎችን ገድሏል፤ መኖሪያ ቤቶችንና ሞተር ሳይክሎችን አቃጥሏል፤ የቀንድ ከብቶችን ዘርፏል። መጋቢት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. በወረዳው ቆታ ከተማ ላይ በፈጸመው ጥቃት 31 ሲቪል ሰዎችን ገድሏል፣ 3 ሲቪል ሰዎችን አቁስሏል፣ የቀንድ ከብቶችንና ሌሎች ንብረቶችን ዘርፏል እንዲሁም ንብረቶችን አቃጥሏል። በዚሁ ጥቃት ወቅት ከደረሰው ጉዳት በተጨማሪ 6 ሲቪል ሰዎችን አግቶ መውሰዱም ታውቋል። ሚያዝያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም. በወረዳው ደራ ቲርቲሪ ቀበሌ ላይ ታጣቂ ቡድኑ በፈጸመው ጥቃት 2 ሲቪል ሰዎችን ገድሏል፣ ከ100 በላይ የተለያዩ የቀንድ ከብቶች ዘርፏል እንዲሁም በሚያዚያ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. በጎምንቦሬ አሊይ ቀበሌ 36 የቀንድ ከብቶችንና 3 ሞተር ሳይክሎችን ዘርፏል። በዚሁ ጥቃት ወቅት ደራ ቲርቲሪ ቀበሌ 27 እንዲሁም ሚያዚያ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. በጎምንቦሬ አሊይ ቀበሌ 15 ሲቪል ሰዎችን አግቶ ወስዷል።

በመጋቢት 1 ቀን 2016 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ ስልካምባ ከተማን ለመቆጣጠር የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች በከፈቱት ጥቃት የወረዳው አበዩ ሄቤን ቀበሌ ነዋሪ የነበሩ አቶ ሹመቴ ፋርስ እና ወ/ሮ ተቀባ አበጋዝ የተባሉ አረጋውያን በመኖሪያ ቤቶቻቸው ፊት ለፊት ተገድለዋል። በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ አንድ የቀበሌው ነዋሪ ለኢሰመኮ ሲያስረዱ፦ *"የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች በብዛት ወደ ስልካምባ ከተማ እያለፉ ነበር፣ ለሰዓታትም ተኩስ ነበር፤ በኋላ ላይ ታጣቂዎቹ ከከተማው ማፈግፈግ ሲጀምሩ ያገኙትን ነዋሪ ያለማመንታት ተኩሰው እየገደሉ ይሸሹ ነበር። አቶ ሹመቴ እና ወ/ሮ ተቀባም ያለምንም ምክንያት በቡድኑ ተገድለዋል" ብለዋል።*

መጋቢት 2 ቀን 2016 ዓ.ም. ከአማራ ክልል፣ ኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን የተነሱ ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች በሰሜን ሸዋ ዞን፣ አስተዳደር በኤፍራታና ግድም እና ቀወት ወረዳዎች በሚገኙ አንዳንድ ቀበሌዎች ላይ በፈጸሙት ጥቃት በሲቪል ሰዎች ላይ ግድያ መፈጸሙን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ ንብረት መውደሙን፣ መኖሪያ ቤቶች መቃጠላቸውን እንዲሁም የቀንድ ከብቶችና የሦስት እግር ተሽከርካሪዎች መዘረፋቸውን ኮሚሽኑ ባደረገው ክትትል አረጋግጧል። መጋቢት 16 ቀን 2016 ዓ.ም. ከምሽቱ 3፡00 እስከ 5፡00 ባሉት ሰዓታት ማንነታቸው በውል ያልታወቀ የታጠቁ ቡድኖች በኦሮሚያ ክልል፣ ምዕራብ አርሲ ዞን፣ ዶዶላ ከተማ 02 ቀበሌ እንዲሁም በዶዶላ ወረዳ ደነባ በሚባል የገጠር ቀበሌ ውስጥ 11 ሰዎችን በጥይት ተኩሰው መግደላቸውን፣ እንዲሁም አምስት ሰዎችን ማቁሰላቸውን ለማወቅ ተችሏል። በዕለቱ በተፈጸመ ጥቃት የቀበሌው ነዋሪ የሆነ እና የምዕራብ አርሲ ሀገረ ስብከት የዶዶላ ደብረ ቅዱሳን ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነ ግለሰብ፣ ከባለቤቱ

እና ከሁለት ልጆቹ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው እያሉ እንዲሁም ሌላ አንድ ዲያቆን ከባለቤቱ እና ከእህቱ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው እያሉ በጥይት ተመተው መገደላቸውን ለማወቅ ተችሏል። በተመሳሳይ በዶዶላ ወረዳ ደነባ ቀበሌ በግምት ከምሽቱ 5:00 ሰዓት አካባቢ 4 የቀበሌው ነዋሪዎች ማንነታቸው ባልታወቁ የታጠቁ አካላት በጥይት ተመተው ሲሞቱ 5 ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸውን ለማወቅ ተችሏል። በባሕር ዳር ከተማ፣ ዳግማዊ ምኒሊክ ክፍለ ከተማ፣ ጋጃ መስክ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ መጋቢት 29 ቀን 2016 ዓ.ም. ከምሽቱ 1:00 ሰዓት አካባቢ ማንነታቸው ባልታወቁ አካላት በተፈጸመ ጥቃት የሶላት ስግደት አከናውነው ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ የነበሩ 5 ሰዎች (አራቱ የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ) መገደላቸውን ኮሚሽኑ ማረጋገጥ ችሏል።

በሲቪል ሰዎች ላይ በትጥቅ ግጭቱ እንዲሁም በግጭቱ ዐውድ ውስጥ ከሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በተጨማሪ ሲቪል ሰዎችን ዒላማ ያደረጉ እገታዎች አሳሳቢነት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው። ጥር 12 ቀን 2016 ዓ.ም. በአማራ ክልል፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን፣ የግብርና መምሪያ ኃላፊ እና ሌሎች ሦስት የግብርና መምሪያው ሠራተኞች ከጅሌ ጥሙጋ ወረዳ ወደ ከሚሴ ከተማ ሲመለሱ ኤፍራታና ግድም ወረዳ ካራቆሬ ተብሎ ከሚጠራ አካባቢ በታጣቂዎች እንደታገቱ እና ከኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን የተነሱ መሆናቸው የተገለጸ ታጣቂዎች ከኤፍራታና ግድም ወረዳ የዘረፏቸውን በርካታ የቀንድ ከብቶች እስኪመለሱ ድረስ ታጋቾችን የማይለቋቸው መሆኑን አጋቾች በስልክ እንደገለጹላቸው የታጋች ቤተሰቦች ያስረዳሉ። ጥር 26 ቀን 2016 ዓ.ም. ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ቡድኖች ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን አባያ ወረዳ ወደ ማእከላዊ ሲዳማ ዞን ሎኮ አባያ ወረዳ ቡኪቶ ቡራ ቀበሌ በመግባት ሁለት የቀበሌው ነዋሪዎችን አግተው በመውሰድ የታጋች ቤተሰቦች የማስለቀቂያ ገንዘብ እንዲከፍሏቸው በመጠየቅ እስከ ጥር 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ አቆይተው ገንዘቡ ከተከፈላቸው በኋላ ግለሰቦቹን መልቀቃቸውን ማወቅ ተችሏል። በአካባቢው የሚፈጸመው ሰዎችን ለገንዘብ የማገት ድርጊት ተደጋጋሚ እና ላለፉት 3 ዓመታት የቆየ እንደሆነ መረዳት ተችሏል። የወረዳው ፖሊስ ጽሕፈት ቤት በወቅቱ ችግሩ ከዐቅሙ በላይ መሆኑን እና ተጨማሪ ኃይል በአካባቢው ማሰማራት አስፈላጊ መሆኑን የጠቀሰ ቢሆንም ተጨማሪ ኃይል ባለመመደቡ እና ከኦሮሚያ ክልል የሚገቡት ታጣቂዎች የሚታጠቁት መሳሪያ ከወረዳ ፖሊስ ዐቅም በላይ በመሆኑ ችግሩን መከላከል አለመቻሉን ገልጸዋል። ወረዳው ይህንኑ በመጥቀስ ለክልሉ መንግሥት ተጨማሪ ኃይል እንዲመደብ የጠየቀ መሆኑን መረዳት ተችሏል።

የካቲት 11 ቀን 2016 ዓ.ም. በአማራ ክልል፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን፣ በሰሜን አቸፈር ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ሱፐርቫይዘር፣ ርዕሰ መምህር እና ሌሎች መምህራን በወረዳው ትምህርት ለማስጀመር መስክ ወጥተው ወደ ወረዳው ዋና ከተማ ሊበን ሲመለሱ መንገድ ላይ በታጣቂ ኃይሎች (በተለምዶ ፋኖ) ተይዘው ለሦስት ቀን ታግተው ከቆዩ በኋላ “የብልጽግናን ዓላማ ለማራመድ ሁለተኛ እንዳትመጡ” በሚል ማስፈራሪያ የካቲት 13 ቀን 2016 ዓ.ም. እንደተለቀቁ ለማወቅ ተችሏል።

ከየካቲት 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ከአማራ ክልል የመጡ መሆናቸው የተገለጸ ታጣቂዎች በኦሮሚያ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን ደራ ወረዳ በሚገኙ አዋሳኝ ቀበሌዎች በሲቪል ሰዎች ላይ በተከታታይ በፈጸሚቸው ጥቃቶች 25 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል፤ 4 ሲቪል ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አድርሰዋል እንዲሁም ለጊዜው ቁጥራቸው ያልታወቀ ሲቪል ሰዎችን አግተው ወስደዋል። በታጣቂዎቹ በተፈጸመው ጥቃት በርካታ የመኖሪያ ቤቶችም ተቃጥለዋል።

በዚሁ ደራ ወረዳ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች ከኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በወረዳው በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች በሲቪል ሰዎች ላይ በፈጸሚቸው ጥቃቶች 15 ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል፤ ቁጥራቸው ለጊዜው በትክክል

ያልታወቀ በርካታ ነዋሪዎችን አግተው ወስደዋል፤ በርካታ የቀንድ ከብቶችን ዘርፈዋል እንዲሁም መኖሪያ ቤቶችን አቃጥለዋል። የካቲት 29 ቀን 2016 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ወንጂ ከተማ ዶዶታ ተብሎ የሚጠራ አካባቢ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች በቀለ ጥሩነህ፣ ተሾመ ሔራም፣ ያለው ተመስገን፣ ካሚል አብዱረማን እና ግርማ በላቸው የተባሉ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሠራተኞችን በሥራ ላይ ባሉበት ወቅት አግተው በመውሰድ ታጋቾችን ለመልቀቅ በእያንዳንዳቸው 75 ሺ ብር እንዲከፈል መጠየቃቸውን ተከትሎ፣ የታጋቾች ቤተሰቦች ገንዘቡን በማሰባሰብ ክፍያውን ለመፈጸም በመሔድ ላይ እያሉ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በመያዛቸውና ገንዘቡ አጋቾች ጋር ሊደርስ ባለመቻሉ የታጋቾች አስክሬኖች መጋቢት 6 ቀን 2016 ዓ.ም. በአዳማ ወረዳ ልዩ ስሙ ኡሞ ፈጫሳ የሚባል ቦታ ተጥሎ ተገኝተዋል። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") መጋቢት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አመያ ወረዳ ቆታ ከተማ ላይ በፈጸመው ጥቃት ቀደም ባለው አንቀጽ ላይ ከተገለጸው የ31 ሲቪል ሰዎች ገድያና የ3 ሲቪል ሰዎች አካል ጉዳት በተጨማሪ 6 ሲቪል ሰዎችን አግቶ ወስዷል። በተጨማሪም ታጣቂ ቡድኑ ሚያዝያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም. በወረዳው ደራ ቲርቲሪ ቀበሌ 27 እንዲሁም ሚያዚያ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. በጎምንቦሬ አሊይ ቀበሌ 15 ሲቪል ሰዎችን አግቶ ወስዷል። መጋቢት 19 ቀን 2016 ዓ.ም. እኩለ ሌሊት ገደማ የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት የሆኑትን ዶ/ር ንጉስ ታደሰን ደብረ ብርሃን ከተማ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ባልታወቁ የታጣቂ ኃይሎች ተይዘው ተወስደው ከተወሰኑ ቀናት በኋላ መለቀቃቸው የሚታወስ ነው።

በበርካታ የአማራ እና የኦሮሚያ ክልል ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የምርት ሂደት ተቋርጧል፣ በዚህም ሰዎች ለምግብ እጥረት እና ለተያያዥ ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተዳርገዋል።

በመንግሥት እና በታጣቂ ኃይሎች በሲቪል ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ከሕግ ውጪ ግድያዎች በኦሮሚያ ክልልም አሳሳቢ ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ ዝርዝር የምርመራ ሪፖርት ይፋ ማድረግን ጨምሮ ኮሚሽኑ ለፌዴራል እና ለክልሉ መንግሥት አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥበት በተደጋጋሚ ማሳሳቡ ይታወሳል።

በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በተለያየ ወቅት የሚከሰቱ ግጭቶች ወይም በትጥቅ ግጭት በሚሳተፉ ኃይሎች ሳቢያ ክልሎቹን ከሌሎች ክልሎች ጋር በሚያዋስኑ አካባቢዎች ላይ ውጥረት፣ የእንቅስቃሴ ገደቦች እና ተያያዥ አሉታዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች ብሎም በአንዳንድ አካባቢዎች ጥቃቶች ያስከተሉበት ሁኔታዎችም አሉ። ለምሳሌ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ ኦነግ ሸኔ) አባላት በተለይም በአሶሳ ዞንና ካማሺ ዞን ወረዳዎች በተለያየ ወቅት ጥቃት ማድረሳቸው በአካባቢው ላይ ውጥረት እና ሥጋት አስከትሏል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ ሸኔ) ኅዳር 19 ቀን 2016 ዓ.ም. በአሶሳ ዞን፣ ቤልሚሊ፣ አልከሻፊ እና ቤላደሩ ቀበሌ በሰነዘረው ጥቃት ሴቶችና ሕፃናትን ጨምሮ 17 ነዋሪዎች የሞቱ ሲሆን፣ በ 7 ሰዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ ጉዳት ደርሷል፣ እንዲሁም አንድ አረጋዊ በታጣቂዎች ተወስደው መሰወራቸው ታውቋል። ይህንን ተከትሎ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ 3 ሲቪል ሰዎች ሲገደሉ በአንድ ግለሰብ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል።

በጋምቤላ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በአብዛኛው የተሻሻለ የጸጥታ ሁኔታ የታየ ቢሆንም፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለያየ ወቅት የተከሰቱ ግጭቶች እና ጥቃቶች እንዲሁም በመንግሥት የጸጥታ አካላት እና በታጠቁ ኃይሎች በሚፈጸሙ ከሕግ ውጪ ግድያዎች ሳቢያ ሰዎች ለሞት እና ለአካል ጉዳት፣ እንዲሁም ለመፈናቀል ተዳርገዋል። ለምሳሌ በጋምቤላ ክልል፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች መካከል በግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. በተከሰተ ግጭት ሳቢያ ከግንቦት እስከ ነሐሴ 2015 ዓ.ም. ባሉት ወራት በተለያዩ ወቅቶች የሚያገረሹ ግጭቶች በርካታ የልዩ ወረዳውን

ነዋሪዎች ለሞት፣ ለአካል ጉዳት እና ለመፈናቀል ዳርገዋል፡፡ ግጭቶቹን እስከ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ ወቅቶች ጋምቤላ ከተማና ወረዳውን ጨምሮ በኢታንግ ልዩ ወረዳ የተለያዩ አካባቢዎች እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ ስደተኞችን ጭምር ለሞት እና ለተለያዩ ጉዳቶች ዳርገው የቆዩ ሲሆን፣ የክልሉ መንግሥት ከፌዴራል የጸጥታ ኃይሎች ጋር በወሰዳቸው የተጠያቂነት እርምጃዎች እና የእርቅ ሂደቶች በእነዚህ አካባቢዎች የነበረው የጸጥታ ሁኔታ ሊሻሻል የቻለ ቢሆንም፣ በተለይም በተቀባይ ማኅበረሰቡ እና በስደተኞች መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት መዋቅር መዘርጋትን ጨምሮ አሁንም ዘላቂ መፍትሔ የሚሹ ናቸው፡፡

ብሔርን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ወይም በክልሎች እና በክልሎች ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች (ዞኖች፣ ወረዳዎች ወይም ቀበሌዎች) መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሰዎች ሞት፣ አካል ጉዳት፣ መፈናቀል እና ለሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ምክንያት ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ በጋምቤላ ክልል ማጃንግ ብሔረሰብ ዞን ጎደሬ ወረዳ አካሽ ቀበሌ ዋንዛ፤ ገንገበቲ እና ትግሬ ሰፈር በሚባሉ አካባቢዎች፤ በጎሸኔ ቀበሌ ኳስ ሜዳ እና ጌሌሻ ቀበሌ ከነሐሴ 29 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. ባልታወቁ ሰዎች በደረሰ ጥቃት 13 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 7 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡ በአኙዋ ብሔረሰብ ዞን፣ አቦቦ ወረዳ፣ ፔርቦንግ መንደር 17 በሚባል አካባቢ ታኅሣሥ 6 ቀን 2016 ዓ.ም. ባልታወቁ ሰዎች በተፈጸመ ጥቃት አንድ አዛውንት፤ አንድ የሦስት ልጆች እናት እና አንድ የ16 ዓመት ልጅ በአጠቃላይ ሦስት ሰዎች ተገድለዋል፡፡ በእዚህ አካባቢ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች አልፎ አልፎ የሚከሰቱ መሆኑን ኮሚሽኑ ከአካባቢው ነዋሪዎች ባሰባሰበው መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአፋር ክልል፣ ማሂ ረሱ (አዲስ የተቋቋመ ዞን) እና በገቢ ረሱ ለረዥም ጊዜ የቆየ የሶማሊ (ኢሳ ጎሳ) እና የአፋር ተወላጆች መካከል በሚያገረሹ አለመግባባቶች ሳቢያ እስከ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ ወቅቶች የተከሰቱ ግጭቶች ሞት ያስከተሉ ሲሆን፣ በዚሁ ምክንያት ሃሩካ ወረዳ፣ ጉሞይሊ አዱ፣ ጉሁም እና ገረኒ ወረዳ ተብለው በሚጠሩ አካባቢዎች ብዛታቸው ያልተረጋገጠ ሰዎችን ለሞት እንዲሁም ነዋሪዎችን ለተለያዩ ጉዳቶች ዳርጓል፡፡

በተጨማሪም በአንድ ክልል ውስጥ ወይም በክልል አዋሳኝ አካባቢዎች በሚከሰቱ ግጭቶች ሳቢያ በአንዳንድ አካባቢዎች ስደተኞች እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችም ጭምር ለአካል ጉዳት እና ለሞት ተዳርገዋል፡፡ ለምሳሌ በመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ለሁለት ቀናት በቆየ እና በኦሮሚያ እና በሶማሊ ክልል አዋሳኝ አካባቢ በሚገኘው በቀሎጂ ካምፕ በተከሰተ ውጥረት እና የተኩስ ልውውጥ፣ በስደስተኛ ካምፕ ውስጥ የሚኖሩ የአምስት ወር ሕፃን ጨምሮ 6 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ ቢያንስ 17 ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል አጠቃቀም ጋር በተያያዘም በአንዳንድ አካባቢዎች ሰዎች ለአካል ጉዳት እና ለሞት ተዳርገዋል፡፡ ነሐሴ 15 ቀን 2015 ዓ.ም. በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በአሶሳ ዞን፣ የባምባሲ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ የጸጥታ ኃይሎች አንድ የማኅበረሰብ ሥነ ልቦና ጉዳት እንዳለው የተነገረን ግለሰብ በቁጥጥር ሥር ለማዋል ባደረጉት ሂደት በተወሰደ ተመጣጣኝ ያልሆነ እርምጃ በግለሰቡ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ፣ በታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም. በመተከል ዞን፣ ማንዱራ ወረዳ፣ ገነተ ማሪያም ከተማ የፌዴራል ፖሊስ ካምፕ ውስጥ በእስር ላይ የነበረን አንድ ሰው ታኅሣሥ ወር በ2016 ዓ.ም. ከካምፕ ውጪ በፌዴራል ፖሊስ ሰራዊት አባላት መገደሉን ማወቅ ተችሏል፡፡ በኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. በሲዳማ ክልል፣ በሃዋሳ ከተማ አንድ የሰዎችን ንብረት ሰርቆ በመሸሽ ላይ የነበረን ተጠርጣሪ ለመያዝ በተደረገ ሂደት የከተማው ፖሊስ አባላት ተጠርጣሪው በስለት አስፈራርቶናል በማለት ተኩሰው መግደላቸው ታውቋል፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ ዞን በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ ቆላ ሻራ ቀበሌ ቀበሌውን አስቀድሞ ከነበረበት የአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ አስተዳደር ክልል ወደ አርባምንጭ ከተማ አስተዳደር ለማካለል በተወሰነው ውሳኔ ምክንያት በቀጠለው አለመግባባት በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. በተከሰተው ግጭት በቀበሌው ነዋሪዎች እና በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች መካከል የተኩስ ልውውጥ ተካሂዷል። በዚህም ሳቢያ ሲቪል ሰዎች እንዲሁም የታጠቁ የቀበሌው ነዋሪዎች ሕይወት አልፏል፣ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ የግለሰቦች ንብረቶች ወድመዋል። በዚሁ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በኮሬ ዞን (በቀድሞ አደረጃጀት አማሮ ልዩ ወረዳ ) በኅዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም. ውስጥ "የኮበለሉ የመከላከያ ሰራዊት አባላትን በሞተር ሳይክል ታስመልጣላችሁ" በሚል ምክንያት በወቅቱ በአካባቢው የነበሩ ሌሎች የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ጥይት በመተኮስ የአከባቢው ነዋሪ የሆኑ እና በሞተር ማሽከርከር ሥራ የሚተዳደሩ ሁለት ወጣቶችን መግደላቸውን፣ እንዲሁም በታኅሣሥ 20 ቀን 2016 ዓ.ም. በጋርዱላ ዞን ዲራሼ ወረዳ ኢቴያ ቀበሌ አንድ ወደ ኮንሶ መስመር በመጓዝ ላይ የነበረ የተሳቢ መኪና አሽከርካሪ "የመከላከያ ሰራዊት መኪናን ደርቦ ለማለፍ ሲሞክር በኦራል መኪናው ላይ መለስተኛ ጉዳት አድርሷል" በሚል ምክንያት በወቅቱ በኦራል መኪና ውስጥ ከነበሩ የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት መካከል አንዱ ጥይት በመተኮስ አሽከርካሪውን መግደሉን ኢሰመኮ ከምስክሮች ማወቅ ችሏል።

በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በጉራጌ ዞን እና በቀቤና ልዩ ወረዳ መካከል የነበረውን አለመግባባት ተከትሎ ጥቅምት 2 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የተከሰተውን የጸጥታ መደፍረስና ያስከተለውን ጉዳት አንድ የፌዴራል ፖሊስ አባልን ጨምሮ አራት ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል፣ ቢያንስ 114 ሰዎች ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

በአፋር እና በሶማሊ ክልሎች መካከል በቅርቡ ሚያዝያ 2016 ዓ.ም. የተኩስ ማቆም ስምምነት የተደረገ ቢሆንም፤ ሁለቱን ክልሎች በሚያዋስኑ አካባቢዎች በግንቦት ወር 2016 ዓ.ም. መጨረሻ የተከሰቱ የትጥቅ ግጭቶች፣ የሲቪል ሰዎች ሕይወት መጥፋት፣ መፈናቀልን እና የንብረት ጉዳት አስከትሏል።

በአማራ ክልል፣ በዋግህምራ ዞን፣ እንዲሁም በትግራይ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች በድርቅ ወይም በሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ፤ በምግብና ሌሎች መሠረታዊ አቅርቦት መዘግየት፣ አለመመጣጠን እና አለመድረስን ጨምሮ በተያያዥ ችግሮች ሳቢያ፣ እንዲሁም በትጥቅ ግጭት እና በጸጥታ ችግሮች ምክንያት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ያሉ እንቅስቃሴዎች እና የየብስ መጓጓዣ መንገዶች አስቸጋሪ በመሆናቸው፤ ሰዎች የጤና አገልግሎት ለማግኘት ባለመቻላቸው ምክንያት፣ ሰዎች ለከፋ ችግርና ለሕይወት አደጋ ጭምር የተዳረጉበት ክስተቶችም ታይተዋል። በጋምቤላ ክልል በ2015 ዓ.ም. በክረምት ወቅት በደረሰ የጎርፍ አደጋ በመቶዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎችን ለመፈናቀል እና ለሰብአዊ ድጋፍ እጥረት የዳረገ ሲሆን፣ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ሰዎች መሞታቸው ታውቋል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማና በአዲስ አበባ መካከል እንዲሁም ክልሉን ከሌሎች ክልሎች በሚያገናኙ መንገዶች የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት በተለይም እናቶች እና አረጋውያን የሪፈራል እና የመሰል ሕክምና አገልግሎት ማግኘት አዳጋች ሆኖባቸዋል። የምግብና ሌሎች መሠረታዊ አቅርቦቶች እጥረት እና ተደራሽና ተመጣጣኝ አለመሆን፣ እንዲሁም እስከ ኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. የዘለቀው የዓለም ምግብ ፕሮግራም (WFP) እና የአሜሪካ ተራድዖ ኤጀንሲ (USAID) የምግብ አቅርቦት ማቋረጥ፣ በተለይም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እና ስደተኞችን ለከፋ ችግር የዳረገ ሲሆን፣ በዚሁ ሳቢያና ከረሃብ ጋር በተያያዙ ሌሎች ችግሮች ለምሳሌ በትግራይ ክልል የሚገኙ ተፈናቃዮች እንዲሁም በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ስደተኞች መሞታቸውን የሚመመለከታቸው የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ኃላፊዎች እና ለስደተኞች ድጋፍ የሚያቀርቡ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ገልጸዋል።


Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/ Meqdelawit Assefa

# ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 ጋር አተገባበር ጋር የተያያዘ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ

## የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 አተገባበር ጋር የተያያዘ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 6 (12) በተሰጠው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ሰብአዊ መብቶችን የመከታተል ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ከሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ የቆየውን የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ አተገባበር ጋር ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል። ኢሰመኮ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት ሰብአዊ መብቶችን የመከታተል ተግባርና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን እና በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታም ውስጥ ቢሆን የጸጥታ እና የፍትሕ አካላት በሰብአዊ መብቶች እና ሕገ መንግሥታዊ መርሖች እንዲመሩ፣ በማናቸውም ሁኔታ ሊገደቡ የማይችሉ መብቶች ሊከበሩ እንደሚገባ፤ እንዲሁም ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈጻጸም ጋር የሚወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች የጥብቅ አስፈላጊነትን፣ የተመጣጣኝነትን፣፣ ከአድሎ ነጻ የመሆንን እና የሕጋዊነትን መርሖች ጨምሮ በሰብአዊ መብቶች መርሖች እና ድንጋጌዎች ሊመሩ እንደሚገባ በማስታወስ፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በላከው ምክረ ሐሳብ፣ እንዲሁም ይፋ ባደረጋቸው ሰነዶች ማሳሰቡ የሚታወስ ነው። ኢሰመኮ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጁ ላይ ለመምከር ከመሰብሰቡ አስቀድሞ ለምክር ቤቱ የሰብአዊ መብቶች ትንታኔ እና ምክረ ሐሳብ አቅርቧል፤ ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታው ጥብቅ አስፈላጊነትና ተመጣጣኝነት በተጨማሪ የፓርላማው ክትትል አስፈላጊነት፣ የዳኝነት ነጻነትና ዋስትና አስፈላጊነትና የኮሚሽኑን የሰብአዊ መብቶች ክትትል አስፈላጊነትን ሊያደናቅፉ የሚችሉ እርምጃዎች የሰብአዊ መብቶች መርሖችን የሚጥሱ መሆናቸውን አመልክቷል።

በምክረ ሐሳቡ ካነሳቸው ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በግልጽ የተጠቀሱት በማንኛውም ሁኔታ ሊታገዱ የማይችሉ መብቶች እንዲከበሩ፣ እንዲሁም የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የአስቸኳይ ጊዜ ክልክላዎችን፣ ግዴታዎችን እና የመብት እገዳዎችን ለማስፈጸም አስፈላጊና ተመጣጣኝ እርምጃዎች ብቻ እንዲጠቀሙ የሚያዙት ድንጋጌዎች የሚገኙ መሆኑ፣
- ለአሻሚ ትርጓሜ ወይም ተገቢ ላልሆነ አጠቃቀም ክፍት በመሆናቸው ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ ሥልጣንን አላግባብ ለመጠቀም እና ለተለያዩ የመንግሥት አካላት ሥልጣን መጋፋት/መሻማት የሚዳርጉ ቃላቶች፣ ሐረጎች እና አንቀጾች እንዲሰረዙ አልያም እንዲሻሻሉ፤ በተለይም በአስቸኳይ ጊዜ ወቅትም ቢሆን ሊታገዱ የማይችሉ መብቶች ተብለው ከተደነገጉ መካከል በሆኑት በሕይወት የመኖር መብት፣ ስቃይን ከሚያስከትል፤ ጨካኝ፤ ኢሰብአዊና አሰቃቂ አያያዝና ቅጣት ነጻ የመሆን መብት፣ በሕግ ፊት እንደሰው የመቆጠር፣ የሐሳብ፣ የሕሊናና የሃይማኖት ነጻነት ላይ ከሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ እና ጥሰቶች አኳያ፣
- እንዲሁም ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ጋር የሚቃረኑ የፍሬ ነገር እና የሥነ ሥርዓት ሕጎች በጅምላ መታገዳቸው እና የዲፕሎማቲክ ልዩ መብቶችን ብቻ ሲቀር ሌሎች ከሥራና ኃላፊነት ነጻነትን ከመጠበቅ አስፈላጊነት የሚመነጩ ልዩ መብቶችንና ጥበቃዎችን (functional immunity) ሊታገዱ መቻላቸው ከሚያስከትላቸው ውጤቶች መካከል አንዱ ለምሳሌ የፓርላማ አባላትና የዳኞችን ያለ ምክር ቤቱ ውሳኔ ያለመያዝና ያለመከሰስ መብቶችን ጭምር አላግባብ ለማገድ በር የሚከፍት ነው። ይህም በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ውስጥም ቢሆን ሊታገድ የማይችለውን የዳኝነት ዋስትና እና በነጻነት ላይ የተመሠረተ የፍትሕ አስተዳደርን የሚያግድ፣ በተለይም በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ውስጥ

ሊደረግ የሚገባውን የፓርላማ ክትትል (parliamentary oversight) መርሕ ተፈጻሚነት የሚያደናቅፍ መሆኑ፣

- ፍትሐዊ የዳኝነት መብት፣ ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ አንጻር በወንጀል ጉዳዮች ተፈጻሚነት ከሚኖራቸው ዝርዝር የሥነ ሥርዓት ዋስትናዎች አንዱ ከመሆን በተጨማሪ፣ በማናቸውም ጊዜ ብቁ ነጻ እና ገለልተኛ የዳኝነት አካላት እና የፍትሕ ሥርዓት መኖር ለሕጋዊነት እና ለሕግ የበላይነት መርሖች መተግበር የግድ የሚል ነው። በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ፤ የዳኝነት ተቋሙ የአስቸኳይ ጊዜ ሕጉ ከሕገ መንግሥቱና ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ጋር የተጣጣመ መሆኑንና አለመሆኑን፤ የመንግሥት ኃላፊዎች እና የሕግ አስፈጻሚ አካላት የአስቸኳይ ጊዜ ሥልጣን አጠቃቀም ከአስቸኳይ ጊዜ ሕጉ ጋር የሚስማማ መሆኑንና አለመሆኑን፤ እንዲሁም የአስቸኳይ ጊዜ ሥልጣን አተገባበር አላስፈላጊና ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ በሕገ መንግሥቱና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት የተረጋገጡ መብቶችን የሚጥሱ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን መወሰን ሊቻል እንደሚገባ የሚገልጹት ይገኙበታል።

ኢሰመኮ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 ተግባር ላይ ከዋለበት ከሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ የሚደርሱትን አቤቱታዎች እና ጥቆማዎች ከመመርመር፣ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን ከማሰባሰብ በተጨማሪ፣ ተጎጂዎችን፣ የተጎጂ ቤተሰቦችን፣ ምስክሮችን እና ሌሎች የመረጃ ምንጮችን፣ እንዲሁም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መርማሪ ቦርድን ኃላፊዎችን ጨምሮ ከሚመለከታቸው የጸጥታ አካላት ጋር በመነጋገር እና የውትወታ ሥራ በመሥራት ከአዋጁ አፈጻጸም እና ከአዋጁ ዐውድ ጋር የተያያዙ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል። በተጨማሪም የተጠቀሱ ቦታዎችን በመጎብኘት በተቋማቱ ውስጥ የተያዙ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ለመከታተል፣ እንዲሁም የሚመለከታቸውን የጸጥታ አካላት ምላሽ በማካተት ምርመራ ለማድረግ በሚያደርገው ጥረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙን እና መርማሪ ቦርዱን በተለያየ ወቅት አነጋግሯል።

በዚሁ ክትትል መሠረት በመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ባወጣው ሪፖርት በአዲስ አበባ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሸገር፣ በቢሾፍቱ፣ በአዳማ እና በሌሎች ከተሞች፣ በአማራ ክልል ደብረ ታቦር፣ ጎንደር እና ባሕር ዳር ከተሞችን ጨምሮ በሌሎች አካባቢዎች፤ እንዲሁም በሲዳማ ክልል፣ ሃዋሳ ከተማ ብዙ ሰዎች ከኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ውጪ ለጅምላ እስር ተዳርገው በተለያዩ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ቦታዎች መያዛቸውን ማመልከቱ የሚታወስ ነው። በወቅቱ ተይዘው ከነበሩ ሰዎች መካከል የኤርትራ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች (migrants) እንደሚገኙበትም ተገልጿል። በአዲስ አበባ ከተማ የኮከበ ጽባሕ እና የወንድይራድ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በ4 ትምህርት ቤቶች ተይዘው የቆዩ ታሳሪዎች ከፊሎቹ የተለቀቁ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ቁጥራቸው በወቅቱ በትክክል ያልታወቀ ታሳሪዎች ወደ ተለያዩ የከተማዋ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ በሚገኙ ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ቦታዎች ተዛውረው ሪፖርቱ ይፋ እስከተደረገበት እስከ መስከረም 9 ቀን ድረስ በእስር ላይ ይገኙ ነበር። በተለይም መደበኛ ባልሆነ እና ከመኖሪያ አካባቢያቸው ርቀው የታሰሩ ሰዎች ንጽሕናው የተጠበቀ አካባቢ፣ የውሃ ተደራሽነት፣ የመጸዳጃ ቦታ፣ የምግብ እና የጤና አያያዝ አሳሳቢ መሆኑን የሚያመላክቱ በርካታ አቤቱታዎች ለኮሚሽኑ ደርሰውታል። የኢሰብአዊ አያያዝ እና የማሰቃየት ተግባራትን ጨምሮ ተይዘው የሚገኙ ሰዎችን አያያዝ በተመለከተ አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮች መኖራቸውን ኮሚሽኑ የደረሱትን አቤቱታዎች ጠቅሶ፣ ሪፖርቱ ይፋ እስከተደረገበት እስከ መስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ ለተራዘመ ጊዜ የጉብኝት መብታቸው የተነፈጉ እና በየትኛው ማቆያ ቦታ እንደሚገኙ ያልታወቀ ሰዎች መኖራቸውም ተመላክቷል።

በተጨማሪም ለምሳሌ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ከከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች በቁጥጥር ሥር ውለው በሲዳማ ክልል በሚገኝ እና የቀድሞ የደቡብ ክልል ፖሊስ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሆነ በተለምዶ አቦስቶ ተብሎ የሚጠራ ቦታ የተወሰዱ በርካታ ተጠርጣሪዎች የነበሩ መሆኑን፣ በርካታ ከአዋጁ ጋር በተያያዘ በሚል ነገር ግን ከኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ውጪ ከጎዳና ላይ እንዲነሱ የተደረጉ ሰዎችን ጨምሮ ሌሎች ሰዎች በኦሮሚያ ክልል፣ ገላን ከተማ "ገላን አዋሽ ሲዳማ" ተብሎ በሚጠራ መደበኛ ያልሆነ የማቆያ ቦታ የተወሰዱ የነበረ መሆኑን፣ እንዲሁም በተለይም በገላን አዋሽ ሲዳማ የተያዙ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ በሚመለከት፣ በማቆያ ማዕከሉ ወረርሽኝ መሰል የጤና አደጋ መከሰቱን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሞቱ እና ሕክምና እርዳታ እንዲያገኙ የተወሰዱ ሰዎችም መኖራቸውን ኢሰመኮ ከቤተሰብ እና ከተለያዩ አካላት አቤቱታዎች መሠረት በማድረግ አስረድቷል ። በዚሁ ክትትልም በተለያየ ወቅት የተወሰኑ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ቦታዎችን በአካል ጎብኝቷል። ለምሳሌ በዋና ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ የተመራ የኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች ባለሞያ ቡድን ነሐሴ 26 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዋሽ አርባ ተይዘው የሚገኙ ሰዎችን ጎብኝቷል፣ ከማቆያ ቦታው ኃላፊዎች እና ከተያዙ ሰዎች ጋር ተወያይቷል።

የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታወጀበት ሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በአዲስ አበባ፣ አማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ በማእከላዊ ኢትዮጵያ እና በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ የሚድያ አባላት፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እና የሲቪክ ማኅበረሰብ አባላት ለእስራት ተዳርገው የነበረ ሲሆን በከፊል በኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ በከፊል ደግሞ ከኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ውጪ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ዐውዱ ብቻ የሚፈጸም እሥር ነበር። ከሚድያ አባላት መካከል፤ አቶ በቃሉ አላምረው፣ አቶ አባይ ዘውዱ፣ አቶ ይድነቃቸው ከበደ (ሁለት ጊዜ)፣ አቶ ፈቃዱ ማኅተመወርቅ፣ አቶ ቴዎድሮስ ዘርፉ፣ አቶ ንጉሤ ብርሀኑ፣ አቶ ተዋቸው ደርሶ፣ አቶ የኋላሸት ዘሪሁን፣ ብርሃኑ ተክለያሬድ (መሪጌታ)፣ አቶ በላይ ማናዬ እና አቶ አብነት ታምራት ይገኙበታል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከመታወጁ አስቀድሞ ከታሰሩት የሚድያ እና የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መካከል የተወሰኑ ሳምንታት አዲስ አበባ በሚገኙ ማቆያ ቦታዎች ቆይተው አዋጁን ተከትሎ ወደ አዋሽ አርባ (የመከላከያ ካምፕ) የተወሰዱ ሲሆን ከእነሱም መካከል መስከረም አበራ፣ ጎበዜ ሲሳይ፣ የኋላሸት ዘሪሁንና አብነት ታምራት ይገኙበታል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ ከታሰሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት መካከል የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)፣ የባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ (ባልደራስ)፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)፣ የዎላይታ ብሔራዊ ንቅናቄ (ዎብን)፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ)፣ የጎጎት ለጉራጌ አንድነት እና ፍትሕ (ጎጎት)፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፣ የሲዳማ ፌዴራሊስት ፓርቲ /ሲፌፓ/ እንዲሁም የእናት ፓርቲ አባላት ይገኙበታል።

ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መውጣት በኋላ ከኮማንድ ፖስቱ ተሰጥቷል በተባለ ትዕዛዝ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት እንዲሁም የክልል ምክር ቤቶች አባላት የታሰሩ ሲሆን፣ እነዚህም ደሳለኝ ጫኔ (ዶ/ር) እና አቶ ክርስቲያን ታደለ (የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት)፣ ካሣ ተሻገር (ዶ/ር) እና አቶ ሀብታሙ ቢልልኝ (የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አባላት)፣ አቶ ዮሐንስ ቧያለው (የአማራ ክልል ምክር ቤት አባል )፣ አቶ ታዬ ደንደአ (የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት (ጨፌ) አባል)፣ አቶ ታረቀኝ ደግፌ (የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት አባል) እና አቶ አማንስያ ቡሽና (የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት አባል) ናቸው። የምክር ቤት አባላቱ ያለመከሰስ መብት ከወራት የእሥር ቆይታ በኋላ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲነሳ ተደርጓል፣ ከታሳሪዎቹ ውስጥም ከእስር የተለቀቁ ይገኙበታል።

በዚሁ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ዐውድ ውስጥም በየካቲት 18 ቀን 2016 ዓ.ም. አቶ በቴ ኡርጌሳ፣ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) የፖለቲካ ኦፊሰር “ከፋኖ እና ኦነግ ሸኔ ጋር በመተባባር ሁከት እና ብጥብጥ ለማስነሳት በመንቀሳቀስ” ተጠርጥረዋል በሚል ለተወሰኑ ሳምንታት በእስር ከቆዩ በኋላ በዋስ የተለቀቁ መሆኑ የሚታወስ ነው። ከአቶ በቴ ኡርጌሳ ጋር አብሮ የተያዘ አንድ በዜግነቱ ፈረንሳዊ የሆነ የዓለም አቀፍ ሚድያ ጋዜጠኛ ከሁለት ቀናት እስር በኋላ ተለቅቆ ከሀገር እንዲወጣ ተደርጓል። አቶ በቴ ኡርጌሳ ሚያዝያ 2 ቀን 2016 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል፣ መቂ ከተማ የተገደሉ ሲሆን፣ ኢሰመኮ ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ አሳስቧል፣ የበኩሉን ክትትልም ማድረግ ቀጥሏል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ጸንቶ በቆየባቸው ጊዜያት ውስጥ ከፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት እና ከሚዲያ አባላት ባሻገር የማኅበረሰብ አንቂዎችና በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሰዎች ከኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ውጪ ለእስራት ተዳርገዋል። ጠበቆች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት የሌላቸው የተቃውሞ ሰልፍ አስተባባሪዎች እና የኪነጥበብ ባለሞያዎች በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

ከተከናወኑት እስራቶች መካከል አንዳንዶቹ “ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር የተያያዘ” የሚል ጠቅላላ ምክንያት የተሰጠባቸው ነገር ግን በቀጥታ በኮማንድ ፖስቱ ያልታዘዙ እስሮች ናቸው። እንደዚሁም ከታጣቂ ቡድኖች ጋር ግንኙነት እና ድጋፍ በማድረግ፣ ሁከትና ብጥብጥ በማነሳሳት ወይም ለማነሳሳት በመሞከር፣ የብሔርና የሃይማኖት ግጭት የሚያነሳሱ መልዕክቶችን በማሠራጨት፣ የተቃውሞ ሰልፍ በማስተባበር፣ ባለሥልጣናትን ለማስገደል በመንቀሳቀስ የሚሉና ሌሎች ምክንያቶች የቀረቡባቸው እስራቶች ተከናውነዋል።

ከእነዚህም መካከል፦

- ከነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች በባጃጅ አሽከርካሪነት፣ በቀን ሥራ እና በተለያዩ ሥራዎች የተሰማሩ በርካታ ወጣቶች መያዝና አንዳንዶች በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከዚያም በደቡብ ክልል በሚገኝ እና በተለምዶ አፖስቶ ተብሎ በሚጠራ ቦታ ተወስደው እስከ አንድ ወር ያህል ለሚሆን ጊዜ በእስር የቆዩ፣
- ነሐሴ 24 ቀን 2015 ዓ.ም. ከመስቀል እና እሬቻ በዓላት ጋር በተያያዘ ከአራት ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎችን በሸገር ከተማ፣ ልዩ ስሙ ገላን አዋሽ ሲዳሞ በቁጥጥር ስር መዋላቸው፣ በማእከሉ በተፈጠረ ወረርሽኝ 3 ሰዎች የሞቱ መሆኑና 190 ሰዎች ሆስፒታል ገብተው ሕክምና እንዲከታተሉ የተደረገ እና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የተለቀቁ፣
- ኅዳር 9 ቀን 2016 ዓ.ም “ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ” ላይ የተሳተፉ ከ20 በላይ ወጣቶች ሁከትና ብጥብጥ አስነስታችኋል በሚል ከሥራ ቦታቸው እና ከመኖርያ ቤታቸው በፖሊስ ተይዘው “የኮማንድ ፖስት እስረኞች” ናቸው በሚል ምክንያት ብቻ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ አንዳዶቹ እስከ ሁለት ወር ለሚደርስ ጊዜ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ በእስር የቆዩ፣
- ከጥምቀት በዓል ጋር በተያያዘ ያልተፈቀደ አለባበስ ለብሰዋል፣ የአዲስ አበባ ነዋሪነት መታወቂያ አልያዙም በሚል በርካታ ወጣቶች ከበዓሉ ጥር 11 ቀን በፊት እና በኋላ በቁጥጥር ሥር ውለው ከተወሰኑ ቀናት በኋላ የተለቀቁ፣
- በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. እንዲሁም ኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ የስደተኝነት መታወቂያቸው አልታደሰም ፣ ፈቃድ ሳይኖራቸው በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተዋል የተባሉ በርካታ ኤርትራዊያን በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው የተወሰኑት ተገደው ከአገር እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን የተቀሩት ለረዥም ጊዜ ለእስር ከተዳረጉ በኋላ የተለቀቁ ይገኙበታል።

በአማራ ክልል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ 'ፋኖን ትደግፋላችሁ' ወይም 'የፋኖ ቤተሰብ ናችሁ' በማለት ብቻ በርካታ ሰዎች ከኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ ውጪ ለእስር ተዳርገዋል። አብዛኞቹ እስሮች መደበኛ ባልሆኑ ስፍራዎች የሚደረጉ እና ለእስር የተዳረጉ ሰዎችም ኢሰብአዊ አያያዝን ጨምሮ ሌሎች የመብት ጥሰቶች እንደሚፈጸምባቸው ኢሰመኮ በተለይም ከተጎጂ ቤተሰቦች እና ከእስር ከተለቀቁ ሰዎች ያሰባሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ። ከመንግሥት በተቃራኒ የሆኑ ሐሳቦችን በማኅበራዊ ሚዲያም ሆነ በሌሎች ዘዴዎች የሚያስተላልፉ የማኅበራዊ ሚዲያ አንቂዎች እና የሚዲያ ሰዎች ለእስር ይዳረጋሉ ወይም ለተደጋጋሚ ዛቻ ወይም ድብደባ መዳረጋቸውንም ማወቅ ተችሏል። በክልሉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፣ ደጋፊዎች እና የሲቪል ማኅበራት አባላት እና ባለሙያዎች እንዲሁ ለእስራት ወይም ወከባ ተዳርገዋል። ለምሳሌ አንድ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ባለሙያ በባሕር ዳር ከተማ የመንግሥት የጸጥታ አካላት እንደሆኑ በተገለጹ ሰዎች ድብደባ የተፈጸመበት መሆኑ ታውቋል።

የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ ዐውድ ከአዲስ አበባ እና ከአማራ ክልል ውጪ ባሉ አካባቢዎችም የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ለምሳሌ በሐረሪ ክልል፣ በሐኪምና ሸንኮር ወረዳዎች የተወሰኑ ሰዎች ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ጋር የተገናኘ ነው በሚል ነገር ግን ያለ ኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. ከመኖሪያቸው ተይዘው ከሁለት ወራት በላይ ያለምንም የፖሊስ ምርመራ በክልሉ ፖሊስ መምሪያ ታስረው እንዲቆዩ ተደርጓል። በፖሊስ ጣቢያ ቆይታቸው ፍርድ ቤት ያልቀረቡ እና ክስም ያልተመሠረተባቸው ሲሆን፣ ከሁለት ወራት በኋላ በፖሊስ ዋስትና ተለቀዋል። በሸገር ከተማ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ በርካታ ግለሰቦች "በኮማንድ ፖስት የሚፈለጉ ናቸው" በሚል ምክንያት ብቻ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለበርካታ ቀናት በእስር እንዲቆዩ ተደርጓል፣ ከእነዚህም መካከል ከተወሰኑ ቀናት እስር በኋላ የተለቀቁ አሉ።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ደግሞ የክልሉ መንግሥት ወቅታዊ የጸጥታ ችግሮችን ምክንያት በማድረግ ሰዎችን በጅምላ የሚያስርበት ሁኔታ ተስተውሏል። ለምሳሌ የአማራ ብሔር ተወላጆች መሆናቸውን የገለጹ ነዋሪዎች 'ፋኖ የተባለው ቡድን ደጋፊ ናችሁ' በሚል እንዲሁም የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች መሆናቸው የተገለጹ ነዋሪዎች ከኦነግ ሸኔ ታጣቂ ቡድን ጋር በማያያዝ የማዋከብና የማሰር እንዲሁም እንቅስቃሴያቸውን የመገደብ ሁኔታ ተስተውሏል።



# የነጻነት እና የፖለቲካ መብቶች

Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Sa' ada Mussa

# የነጻነት እና የፖለቲካ መብቶች

የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጁ ተፈጻሚ ከሆነባቸው በተለይ ከአማራ ክልል እና ከአዲስ አበባ ውጪ እና የአዋጁን የአሰራር ደንብ ሳይከተልም በአብዛኛው ክልሎች የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች፣ በተለይም የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ እና ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብቶች ላይ ተጥለው የነበሩ የዘፈቀደ ገደቦች መኖራቸው ተመልክቷል።

በኦሮሚያ ክልል ካለው የጸጥታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ፣ 'ወቅታዊ ጉዳይ' በሚል ምክንያት ሰዎችን በተለይም የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን ማሰር፤ በክልሉ ታጥቆ የሚንቀሳቀስ ቡድንን ትረዳላችሁ በሚል ሰዎችን በጅምላ ማሰር እንዲሁም የመንቀሳቀስ መብታቸውን ማገድ ታይቷል። በሸገር ከተማ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") አባላት ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ክስ ሳይመሠረትባቸው ለወራት በእስር ይቆያሉ። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) አመራር የሆኑ 7 ግለሰቦች ከ2014 ዓ.ም. ጀምሮ በእስር ላይ ይገኛሉ። ኢሰመኮ አያያዛቸውን በተመለከተ ክትትል የሚያደርግ ሲሆን፣ በዚህ የበጀት ዓመትም በየካቲት ወር 2016 ዓ.ም. እስረኞቹ አሁንም ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውጪ በእስር የሚገኙበትን ሁኔታ ተመልክቷል፤ ይህንኑ እስር በተመለከተ የሚያደርገውን የውትወታ ሥራም ይቀጥላል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ኢሰመኮ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመነጋገር እና የውትወታ ሥራ በማከናወን ለችግሮች እልባት ማስገኘት ችሏል። ለምሳሌ በአፋር ክልል፣ ሰመራ ከተማ ከነሐሴ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ አደገኛ ቦዘኔነትን ለመከላከል በሚል ከሰመራ፣ ከሎግያ፣ ከዱብቲ እና ከሚሌ የተያዙ ቢያንስ 189 ወጣቶች በእስር ላይ የነበሩ ሲሆን፣ ኢሰመኮ ባደረገው ክትትልና ውትወታ 93 ሰዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ተገቢውን የፍርድ ሂደት እንዲከታተሉ እና ቀሪዎቹ በዋስትና እንዲለቀቁ ተደርጓል። በክልበቲ ረሱ፣ በራህሌ ወረዳ የመልካም አስተዳደር ጥያቄን አስመልክቶ ሐምሌ 29 ቀን 2015 ዓ.ም. በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ ምክንያት 16 ሰዎች የታሰሩ እና 18 ሰዎች ከመንግሥት ሥራ የተባረሩ ሲሆን፣ የታሠሩ ሰዎችን የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በራሳቸው ከእስር እንዲፈቱ ሲያደርጉ፣ ከሥራ የተባረሩት ሰዎች በኢሰመኮ ጥረት ወደ ሥራ እንዲመለሱ ተደርጓል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን፣ አሶሳ ከተማ አቅራቢያ በሚገኝ የወንጀል ተጠርጣሪዎች ማቆያ ካምፕ ውስጥ ከ3 ወራት በላይ ተይዘው እንዲቆዩ የተደረጉ የትጥቅ ቡድን አባልነታቸውን የተው (በተለምዶ "የሰላም ተመላሽ") 11 የጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጉሕዴን) ታጣቂ ቡድን የቀድሞ አባላት ኢሰመኮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ባደረገው ንግግር ወደ ቀድሞ መኖሪያ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ተደርጓል። በመተከል ዞን፣ ግልገል በለስ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ 5 የአገው ለፍትሕና ዴሞክራሲ የፖለቲካ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች በግልገል በለስ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውለው ለ6 ቀናት በፖሊስ ጣቢያ በእስር እንዲቆዩ ከተደረጉ በኋላ ኢሰመኮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ባደረገው ውይይት እና ክትትል ከእስር እንዲፈቱ ተደርጓል። በሐረሪ ክልል የሐረሪ ክልል መንግሥት በ2010 ዓ.ም. ለማኅበራት እንደሰጠ የተገለጸን ብድር "መመለሻው ጊዜ አልፏል" በማለት ከታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም ጀምሮ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የታሰሩ ሰዎች ኢሰመኮ ከክልሉ መንግሥት ጋር ባደረገው ንግግር እንዲፈቱ ማድረግ ተችሏል።

ሆኖም፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከክልሉ መንግሥት ዕውቅናና ፈቃድ ውጪ ለተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች በነጻነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ አዳጋች ነው። ለምሳሌ በአሶሳ ዞን ኡራ አብራሞና ብልድግሉ ወረዳዎች የሚገኙ የቤኒሻንጉል ሕዝቦች ነጻነት ንቅናቄ (ቤሕነን) ፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች በመንግሥት የጸጥታ አካላት ወከባና እስራት የሚደርስባቸው ስለመሆኑ ለኢሰመኮ በርካታ አቤቱታዎች እና ጥቆማዎች ቀርበዋል። በሌላ

በኩል የአባይ ሕብረ ብሔራዊ የፖለቲካ ፓርቲ ሊቀመንበር በክልሉ መንግሥት ላይ ተገቢ ያልሆነ ትችትና አስተያየት በማኅበራዊ ሚዲያ ሰጥተዋል በሚል ምክንያት በክልሉ የጸጥታ ኃይል ቁጥጥር ሥር ውለው በእስር ላይ ቆይተዋል።

በአፋር ክልል በ2016 ዓ.ም. ለ6 ወራት ያክል በእስር ላይ የቆዩ እና በማኅበራዊ ሚድያ ላይ መንግሥትን የሚቃወም ሐሳብ አስተላልፋችኋል በሚል ምክንያት የተያዙ ሰዎች አሉ። “በማኅበራዊ ሚዲያ የክልሉን አመራሮች ስም እያጠፉ እና ሕገወጥ ተግባራትን እየፈጸሙ ነው” በሚል የታሰሩ 3 ወጣቶችን እስር በመቃወም ሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. በሰመራ ከተማ ሊደረግ የነበረ ሰላማዊ ሰልፍ በፖሊስ ትእዛዝ ተከልክሏል።

በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የክልሉ የጸጥታ እና የፍትሕ ተቋማት በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ዞኖች እና ወረዳዎች (በዋናነት በቀቤና እና ጉራጌ፣ በምሥራቅ ጉራጌ ዞን እና በሀዲያ ዞን፣ ምሥራቅ ባደዋቾ ወረዳ) “ሕዝብን እርስ በርስ ለማጋጨት በማሰብ፣ በክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች ላይ ሀሰተኛ መረጃዎችን በተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያ ድረገጾች አማካኝነት አሰራጭተዋል”፣ ወይም “በአካባቢዎቹ በተከሰቱ ግጭቶች ላይም እጃቸው አለበት” በሚል የተያዙ 244 ሰዎች በሆሳዕና ማረሚያ ተቋም እና በሌሎች የዞን እና ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች በእስር እንዲቆዩ ተደርጓል። በታኅሣሥ 11 ቀን 2016 ዓ.ም. ሀዲያ ዞን፣ ምሥራቅ ባዳዋቾ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ 4 ቀበሌዎች (1ኛ ቁራንሶ፣ 2ኛ ቁራንሶ፣ ገገራ እና ቁራንሶ ታዳጊ ማዘጋጃ ቀበሌዎች) ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ ነዋሪዎች ወደ ሀላባ ዞን ለመካለል ባነሱት ጥያቄ መነሻ በተፈጠረ የጸጥታ ችግር ቁጥራቸው ወደ አርባ የሚጠጉ ነዋሪዎች በአከባቢው የመንግሥት ጸጥታ አካላት በቁጥጥር ሥር ውለው በሾኔ ከተማ በሚገኘው የወረዳው ፖሊስ ጣቢያ መታሰራቸውን ማወቅ ተችሏል።

በሲዳማ ክልል በኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. “የክልሉ መንግሥት የጸጥታ አካላት በክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች ላይ ስም የማጥፋት ሥራ ሠርተዋል፤ በማኅበራዊ ሚዲያ ድረ-ገጾች አማካኝነት ሀሰተኛ መረጃዎችን በማሰራጨት በኅብረተሰቡ መካከል ግጭት እንዲፈጠር ተንቀሳቅሰዋል” ያላቸው የሲዳማ ፌዴራሊስት ፓርቲ /ሲፌፓ/ አመራሮችና አባላት ታስረዋል። የክልሉ ጸጥታ አካላት በሃዋሳ ከተማ በሚገኘው የፓርቲው ጽሕፈት ቤት ብርበራ በማድረግ ንብረታቸውን እንደወሰዱባቸውም የፓርቲው አባላት ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ ዞን አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የዛይሴ ብሔረሰብ አባላት በሚኖሩባቸው ቀበሌዎች ከኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ባሉት ጊዜያትውስጥ ሲጠየቅ በነበረው የመዋቅር ጥያቄ መነሻነት፣ “አካባቢው እንዳይረጋጋ እንዲሁም በሰው ሕይወት እና አካል ላይ ጉዳት እንዲደርስ አድርገዋል” በሚል ምክንያት በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ እና በጋሞ ዞን በሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ /ኢዜማ/ ፓርቲ አመራሮች እና አባላት ላይ እስር ተፈጽሟል። በወቅቱ ቁጥራቸው ዘጠና የሚደርሱ የፓርቲው አባላትና አመራሮች በአከባቢው ተከስቷል ከተባለው የጸጥታ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በመንግሥት የጸጥታ አካላት ተይዘው በአርባ ምንጭ ማረሚያ ተቋም፣ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት፣ በአርባ ምንጭ ከተማ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት እና በዘይሴ ኤልጎ ቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተይዘው እንዲቆዩ ተደርጓል።

በተለያዩ አካባቢዎች በጸጥታ ወይም በሌላ ምክንያት በተለይም በመንቀሳቀስ መብት ላይ የሚደረጉ ገደቦች በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያ እንዲሁም በአማራ ክልል በዘንድሮ በጀት ዓመትም ተስተውለዋል። ለምሳሌ በሰመራ እና አካባቢው ለባለ3 እግር ተሽከርካሪዎች (በተለምዶ “ባጃጅ”) ከምሽት 2፡30 እስከ ጠዋት 12፡00 ሰዓት፣ ለመኪና ከምሽት 4፡00 ሰዓት እስከ ንጋት (ኢትዮ ጅቡቲ የሚሠሩ ከባድ መኪኖችን ሳይጨምር)፣ እንዲሁም በእግረኞች ላይ ከምሽቱ 5፡00 እስከ 12፡00 ሰዓት ባለው ክልክል የነበረ ሲሆን፣ ይህንን

የተላለፉ ሰዎችም በፖሊስ ጣቢያ ወይም በማረሚያ ቤት እንዲያድሩ ይደረጋል፡፡ ነዋሪዎች ተቃውሞ ለማሰማት አልያም ታጣቂ ቡድኖች በሚያደርጉት እንቅስቃሴዎች ሳቢያ መንገዶች የተዘጉበት ሁኔታም አለ፡፡ ለምሳሌ አፋር እና አማራ ክልልን የሚያገናኘው አደአር ወረዳ፣ ኤለውሃ ከተማ፣ በሰመራ ከተማ የተከለከለውን ሰልፍ በሚቃወሙ ነዋሪዎች ለተወሰኑ ቀናት ተዘግቶ ቆይቷል፡፡ በአማራ ክልል የተለያዩ ወረዳዎችም በታጣቂ ቡድኖች አልያም በነዋሪዎች መንገዶች ለተወሰኑ ቀናት ተዘግተው ቆይተዋል፡፡ በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በታኅሣሥ 12 ቀን 2016 ዓ.ም. ከአስተዳደራዊ እና መዋቅራዊ ጥያቄዎች ጋር ተያይዞ ተቃውሞ በሚያሰሙ ነዋሪዎች ከአዲስ አበባ ወደ ወላይታ ሶዶ የሚወስደው ዋናው የአስፋልት መንገድ ለ1 ቀን ያኽል ተዘግቶ ውሏል፡፡ በሲዳማ ክልል ሰሜናዊ ዞን ወንዶ ገነት ወረዳ ውስጥ በሚገኙ 3 ቀበሌዎች ውስጥ ሲነሳ ከነበረው የወሰን ማካለል ጥያቄ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ጊዜያት ከወንዶ ገነት ወረዳ ወደ ሀዋሳ የሚወስደው ዋና የአስፋልት መንገድ በተደጋጋሚ ጊዜ ለሰዓታት እንዲዘጋ ሆኗል፡፡ በጥቅምት 10 ቀን 2016 ዓ.ም. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት በማኅበራዊ ሚዲያ ያወጀው የሰዓት እላፊ ገደብ እንዲሁም አጠቃላይ የክልል የጸጥታ ሁኔታ በነዋሪዎች ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል፡፡

በአማራ ክልል ካለው ግጭት ጋር በተያያዘ ከከተማ ከተማ የሚደረግ እንቅስቃሴ አዳጋች ሆኗል፡፡ በየኬላው በመንግሥት የጸጥታ አካላት፣ እንዲሁም በፋኖ ኃይሎች ፍተሻ የሚደረግ ሲሆን፣ በሌላ በኩል በመንገድ ላይ ድንገት የተኩስ ልውውጥ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛው ማኅበረሰብ እጅግ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር የመንገድ የትራንስፖርት አማራጮችን አይመርጥም፡፡ በትጥቅ ግጭቱ ሳቢያ በክልሉ የነዳጅ አቅርቦት ላይ የተፈጠረውን እጥረት ተከትሎ፣ ነዳጅ በአብዛኛው መደበኛ ባልሆነ መንገድ (በጥቁር ገበያ) የሚሸጥ ሲሆን፣ የትራንስፖርት ክፍያን እጅግ እንዲንርና በሰዎች እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

ከዚሁ ከጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ እና በወንጀል መበራከት ምክንያት፣ እንዲሁም በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ወይም በታጣቂ ቡድኖች ለተከታታይ ቀናት ወይም ለአጭር ጊዜ በሚዘጉ መንገዶች ምክንያት የሚደርሱ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ችግሮች፣ በሸቀጦች ዋጋ እና በገቢ ላይ እንዲሁም በጤና እና ትምህርት አገልግሎቶች ተደራሽነት ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተጽዕኖዎች በዘንድሮ በጀት ዓመትም በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ እና በኦሮሚያ ክልሎችም ቀጥሏል፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከሚነሱ በርካታ የወሰን ማካለል ወይም የአስተዳደር ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች በሚነሱ ተቃውሞዎች ወይም የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በሚውስዷቸው እርምጃዎች የተነሳ ወይም በተለያዩ ታጣቂ ኃይሎች መንገዶች ለተወሰኑ ወይም ረዘም ላለ ጊዜ ተዘግተው ይቆያሉ፡፡ ለአብነት በመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. በኮሬ ዞን፣ ዳኖ ቀበሌ ከወረዳ መዋቅር ጥያቄ ጋር በተያያዘ በተፈጠረ የጸጥታ ችግር ከኮሬ ዞን ወደ ቡርጅ ዞን የሚወስደው ዋና መንገድ ለሰዓታት ተዘግቶ ቆይቷል፡፡ የቀድሞ አማሮ ልዩ ወረዳ (የአሁኑ ኮሬ ዞን) እና ጌዴኦ ዞን የሚያገናኘው ዋና መንገድ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") አባላት መሆናቸው በተነገረ ኃይሎች ከተዘጋ 3 ዓመት ያኽል ጊዜ እንደሆነውና መፍትሔ እንደሚሻ ታውቋል፡፡ በኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. በጋሞ ዞን አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ዘይሴ አካባቢ ሲነሳ ከነበረው የመዋቅር ጥያቄ ጋር በተያያዘ ከአርባ ምንጭ ከተማ ወደ ኮንሶ መስመር የሚወስደው መንገድ ለሰዓታት ተዘግቶ ቆይቷል፡፡

በትግራይ ክልል ኢሰመኮ ከተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ጋር በመተባበር ከሰኔ 30 እስከ ሐምሌ 23 ቀን 2015 ዓ.ም. በክልሉ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ያከናወነውን ክትትል ተመሥርቶ ይፋ ባደረገው ሪፖርት በአንዳንድ ሕግ አስከባሪ ተቋማት ሕገ ወጥ እና የዘፈቀደ እስራት እንደሚፈጸምና ይህንኑ በተመለከተ ከክልሉ የአስተዳደር እና የጸጥታ ኃላፊዎች ጋር የሚያደርገውን የውትወታ ሥራ የሚቀጥል መሆኑን መግለጹ ይታወሳል፡፡

ኢሰመኮ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. አስገድዶ መሰወርን እና ሰዎችን መደበኛ ባልሆኑ ማቆያ ቦታዎች መያዝን በተመለከተ ይፋ ባደረገው ሪፖርት እንዳሳሰበው "በመንግሥት ወኪሎች ወይም ከመንግሥት ፈቃድ ወይም ድጋፍ በተሰጣቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች ወይም በመንግሥት ስምምነት አንድን ሰው በማሰር፣ አፍኖ በመውሰድ፣ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ነጻነቱን በማጥፋትና፤ በቁጥጥር ሥር መዋሉን በመካድ፣ በመደበቅ፣ ያለበትን ቦታ ባለማሳወቅ ወይም ደብዛውን በማጥፋት ፈጽሞ ከሕግ ጥበቃ ውጪ እንዲሆን ማድረግ" አስገድዶ መሰወርን የሚያቋቁም ሲሆን፣ አስገድዶ መሰወር ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ነው። በተጨማሪም አንድን ሰው የሚገኝበት ቦታና ሁኔታ ሳይታወቅ በእስር መያዝ (Incommunicado Detention) ማለት በተለይ በከባድ ወንጀል ተጠርጥሯል የተባለን ሰው ለወንጀል ምርመራ በሚል ምክንያት ከቤተሰብ እና ከጠበቃ እንዳይገናኝ አድርጎ በእስር የማቆየትን ተግባር የሚገልጽ ፅንሰ ሐሳብ ሲሆን፤ ይህም ድርጊት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ነው።

ተይዘው የሚገኙበት ቦታ ሳይገለጽ፣ በአብዛኛው መደበኛ ባልሆኑ ማቆያ ቦታዎች ለሳምንታት ብሎም ለወራት ተይዘው የሚቆዩ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች አስገድዶ መሰወርን የሚያቋቁሙ ሁኔታዎችን በተመለከተ ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ብዛት በ2016 ዓ.ም. አሳሳቢ ሆኖ ቀጥሏል። በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ 9 ወራት በአዲስ አበባ 42 አቤቱታዎች የቀረቡ ሲሆን፣ በጅማ እና በባሕር ዳርም አስገድዶ መሰወርን የተመለከቱ አቤቱታዎች ቀርበዋል። ከቀረቡት አቤቱታዎች መካከል በኢሰመኮ ክትትል አማካኝነት ወደ መደበኛ ማቆያ በመዛወራቸውም ሆነ በመለቀቃቸው እልባት ያገኙ ቢኖሩም፣ አሁንም ያሉበት ቦታ የማይታወቁ ሰዎችን የተመለከቱ እና መፍትሔ ያልተሰጣቸው አቤቱታዎች አሉ። ኢሰመኮ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ከእነዚህ አቤቱታዎችና ጥቆማዎች በመነሳት ሲያደርግ በነበረው ክትትል መሠረት በርካታ የአስገድዶ መሰወርን ድርጊት የሚያቋቁሙ ድርጊቶች መከሰታቸውን አረጋግጦ ይፋዊ መግለጫዎች ማውጣቱ የሚታወስ ነው።

ቀደም ሲል በተጠቀሰው መግለጫው እንዳመላከተው የአስገድዶ መሰወር ድርጊት ሰለባ በሆኑ ሰዎች ላይ በቀጥታ ከሚደርሰው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በተጨማሪ በቤተሰብ ላይ የደረሰውን ዘርፈ ብዙ ጉዳት፣ የሥነ ልቡና ጉዳት እና ጭንቀት እንዲሁም በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ በሕግ ሥርዓት ላይ ያለውን እምነት የመሸርሸር አደጋ ኢሰመኮ በቅርበት ተመልክቷል።

ኢሰመኮ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. በ6ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ ወቅት ምርጫ ባልተካሄደባቸው የአፋር እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች፣ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግባቸው ውሳኔ በተሰጠባቸው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የመስቃን እና ማረቆ አካባቢዎች ውስጥ በሚገኙ 29 የምርጫ ክልሎች ውስጥ (ለ9 የተወካዮች ምክር ቤት እና ለ 26 የክልል ምክር ቤቶች) እና በሶማሊ ክልል የጅግጅጋ ከተማ የሚካሄዱትን የምርጫ ሂደቶች የሰብአዊ መብቶች ክትትል አድርጓል። ኢሰመኮ በተሻሻለው መቋቋሚያ አዋጁ ቁጥር 210/2012 አንቀጽ 6(11) መሠረት በ2013 ዓ.ም. የተካሄደውን ጠቅላላ ምርጫ እንዲሁም በቀድሞው ደቡብ ክልል ጥር 29 ቀን 2015 እና ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም. የተደረጉት ሕዝበ ውሳኔዎች የሰብአዊ መብቶች ክትትል በማድረግ ሪፖርቱን ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው።

የኢሰመኮ የምርጫ ወይም የሕዝበ ውሳኔ ወቅት የሰብአዊ መብቶች ክትትል በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ ወቅት እና በድኅረ ምርጫ ወቅት የሚከናወን ሲሆን፣ ክትትሉ በዋናነት በእነዚህ ሂደቶች ወቅት ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚገባቸውን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች እና መርሖችን መሠረት የሚያደርግ ነው። ከአራቱም ክልሎች በተመረጡ ከ200 በላይ የምርጫ ጣቢያዎች የተሰማሩ የኢሰመኮ የክትትል ባለሞያዎች በምርጫ ወቅት ካደረጉት የመስክ ምልከታ በተጨማሪ፣ መራጮችን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን፣ የፀጥታና የአስተዳደር አካላትን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል እጩዎችን፣ ልዩ ልዩ ታዛቢዎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን

በማነጋገር መረጃ እና ማስረጃ የሚሰበስቡ ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. የሚከናወነውን ቀሪ እና ድጋሚ ምርጫ አስመልክቶ የቅድመ ምርጫ ሂደት በተወሰኑ አካባቢዎች የሰብአዊ መብቶች ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል። የኢሰመኮ የአቤቱታ መቀበያ ነጻ የስልክ መስመር 7307 በምርጫው ሂደት ወቅት የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች እና ጥቆማዎችም አስተናግዷል።

በዚህም መሠረት የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች እና መርሖች በሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. ተሳታፊ የሆኑ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የመንግሥት አካላት፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የሚዲያ ተቋማት ሊያከብሯቸው፣ ሊፈጽሟቸው እና ሊያስፈጽሟቸው የሚገባ መሆናቸውን በማስታወስ፣ በተለይም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን በምርጫው ሂደት የመሳተፍ መብት እንዲረጋገጥ አስፈላጊውን በማድረግ ረገድ እንዲሁም በሕግ የተደነገጉ የምርጫ ወቅት መመሪያዎችን በማክበር ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ጥረት ሁሉ እንዲያደርጉ ኢሰመኮ ሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ ጥሪ አቅርቧል።

ኢሰመኮ በዚህ መሠረት ባካሄደው ክትትል ተመሥርቶ ይፋ ባደረጋቸው ግኝቶች፦

- በጸጥታ ችግር ምክንያት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫው እንዲሰረዝ ወይም እንዳይካሄድ ከወሰነበት የምርጫ ጣቢያዎች በስተቀር ምርጫው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች በተረጋጋ ሁኔታ እና አሳሳቢ የጸጥታ አደጋ እና ሥጋት ሳይደርስ መከናወኑ፤
- ምርጫ ቦርድ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመራጭነት በመሳተፍ ሂደት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ 7 ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን፣ ጉባ እና ድባጤ ወረዳዎች ያቋቋመ መሆኑ፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን፣ ማንቡክ ወረዳ ከድምፅ መስጫው ዕለት አንድ ቀን አስቀድሞ ተከስቶ ከነበረ የጸጥታ መደፍረስ ጋር በተገናኘ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ እስከ ረፋዱ 4 ሰዓት ድረስ ዘግይቶ ከጀመረባቸው የወረዳው አካባቢዎች በቀር ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በሰዓቱ የተጀመረና በሰዓቱ የተጠናቀቀ መሆኑ፤
- የኢሰመኮ የክትትል ባለሙያዎች በተሰማሩባቸው ሁሉም አካባቢዎች ክትትል እንዳያደርጉ በማንኛውም አካል ክልከላ ወይም መሰል እንቅፋት ያላጋጠማቸው መሆኑ፤ እንዲሁም
- ምርጫ ቦርድ በተለይም በድምፅ መስጫው ዕለት ከኢሰመኮ ለተላኩለት አሳሳቢ ጉዳዮች ፈጣን ምላሽና የማስተካከያ እርምጃዎችን የወሰደ መሆኑን አመላክቷል።

በምርጫ ክትትል ሪፖርቱ ከተካተቱና በሂደቱ በተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ከታዩ ክፍተቶች መካከል፡

- በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ወይም በ500 ሜትር አቅራቢያ የደንብ ልብስ የለበሱ (አልፎ አልፎም የታጠቁ) የጸጥታ አካላት ታይተዋል። ምንም እንኳን የጸጥታ አካላቱ የምርጫ ጣቢያውን ጸጥታ በሚያደፈርሱ ሁኔታዎች ላይ የተሳተፉባቸው አሉታዊ አጋጣሚዎች በዕለቱ ባይመዘገቡም፤ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በግልጽ ካልተፈቀደላቸው በቀር በምርጫ ጣቢያው 500 ሜትር አቅራቢያ መገኘት አልነበረባቸውም።
- ክትትሉ በተከናወነባቸው የተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ በሕግ ከተፈቀደላቸው ሰዎች (ከመራጮች፣ ከምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ከእጩ ወኪሎች፣ ከታዛቢዎችና ከቅሬታ

ሰሚ ኮሚቴ አባላት) ውጪ የሆኑ በተለይም የቀበሌ/ወረዳ አመራሮች እና የብልጽግና ፓርቲ አባላት በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መራጮች ላይ ጫና ሊያሳድሩ በሚችሉ ድርጊቶች ላይ ሲሳተፉ መስተዋላቸው ተመላክቷል፡፡



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Mussie Tewolde

# በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች አያያዝ

# በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች አያያዝ

## አጠቃላይ ምልከታ

ኢሰመኮ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራባቸው የሰብአዊ መብቶች ዘርፎች መካከል በፖሊስ ጣቢያዎች እና በማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ተጠርጣሪዎችን ወይም ታራሚዎችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ በመከታተል የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አንዱ ነው። ለዚህም ኢሰመኮ ፖሊስ ጣቢያዎችንና ማረሚያ ቦታዎችን እንዲሁም መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ቦታዎችን ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የመጎብኘት እና በተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች መብቶች ዙሪያ ያሉ የሕግ ማዕቀፎችን አተገባበር በተመለከተ ክትትልና ምርመራ እንዲሁም ዘርፈ-ብዙ የውትወታ ሥራዎችን ያከናውናል።

በ2016 በጀት ዓመት ኢሰመኮ በአጠቃላይ 287 ፖሊስ ጣቢያዎችን እና 52 ማረሚያ ቤቶችን የጎበኘ ሲሆን፣ ዝርዝሩ በሚከተለው ሠንጠረዥ ተካትቷል። በአማራ ክልል የሚካሄደው የትጥቅ ግጭት እና ከሐምሌ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ኢሰመኮ በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎችን አያያዝ በተመለከተ የሚያደርገውን መደበኛ የክትትል ሥራ አዳጋች አድርጎት ነበር።

| ቦታ | ፖሊስ ጣቢያ | ማረሚያ ቤቶች |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ | 8 | 4 |
| አፋር | 14 | 2 |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 25 | 3<br>በተጨማሪም 3 መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ቦታዎች |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | 38 | 5 |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 20 | 6 |
| ድሬደዋ | 8 | 1 |
| ጋምቤላ | 15 | 4<br>በተጨማሪም 5 መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ቦታዎች |
| ማእከላዊ ኢትዮጵያ | 18 | 1 |
| ሲዳማ | 13 | 1 |
| ኦሮሚያ | 87 | 16 |
| ሶማሊ | 24 | 7 |
| ትግራይ | 17 | 2 |

በአማራ ክልል የአስቸኳይ ጊዜ መምሪያ ኮማንድ ፖስት ለሕዝብ ይፋ ካደረጋቸው እስሮችና ቦታዎች ውጪ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በአስቸኳይ ጊዜ ዐውድ ውስጥ በተለይም በባሕር ዳር፣ ደብረ ታቦር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ጎንደር፣ ላሊበላ፣ መካነሰላም፣ ቆቦ እና ሸዋ ሮቢት ከተሞች የተፈጸሙ የዘፈቀደ እስሮች ስለመኖራቸው ኢሰመኮ ከታሳሪ ቤተሰቦች እና እማኞች በርካታ አቤቱታዎች ደርሰውታል። በመንግሥት የጸጥታ አካላት የሚታሰሩ ሰዎች በአብዛኛው "ለታጣቂ ቡድኑ ድጋፍ ታደርጋላችሁ" እና/ወይም «የጦር መሣሪያ ደብቃችኋል» በሚል ሲሆን፣ የተያዙ ሰዎች አያያዝ ሰብአዊነት የጎደለው መሆኑን ጠቅሰው የታሳሪ ቤተሰቦች በተደጋጋሚ ለኢሰመኮ አቤቱታ አቅርበዋል። በሌላ በኩል በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች (በተለምዶ "ፋኖ") በግጭት ዐውድ ውስጥ ወይም በተለያየ ቦታ

ለተለያየ ወቅት አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በሚቆዩበት ጊዜ ማረሚያ ቤቶችን እና ፖሊስ ጣቢያዎችን በማጥቃት ተጠርጣሪዎችንና ታራሚዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማስለቀቃቸውንም የሚያመለክቱ በርካታ ጥቆማዎች ለኢሰመኮ ይደርሳሉ። በተጨማሪም ታጣቂ ኃይሎቹ አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በሚቆዩበት ወቅት ወንጀል ፈጽመዋል አልያም የመንግሥት ኃይሎችን ደግፈዋል በሚል የተጠረጠሩ ሰዎችን ለተለያዩ ኢሰብአዊ አያያዝ እና ቅጣት ብሎም ለግድያ መዳረጋቸውን የሚያመላክቱ መረጃዎች እና ጥቆማዎች ለኢሰመኮ ቀርበዋል።

በሁሉም ክልሎች ለማለት በሚያስችል ሁኔታ የዘፈቀደ እስር፣ የጅምላ እስር ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ባለማክበር ሰዎችን ይዞ የማቆየት፣ መደበኛ ባልሆኑ ማቆያ ቦታዎች ሰዎችን የመያዝ ተግባራት ተፈጽመዋል። በተለይም ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ አፈጻጸምና ዐውድ ጋር ተይይዞ መደበኛ ያልሆኑ ማቆያ ቦታዎች በሚወሰዱ ሰዎች ላይ ችግሩ ተባብሶ ተስተውሏል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ ፍርድ ቤት ቀርበው የዋስትና መብታቸው የተከበረላቸው ሰዎች "በኮማንድ ፖስት ይፈለጋል፤ የበላይ ትእዛዝ ይምጣ" በሚል ሳይፈቱ ለረዥም ጊዜ በእስር የሚቆዩ መሆኑ፤ በተለይም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ በርካታ ሰዎች በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ "በወቅታዊ ጉዳይ ነው" በሚል ምክንያት ብቻ ለረዥም ጊዜ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ቆይተው እንደነበር ታውቋል።

በአዋሽ አርባ የሚገኘው የተጠርጣሪዎች ማቆያ በአካባቢው ባለው ከፍተኛ ሙቀት እንዲሁም ከታሳሪዎቹ መደበኛ የመኖሪያ አካባቢና ከሕክምና እና ሌሎች አገልግሎት ማእከላት ባለው ርቀት ምክንያት ታሳሪዎቹ የቤተሰብ ጥየቃ እና የሕክምና አገልግሎት አለማግኘትን ጨምሮ ለሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተዳርገዋል። የካቲት 7 ቀን 2016 ዓ.ም. በአካባቢው በተከሰተ አውሎ ንፋስ ምክንያት በቦታው የተያዙ ሰዎች ለጉዳትና ለሕመም የተዳረጉ ስለመሆናቸው ኢሰመኮ አቤቱታዎች እና ጥቆማዎች የደረሱት ቢሆንም በአካል ተገኝቶ ለመጎብኘት ያደረገው ጥረት አልተሳካም።

ኢሰመኮ በተለይም በ2014 እና በ2015 ዓ.ም. ክትትል ባደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች ያቀረባቸው ምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም ሲከታተል እና በክልል እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከፖሊስ ጣቢያዎቹ ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም የሲቪክ ማኅበረሰቦች አባላትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት የውትወታ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። ክትትል በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች በርካታ መሻሻሎች ተስተውለዋል። ኢሰመኮ በተለይም የማቆያ ቦታዎችን በተመለከተ የሚያደርገው መደበኛ ክትትል እና ያለቅደመ ማስጠንቀቂያ የማቆያ ቦታዎችን የመጎብኘት ሥራ እና ስለኃላፊነቶቹ የተሟላ አረዳድ እንዲሁም በጎ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል።

ለምሳሌ በ2015 ዓ.ም. በተደረጉ የፖሊስ ጣቢያ ክትትሎች የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች አፈጻጸም ክትትል መሠረት በአብዛኞቹ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ከቤተሰቦቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር እንዲገናኙ የሚፈቀድ መሆኑ ወይም ክልከላ አለመኖሩ፣ በፖሊስ ጣቢያዎች ላይ በሚደረግ ክትትል አማካኝነት ያለአግባብ እስር ላይ የነበሩ በርካታ ተጠርጣሪዎች መፈታታቸው፣ በአዲስ አበባ የተወሰኑ "ሞዴል" የማቆያ ቦታዎች ተገንብተው ሥራ መጀመራቸው፣ በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች (ለምሳሌ በአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ) በሚገኙ የተጠርጣሪዎች ማቆያ ክፍሎች የተጠርጣሪዎች አያያዝን ለመቆጣጠር የደኅንነት ካሜራዎች አገልግሎት ላይ መዋላቸው፤ በአብዛኛው ተጠርጣሪዎች ወደ ጣቢያ ሲገቡ በአግባቡ የሚመዘገቡ መሆኑ፣ በአንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች የምግብ አገልግሎት የሚቀርብ መሆኑ እና ኢ-ሰብአዊ አያያዝ የፈጸሙ የተወሰኑ የጸጥታ አባላትን ተጠያቂ ማድረግ መጀመሩ ከታዩ አዎንታዊ መሻሻሎች መካከል ናቸው። ለምሳሌ በሶማሊ ክልል የፖሊስ ጣቢያዎችን አያያዝ በተመለከተ ድብደባና ኢ-ሰብአዊ የሆኑ የተጠርጣሪዎች

አያያዝ መቀነስ፣ ለተጠርጣሪዎች የተመደበ የምግብ በጀት ባይኖርም ለፖሊስ አባላት ከሚዘጋጀው ምግብ ላይ ቤተሰብ ምግብ ለማያቀርብላቸው ተጠርጣሪዎች በተወሰነ ደረጃ ምግብ መቅረቡ፣ የቤተሰብ ጉብኝትን በተመለከተ በጣቢያዎች ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር ጥሩ መሻሻሎች መታየታቸው፣ እንዲሁም ተጠርጣሪን በ48 ሰዓት ፍርድ ቤት ማቅረብ ላይ መልካም የሚባል መሻሻል አንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል።

ማረሚያ ቤቶችን በተመለከተ ኢሰመኮ በማረሚያ ቤቶች ለሚያካሄደው ክትትልና ምርመራ የፌዴራል እና የክልል የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የሚያደርጉት ትብብር እና ድጋፍ፣ ኢሰመኮ ከፌዴራል መንግሥት እና ከክልል መስተዳደር ጋር ባደረገው ተደጋጋሚ ምክክር እና ውትወታ መሠረት በአንዳንድ ክልሎች ለታራሚዎች የሚመደበው ዕለታዊ የምግብ በጀት ከፍ እንዲል መደረጉ፣ እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት እንዲሁም በተወሰኑ ክልሎች ማረሚያ ቤቶች ውስጥ በታራሚዎች፣ በማረሚያ ቤቶች አመራሮች እና አባላት መካከል ያለው መልካም ግንኙነት ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም በፌዴራል መንግሥት እንዲሁም በክልሎች ማረሚያ ቤቶች ውስጥ በሚገኙ ታራሚዎች ላይ አካላዊ ጥቃቶች እንዳይፈጸም በየማረሚያ ቤቶች ያለው ክትትል እና ቁጥጥር፣ ኢሰመኮ ከጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ጋር ባደረገው የውትወታ ሥራ ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ የቆየው የነጻ ሕክምና አገልግሎት ከኅዳር 12 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ አገልግሎቱ ያለክፍያ እንዲቀጥል ለማድረግ መቻሉ፣ እንዲሁም በበርካታ ማረሚያ ቤቶች ለታራሚዎች የሚቀርብ የሕክምና አገልግሎት እየተሻሻለ መምጣቱ፣ በአንዳንድ ማረሚያ ቤቶች ለሚገኙ ሴት ታራሚዎች እና ተከሳሾች በእርግዝና ወቅት እና በወሊድ ጊዜ የሚደረገው የሕክምና ድጋፍ ክትትል እየጨመረ መምጣቱ፣ እንዲሁም በተለያዩ ማረሚያ ቤቶች የመኝታ ፍራሽና አልጋ፣ ብርድ ልብስ፣ እና የጽዳት መጠበቂያ ዕቃ አቅርቦት እየተሻሻለ መምጣቱን መመልከት ተችሏል። ለምሳሌ በሶማሌ ማረሚያ ቤቶች በመጠን በቂና ንጹሕ ምግብ በተሻለ መልኩ መቅረቡ (የተለያየ ተመጣጣኝ የሆነ ምግብ አለመቅረቡ እንዳለ ሆኖ)፣ የታራሚዎች ኢ-ሰብአዊ አያያዝ መቀነስ፣ የቆረሃይ ዞን ማረሚያ ቤት ከዞኑ ፖሊስ ጣቢያ ጋር እንዲለያዩ መደረጉ፣ በሊበን ዞን ማረሚያ ቤት ታዳጊ ታራሚዎች ለአካለ መጠን ከደረሱት በአጥር ተለይተው እንዲያዙ መደረጉ፣ ለታራሚዎች እንደ ፍራሽና ንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች የመሳሰሉት መሠረታዊ አቅርቦቶች ላይ መሻሻል መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል።

ሆኖም በፖሊስ ጣቢያም ሆነ በማረሚያ ቤቶች ተይዘው የሚቆዩ ሰዎች አያያዝን በተመለከተ አሁንም በሀገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ዘላቂ መፍትሔ ሊሰጣቸው የሚገባ እና በዋናነት በ2 ደረጃዎች ሊከፈሉ የሚችሉ አሳሳቢ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ።

## ከፋይናንስ እና አስተዳደር ጋር የተያያዘ

በዚህ ክፍል ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ እና በተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች አያያዝ እና የሰብአዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች በዋነኝነት ከበጀት ወይም የገንዘብ ዐቅም እጥረት ጋር የሚያያዙት ናቸው። ይህ ችግር በሁሉም ክልሎች በተኀበኙ የፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች የተስተዋለ ሲሆን፣ በኢሰመኮ የ2014 እና 2015 በጀት ዓመት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርቶች የተመላከተ እና ኢሰመኮ በሚያከናውናቸው የምክክር እና የውትወታ ሥራዎች ሁሉ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጉዳይ ነው።

በተለይም በ2016 ዓ.ም. በአዲስ መልክ በተዋቀሩት የደቡብ ምዕራብ፣ የማእከላዊ ኢትዮጵያ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች፣ እንዲሁም በብዙ መልኩ በሲዳማ ክልል ክትትል የተካሄደባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች በሂደት ላይ በሚገኙ የክልሎቹ አስተዳደራዊ እና ተያያዥ የበጀት አስተዳደር ጉዳዮች ምክንያት ለዚሁ ዓላማ ባልታቀዱ ወይም ጊዜያዊ በሆኑ ቦታዎች የተዘጋጁ ናቸው። ስለሆነም የንጽሕና

ጉድለት፣ የውሃ እና የመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ እንዲሁም የጤና እና የምግብ አገልግሎት በቂ አለመሆን ከተስተዋሉ ችግሮች ዋነኞቹ ናቸው። ለተጠርጣሪዎች ምግብ የማይቀርብ መሆኑ እንዲሁም ነጻ የሕክምና አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤ ከፖሊስ ጣቢያዎቹ የሰው ኃይል እጥረት እና የዐቅም ማነስ ጋር ተያይዞም በአንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች (ለምሳሌ በደቡብ ምዕራብ፣ ቤንች ሸኮ ዞን ፖሊስ መምሪያ) በምርመራ ወቅት ድብደባ እና ሌሎች ተግባራት መፈጸማቸውን ማወቅ ተችሏል። በተመሳሳይ መልኩ በርካታ በሸገር ከተማ የሚገኙ የፖሊስ መምሪያዎች በአዲስ መልኩ የተደራጁ በመሆኑ የተጠርጣሪዎች ማቆያዎች የተጨናነቁና ንጽሕናቸው ያልተሟሉ ናቸው።

ከሰው ኃይል እና ከበጀት እጥረት ጋር ተያይዞ ለምሳሌ በአፋር ክልል የበጀት እጥረት፣ ከፍተኛ የሆነ የቢሮ ጥበትና ረዘም ላለ ጊዜ እድሳት ያልተደረገላቸው መሆኑ፣ እንደ የተጠርጣሪዎች ማረፊያ፣ መጸዳጃ እና ሻወር ያሉ መሠረታዊ ክፍሎች አለመሟላት፣ የቁሳቁስ/የተሽከርካሪ አለመሟላት በ2016 ዓ.ም. ጉብኝት በተካሄደባቸው የፖሊስ ጣቢያዎች ከታዩ ችግሮች መካከል ናቸው።

በአብዛኛው ክልሎች በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች የምግብ እና የውሃ አቅርቦት የማይደረግ ሲሆን፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ በፖሊስ ጣቢያዎች ማደሪያ ክፍሎች ፍራሽ፣ የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲሁም ለሴት ተጠርጣሪዎች የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች አቅርቦት የለም። ለምሳሌ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጉብኝት በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች የተስተዋሉ ችግሮች በአብዛኛው ከማቆያ ቦታዎች ሁኔታ እና ከአገልግሎት አቅርቦት ችግሮች ጋር የተያያዙ ናቸው። በአፋር ክልል ክትትል በተደረገባቸው የፖሊስ ጣቢያዎች የተስተዋሉ ችግሮች በአብዛኛው በተለይም ከክልሉ የአየር ንብረት (ከፍተኛ ሞቃታማነት) ጋር በተያያዘ የፖሊስ ጣቢያዎች በበጀት እጥረት ሳቢያ ባሉ የውሃ፣ የክፍል ማቀዝቀዣ እንዲሁም ሌሎች መሠረተ ልማት አቅርቦት እጥረት ምክንያት የሚከሰቱ ናቸው። በጋምቤላ ክልል የሚገኙ የአብዛኛው ማረሚያ ቤቶች ማቆያ ክፍሎች በ2015 ዓ.ም. ከነበረው ሁኔታ አንጻር ብዙም መሻሻሎች እንዳላሳዩ ነገር ግን የማጃንግ ዞን ማረሚያ ቤት ተጨማሪ ክፍሎች በመገንባቱ እስረኞች በቂ የማደሪያ ክፍል ማግኘታቸው እንደ እመርታ ይጠቀሳል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የበጀት እጥረቱ ችግር ተጠርጣሪዎችንና ታራሚዎችን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት የሚዳርግ ነው። ለምሳሌ በአፋር ክልል በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች ታዳጊዎች ለአካለ መጠን ከደረሱ ተጠርጣሪዎች ጋር አብረው እንዲቆዩ የሚደረግ መሆኑ፣ በጋላፊ ንዑስ ፖሊስ ጣቢያ ምንም ዐይነት የማቆያ ክፍል ያልተሠራ በመሆኑ ተጠርጣሪዎች ክፍት ሜዳ ላይ እንዲቆዩ የሚደረግ ሲሆን፣ በአፋምቦ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ እና በአርጎባ ልዩ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ደግሞ ሴት ተጠርጣሪዎች የተለየ ማቆያ ክፍል ባለመኖሩ፣ ደጅ ወይም ከማደሪያ ክፍል ውጪ እንዲያድሩ ተደርጓል። በአፋር ክልል በገለአሉ ፖሊስ ጣቢያ የሚገኘው ማቆያ ክፍል የአየር ማስገቢያ ወይም መስኮት የሌለው በመሆኑ ተጠርጣሪዎች ከአካባቢው ሙቀት ጋር ተዳምሮ ለከፍተኛ ችግር ይዳረጋሉ። በዚሁ በገለአሎ ፖሊስ ጣቢያ የሴት እና የወንድ ማደሪያ ክፍል በአግባቡ በአጥር ያልተለየ ሲሆን፣ የሴት ተጠርጣሪዎች ማቆያ ክፍሉ በር የለውም።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ጉብኝት በተደረገባቸው ፖሊስ ጣቢያዎች በሙሉ ታዳጊዎች ከሌሎች ተጠርጣሪዎች ተለይተው እንዲቆዩ ማድረግ የሚያስችል ክፍሎች/ቦታዎች አልተዘጋጁም። በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች የማደሪያ ክፍሎችን በተመለከተ በ2015 ዓ.ም. ከነበረው ሁኔታ አንጻር ብዙም መሻሻሎች አልታዩም፤ በተለይ የጋምቤላ ከተማ፣ ሜጢ እና ዲማ ፖሊስ ጣቢያዎች እጅግ አሳሳቢ በሚባል ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ሆኖም በአንጻሩ በጋምቤላ ወረዳ፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ እና ጂኮው ወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጨማሪ ክፍሎች መገንባታቸው ከተለዩ መልካም ነገሮች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

የፖሊስ ጣቢያዎች የበጀት እጥረት በአንዳንድ ሁኔታዎች ሌሎች ተያያዥ ችግሮች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሲያስከትሉ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ በአፋር ክልል ፍርድ ቤት ክስ ተመሥርቶባቸው በመደበኛ ቀጠሮ ላይ ያሉ ተጠርጣሪዎችን ወደ ሚመለከተው ማረሚያ ቤት በመላክ ረገድ የማረሚያ ቤት ከፖሊስ ጣቢያዎች መራቅ፣ በተወሰኑ ወረዳዎች የፍርድ ቤት ዳኞችና ዓቃቤ ሕግ አባላት በወቅቱ አለመገኘት ረዘም ላለ ጊዜ የቆዩ ችግሮች ናቸው፡፡

የተሟላ እና ወጥ የሆነ የታራሚዎች መረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመኖርም በበርካታ ማረሚያ ቤቶች መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ ታራሚዎች ወደ ማረሚያ ቤት ስለመግባታቸው፣ ወደ ሌላ ማረሚያ ቤት ስለመዘዋወራቸው፣ ስለመለቀቃቸው፣ ስለመሞታቸው እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች ለቤተሰቦቻቸው ወይም ተጠሪዎቻቸው ወጥ በሆነ ሁኔታ መረጃ የሚደርስበት ሥርዓት መዘርጋቱ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመከላከል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት እና ከበጀት ጋር ከተያያዙ ችግሮች በተጨማሪ ለምሳሌ በሶማሊ ክልል ተጠርጣሪዎች በፖሊስ ጣቢያ ቆይታቸው ቅሬታ የሚያቀርቡበት ሥርዓት አለመኖሩ፣ የአፍዴር ዞን ፖሊስ ጣቢያና የሀርጌሌ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ አንድ ላይ መሆኑ የፈጠረው መጣበብ በከፍተኛና በዝቅተኛ ወንጀል የተጠረጥሩ ግለሰቦች በአንድ ላይ እንዲቆዩ መደረጉ የሚሉት አሳሳቢ ሁኔታዎች ተለይተዋል፡፡ በጅግጂጋ ከተማ፣ ገረብአሴ የተጠርጣሪዎች ማቆያ በየትኛው የመንግሥት መዋቅር ሥር እንዳለ ለሕዝብ ግልጽ አለመደረጉ፣ ለበርካታ ወራት ምርመራ ሳይደረግባቸውና ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ የቆዩ የአልሸባብ ታጣቂዎችን ጨምሮ በሽብር ወንጀል የተጠረጠሩ በርካታ ሰዎች መኖራቸው፣ የተጠርጣሪ ቤተሰቦች መጎብኘት የማይፈቀድላቸው መሆኑ፣ በዋናነት የተስተዋሉ አሳሳቢ ችግሮች ናቸው፡፡ ኢሰመኮ እነዚህ ችግሮች እንዲስተካከሉ ምክረ ሐሳብ የሰጠ ሲሆን በቅርቡ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ከፌዴራል ፖሊስ ጋር በመሆን የተጠርጣሪዎቹ ምርመራ እንዲጀመር መደረጉ አበረታች ቢሆንም በሚያስፈልገው ፍጥነት እና መጠን ክፍተቶቹን የመቅረፍ ጥረቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ማረሚያ ቤቶችን በተመለከተ ግልጽና ወጥ የሆነ ሀገር አቀፍ የይቅርታና የአመክሮ አሰጣጥ ሥርዓት አለመኖሩም በተለይ ለማረሚያ ቤቶች መጨናነቅ መንስኤ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በማረሚያ ቤቶች የሚስተዋለው የንጽሕና፣ የመሠረተ ልማት፣ የጤና እና የምግብ አገልግሎት እጥረት ወይም አለመኖር ችግር በሀገር አቀፍ ደረጃ ዘላቂ መፍትሔ የሚሻ ነው፡፡ በተለይም የማረሚያ ቤቶችን ነፍስ ወከፍ የምግብ ወጪ በሁሉም ክልሎች ወጥ የሆነ ቀመር ወይም አሠራር ማበጀት እና በየወቅቱ ከኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ሊዘገይ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የአንድ ታራሚ የነፍስ ወከፍ የምግብ ዕለታዊ በጀት 25 ብር ሲሆን፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 40 ብር፣ በኦሮሚያ ክልል 53 ብር ነው፡፡

ለታራሚዎች የሚቀርቡ ለምሳሌ የስልጠና እና የትምህርት ዕድሎች የተሟላ አለመሆን፣ ወይም ከእናቶቻቸው ጋር በእስር ቤት ለመቆየት ለተገደዱ ሕፃናት ምቹ አካባቢ አለመኖር ከበጀት እጥረት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ችግሮች ቢሆኑም፣ አንዳንድ ከአስተዳደር ጋር ብቻ የሚገናኙ ሆኖም በታራሚዎች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ከፍተኛ መሻሻል የሚያመጡ (ለምሳሌ ታራሚዎችን ለቤተሰቦቻቸው/ጠያቂዎቻቸው ቅርብ ወደሆኑ ማረሚያ ቤቶች ማዘዋወር፣ የፍሳሽና ሌሎች የጽዳት ተግባራትን ፍጥነት ወይም አቅርቦት ማሻሻል) ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

## የተጠርጣሪዎች እና የታራሚዎች መብቶች

ሌሎች ችግሮች መካከል ከተጠርጣሪዎች መብቶች ጥበቃ/መከበር ጋር የተያያዙና አፋጣኝ መፍትሔ ሊሰጣቸው የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ ተላላፊ ሕመም ያለባቸው ተጠርጣሪዎችን እና ታራሚዎችን በአፋጣኝ የመለየት እና ከሌሎች ተጠርጣሪዎች በተለየ ቦታ ማቆየት፣ በተመሳሳይ መልኩ የማኅበረ ሥነልቦና ጉዳት ያለባቸውን ወይም በአካል ጉዳተኝነታቸው፣ በአረጋዊነታቸው ወይም በሌላ ምክንያት ልዩ ፍላጎት /እንክብካቤ/ (special needs) ለሚያስፈልጋቸው ተጠርጣሪዎች ከአቅርቦት ጀምሮ ሌሎች አፋጣኝ መፍትሔዎችን ማፈላለግ አንዱ ተጠቃሽ ችግር ነው። ታራሚዎች ወደ ማረሚያ ቤት ሲዛወሩ ከሌሎች ታራሚዎች ጋር ከመገናኘታቸው በፊት መሠረታዊ ምርመራ በማድረግ እንዲሁም በእራሳቸው ወጪ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ለሚፈልጉ ታራሚዎች ይህ የሚፈቀድበት አሠራር መዘርጋትን ጨምሮ በአሠራር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን መለየት እና አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት ይገባል።

በማረሚያ ቤት፣ በፖሊስ ጣቢያ ምርመራ ወቅትም ሆነ በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚቆዩበት ወቅት በተጠርጣሪዎች ላይ የሚደርሱ ድብደባዎች እና ሌሎች ተግባራት በአፋጣኝ ሊቆሙ የሚገባ እና ይህንን ተግባራት በፈጸሙ አባላት ላይ ተገቢው ምርመራ ተደርጎ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ ነው። ለምሳሌ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተጠርጣሪዎች ላይ ድብደባ የሚፈጽሙ፤ በካቴና በማሰር ኢሰብአዊ የሆኑ ተግባራትን የሚፈጽሙ የፖሊስ አባላት ስለመኖራቸው ኢሰመኮ በተለያዩ ጊዜያት ባደረጋቸው ክትትሎች ለማወቅ ችሏል። በአፋር ክልል፣ በፈንቲ ረሱ ማረሚያ ቤት እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተወሰኑ ማረሚያ ቤቶች ታራሚዎች ለሠሩት የጉልበት ሥራ የማይከፈላቸው መሆኑን ለኢሰመኮ አስረድተዋል። በጋምቤላ ክልል በአንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች ኢሰብአዊ አያያዝ አሁንም የቀጠለ ሲሆን፣ ለምሳሌ በአኝዋ ዞን አቦቦ ወረዳ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት ግቢ እና ከግቢ ውጪ አልቄሮ የውሃ ግድብ በመውሰድ ተጠርጣሪዎችን ግድብ ውስጥ በመንከር እና ተደጋጋሚ ድብደባ እና ጭካኔ የተሞላበት አያያዝ በመፈጸሙ 3 ተጠርጣሪዎች ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ተጠርጣሪን ፍርድ ቤት ሳያቀርቡ ለረጅም ጊዜ የማሰር ተግባር በአንዳንድ ክልሎች ታይቷል።

በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በኦሮሚያ፣ ክልሎች በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች በአስፈጻሚ አካላት ትእዛዝ ወይም "በአደራ" ወይም ማንነታቸው ባልተገለጸ የመንግሥት አካላት እና ባለሥልጣናት ትእዛዝ ተይዘው ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ ሰዎች፣ አልያም የፍርድ ቤት ትእዛዞች በመተላለፍ ተይዘው እንዲቆዩ የሚደረጉ ሰዎች መኖራቸውንም ኢሰመኮ ተመልክቷል። ለምሳሌ በአፋር ክልል፣ በዱሊሳ ወረዳ እና በሃሩካ ወርዳ ጣቢያዎች በአስፈጻሚ አካላት ትእዛዝ መታሰራቸው የተገለጸ 8 አረጋውያን ተገኝተዋል። ኢሰመኮ የአረጋውያኑን ጉዳይ በተመለከተ የሚያደርገውን ክትትል ይቀጥላል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በከማሽ እና አሶሳ ዞን ማረሚያ ቤቶች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ሳያገኙ ከ4 ዓመታት በላይ በጊዜ ቀጠሮ ገብተው በእስር ላይ የሚገኙ ጉዳያቸው በፌደራል ፍትሕ አካላት የተያዙ ተጠርጣሪዎች ጉዳይ ኢሰመኮ ቀጣይ ክትትል እያደረገባቸው ከሚገኙ ጉዳዮች መካከል ነው። በክልሉ ማረሚያ ቤቶች ከታዩ አሳሳቢ ችግሮች መካከል የመተከል ዞን ማረሚያ ቤት ውስጥ በታራሚዎች መኖሪያ ክፍሎች ከፍተኛ የሆነ የትኋን ተባይ ስርጭት መኖር፤ በአሶሳ፣ በመተከልና ከማሽ ዞን ማረሚያ ቤቶች እንደቅጣት ታራሚዎችን እጅና እግራቸውን በካቴና ለቀናት የማሰርና የማሰቃየት ተግባራት መኖራቸው የሚሉት ይገኙበታል። በጋምቤላ ክልል በአንዳንድ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ጭካኔ የተሞላበት ከፍተኛ ድብደባ እንደሚፈጸም (ለምሳሌ የአኝዋ ዞን ማረሚያ ቤት) ለማወቅ ተችሏል።

በኦሮሚያ ክልል ካለው የጸጥታ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በመንግሥት የአስተዳደር፣ የሚሊሻና ሌሎች የጸጥታ አካላት ሰዎችን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በዘፈቀደና በጅምላ ማሰር፤ እንዲሁም በሕግ ቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኃላ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡና ክስ ሳይመሠረትባቸው ለረጅም ጊዜ በእስር ማቆየት በስፋት ይስተዋላል። ሰዎች በሕግ ቁጥጥር ሥር በሚውሉበት ጊዜ በክልሉ ሚሊሻ፣ በፖሊስና በመከላከያ ሰራዊት አባላት ድብደባ መድረሱ፣ በፖሊስ ጣቢያ እንዲሁም በጊዜያዊ ማቆያዎች ድብደባ፣ በካቴና ማሰርና ሌሎች ኢ-ሰብአዊ ተግባራት መፈጸማቸውን ኢሰመኮ ከተጎጂዎች፣ ከተጎጂ ቤተሰቦች እና ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ያሰባሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ።

በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎች ቃል በሚሰጡበት ጊዜ ያለመናገር መብት እንዳላቸው መግለጽን ጨምሮ የሚሰጡት ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት እንደሚቀርብባቸው በፖሊስ አባላት የማይነገራቸው መሆኑ፣ እጅ ከፍንጅ የሆነ ወንጀል ያልፈጸሙ ተጠርጣሪዎችን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በቁጥጥር ሥር ማዋል፣ እንዲሁም በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች ተጠርጣሪዎችን በተያዙ በ48 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት አለማቅረብ፣ ተጠርጣሪዎችን እንደጥፋተኛ ወይም እንደተፈረደባቸው ታራሚዎች መቁጠር፣ ለፖሊስ የሚሰጡት ቃል በሚገባቸው ቋንቋ ተነቦላቸው እንዲፈርሙ አለማድረግ፣ ተጠርጣሪዎች የቀረበባቸውን ክስና ምክንያት በሚገባቸው ቋንቋ በዝርዝር ወዲያውኑ አለመናገር እና መሰል ከሕግ አተገባበር ጋር የተያያዙና በፖሊስ ጣቢያ የተስተዋሉ ችግሮች በመሠረቱ አፋጣኝ እና ዘላቂ መፍትሔ ሊሰጣቸው የሚችሉ ናቸው። በሀገር አቀፍ ደረጃ ወይም በክልል ደረጃ በሚወሰዱ የውሳኔ እርምጃዎች መሠረት መፍትሔ ሊያገኙ ከሚችሉ ችግሮች መካከል ለምሳሌ በቀላል ወንጀል የተጠረጠሩ ግለሰቦችን ጨምሮ መጥሪያ፣ የፍርድ ቤት የመያዣ እና የብርበራ ትእዛዝ የመሳሰሉ ሁኔታዎች ሳይሟሉ በቁጥጥር ሥር የማዋል እና በዘፈቀደ የመኖሪያ ቦታ እና የአካል ፍተሻ ማካሄድ የመሳሰሉት ይገኙበታል።

በተጨማሪም በወንጀል ጉዳይ ትፈለጋላችሁ በሚል በተለይ በአመራር እና ግለሰቦች ሕጉን ባልተከተለና በቂ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ግለሰቦች በጸጥታ አካላት ቁጥጥር ሥር ውለው ከቀናት ቆይታ በኋላ ያለምንም ክስ የሚለቀቁ፣ እንዲሁም በአንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች በፍትሐ ብሔር ጉዳይ በቁጥጥር ሥር ውለው ለቀናት ታስረው የሚለቀቁ ሰዎች መኖራቸውን ማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ከፖለቲካና ወቅታዊ የጸጥታ ሁኔታ ጋር በተያያዘ የሚያዙ ግለሰቦች በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውለው ፖሊስ ጣቢያ ከገቡ በኋላ መደበኛ ወዳልሆኑ ስፍራዎች ተወስደው የሚያዙበት ሁኔታ መደጋገም፤ በቀላልና የዋስትና መብትን በማያስነፍጉ ወንጀሎች የሚያዙ ተጠርጣሪዎችን በፍጥነት ቃል ተቀብሎ በዋስ ከመልቀቅ ይልቅ ከብዙ ቀናት የፖሊስ ጣቢያ የእስር ቆይታ በኋላ በነጻ የሚለቀቅበት ሁኔታ በብዛት የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተጠርጣሪዎችን በክልሉ አድማ ብተና እንዲሁም በመከላከያ ካምፖች ጨምሮ መደበኛ ባልሆኑ የማቆያ ቦታዎች አስሮ የማቆየት ተግባራት ተስተውለዋል።

በተለይም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ እና በኦሮሚያ ክልሎች በጸጥታ ችግር ሳቢያ በሚዘጉ መንገዶች እና ተያያዥ የአቅርቦት እጥረትና የሸቀጦች ዋጋ መጨመር ምክንያት በበርካታ ማረሚያ ቤቶች የጤና አገልግሎት ተስተጓጉሏል።

በሸገር ከተማ በሚገኙ ማቆያ ቦታዎች የዋስትና መብታቸው የተከበረላቸው ተጠርጣሪዎች የተሽከርካሪ ባለቤትነት ማረጋገጫ፣ የቤት ካርታ ወይም ቋሚ ሥራ እና ደሞዝ ያለው ዋስ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁበት አሠራር መኖሩን የሚያመላክቱ መረጃዎች ለኮሚሽኑ ደርሰዋል።

በትግራይ ክልል በሚገኙ የተወሰኑ ማረሚያ ቤቶች እና ፖሊስ ጣቢያዎች በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ክትትል የተካሄደ ሲሆን፣ የተለዩት ግኝቶች በአብዛኛው የክልሉን የፍትሕ እና የጸጥታ

መዋቅር ከጦርነት በኋላ በአዲስ መልኩ ከማደራጀት አስፈላጊነት እና ከበጀት ጉዳዮች ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ ክትትል የተደረገባቸው ሁሉም ማቆያ ቦታዎች ውሃ፣ መጸዳጃ ቤት፣ ንጹሕ የማደሪያ ክፍል እና መሠረታዊ ቁሳቁሶች ያልተሟሉላቸው ናቸው፡፡ ሆኖም በተወሰኑ ማቆያ ቦታዎች የዘፈቀደ እስር፣ የተራዘመ የቅድመ ክስ እስር እንዲሁም የድብደባ ተግባራት መፈጸማቸው በግኝቱ ተረጋግጧል፡፡



# ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች

Photo credit: EHRC/AHRF submission/2016/Ermias Getahun

## ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች

### አጠቃላይ ምልከታ

ኢሰመኮ ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች መከበራቸውንና መጠበቃቸውን የማረጋገጥ፤ ተጥሰውም ሲገኙ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ፤ ኮሚሽኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በክልል ወይም በፌዴሬሽን ምክር ቤቶች፣ አልያም በማንኛውም ፍርድ ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ካሉ ጉዳዮች በስተቀር የሰብአዊ መብቶች መጣስን አስመልክቶ በማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ሁሉ ተቀብሎ የመመርመር እና መፍትሔ የመስጠት ሥልጣን አለው።

ይህንንም የተሻሻለውን ማቋቋምያ አዋጅ ተከትሎ እያካሄደ ባለው የለውጥና የአቅም ግንባታ ሥራዎች መካከል፤ የአቤቱታ ቅበላ እና አያያዝ ሥርዓቱን በመፈተሽ በአጠቃላይ አገልግሎቱን ተደራሽ፣ ግልጽ፣ ምቹ፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ዋነኛው ነው። በዚህም መሠረት አቤቱታዎችን ተቀብሎ የሚያስተናግድበትንና ምላሽ የሚያስጥበትን የአቤቱታ አቀራረብና አያያዝ ሥርዓት ከኮሚሽኑ አዲስ አደረጃጀት እና አሠራር ሥርዓት ጋር የተጣጣመ ማድረግ ሥራ ተሠርቷል። እነዚህም የተከናወኑ ተግባራት የተሟላ የአቤቱታ ቅበላ ሥርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ፣ ባለሞያዎችን ማሠልጠን፣ በማንኛውም መንገድ እና በሁሉም የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤቶች በኩል የሚቀርቡ አቤቱታዎች በተማከለ እና የአቤቱታ አቅራቢዎችን መረጃ ደኅንነት በጠበቀ መልኩ መከታተል የሚያስችል ዲጂታል የመረጃ ቋት አዘጋጅቶ በሁሉም ጽሕፈት ቤቶች መዘርጋት ያካትታሉ። ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑና አገልግሎቱን ለማግኘት ተመጣጣኝ ማመቻቸትን ለሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን)፣ እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች አቤቱታቸውን በአካል ለማቅረብ አዳጋች ለሚሆንባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ኮሚሽኑ የሚሰጠውን አገልግሎት ምቹ እና ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል፣ ኮሚሽኑ አቤቱታዎችን በነጻ የስልክ መስመር፣ በፖስታ፣ በማኅበራዊ ሚድያ እና በሌሎች መገናኛ መንገዶች ይቀበላል።

ኮሚሽኑ ዓመታዊ ሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ማጠናቀር እና ይፋ ማድረግ ከጀመረበት ከ2014 በጀት ዓመት አንስቶ ላለፉት ሦስት ዓመታት ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ብዛት በየጊዜው መጨመሩ ማየት ይቻላል። አቤቱታ የሚያቀርቡ ሰዎችም በአብዛኛው ወንዶች ቢሆኑም ሴቶች፣ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች እና በተወሰነ ደረጃ አረጋውያን አቤቱታ አቅራቢዎችም ወደ ኮሚሽኑ ይመጣሉ። በሦስቱም ዓመታት በአዲስ አበባ የሚቀርቡ አቤቱታዎች አብላጫ ያላቸው ቢሆንም፣ በመቀጠል ከጅማ ጽሕፈት ቤት እና በባሕር ዳር ጽሕፈት ቤት በኩል የሚቀርቡ አቤቱታዎችም በዛው ልክ ጨምረዋል። በሌሎች ጽሕፈት ቤቶች ከሚቀርቡ አቤቱታዎች መካከል በተለይም የዲጂታል አቤቱታ ቅበላ ሥርዓቱ በዘንድሮ ዓመት በአዲስ መልኩ በተጠናከረበት በጅግጅጋ ጽሕፈት በኩል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ብዛት፣ እንዲሁም በተወሰነ መጠንም ቢሆን በአዲስ መልክ ከተዋቀሩት ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎችም ጭምር አቤቱታ መቅረባቸው የኮሚሽኑን ተደራሽነት መሻሻሉን አመላካች ነው። ከመጋቢት ወር 2015 ዓ.ም. ገደማ ጀምሮ ደግሞ ኢሰመኮ በመቀሌ የሚገኘውን ጽሕፈት ቤቱን ሥራ በተሟላ መልኩ ለማስጀመር የሚያስችለውን አስተዳደራዊ እና ሌሎች ተግባራትን አከናውኗል። በዚህም አማካኝነት በክልሉ ከተካሄዱ የተለያዩ የምክክር ውይይቶች እና በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ከተከናወነ ሰፋ ያለ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ሥራ በተጨማሪ በክልሉ የሚገኙ ማቆያ ቦታዎች መደበኛ ክትትል ሥራ በተወሰነ መልኩ ማስጀመር ተችሏል። እንዲሁም ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ጥር 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ 15 አቤቱታዎችን በአዲስ አበባ እና በመቀሌ በሚገኙ ባለሙያዎቹ አማካኝነት መቀበል እና ማስተናገድ ችሏል።

ኢሰመኮ በተለይም ከ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ያደረገው የተንቀሳቃሽ የአቤቱታ ቅበላ አሠራር (ማለትም ኢሰመኮ ጽሕፈት ቤት በሌላቸው ክልሎች ወይም አካባቢዎች ባለሙያዎችን በመላክ እና ማእከላዊ በሆኑ ቦታዎች በመንቀሳቀስ ኮሚሽኑን ማስተዋወቅ፣ የአቤቱታ ቅበላ አሠራሩን ማስረዳት እና ተቀብሎ ማስተናገድ) የኮሚሽኑን ተደራሽነት በእጅጉ አሻሽሏል።

በዚህም መሠረት በ2016 በጀት ዓመት ኢሰመኮ በተንቀሳቃሽ የአቤቱታ ቅበላው አማካኝነት ጽሕፈት ቤት በሌለው አካባቢዎች ተደራሽ መሆን የቻለ ሲሆን፣ ለምሳሌ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ኮንሶ ዞን 51 አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለ39 አቤቱታዎች እልባት መስጠት ችሏል።

በተለያዩ ጽሕፈት ቤቶች እና በሌሎች መንገዶች ከሐምሌ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ የቀረቡ እና መፍትሔ የተሰጣቸው አቤቱታዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፦

| 2016 በጀት ዓመት | የቀረቡ አቤቱታዎች ብዛት | መፍትሔ የተሰጣቸው |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ | 415 | 342 |
| አሶሳ | 74 | 66 |
| ባሕር ዳር | 124 | 68 |
| ጋምቤላ | 67 | 43 |
| ሃዋሳ | 161 | 152 |
| ጅግጅጋ | 37 | 32 |
| ጅማ | 329 | 273 |
| መቀሌ | 21 | 9 |
| ሰመራ | 264 | 251 |

በበጀት ዓመቱ በድምሩ 1492 አቤቱታዎችን ከ1830 አቤቱታ አቅራቢዎች ተቀብሏል። በኢሰመኮ ሥልጣን እና ኃላፊነት ሥር የማይወድቁ ወይም በሌሎች ተቋማት መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ሆነው፣ አልያም በሕዝብ ተወካዮች፣ በክልል ወይም በፌዴሬሽን ምክር ቤቶች፣ አልያም በማንኛውም ፍርድ ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች ሆነው ኢሰመኮ ወደሚመለከታቸው ተቋማት የመራቸው ጉዳዮች ብዛት 438 ነው።

ኢሰመኮ በሁሉም ጽሕፈት ቤቶቹ እና በሌሎች መንገዶች ተቀብሎ የሚያስተናግዳቸው አቤቱታዎች ሀገራዊውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ወይም በሀገር አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ፣ እንዲሁም በየክልሎቹ የሚታዩትን ዋና ዋና ጉዳዮች የሚመለከቱ ናቸው። ለምሳሌ በአዲስ አበባ በብዛታቸው ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሚመደቡ አቤቱታዎች ይዘት/ጉዳይ ወይም የጥሰቶቹ ዐይነት የአካል ደኅንነትና የነጻነት መብት፤ በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች መብት እና ፍትሕ የማግኘት መብትን የተመለከቱ ናቸው። ይህ አዝማምያ በሁሉም ክልሎች በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። አቤቱታ የሚቀርብባቸው አካላት የመንግሥት የጸጥታ አካላት ሲሆኑ፣ በተለይም በፖሊስ ጣቢያዎች ካሉ የአያያዝ እና የዘፈቀደ እስር ችግሮች ጋር የሚያያዙ ናቸው።

የክልሎቹ ወቅታዊ ሁኔታም ለኢሰመኮ የሚቀርቡት አቤቱታዎች ይዘት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ለምሳሌ በአማራ ክልል እየተካሄደ ካለው የትጥቅ ግጭት እና የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ጋር ተያይዞ፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በርካታ አካባቢዎች በየጊዜው ከሚያገረሹ

ግጭቶች እና አጠቃላይ የጸጥታ ሁኔታ ሳቢያ በባሕር ዳር እና በጅማ ጽሕፈት ቤቶች የቀረቡ አቤቱታዎች ከሕግ ውጭ ግድያ፣ በከባድ መሣሪያ/በድሮን ጥቃት የተፈጸሙ ግድያዎች፣ የንብረት ጉዳት/ውድመት፣ አስገድዶ መሰወር፣ ኢ-ሰብአዊ አያያዝ፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶች ጥሰት፣ አስገድዶ መድፈር እና እገታ ያካትታሉ።

በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በሚለው ክፍል ሥር እንደተመለከተው የኮሚሽኑ መደበኛ የማቆያ ቦታዎች ክትትል ሥራ፣ በዚህ አማካኝነት የተፈጠሩ ወይም የተጠናከሩ ግንኙነቶች አብዛኛዎቹን የነጻነት፣ የአካል ደኅንነት እና በማቆያ ቦታዎች ያሉ አያያዞችን የተመለከቱ አቤቱታዎችን በተፋጠነ እና ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር መፍትሔ ማስጠት ተችሏል። በዚህ መልኩ መፍትሔ የሚያገኙት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አቤቱታዎች ብዛት አማካይ ከግማሽ በላይ (ወደ 65%) የሚጠጋ ሲሆን፣ በአንዳንድ ክልሎች በኢሰመኮ ክትትል እና ውትወታ ሥራ አማካኝነት መፍትሔ የሚያገኙት አቤቱታዎች አማካይ ብዛት ወደ 80% የሚጠጋ ነው። ለምሳሌ ከነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ጥር 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ መልኩ በተዋቀሩት በደቡብ ኢትዮጵያ እና በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የቀረቡ እና በአብዛኛው በማቆያ ቦታዎች ያሉ ሰዎችን አያያዝ የተመለከቱ 27 አቤቱታዎች ሁሉም ፈጣን እልባት አግኝተዋል። በተመሳሳይ ወቅት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ከቀረቡ 55 አቤቱታዎች መካከል 51፣ በሲዳማ ከ18 አቤቱታዎች 17፣ በአፋር ከቀረቡ 240 አቤቱታዎች መካከል ደግሞ 190 የሚሆኑት መፍትሔ አግኝተዋል። ኢሰመኮ የሚቀበላቸውን አቤቱታዎች ላይ የሚደረጉ ምርመራዎች ላይ ትብብር ማድረግ እና ምክረ ሐሳቦችን መፈጸምን በተመለከተ በሶማሊ እና ሐረሪ ክልሎች ጥሩ መሻሻሎች ታይተዋል።

እነዚህ በእያንዳንዱ አቤቱታዎች ደረጃ የሚገኙ እልባቶች እና መፍትሔዎች በዋናነት ለአቤቱታ አቅራቢው፣ ለቤተሰቡ እና በዙርያው ላሉ ማኅበረሰቦች እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ አቤቱታ ለቀረበበት ተቋም የጉዳዩን መቋጫ እና ፍትሕ የሚያስገኙ በመሆኑ የሚበረታቱ እና ሊጠናከሩ የሚገቡ መልካም እመርታዎች ናቸው። የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአብዛኛው በፖሊስ ጣቢያዎች እና በማረሚያ ቦታዎች ካሉ አያያዞች ጋር የተገናኙ እንደመሆናቸው ለአቤቱታዎች በክትትል እና በውትወታ ሥራ የሚገኙ እልባቶች ብዙውን ጊዜ በአጠቃላይ በማቆያ ቦታው ላሉ ሌሎች ሰዎችም መፍትሔ እና ጠቀሜታ የሚያስገኙና በማቆያ ቦታው ያለውን ሁኔታ የሚያሻሽሉ ናቸው። ስለሆነም በአንድ የአቤቱታ መዝገብ አማካኝነት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ የሚሆኑ ሰዎች በርካታ ናቸው።

ሆኖም በአንድ በኩል ለሦስት ተከታታይ ዓመታት የሚቀርቡ አቤቱታዎች አብዛኛው ይዘት እና የጥሰት ዐይነት፣ አቤቱታ የቀረበባቸው አካላት ተመሳሳይ መሆን በተለይም በማቆያ ቦታዎች ሁኔታ፣ በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች አያያዝ እና የማቆያ ቦታዎችን አሠራር፣ የሰው ኃይል፣ የገንዘብ ዐኖም በአንድ በኩል ለሦስት ተከታታይ ዓመታት የሚቀርቡ አቤቱታዎች አብዛኛው ይዘት እና የጥሰት ዐይነት፣ አቤቱታ የቀረበባቸው አካላት ተመሳሳይ መሆን በተለይም በማቆያ ቦታዎች ሁኔታ፣ በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች አያያዝ እና የማቆያ ቦታዎችን አሠራር፣ የሰው ኃይል፣ የገንዘብ ዐቅም እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ትኩረት እና ማሻሻያ የሚሻ መሆኑን አመላካች ነው።

በሌላ በኩል የሰብአዊ መብቶች ጥሰቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአሠራር፣ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ፣ የመዋቅር ወይም የበጀት ውሳኔዎችና እርምጃ የሚሹ በመሆናቸው በሚቀርቡ አቤቱታዎች ደረጃ እልባት ለማስገኘት ወይም ዘላቂ እና የተሟላ መፍትሔ ለማስገኘት አዳጋች የሚያደርጋቸው አቤቱታዎችም አሉ። ለምሳሌ በሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ረገድ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መታወቂያ እና ሌሎች ሰነዶች የተመለከቱ አቤቱታዎች፣ መደበኛ ባልሆኑ ቦታዎች የመያዝ፣ “በበላይ ትእዛዝ፣ በሀገር መከላከያ ወይም በደኅንነት አካላት ትእዛዝ” በመያዛቸው በሚል ምክንያት የጥየቃ መብታቸውን የተከለከሉ፣ ባልታወቁ ቦታዎች ረዘም

ላለ ጊዜ መያዝ እና የአያያዝ ሁኔታ እንዲሁም የአስገድዶ መሰወርን የተመለከቱ አቤቱታዎች መፍትሔ የማስገኘት ሥራ ከእነዚህ ሀገር አቀፍ እና የሁሉም የሚመለከታቸው አካላትን ትኩረት ከሚሹ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መካከል ዋነኞቹ ናቸው።

## ሌሎች መብቶችን የተመለከቱ

በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ፣ እንዲሁም በሌሎች የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዘርፍ ኢሰመኮ በ2016 በጀት ዓመት ተቀብሎ ካስተናገዳቸው የመብቶች ዘርፎች መካከል ከመኖርያ እና ከንግድ ቤት ፈረሳ ጋር የተያያዙት በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። አብዛኛው ይህንን የተመለከቱ አቤቱታዎች ከአዲስ አበባ እና ከሸገር የቀረቡ ቢሆንም፣ በጅማ እና በጅግጅጋ ጽሕፈት ቤት በኩልም ከመሬት ይዞታ ጋር እና ከመኖርያ ቤት ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች ቀርበዋል። በአዲስ አበባ ከመኖርያ ወይም ንግድ ቤት መፍረስ ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች በአብዛኛው ሕጋዊ ይዞታ ሆነው የፈረሱ፣ ያለ በቂ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የፈረሱ፣ በቤት ፈረሳ ሂደት ውስጥ የደረሱ ጉዳቶች፣ ወይም የካሳ ክፍያን የተመለከቱ ናቸው። ይህን መሰል በርካታ ሰዎችን የሚመለከቱ እና በክልል ወይም እንደአግባቡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ምላሽ የሚሹ ጉዳዮች ቢሆኑም፣ ኢሰመኮ የሚመለከታቸውን የአስተዳደር አካላት በማነጋገር፣ በአንዳንድ ሁኔታዎችም በጉዳዩ ላይ ባለድርሻዎችን ያሳተፈ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት እልባት ለመስጠት ጥረት ያደርጋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች በአስተዳደር አካላቱ ሥር የተዋቀሩት የቅሬታ መዋቅሮች ምላሽ ወይም መፍትሔ ይሰጣሉ። ሆኖም በነጠላ ወይም በቡድን የሚቀርቡ ቢሆንም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወይም የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች በዋነኝነት በአስፈጻሚው አካል ወይም አስተዳደር ውስጥ ግልጽ እና ተገቢውን የሕግ ድንጋጌዎች የተከተለ የቅሬታ ሰሚ እና መፍትሔ አፈላላጊ ሥርዓት አስፈላጊነትን፣ የበቂ እና ትርጉም ያለው የሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ እና ለተፈጸሙ ጥሰቶች ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ተጠያቂነት የማረጋገጥ አስፈላጊነት አመላካች ናቸው።

ፍትሕ የማግኘት እና የተፋጠነ ፍትሕ ከማግኘት መብቶች ጋር የተያያዙ በርካታ አቤቱታዎችም ለኢሰመኮ ቀርበዋል። በአፋር ለምሳሌ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ 7 አቤቱታዎች በፍርድ ቤቶች የተሰጡ እና እጅግ የተራዘሙ (ከሁለት እስከ ስድስት ወራት) ቀጠሮዎችን የተመለከቱ ናቸው። በተለይም በአዲስ መልኩ በተዋቀሩት በማእከላዊ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የተለያዩ የአስተዳደር እና የፍትሕ አካላት መልሶ ማደራጀት እና ማዋቀር ጋር በተያያዘ ከዚህ ከተፋጠነ ፍትሕ ከማግኘት መብቶች ጋር በተያያዘ የተለያዩ ቅሬታዎች ይነሳሉ። ለምሳሌ ማቆያ ቤቶች ከፍርድ ቤቶች በረዥም ርቀት በመገኘታቸው እና ማቆያ ቦታዎች ካላቸው የዐቅም ማነስ ጋር ተዳምሮ ተጠርጣሪዎች በተገቢው ወቅት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ እና ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ አለመቻል፣ ከማቆያ ቦታዎች ስፍራ መቀያየር ጋር ተያይዞ የሚነሱና የጥየቃ እና የሕግ አገልግሎትን ጨምሮ ያሉ የሰብአዊ መብቶች ጥያቄዎች እንዲሁም ከፍርድ ቤቶች አሠራር፣ በተለይም ከተንቀሳቃሽ ፍርድ ቤት አገልግሎት እና ባለው ፍላጎት አለመጣጣም ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች እና ጉዳዮች በርካታ ከመሆናቸው አንጻር የፍትሕ ሚኒስቴር እና የፍትሕ አካላቱን አፋጣኝ ትኩረት የሚሹ ናቸው።

ከሥራ እና ተያያዥ መብቶች ጋር በተገናኘ ከማእከላዊ፣ ከደቡብ እና ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ከደመወዝ ወይም ጥቅማ ጥቅም አላግባብ መዘግየት እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች ቀርበዋል። በአብዛኛው ከክልሎቹ አስተዳደራዊ አደረጃጀት ሂደት መዘግየት ጋር የተያያዙ ቢሆኑም ጥቂት የማይባሉ ጉዳዮች ከቀድሞ ክልሎች አስተዳደሮች አላግባብ ከሥራ መባረር ጋር የተያያዙም አቤቱታዎች ቀርበዋል። ከሥራ መብቶች ጋር በተያያዘ ከጡረታ ውዝፍ ክፍያዎች ጋር (በአብዛኛው ከትግራይ ክልል)፣ ከሥራ ከአላግባብ መሰናበት (ከአብዛኞቹ ክልሎች) እንዲሁም ከሥራ ስምሪት ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች

ለኢሰመኮ ቀርበዋል። በተለይም ከሥራ ስምሪት ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች አካል ጉዳተኛ ባለሙያዎችን የሚመለከቱ ሲሆን፣ አካል ጉዳታቸውን ያላገናዘቡና ሥራቸውን ለመሥራት አዳጋች ወደሚሆንባቸው አካባቢዎች እንዲሄዱ መገደድ ጋር ይያያዛሉ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው አብዛኛውን ጊዜ አቤቱታ አቅራቢዎች ወደ ኢሰመኮ ከመምጣታቸው በፊት በሚመለከተው አስተዳደር በኩል ቅሬታቸውን ለማሰማት የአስተዳደሩን ከፍተኛ ኃላፊዎች ጨምሮ የተቀመጡ ማናቸውንም አማራጮች ለመጠቀም ጥረት ያደርጋሉ። ኢሰመኮ ለአቤቱታዎች መፍትሔ የሚያፈላልግበት ዋነኛው መንገድም አቤቱታ የቀረበበትን ወይም የሚመለከተውን አስተዳደር ጋር በመነጋገር እና ውትወታ በማድረግ ነው። ይህም በሀገር አቀፍ ወይም በፌዴራል ደረጃ ብቻ ሳይሆን በክልል፣ በዞን በወረዳ ደረጃ እና በየአስፈጻሚ አካሉ አስተዳደር ቅሬታዎች በአግባቡ የሚስተናገዱበት ግልጽ አሠራር የመኖር አስፈላጊነትን ምክረ ሐሳብ መልሶ የሚያጠናክር ነው።

# ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች



Photo credit: EHRC/ AHRFF submission/2016/ Hiwot Taddesse

# ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች

የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ዘርፍ በርካታ ሰብአዊ መብቶችን የሚያካትት ቢሆንም ይህ ምዕራፍ ኢሰመኮ በተለይም በ2016 በጀት ዓመት ከሀገራዊ እና ከክልሎች ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ትኩረት አድርጎ ክትትል ሲያደርግ በቆየባቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው። ይህም የአካባቢዎቹን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ በተለይም መሠረታዊ የሆኑ የምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ፍጆታዎች አቅርቦት እና ዋጋ፣ በትምህርት እና በጤና እንዲሁም እንደየሁኔታው ሌሎች መሠረተ ልማት አቅርቦቶች፣ ከሥራ መብት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እና እንደ ሴቶች፣ ሕፃናት እና ሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ያሉ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች መሠረታዊ አቅርቦት እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን የሚያካትት ነው።

## አጠቃላይ ምልከታ

በርካታ የሀገሪቱ አካባቢዎች በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያሉ ወይም በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያለፉ መሆናቸው በ2016 በጀት ዓመት አጠቃላይ የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩን ቀጥሏል። በዋነኝነት በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያሉ አካባቢዎች፣ ወይም ግጭት በየጊዜው የሚያገረሽባቸው ወይም በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያለፉ አካባቢዎች፣ በአንዳንድ ሁኔታዎችም በተፈጥሮ አደጋ ወይም በድርቅ ምክንያት የምርታማነት እና የማምረት ተግባር መቀዛቀዝ ብሎም ማቆም በክልሎቹ ወይም በአካባቢዎቹ ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ መሠረታዊ የሆኑ የምግብ ፍጆታዎች ጭምር ላይ የዋጋ ንረት ያስከተለ፣ እንዲሁም በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች አስቸኳይ የምግብ እና የሰብአዊ ድጋፍ እንዲፈልጉ አድርጓል።

በጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም. የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) የሰብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት (UNOCHA) በጣምራ ባወጡት መግለጫ እንደተመለከተው አማራ፣ አፋርና ትግራይ ክልሎች ከጦርነት ባለማገገማቸው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች በተከሰተ ድርቅ እና ክልሎቹ በሚያስተናግዷቸው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ብዛት ድምር ውጤት የምግብ ዋስትና እና የተመጣጠነ ምግብ የማጣት ችግሮች በእጅጉ ጨምረዋል። በመሆኑም ሁለቱ ተቋማት በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ባወጡት መግለጫ እስከሚቀጥለው በጀት ዓመት መባቻ አጠቃላይ እጅግ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸው (critically food insecure) ሰዎች ቁጥር 10.8 ሚልየን እንደሚደርስ መደምደም እንደቻሉ አስታውቀው ነበር። እነዚህም በተለይም በአፋር፣ በአማራ፣ በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚገኙ መሆናቸውንም በወቅቱ ገልጸው ነበር።

በመካሄድ ላይ ባሉ ወይም በየጊዜው በሚያገረሹ የትጥቅ ግጭት ሁኔታ ውስጥ ባሉ የአማራ እና የኦሮሚያ ክልሎች አካባቢዎች ያለው አጠቃላይ የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ነው። ቀደም ባሉ የሪፖርቱ ክፍሎች/ምዕራፎች እንደተመለከተው በተለይም በትጥቅ ግጭቶች ወቅት ማንኛውም እንቅስቃሴ ለተወሰኑ ቀናት ወይም ረዘም ላለ ጊዜ የሚቋረጥ እና የሚቀዛቀዝ መሆኑ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ይህ ሁኔታ በተደጋጋሚ የሚከሰት መሆኑ የአካባቢዎቹን ብቻ ሳይሆን የአጎራባች ቦታዎችን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ ሁኔታ የሚጎዳ ነው። በአማራ ክልል ለምሳሌ በክልሉ አብዛኛው አካባቢዎች በሚጣለው የእንቅስቃሴ ገደብና የሰዓት እላፊ እንዲሁም በጸጥታ መደፍረስ የተለያዩ ወረዳዎችን የሚያገናኙ የመንገድ መጓጓዣዎች በመቋረጣቸው አልያም ውስን መሆናቸው፣ የንግድ እና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በፈጠረው ተጽዕኖ ነዋሪዎች ለአቅርቦት እጥረት፣ ለዋጋ ንረት እንዲሁም ለተያያዥ ችግሮች ተዳርገዋል። በኦሮሚያ ክልልም በተመሳሳይ በክልሉ በሚገኙ

አንዳንድ ቦታዎች በመንግሥትና በታጣቂ ቡድኖች መካከል በሚደረገው የትጥቅ ግጭት ምክንያት ከወረዳ ወደ ወረዳ፣ ከወረዳ ወደ ከተማ፣ ከከተማ ወደ ከተማዎች የሚደረገው የሕዝብ እንቅስቃሴ በመስተጓጎሉ ገበሬዎች የእርሻ ሥራቸውን፣ ነጋዴዎች የንግድ ሥራቸውን እንዲሁም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አገልግሎት መስጠት አዳጋች የሆነባቸው ሲሆን፣ ነዋሪዎች ለማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋልጠዋል:: በትጥቅ ግጭት ውስጥ በሁሉም ተሳታፊ ወገኖች የሚፈጸሙ እና የትጥቅ ግጭቱ የሚያደርሰው የንብረት፣ የመኖርያ እና መጠለያዎች እና የእርሻ ማሳዎችን እና ምርቶች፣ እንዲሁም የመሠረተ ልማት ውድመትም ሌላው የነዋሪዎቹን እና የአካባቢዎቹን ችግር እንዲከፋ የሚያደርግ ጉዳይ ነው:: በኦሮሚያ ክልል ለምሳሌ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች ንብረት ላይ ውድመት ማድረሳቸው (በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን ማቃጠል እና ቀምቶ መውሰድ፤ የቀንድ ከብቶችን መዝረፍ እንዲሁም ሰዎችን አግቶ ለማስለቀቂያ ገንዘብ መቀበል)፣ እንዲሁም የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን ማውደም (ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፣ የገበሬዎች መሰልጠኛ ተቋማት የመሳሰሉ) በክልሉ ያለውን አሳሳቢ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታ ይበልጥ እንዲወሳሰብ አድርጓል::

ግጭቶቹ ያስከተሉት መፈናቀል እና በግጭት ምክንያት ከሌሎች ክልሎች ወይም አካባቢዎች ተፈናቅለው የተጠለሉ ሰዎች በግጭት ወቅት ለሚከሰቱ የሰብአዊ ድጋፍ እና ሌሎች አቅርቦት እጥረቶች እና ችግሮች ይበልጥ ተጋላጭ ሆነዋል:: (በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ክፍል በዝርዝር የሚታይ ይሆናል) በኦሮሚያ ክልል ለምሳሌ በግጭቶች ውስጥ ያለፉ እና በ2016 በጀት ዓመትም ግጭት የተካሄደባቸው አካባቢዎች መኖሪያ ቤቶች መቃጠል እና የንብረት ውድመት ሰዎችን በክልሉም ውስጥ ሆነ ከክልሉ ውጪ እንዲፈናቀሉ ካደረጉ ሁኔታዎች አንዱ ሲሆን፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች አካባቢዎቹ አንጻራዊ ሰላም የሰፈነባቸው ቢሆንም የመኖሪያ ቤት ችግሩ ያልተቀረፈ በመሆኑ ሰዎች ወደ መኖሪያ ቀያቸው እንዳይመለሱ ተጨማሪ እንቅፋት ሆኗል::

የትጥቅ ግጭቱ ሌላኛው ተጽዕኖ በጤና መብት ላይ ሲሆን ይህም የእንቅስቃሴ ገደቡ፣ የሰዎች መፈናቀል፣ የመሠረተ ልማት ውድመት ተደራራቢ ውጤት፣ እንዲሁም ባለሞያዎች በአንጻራዊነት ሰላም ወደ ሆኑ አካባቢዎች መሄድ፣ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የመድኃኒት አቅርቦት ሁኔታ እና የመድኃኒት ዋጋ እንዲሁም በግጭት ላይ ባሉ አካባቢዎች በሚከሰተው የባለሞያዎች እጥረት ምክንያት የሚከሰት የጥራት እና አገልግሎት መቀነስ/ማሽቆልቆል ጋር የሚዳመር ነው:: ይህ ሁኔታ በሁሉም በግጭት ውስጥ ያለፉ አካባቢዎች በአሉባቸው ክልሎች የሚታይ ሁኔታ ሲሆን፣ በተለይም በትጥቅ ግጭት ወቅት ሴቶች፣ ሕፃናት እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በጤና አገልግሎት መቋረጥ ሳቢያ ተጋላጭነታቸው እንዲጨምር ያደርጋል:: በአማራ ክልል ለምሳሌ መደበኛ ክትትል እና ሕክምና የሚያስፈልጋቸው እናቶች እና ሕፃናት እንዲሁም የተለያዩ ዘላቂ የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች በአሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ:: እየተካሄደ ባለው ግጭት ምክንያት በብዙ ቦታዎች ላይ አስፈላጊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት ሕሙማን ወደ ጤና ተቋማት መሄድ አለመቻልን ጨምሮ የመድኃኒት እና ሌሎች የሕክምና ግብዓቶች እጥረት እንዲሁም የጤና ተቋማት አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ ማቆም አልያም ጨርሶ ሥራ ማቆም እየተስተዋለ መሆኑን ኢሰመኮ በተለያዩ ወቅቶች ባወጣቸው መግለጫዎች ይፋ አድርጓል:: በዚሁ በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ በአማራ ክልል የሚገኙ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የጤና ተቋማት የሕክምና እርዳታ ለማግኘት የሄዱ ሴቶች እና ሴት ሕፃናትን ብዛት መሠረት በማድረግ ያለው አሳሳቢ ጾታዊና ወሲባዊ ጥቃት በተመለከተም በመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ኢሰመኮ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች አስፈላጊውን የተሟላ አገልግሎት ማቅረብ ጨምሮ ይህ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እንዲቆም፣ በአፋጣኝ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥና ዘላቂ መፍትሔ እንዲሰጥ ማሳሰቡ የሚታወስ ነው:: የአማራ ክልል የጤና ቢሮ በየካቲት ወር 2016 ዓ.ም. "በክልሉ ያለው ጦርነት የጤና ሥርዓቱን እንደፈተነ" ገልጾ "የሕጻናት ክትባት ከ60 በመቶ እንደማይሻገር እና ክትባትን ጨምሮ የኤችአይቪ፣ የቲቢ፣ የወባ እና የሌሎችም በሽታዎች መድኃኒቶች አቅርቦቶች እየተቋረጡ

መሆናቸውን” ለክልሉ የመገናኛ ብዙኃን ገልጾ ነበር። በተመሳሳይ የኦሮሚያ ጤና ቢሮ በጥር ወር 2016 ዓ.ም. “ከዚህ ቀደም ግጭት በተስፋፋባቸው የክልሉ አከባቢዎች የጤና መሠረተ ልማቶች ላይ ጉዳት መድረሱ መሠረታዊ ክትባቶችን ጨምሮ በቀላሉ ተላላፊ ሆኑ በሽታዎችን መከላከል ፈታኝ መሆኑን” አሳውቆ ነበር።

በግጭቶች በቆዩ አካባቢዎች ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለው የጤና አገልግሎት እና አቅርቦት ደረጃ አፋጣኝ እና የተቀናጀ ትኩረት የሚሻ ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በጥር ወር 2016 ዓ.ም. በጀት ዓመት የመጀመሪያ አምስት ወራት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የወባ በሽታ በምርመራ የተገኘባቸው ሰዎች ቁጥር፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር “ከፍተኛ” መሆኑን ማሳወቁ የሚታወስ ነው። ኢንስቲትዩቱ እንዳስታወቀው “ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ በወባ በሽታ ተጠርጥረው ምርመራ ከተደረገላቸው 6.3 ሚሊዮን ሰዎች ውስጥ፤ ከ1.3 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በሽታው ተግኝቶባቸዋል። በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በኦሮሚያ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች በሕፃናት ላይ ኩፍኝ መገኘቱ በበጀት ዓመቱ በተለያየ ወቅት በሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ተገልጿል። ለምሳሌ በጥር ወር 2016 ዓ.ም. በደቡብ ኢትዮጵያ፣ ኮሬ ዞን (በቀድሞ አጠራሩ አማሮ ልዩ ወረዳ) “በጥቂት ቀናት ውስጥ በተዛመተ የኩፍኝ ወረርሽኝ አንድ የሦስት ዓመት ሕፃን ሕይወቱ ሲያልፍ 31 ሕፃናት በወረርሽኙ መያዛቸውን” የዞኑ ጤና ጥበቃ ጽሕፈት ቤት አስታውቋል። በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የወባ እና የኩፍኝ ወረርሽኞች ለብዙዎች ሕመም እና ሞት ምክንያት ሆነዋል። በተመሳሳይም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በሐዲያ ዞን ሾኔ ከተማ በተከሠተ የኩፍኝ ወረርሽኝ፣ የ22 ሕፃናት ሕይወት እንዳለፈ የዞኑ ጤና መምሪያ የጥር ወር 2016 ዓ.ም. መረጃ ያመላክታል። በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ሁኔታን በተመለከተ የደቡብ ኢትዮጲያ ክልል የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት መረጃ እንደሚያሳየው በክልሉ በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ 9,239 ሰዎች በወባ በሽታ ተይዘዋል። የመድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች እንዲሁም የሕክምና ባለሞያዎች እጥረት ለወረርሽኞቹ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት እንቅፋት ሆኗል። የዓለም ጤና ድርጅት በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. “በኢትዮጵያ በስምንት ክልሎች 41 ሺህ ሰዎች በኮሌራ በሽታ መያዛቸውን” ጠቅሶ “በሽታው በዚህ ልክ በኢትዮጵያ ሲከሰት በታሪኳ ከፍተኛው እንደሆነ” አስረድቷል። ድርጅቱ አክሎም ለወረርሽኙ ስፋት መንስኤ ካላቸው ሁኔታዎች መካከል “የተስፋፋ ድርቅና በሽታ በሚሊየን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት አደጋ ላይ መጣሉ እና በተለይም በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና ሌሎች አካባቢዎች የተፈጠረው ግጭት እና ጦርነት በርካታ የጤና ተቋማት እና መሠረተ ልማቶች ላይ ውድመት እና ሌሎች ጉዳቶች” እንደሚጠቀስ ገልጿል።

በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል በግጭት ላይ ያሉ እና በግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ ወይም መቆም በአዋሳኝ ክልሎች ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ለምሳሌ በአፋር እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የጤና እና የምግብ ሸቀጦች እጥረት እንዲሁም ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ አሳይቷል። በአፋር ክልል፣ ለአማራ ክልል አጎራባች በሆኑት በገቢ ዞን የአርጎባ ልዩ ወረዳ (ሰሜን ሸዋ አንኮበር ወረዳ አጎራባች)፣ ሃሪ ዞን ሰሙ ሮቢ ወረዳ (ሰሜን ሸዋ ዞን ሸዋሮቢት ከተማ እና ቀወት ወረዳ አጎራባች) ሃሪ ዞን ሃደለኤላ ወረዳ (ከኦሮሞ ብሄረሰብ አስተደደር ዞን ሰንበቴ ከተማ/ጅሌ ጥሙጋ ወረዳ ጋር አጎራባች) የመንቀሳቀስ መብት የተገደበ በመሆኑ እና ከኅብረተሰቡ አርብቶ አደር ከመሆን ጋር ተዳምሮ እንስሳዎቹን ወደገበያ ማቅረብ አለመቻሉ፣ የባንክ አገልግሎትም በአካባቢው ባለመኖሩ ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ችግር እየተጋለጠ ነው።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ3 እስከ 4 ሚልየን የሚቆጠሩ ሕፃናት በተለያዩ ምክንያቶች ከትምህርት ውጪ እንደሆኑ እንደሚገመት የትምህርት ሚኒስቴር በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለምአቀፉ የሕፃናት አስቸኳይ ፈንድ

(UNICEF) ይፋ ያደረገው ሪፖርት ከትምህርት ውጪ የሆኑ ሕፃናት ቁጥር በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ 8 ሚልየን እንደሚጠጋ ያመለክታል።

በአማራ ክልል ያለውን ሁኔታ በተመለከተ በክልሉ ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት የክልሉ የትምህርት እንቅስቃሴ በአብዛኛው የክልሉ ቦታዎች በየጊዜው የሚስተጓጎል ሲሆን፣ የክልሉ ትምህርት ቢሮ በጥር ወር 2016 ዓ.ም. እንደገለጸው በክልሉ የሚገኙ 3516 አንደኛ እና መለስተኛ ደረጃ እና 225 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2016 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ሥራ አልጀመሩም። በበጀት ዓመቱ ከ6.2 ሚሊዮን ተማሪዎች በላይ ለመመዝገብ ታቅዶ ተመዝግበው እየተማሩ ያሉት 3.6 ሚሊየን ተማሪዎች ብቻ መሆናቸውን እና በክልሉ በአጠቃላይ በሦስት ዞኖች እና በ31 ወረዳዎች ላይ የትምህርት ሥራ እንቅስቃሴ መስተጓጎሉን አስታውቋል። በክልሉ ከሚካሄደው የትጥቅ ግጭት ጋር ተያይዞ በትምህርት ተቋማት ላይ ከሚደርሰው ውድመት፣ አልያም የትምህርት ተቋማትን ለውትድርና ዓላማ ከማዋል በተጨማሪ በተሳታፊ አካላት የትምህርት ተቋማትን ዒላማ ያደረገ ጥቃት አሳሳቢ ነው። ለምሳሌ በባሕር ዳር ከተማ የትጥቅ ግጭቱ ከተስፋፋበት ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ጥር ወር መጨረሻ 2016 ዓ.ም. ድረስ በሦስት ትምህርት ቤቶች ላይ በተፈጸመ የቦንብ ጥቃት አንድ መምህር ስትገደል፣ ሦስት መምህራንና አንድ ተማሪ ቆስለዋል፣ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሥነ ልቦና ጉዳት ደርሷል። በኦሮሚያ ክልል በጸጥታ ሁኔታው፣ በመፈናቀል፣ እንዲሁም በተከሰተው የምግብ እጥረትና በትምህርት ቤቶች ላይ በሚደረሱ ጉዳቶች እና ከዚሁ ጋር በተያያዙ ተግዳሮቶች በሚከሰቱ በኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች በክልሉ በተለያዩ አከባቢዎች በሺዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት ትምርት አቋርጠዋል።

በትግራይ እና በአፋር ክልሎች በተለይም በ2016 ዓ.ም. በግጭት ምክንያት በትምህርት ላይ የደረሰውን ጉዳት ለማካካስ በክልል እና በፌዴራል ደረጃ የተወሰዱ እርምጃዎች አበረታች ቢሆኑም፣ በሁሉም ክልሎች በግጭት ውስጥ ባለፉ ወይም በግጭት ውስጥ ባሉ አካባቢዎች፣ በድርቅ ወይም በተፈጥሮ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች ያለው ሁኔታ በተመሳሳይ መልኩ አሳሳቢ ነው።

በአንዳንድ አካባቢዎች በኮቪድ ወረርሽኝ ሳቢያ ትምህርት ያቋረጡና ወደ ትምህርት ያልተመለሱ ሕፃናት ፣ እንዲሁም በኦሮሚያ፣ በሶማሊ እና በቀድሞ ደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ ሳቢያ ትምህርት ያቋረጡ ሕፃናት ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ ጨምሮ በበርካታ ክልሎች የሚታየው የሕፃናት ከትምህርት ማቋረጥ እና መንስዔዎቹ በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ተገቢውን ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ በአፋር ክልል የተማሪዎች ቁጥር እጅግ መቀነሱን እና በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ትምህርት ቤቶችን መልሶ የማቋቋም ሥራ መዘግየት፣ እንዲሁም በግጭት ሳቢያ የተፈናቀሉ ሰዎችም ተጠቃለው ወደ ቀዬአቸው ያልተመለሱ በመሆኑ፣ በተጨማሪም በክልሉ የሚታየው ከግጦሽ መሬት ጋር በተያያዘ ወላጆች ልጆቻቸውን ከትምህርት እያቋረጡ ለከብቶቻቸው ግጦሽ ፍለጋ የመሄድ ችግሮች ተደማምረው የሕፃናት ትምህርት የማግኘት መብት ሁኔታን አሳሳቢ እንዳደረገው ኢሰመኮ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ባለድርሻዎች ያሰባሰበው መረጃ ያሳያል። በግጭት ባሉ አካባቢዎች ያለው የትምህርት አቅርቦት ሁኔታ እና በግጭቱ ሳቢያ የሚከሰቱ መፈናቀሎች በሴቶች ሕፃናት ተማሪዎች ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ፣ በሲዳማ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ቁጥሩ እየጨመረ የመጣው የሴቶች ሕፃናት ጠለፋ (በደቡብ ኢትዮጵያ ኮሬ ዞንዳ ለምሳሌ የችግሩ ስፋት ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሴት ሕፃናት ቁጥርን እንዲቀንስ ማድረጉን የተጎጂ ቤተሰቦች እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ያስረዳሉ) ችግር በዚሁ ሀገር አቀፍ የትምህርት ሁኔታ ጥናት እና ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች ውስጥ ሊካተት የሚገባው ነው።

በአንጻራዊ ሰላም ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች የትምህርት አገልግሎትን ለማስጀመር ወይም መልሶ ለማቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎች ቢኖሩም በዋነኝነት በገንዘብ አቅም ማነስ አቅርቦቱ/አገልግሎቱ የተሟላ እንዳይሆን አድርጓል። ለምሳሌ በቤኑሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚታየው የመልሶ ማቋቋም ሥራ አበርታች ቢሆንም ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ ባለመሆኑ በርካታ የወደሙ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማትና የእንስሳት ሕክምና ተቋማት አለመሥራታቸውና አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ አለመሆናቸው፣ እንዲሁም ጉዳት ያልደረሰባቸውና በወረዳ ማዕከላት የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማትና የእንስሳት ሕክምና ተቋማት ከመንገድ መዘጋትና ከበጀት እጥረት ጋር ተያይዞ በቂ የመማሪያ መጽሐፍትና ቁሳቁስ፣ በቂ የሕክምና ቁሳቁስ እና መድኃኒት ማቅረብ አለመቻላቸው ለነዋሪዎች ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኗል። ከመልሶ ማቋቋም ሥራ መዘግየት ወይም ተመጣጣኝ አለመሆን በተጨማሪ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የባለሞያዎች እጥረት ወይም አለመኖር የትምህርት አገልግሎቱንም ሆነ የጤና አገልግሎቱን መልሶ የማስጀመር ሥራውን አስተጓጉሏል። ለምሳሌ ኢሰመኮ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. በትግራይ ክልል ያለውን ወቅታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተመለከተ ባደረገው ሰፋ ያለ ክትትል ሥራ ሪፖርት እንዳመለከተው በክልሉ በተለይም ከኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች አጠቃላይ ሁኔታ በተጨማሪ መሠረታዊ ለሆኑ እንደ ፍትሕ አገልግሎት ተቋማት፣ የትምህርት እና የጤና ተቋማት በሌሎች ክልሎች በማገልገል ወይም በክልሉም ቢሆኑ ወደ ሥራ ባልተመለሱ ባለሞያዎች ምክንያት እና ይህም ያስከተለው እጥረት ተጨማሪ ተግዳሮት ሆኗል።

በተጨማሪም ድርቅ እና የተፈጥሮ አደጋዎችም ለትምህርት መብት ሁኔታው መባባስ መንስ ሆነዋል። ለምሳሌ በሶማሊ ክልል በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ምክንያት ኅብረተሰቡ ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ ጉዳት ማስከተሉን ኮሚሽኑ በተለያዩ ወቅቶች ይፋ ባደረጋቸው የክትትል ሰነዶች አመልክቷል። በተለይም በክልሉ በሚገኙ ሦስት ዞኖች ላይ ማለትም በሸቤሌ፣ ሊበን፣አፍዴር እንዲሁም በ10 የተለያዩ ወረዳዎች ላይ ከባድ የሆነ ጉዳትን አስከትሏል። በጉዳቱም በቁጥርም 66,810 በላይ የሚሆኑ በርካታ ነዋሪዎች ከቤት ንብረታቸው እንዲሁም ከቀያቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ውስጥ ተጠልለዋል፣ በርካታ እንስሳቶቻቸው አልቀዋል። በተጨማሪም እስከ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ 224 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች በአደጋው ምክንያት መዘጋታቸውን ኢሰመኮ ከሚመለከታቸው አካላት ማወቅ ችሏል። የመንግሥት ተቋማት እና አጋር ድርጅቶች ለደረሰው አደጋ በወቅቱ ከሞላ ጎደል ድጋፍ ቢያደርጉም የሶማሊ ክልል አደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ቢሮ ባወጣው ሪፖርት መሠረት እስከ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ ወደ ቀዬአቸው መመለስ የቻሉት ከ66,810 ተፈናቃዮች ውስጥ 46,109 ብቻ መሆናቸውን ገልጿል።

በአዲስ መልኩ በተዋቀሩት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች ቀደም ባሉ ክፍሎች እንደተመላከተው የደመወዝ መዘግየት እና ተያያዥ ጉዳዮችን ጨምሮ ከመዋቅሮቹ አደረጃጀት ሂደት ጋር የተያያዙ የተለያዩ ችግሮች በክልሎቹ የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች እና አቅርቦቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል። በተለያዩ አካባቢዎች የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለተወሰነ ጊዜ ሥራ አቋርጠው ቆይተዋል፣ ለምሳሌ በሃዲያ ዞን በአስተማሪዎች ደመወዝ አለመከፈል ምክንያት የዞኑ ትምህርት ቤቶች ለበርካታ ወራት ሥራ ሳይጀምሩ ቆይተዋል። በማከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ መረጃ ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ያልተከፈለ ደሞዝ ያለባቸውን ተቋማት በመለየት ክልሉ ለደመወዝ ብቻ በወር እስከ 130 ሚሊየን ብር በብድር እየሰጠ እንደሚገኝ ቢያሳይም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ችግሩ የቀጠለባቸው አካባቢዎች (ለምሳሌ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ እና ሥልጤ ዞን) መኖራቸውን ማወቅ ተችሏል። በደመወዝ አለመከፈል ወይም መዘግየት ምክንያት ትምህርት እና ሌሎች አገልግሎቶች ካልተጀመረባቸው ሌሎች አካባቢዎች መካከል ትግራይ፣ በርካታ የአማራ ክልል እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አካባቢዎች ይገኙበታል።

በቂ የሆነ መኖርያ የማግኘት መብትን በተመለከተ በአዲስ አበባ እና በሸገር ከተሞች በ2016 በጀት ዓመት ከተካሄዱት የቤት ፈረሳዎች ጋር ተያይዞ ከታዩት ችግሮች በተጨማሪ በግጭት ውስጥ ባሉ ወይም በቆዩ አካባቢዎች በወደሙ መኖርያ ቦታዎች ሳቢያ፣ እንዲሁም ከአቅርቦት ማነስ ጋር የተያያዙ ችግሮች ታይተዋል። በተለይም በመጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄዱ መጠነ ሰፊ የመኖርያ ቤት ፈረሳዎችን በተመለከተ የከተማዋ አስተዳደር 5400 የሚሆኑ ቤቶች መፍረሳቸውን የገለጸ ሲሆን፣ የከተማዋ አስተዳደር በዚህ ሂደት እስከ ሚያዝያ ወር አጋማሽ 2016 ዓ.ም. ድረስ ልዋጭ መኖርያ አካባቢ ወይም ይዞታ ያልተሰጠው ነዋሪ ከአጠቃላይ ቁጥሩ 20% የማይበልጥ መሆኑን አክሎ መግለጹም የሚታወስ ነው። በሰኔ እና በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. የሸገር ከተማ አስተዳደር በበኩሉ በአካባቢው በተደረጉ የይዞታ ማስለቀቅ ሂደት እስከ 100ሺህ የሚሆኑ ነዋሪዎች አካባቢውን እንዲለቁ እንደሚደረግ ማሳወቁ ይታወሳል።

ኢሰመኮ የቀረቡለትን አቤቱታዎች መሠረት በማድረግ የመኖርያም ሆነ የንግድ ቤቶችን “ለሕዝብ ጥቅም ወይም ለልማት ሥራዎች” ተግባር በማንኛውም ጊዜ ቢሆን በቅድመ ማስለቀቅ፣ በማስለቀቅ ወቅት እንዲሁም ድኅረ ማስለቀቅ ጊዜ መንግሥት ሊያሟላ የሚገባቸው የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ሊከተል እና በተገቢው የሕግ አግባብ ሊፈጸም የሚገባ መሆኑን በማሳሰብ ከሚመለከታቸው የከተማዋ አስተዳደሮችን ሲያነጋግር እና ለቀረቡ አቤቱታዎች መፍትሔ ለማስገኘት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ሆኖም በአንድ በኩል የከተማዋ አስተዳደር በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. የከተማዋ አስተዳደር እንደገለጸው መግለጫው ይፋ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ብቻ በአዲስ አበባ ያለውን ከፍተኛ የመኖርያ ቤት እጥረት ችግር ለመፍታት ቢያንስ 1.5 ሚልየን መኖርያ ቤቶች እንደሚያስፈልጉ ማሳወቁ የሚታወስ ነው። ከዚሁ ከቤት አቅርቦት ጋር ተያይዞ የከተማዋ አስተዳደር ከ2014 ዓ.ም. በጀት ዓመት ጀምሮ ሲያደርግ ከነበረው የኪራይ ቤት ጭማሪ እገዳዎች በተጨማሪ በመጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. አዲስ የአከራይ ተከራይ ሕግ ይፋ መደረጉ የሚታወስ ነው። ስለሆነም እስከ ሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩ በመጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. በፈረሱ የመኖርያ ወይም የንግድ ቦታዎች ተቀያሪ ይዞታ እንዳልተሰጣቸው ለገለጻቸው ወደ 1400 የሚጠጉ የከተማዋ ነዋሪዎች በአፋጣኝ ልዋጭ ይዞታ ማቅረብን ጨምሮ፣ በይዞታ የማስለቀቅ ተግባር በአጠቃላይ ሰዎችን ቤት አልባ እንዲሆኑ እና መተዳደሪያ ገቢ ማጣት እና ለሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ ማድረግ እንዳይሆኑ አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዲደረግ ኢሰመኮ በድጋሚ ያሳስባል።

በተለይም በቂ የሆነ ቅደመ ማስጠንቀቅያ የመስጠት፣ በተለይም በሂደቱ ወቅት ከመጠን በላይ የሆነ የኃይል አጠቃቀም መከላከልን፣ እንዲሁም በተለይም ተጋላጭ የሆኑ እና አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ትርጉም ባለው መልኩ ማሳተፍን ጨምሮ ይዞታዎቹ የማስለቀቅ ምክንያት በሆነው የሕዝብ ጥቅም ወይም የልማት ሥራን በተመለከተ በሕግ አግባብ አሳታፊ እና አካታች ሕዝባዊ ምክክር/ተሳትፎ ማድረግ እና ይዞታዎች ከመለቀቃቸው አስቀድሞ ለሁሉም ተነሾች ተመጣጣኝ የቅያሪ ይዞታ አቅርቦት ማረጋገጥ ሊታለፉ የማይገባቸው የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች እና መርሖች ናቸው። በአንድ ከተማ ውስጥ ሆነ በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ሁሉንም አካባቢዎች በተመሳሳይ ጊዜ እና የአየር ሁኔታውም አመቺ ባልሆነበት ወቅት ይዞታ የማስለቀቅ ተግባራትም ነዋሪዎችን ለእንግልት የሚዳርግ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት።

በ2016 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ “ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1161/2011” ለማሻሻል ረቂቅ አዋጅ መዘጋጀቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ይህ አዋጅ እና ረቂቅ ማሻሻያው በዋናነት ሕጋዊ ይዞታዎችን የሚመለከት ነው። በተመሳሳይ መልኩም የሕገ ወጥ ይዞታዎችን በተመለከተም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉንም የሚመለከታቸውን የመንግሥት

እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ያቀናጀ ዘላቂ እልባት ሊሰጥ የሚችል ፖሊሲ ሊቀረጽ ይገባል፡፡

ከአዲስ አበባ ውጪም በተለይም የክልል ዋና እና ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ባሉባቸው ከተሞች ያለው የመኖሪያ ቤት እጥረትም ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ለምሳሌ በአፋር ክልል በተለይም በክልሉ በሚገኙ ትልልቅ ከተሞች ሰመራ፣ ሎግያ እና አዋሽ ሰባት ኪሎ በ2016 ዓ.ም. ከፍተኛ የሆነ የቤት ኪራይ ዋጋ ጭማሪ የታየ ሲሆን፣ በኦሮሚያ ክልል ከተሞችም እንዲሁ በተለይም በግጭት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢዎቻቸው ተፈናቅለው ወደ አንጻራዊ ሰላም ወዳለባቸው ከተሞች የሄዱ ሰዎች ብዛት ጋር ተዳምሮ፣ አልያም በአዲስ መልኩ በተደራጁ ክልሎች በዋና ከተማነት በተሰየሙ ከተሞች የሕዝብ ቁጥር ጭማሪ በመኖሩ ምክንያት የመኖሪያ ቤት እጥረት መከሰቱ እየታየ ነው፡፡

በቂ የሆነ መኖሪያ ከማግኘት መብት ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የሚታየው የመሠረተ ልማት አቅርቦትና በተለይም ንጹሕ ውሃ አቅርቦት ችግር ትኩረት የሚሻ ሲሆን፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ያለው የንጹሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ በ2016 የበጀት ዓመት ከወልቂጤ ከተማ የንጹሕ ውሃ አቅርቦት ችግር ጋር ተያይዞ ነዋሪዎች በሰልፍ ተቃውሞ ማሰማታቸው እና በዚሁ ወቅት የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል በመጠቀማቸው ምክንያት የሞቱ እና አካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች መኖራቸው የሚታወስ ነው፡፡ ሆኖም የከተማዋ የውሃ አቅርቦት ችግር እስከ ሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ እልባት አላገኘም፡፡ በአፋር ክልል ሰመራን ጨምሮ ዱብቲ አይሳኢታ ሎግያ አዋሽ 7 ኪሎ ገዋኔ አበአላ የውሃ ስርጭት ችግር ያለባቸው ሲሆን፣ አፍዴራ ኮሪ ኤሊደአር አፋምቦ ቴሩ የመሳሰሉት ወረዳ ነዋሪዎች በአካባቢው ውሃ የሌለ በመሆኑ ከሰመራ በቦቲ ተጭኖ ለአንድ 20 ሊትር ጀሪካን እስከ 50 ብር ያስፈልጋል፡፡



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/ Firehiwot Gizaw

# የሴቶች እና ሕፃናት መብቶች

## የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች

ይህ ምዕራፍ ኢሰመኮ በተለይም በ2016 ዓ.ም ትኩረት አድርጎ ክትትል፣ ምርመራ፥ ጥናት እና ውትወታ ሲያደርግ በቆየባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። በዚህ መሰረት የሴቶች እና የሕፃናት የጤና መብት፣ የትምህርት፣ ከጎጂ ልምዶች የመጠበቅ መብት፣ ፍትሕና ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት፣ የሴቶች የሥራ መብት፣ የሕፃናት ከአስከፊ የጉልበት ብዝበዛ የመጠበቅ መብት፣ የሕፃናት ልዩ ጥበቃ እና ድጋፍ የማግኘት መብቶችን ለሚሟላት የተዘረጉ የሕግ እና የአተገባበር ሁኔታዎችን የተመለከቱ ግኝቶች ተካተዋል።

ኢሰመኮ የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ሁኔታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በቀጠሉ ግጭቶች፣ በድህረ ግጭት ሁኔታ ውስጥ ባሉ አካባቢዎች፣ በመፈናቀል እና በድርቅ ሳቢያ የጤና፣ የትምህርት እንዲሁም ሁሉም ዐይነት ጥቃቶች የመጠበቅ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢ ሆኖ አግኝቶታል።

በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ ባሉ አካባቢዎች በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ፣ በአማራ ክልል በትጥቅ ግጭት ውስጥ ባሉ አካባቢዎች በተለይም በመንግሥት የጸጥታ አካላት አባላት የሚፈጸሙ የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃትን ኢሰመኮ ከመንግሥት የጤና ተቋማት ጨምሮ የተገኙ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ መንግሥት በአፋጣኝ ይህ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በአፋጣኝ እንዲቆም እና የጥሰቱ ሰለባ ለሆኑ ሴቶችም ተገቢው አገልግሎቶች መቅረቡን እንዲያረጋግጥ ማሳሰቡ የሚታወስ ነው። በክልሉ አካባቢዎች በትጥቅ ግጭት ሳቢያ የደረሱ የጤና እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሰጪ ተቋማት መውደም ወይም አገልግሎት መቋረጥ እና መስተጓጎል የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች አስከፊ ሁኔታን የሚያባብስ ነው። ለተለያዩ ጊዜያት በግጭት ውስጥ በቆዩ ሌሎች ክልሎችና አካባቢዎችም የወደሙ የጤና እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን መልሶ የማቋቋም እና አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረጉ ሥራ መዘግየት ምክንያትም የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኙ ከሚያደርጉ ምክንያቶች በመሆኑ የመልሶ ማቋቋሙ ሥራ ተገቢውን ትኩረት ሊያገኝ ይገባል።

ኢሰመኮ በድኅረ ግጭት ዐውድ ባሉ በአፋር፣ በትግራይ እና በቤኒሻንጉል ክልሎች የእናቶች እና የጨቅላ ሕፃናት የጤና መብቶችን የተመለከተ ባደረገው ክትትል መንግሥት በያዘው እቅድ መሠረት የጤና ተቋማት መልሶ አለመገንባት፣ የመሠረተ ልማት ውድመት፣ የሰው ሀብት፣ የመድሃኒት፣ የክትባትና የምግብ አቅርቦት ውስንነት፣ የድጋፍና የበጀት የተገኝነት ችግሮች ሳቢያ እናቶችና ጨቅላ ሕፃናት በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ፣ ድህረ ወሊድ፣ በድንገተኛ ወሊድ ወቅት ሊያገኙ የሚገባቸውን መሠረታዊ አገልግሎቶች እያገኙ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ለጨቅላ ሕፃናትም በሕይወት የመኖር መብትን ተግባራዊ ለማድረግ መሠረታዊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶች በተሟላ መልኩ ተገኚ አይደሉም። በዚህም ሳቢያ በሕክምና ተቋማት የሚወልዱ እናቶች ቁጥር መቀነሱ፣ በከፍተኛ የምግብ እጥረት የተጠቁ ሕፃናት እና እናቶች ቁጥር መጨመር ማሳየቱን በዚህም ሳቢያ ክትትል በተደረገባቸው አካባቢዎች የእናቶችና የጨቅላ ሕፃናት ሞት እንደጨመረ ታውቋል።

ኢሰመኮ በትግራይ ክልል ባከናወነው ክትትል እና የውትወታዎች በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ሳቢያ ለወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃቶች ተጎጂ ለሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት የሚሰጡ የማገገምና የመልሶ ማቋቋም ድጋፎችን ሁሉን አቀፍ እና የቀናጀ አለመሆኑ፣ ተጎጂዎች ሰብአዊ ክብራቸው የጠበቀ፣ ተደራሽ እና ሚስጥራዊነቱ የጠበቀ አገልግሎት ማግኘት መብታቸውን የሚያጓድል መሆኑ ተረድቷል። ለተጎጂዎች የሚሰጡ የሕክምና፣ ማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ አገልግሎት፣ የሕግ፣ የመጠለያ፣ መልሶ የመቀላቀል ሥራዎች አካባቢያዊ ተደራሽነት ውስን መሆን በተለይም በገጠር ለሚኖሩ ተደራሽ አለመሆኑ እንዲሁም አገልግሎቶች ባልመጣጠነ

መልኩ ስልጠናዎች ላይ ማተኮራቸው ታውቋል። የኢሰመኮ ግኝቶችን መሰረት ችግሮቹን ለማስተካከል የክልሉ መንግሥት እና በክልሉ አገልግሎት የሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያሳዩት ተነሳሽነት አበረታች ሆኖ ኮሚሽኑ አግኝቶታል።

በትጥቅ ግጭት ሳቢያ የደረሱ የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሰጪ ተቋማት መውደም ወይም አገልግሎት መቋረጥ እና መስተጓጎል ወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች የደረሰባቸውን አስከፊ ጉዳትን የሚያባብስ ነው። ለምሳሌ በ2016 ዓ.ም. ከአማራ ክልል 4 ሚልዮን የሚሆኑ ሕፃናት ከትምህርት ውጪ መሆናቸውን የአማራ ክልል መንግሥት በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. አስታውቋል። በተለያዩ ጊዜያት በግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎችም የወደሙ የጤና እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን መልሶ የማቋቋም እና አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረጉ ሥራ መዘግየት ምክንያትም የወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃት ሰለባዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኙ ከሚያደርጉ ምክንያቶች በመሆኑ የመልሶ ማቋቋሙ ሥራ ተገቢውን ትኩረት ሊያገኝ ይገባል።

ኢሰመኮ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የሚያልፉ የጥቃቶች ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን በተመለከተ ከሐምሌ 29 እስከ ነሐሴ 8 ቀን 2015 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ ጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ ወረዳ፣ በሐረሪ ክልል፣ በሐረር ከተማ እና በኤረር ወረዳ ክትትል አድርጓል። ክትትሉ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ከወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የሚያገኙት አገልግሎት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው የሰብአዊ መብቶች መርሖችን እና ድንጋጌዎችን የተጣጣመ አለመሆኑ አሳሳቢ ሆኖ አግኝቶታል። ለዚህም ምክንያቶቹ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናትን አስመልክቶ ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት የተለየ የሥነ ሥርዓት ሕግ አለማስቀመጡ፤ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ውጪ ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን የተመለከተ አስገዳጅና ወጥ የሆነ ሀገር አቀፍ የሥነ ሥርዓት መመሪያ/ፕሮቶኮል አለመኖሩ፤ የጥቃት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶችና ሕፃናት እንደ የማገገሚያ፣ የመጠለያ፣ የሕክምና እና የሥነ ልቦና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስችሉ መፍትሔዎች በሕግ አለመንደንገጉ እንዲሁም የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተቀመጠላቸው የአሠራር ሥርዓት ማኑዋል መሠረት አለመሥራታቸውን ዋነኛ ምክንያቱ መሆኑን ተረድቷል።

ከዚህ በተጨማሪ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ በሆኑ ምክንያቶች በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሴቶች እና ሕፃናት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ነው። ከሰብአዊ ድጋፍ እጦት ወይም እጥረት በተጨማሪ በግጭት አካባቢዎች በሚገኙ የስደተኛ እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያዎች የጸጥታ እና የደኅንነት ስጋት የተፈጠረባቸው ክስተቶች በዘንድሮ በጀት ዓመት ተመዝግበዋል። በዚሁ በጀት ዓመት ከትጥቅ ግጭት በተጨማሪ በጎርፍ እና በድርቅ ሳቢያ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሴቶች እና ሕፃናትን ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል። ዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት ባወጣው ሪፖርት መሠረት እስከ ታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ከተመዘገቡት ወደ 3.2 ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ውስጥ ከ52 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ 55 በመቶ የሚጠጉት ደግሞ ከ18 ዓመት በታች ናቸው። በተመሳሳይ የተ.መ.ድ. የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ባወጣው ሪፖርት መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ 1.1 ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች 52 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ 54 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከ18 ዓመት በታች ናቸው። ስለሆነም ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ሕፃን ተፈናቃዮች እና ለሴት ተፈናቃዮች ልዩ ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ የሰብአዊ ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም በአብዛኛው ከትምህርት ውጪ ለሆኑ እና በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት የትምህርት አገልግሎት ማግኘት ጉዳይ አስቸኳይ ትኩረት የሚሻ ነው።

በተለይም ለረዥም ጊዜ በትጥቅ ግጭት ውስጥ የቆዩ አካባቢዎች ባሉባቸው የኦሮሚያ፣ የጋምቤላ እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ዋና ከተሞች በጎዳና ላይ የሚኖሩ ሴቶች እና ሕፃናት ቁጥር በሚታይ መልኩ መጨምሩን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች አሉ። ይህ አዝማምያ በማዕከላዊ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በሲዳማ ክልሎች ከተሞችም ጭምር የሚታይ ነው። በአዲስ መልኩ በተዋቀሩ የደቡብ ክልሎች ብቻ ሳይሆን፣ በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች በተለይም ሕፃናትና ታዳጊዎች በጉልበት ሥራ የተሰማሩ እና ለጉልበት ብዝበዛ የተጋለጡ ሕፃናትና ታዳጊዎች ብዛት ከፍ እንዲል የሚያደርግ እና ክፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው።

በሀገር አቀፍ የጸጥታ ሁኔታውና በሌሎች ተጓዳኝ ምክንያቶች ቀደም ሲል ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚሠሩባቸው የሴቶች እና የሴት ሕፃናት ጉዳዮች ትኩረት እንዲነፈጋቸው ወይም እንዲቀንስ አድርጓል። በዚህም ምክንያት የሴቶች ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ሌሎች ጎጂ ልማዶች በብዙ ክልሎች መልሶ እያገረሸ ወይም እየተስፋፋ ስለመምጣቱ የሚያመላክቱ በርካታ መረጃዎች አሉ። ለምሳሌ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ ኮሬ ዞን በተስፋፋ ጠለፋ ሳቢያ ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት መላክ እስከማቆም መድረሳቸውን ኢሰመኮ መረጃዎች ደርሰውታል። የሴቶች ጠለፋ በሲዳማ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች አሳሳቢ የሰብአዊ መብት ጥሰት እየሆነ መጥቷል። በጋምቤላ ክልል በአንድ በኩል በጋብቻ ላይ የሚፈጸም ጋብቻ እየጨመረ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ለጋብቻ የሚጠየቅ የጥሎሽ ገንዘብ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ጋብቻ የሚፈጽሙ ወጣቶች ቁጥር መቀነሱ ይታያል። የጋምቤላ ክልል ፍትሕ ቢሮ የቀድሞውን የክልል የቤተሰብ ሕግ ለማሻሻል ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል። በተመሳሳይ በአፋርና ሱማሌ ክልሎች የተዘጋጁ ረቂቅ የቤተሰብ ሕጎች እንዲጸድቁ የሚደረጉ ጥረቶች ቀጥለዋል። በሶማሌ ክልል፣ በጅግጅጋ ከተማ ከሚገኘው የአንድ መስኮት አገልግሎት የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶች እየጨመሩ መጥተዋል።

በዚህ ረገድ ለምሳሌ ኢሰመኮ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሃዲያ ዞን፤ ሻሸጎ፣ ሶሮና ምዕራብ ሶሮ ወረዳዎች በሚገኙ ወረዳዎች የሚፈጸም የሴት ልጅ ግርዛት እና ዳግም ግርዛትን በተመለከተ አፋጣኝ የሰብአዊ መብቶች ክትትል አድርጎ ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የውትወታ መድረክ አዘጋጅቷል። በወረዳዎቹ የሴት ልጅ ግርዛት እና ዳግም ግርዛት በየትኛውም የእድሜ ክልል ላይ ያሉ ሴቶችና ሕፃናት መራቢያ አካላቸው አካባቢ ከሚያጋጥማቸው የጤና እክል ይፈወሳሉ በሚል የተሳሳተ አመለካከት ግርዛቱ እንደተስፋፋ ለማረጋገጥ ችሏል። ክትትል በተደረበት ወቅት ለጤና እክሉ የሚሰጡ መፍትሔዎች ኣናሳ መሆናቸው፥ የግንዛቤ ችግሮች እና የተጠያቂነት መላላት እንደዋና ምክንየት ተለይቶ ነበር። ኢሰመኮ የገና በዓልን አስታኮ ሊፈጸሙ የታቀዱ ግርዛቶችን ለማስቀረት እና የወንጀሉ ፈጻሚዎችም ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያስችሉ እርምጃዎች በባለግዴታዎች እንዲወሰዱ መደረጉ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና ግንዛቤን ለማሳደግ የተወሰዱ እርምጃዎችን መኖራቸው አበረታች ሆኖ አግኝቶታል።

በአፋር፣ በአማራ እና በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች በመንገድ የሚጣሉ አዲስ የተወለዱ ጨቅላ ሕፃነት ቁጥር ማሻቀቡን ከጸጥታ አካላት በየጊዜው ከክልሎቹ የጸጥታ አካላት የሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይም በትጥቅ ግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች፣ እንዲሁም በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ያሉ እና ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናት እና ታዳጊዎች ብዛት በአግባቡ ለመሰነድ እና አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ በቂ ጥረት ካለመደረጉ ጋር ተዳምሮ ይህ በመንገድ ዳር የሚጣሉ ጨቅላ ሕፃነት ጉዳይ የሕፃናት ማሳደጊያዎችን ማቋቋም፣ ማስፋፋት እና ማጠናከርን ጨምሮ አፋጣኝ እና ተገቢውን ትኩረት የሚሻ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ኢሰመኮ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ውስጥ ያሉ ሕፃናት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን የተመለከተ የክትትል ሪፖርት በጥር ወር 2016 ዓ.ም. አውጥቷል። በአማራ፣

በሐረሪ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙ 25 የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ላይ ያደረገው ክትትል አንዳንድ ሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተሟላ መልኩ የሕፃናቱን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የተሰባጠረ እና ዝርዝር መረጃ እንዳልያዙ፣ ከሁለት ተቋማት በስተቀር በሁሉም ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት ለተለያዩ ጥቃቶች የተጋለጡ መሆናቸው፣ የሕፃናት ምግብ የማግኘት መብት በአቅርቦት፣ በጥራትና በተስማሚነት እንዲሁም ከምግብ ሥርዓት ተገቢነት አንጻር የተሟላ እንዳልሆነ፤ በአንድ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት መኖራቸው እና በአብዛኞቹ ተቋማት ሕፃናቱ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል እንዲሁም ወጥና ለሕፃናት ምቹ (child friendly) የሆነ የቅሬታ መቀበያ እና መፍቻ ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ አለመኖሩ በክትትሉ ከተለዩ ዋና ዋና የመብት ጥሰቶች መካከል ናቸው። በተጨማሪም ክትትል የተደረገባቸው አብዛኛዎቹ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የአካል ጉዳተኛ ሕፃናትን የአካል ጉዳት ዓይነት እና ፍላጎት መሠረት ያደረገ አገልግሎትን ከማቅረብ አንጻር ክፍተት እንዳለባቸው በሪፖርቱ ተመላክቷል።

ኮሚሽኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው በተሐድሶ (ማቆያ) ማዕከል ውስጥ በሚገኙ ሕፃናት የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ ባከናወነው ክትትል ተቋሙ በቅበላ ወቅት የሕፃናቱን ሁኔታ የሚመለከት የተሟላ እና ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ የመረጃ አያያዝ የሌለ መሆኑ፤ ከሕፃናት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰራተኞች በሕፃናት መብቶች ዙሪያ የተለየ ሥልጠና የወሰዱ አለመሆናቸው፤ በማዕከሉ ለሚገኙ ሁሉም ሕፃናት ስለሚገኙበት ዝርዝር ሁኔታ ለቤተሰቦቻቸው የማይገለጽ መሆኑ፤ በቂ የሕግ ባለሙያ ድጋፍ ለማግኘት ያለመቻላቸው፤ ሕፃናትን በማደሪያ ክፍሎቻቸው በዝግ ማቆየት፣ ስድብ፥ ማስፈራርያ እና ድብደባ የሚደርስባቸው እና የጉልበት ሥራ የሚሰሩ መሆኑን ተገንዝቧል። በተጨማሪም አንዳንድ ሠራተኞች ማታ ላይ ጠጥተው እየገቡ የሚሰድቧቸው እና የሚደበድቧቸው መሆኑ፤ ሕፃናት ከማእከሉ የሚወጡበት እና ከወጡ በኋላ ያሉበትን ሁኔታ የሚመለከት መመሪያ እና ወጥ አሠራር አለመኖሩ፤ የተሐድሶ ተቋሙ የሚያጋጥሙትን ችግሮች በአፋጣኝ ለመቅረፍ የሚያስችል አሠራር አለመዘርጋቱ፤ ለአካል ጉዳተኛ እና ሴት ሕፃናት አካታች እና ምቹ አገልግሎት አለመኖሩ፤ ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች እጥረት መኖሩ እና በቂ የሆነ የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የሕክምና አገልግሎት አለመኖሩን አሳሳቢ ሆኖ አግኝቶታል።



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Nahom Girma

# አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን

# የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች

ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የጤና፣ የትምህርት፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን እና አካባቢዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከሕግ እና ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ ከሀብት ምደባ እንዲሁም ከሰው ኃይል የግንዛቤ አቅም አኳያ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰጠው ትኩረት የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶችን ድንጋጌዎችን እና መርሖችን ለማሟላት በርካታ ክፍተቶች ያሉበት ነው፡፡ ኢሰመኮ ባለፉት ሦስት ዓመታት በተለይም ቅድሚያ ሰጥቶ ክትትል ባደረገባቸው የፍትሕ፣ የትምህርት እና የትራንስፖርት ተደራሽነት እንዲሁም የአረጋውያን እንክብካቤ ማዕከላት ምቹነት ከታዩ ግኝቶች በመነሳት በሰጣቸው ምክረ ሐሳቦች የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ወጥ የሆነ እና የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ፣ እንዲሁም ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግ አስፈጻሚ መዋቅር ጨምሮ በተለይም የትምህርት፣ የፍትሕ እና የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት ከባቢያዊ፣ ተቋማዊ እና የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነትን የማረጋገጥ አስቸኳይነት እና አስፈላጊነትን በተመለከተ በተደጋጋሚ ውትወታ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከዚሁ ከተደራሽነት ጋር ተያይዞ በተለይም ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተደራሽ ለማድረግ በክልልም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን ብዛት በተመለከተ ያለው የመረጃ ክፍተት የችግሩን አሳሳቢነት ደረጃ በአግባቡ ለመረዳትም ሆነ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑን ኮሚሽኑ አመላክቷል፡፡

በትጥቅ ግጭት ሳቢያ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች፣ እንዲሁም በመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ በመሆናቸው አልያም የገቢ እና የድጋፍ ምንጫቸውን በማጣታቸው ምክንያት፣ እንዲሁም በተለይም ለተደራራቢ ተጋላጭነት የተዳረጉ ሴት አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቁጥር በሺዎች የሚቆጠር እንደሆነ የሚገመት ነው፡፡ በተጨማሪም የትጥቅ ግጭቶች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች እና መፈናቀል የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያንን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሁኔታ የሚያባብስ እና ለጥሰቱም ያላቸውን ተጋላጭነት የሚጨምር ነው፡፡ ለምሳሌ በአማራ ክልል፣ ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታና በትጥቅ ግጭቱ ሳቢያ በሚጣሉ የሰዓት እላፊና የእንቅስቃሴ ገደቦች ምክንያት በተለይም በአነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ሥራ ዘርፍ የሚተዳደሩ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ለችግር ተዳርገዋል፣ በደሴ እና በደብረ ማርቆስ የሚገኙ የአረጋውያን ማእከላት ግንባታ በግጭቱ ምክንያት ተቋርጧል፣ በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች በተከሰተ ድርቅ እንዲሁም የሰብአዊ ድጋፍ እጥረት ምክንያት በርካታ አካል ጉዳተኞችና አርጋውያን ለምግብ እጥረት ተጋልጠዋል፡፡

በአብዛኛው የሀገሪቱ ክልሎች በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያሉ ወይም በትጥቅ ግጭት ውስጥ የቆዩ አካባቢዎች የሚገኙ እንደመሆኑ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አካባቢዎቹን እና ተጎጂዎቹን መልሶ በማቋቋምም ሆነ የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት በማረጋገጥ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ሆኖም በዘንድሮ በጀት ዓመት በተወሰኑ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያዎች በተደረጉ ክትትሎች (በአማራ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በኦሮሚያ እና በትግራይ ክልሎች) ለአካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ተፈናቃዮች ልዩ ፍላጎታቸውን ያማከለ ሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት በማድረግም ሆነ የመጠለያዎቹን ከባቢያዊ ተደራሽነት በማረጋገጥ ረገድ አሁንም በቂ ትኩረት አለመሰጠቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ደቡብ ኦሞ ዞን፣ ዳሰነች ወረዳ በጥር ወር 2016 ዓ.ም. የተደረገ ክትትል አካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን ጨምሮ ለተደራራቢ የመብቶች ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂ እና ፍላጎታቸውን ያማከለ ሰብአዊ ድጋፍ የማይቀርብ መሆኑን ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡ በኦሮሚያ ክልል፣ በምሥራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የመመለስ ቅድመ ዝግጅት ሂደት አካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን ጨምሮ ለተደራራቢ የመብቶች ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ ተቀባይ ዞኖቹም ሆነ ወረዳው የተሰባጠረ መረጃ (disaggregated data)

የሌላቸዉ በመሆኑ ተደራራቢ ተጋላጭነት ያለባቸውን ሰዎች ፍላጎት መሠረት ያደረገ ምላሽ ለመስጠት በቂ ቅድመ ዝግጅት አለመደረጉ፣ ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ተመላሾች የተለየው ማቆያ ቦታ ምቹ እና ተደራሽ አለመሆኑ፣ የጤና አገልግሎት አለመኖሩ፤ በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ ፍጆታ ያልተዘጋጀ እና በምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ ዋዩ ቱቃ ወረዳ ልዩ ስሙ ገባ ሰንባታ በተባለ ስፍራ በሚገኝ ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ ለተመለሱ ተፈናቃዮችም በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ ያልቀረበ መሆኑ ኮሚሽኑ በዘንድሮ በጀት ዓመት ባደረገው ክትትል ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ተፈናቃዮችን መሠረት ያደረጉ ሰብአዊ ድጋፍና ማኅበራዊ አገልግሎቶች አለመኖራቸው ፣ ተፈናቃይ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን መልሶ የማቋቋምና የተመቻቸ የሥራ ዕድል አለመኖሩ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ለነዚህ ተደራራቢ የመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች በበቂ ሁኔታ ልዩ ክትትልና ድጋፍ እያደረጉ አለመሆኑን ተመልክቷል፡፡

በተደራራቢ ተጋላጭነት ውስጥ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ሁኔታ አፋጣኝ እርምጃዎችን የሚሻ ሲሆን፣ የትምህርት አገልግሎትን ለአካል ጉዳተኛ ሕፃናት እና ታዳጊዎች ተደራሽ ማድረግ፣ እንዲሁም በተለይም በትጥቅ ግጭት ሳቢያ የገቢ ምንጫቸውን ላጡ አረጋውያን ድጋፍ የሚደረግበትን መንገድ ማመቻቸት ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ እና በመካከለኛ እና በረዥም ጊዜ ሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚፈጥር ነው፡፡

በ2016 በጀት ዓመት በክልል ደረጃ የታዩ እና የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን መብቶች የተመለከቱ የተወሰኑ መልካም ጅማሮዎች ቢኖሩም በሀገር አቀፍ ያለውን እና በተለይም ከትጥቅ ግጭት ዐውድ ጋር የተያያዙ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አንጻር በቂ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ በአዲስ መልኩ በተዋቀሩት የደቡብ፣ የማዕከላዊ እና የደቡብ ምዕራብ ክልሎች የተወሰኑ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች ጸድቀዋል፡፡ በአዲሱ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 127 ጀምሮ በተደነገገው የክልሉ የፖሊሲ ዓላማዎች አካል ጉዳተኞች ትኩረት እንደሚደረግላቸው መደንገጉ እና ለዚሁም ዓላማ የተለያዩ ሕግጋት መውጣት እንዳለባቸው መጠቀሱ፤በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የአረጋውያን እና ጡረተኞች ማኅበር መመስረቱ እና በማእከላዊ ኢትዮጵያ የማኅበር ምስረታ ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ያለ መሆኑ፣ ከነሐሴ 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ የገባው የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 27/1 ላይ አካል ጉዳተኝነትን መሠረት ያደረገ መድሎን በግልጽ የከለከለ መሆኑ እንዲሁም የማእከላዊ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት ህብረት/ፌደሬሽን መቋቋሙ እና ለአካል ጉዳተኞች ማኅበራት ኅብረቶቹ የሚሆን በፈረሰው ክልል ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት መያዙ ሊጠቀሱ ከሚችሉ እመርታዎች መካከል ናቸው፡፡ በሲዳማ የሲዳማ ክልል ትምህርት ቢሮ ለተማሪዎች ተስማሚ የመማሪያ ቁሳቁሶች መግዛቱም እንዲሁ መልካም ጅማሮ ነው፡፡

ኢሰመኮ በ2015 በጀት ዓመት 5 የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ያላቸውን ተደራሽነት አስመልክቶ ባከናወነው ክትትል እና በ2016 በጀት ዓመት ባካሄደው የውትወታ እና የምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል አማካኝነት በተለዩ ግኝቶች ላይ ማሻሻያዎች እየተደረጉ ያሉ መሆናቸው እና በዩኒቨርሲቲዎቹ ኃላፊዎች እንዲሁም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የኮሚሽኑን ምክረ ሐሳቦች ለመተግበር ቁርጠኝነት መታየቱ አበረታች ነው፡፡ ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል፣ ጅማ ዩንቨርሲቲ በተሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት ተቋሙን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ የማሻሻያ ሥራዎችን ማካሄዱ እና የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ነባር ሕንጻዎችን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ለማድረግ የራምፕ ግንባት ማስጀመሩን በግንቦት 19 ቀን 2016 ዓ.ም. በይፋዊ ድረ ገጹ ላይ ማሳወቁ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ተደራሽ ባልሆነ አካባቢ እንዲያስተምሩ የተመደቡ እና በዚሁ ምክንያት በሥራ ቦታቸው ላይ መገኘት ባለመቻላቸው የታገዱ እንዲሁም ደሞዛቸው የተቋረጠ 8 አይነስውራን መምህራንን አስመልክቶ የአማራ

ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ከሥራ እንዲታገዱ የተደረገበት አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲነሳ እና ወደ ሌላ አመቺ የሆነ ስፍራ እንዲመደቡ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት መምህራኑ ሳይከፈላቸው የቀረው ደመወዝ ተከፍሎ አመቺ ወደሆነ ስፍራ ምደባ እንዲያገኙ መደረጉ፤ ክልሉ ከ5ኛ-8ኛ ላሉ አይነ ስውራን ተማሪዎችና መምህራን የመማሪያ መጽሐፍት በብሬል እያሳተመ መሆኑም ተጠቃሽ እመርታዎች ናቸው።

የአረጋውያን ሰብአዊ መብቶች በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል፣ በበደሌ እና በዝዋይ ከተሞች በግንባታ ላይ የነበሩት የአረጋውያን ማእከላት ተመርቀው ሥራ መጀመራቸው በአበረታች ጅማሮ የሚጠቀስ ነው። በትግራይ ክልል የሚገኙ ጡረተኞች በጦርነቱ ምክንያት ሳይከፈላቸው የቆየው የ18 ወራት የጡረታ አበል ክፍያ እንዲከፈል መወሰኑ የአረጋውያን የሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ በዚህ በጀት ዓመት ከተመዘገቡ መልካም እመርታዎች መካከል ነው።

የማኅበራዊ አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተደራሽነት ሁኔታን በተመለከተ ኢሰመኮ ከሚያደርገው ክትትል በዘንድሮ በጀት ዓመት ትኩረት ካደረገባቸው ዘርፎች አንዱ ትራንስፖርት ሲሆን፣ በተለይም ከመዳረሻዎች ቁጥር ውስንነት እና በወቅታዊው ሀገራዊ የጸጥታ ሁኔታ ሳቢያ ተመራጭነቱ እየሰፋ በመጣው የአየር ትራንስፖርት ላይ ዋነኛ ትኩረቱን አድርጓል። በዚህም የተወሰኑ የአየር ማረፊያዎች ለአካል ጉዳተኞች ያላቸውን የተደራሽነት ሁኔታ (ተቋማዊ፣ ከባቢያዊ ፣ የመረጃ እና ተግባቦት ተደራሽነት እንዲሁም የአመለካከት ተግዳሮቶች) በተመለከተ ባደረገው የአካል ምልከታ፣ የተጠቃሚዎች እና የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር እንዲሁም ተገቢውን የሕግ ማዕቀፍ በማጣቀስ በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት የአየር መንገዱ አስፈላጊውን ማሻሻያዎች ለማድረግ ተነሳሽነቱን በመግለጽ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ መጀመሩን ለኮሚሽኑ አሳውቋል። የኮሚሽኑ ክትትል የሚቀጥል ይሆናል።

የአካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ በክልል ደረጃ የታዩ እመርታዎች እንደመኖራቸው ሁሉ ካለፈው በጀት ዓመት አኳያ የተባባሱ ወይም አሳሳቢነታቸው አሁንም የቀጠለ ጉዳዮችም ታይተዋል። ለምሳሌ በ2015 በጀት ዓመት በአፋር ክልል፣ በሰመራ የተገነባው የአካል ጉዳተኞች የተሐድሶ ማእከል በዘንድሮ በጀት ዓመትም ወደ ሥራ ባለመግባቱ በክልሉ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች የአካል ድጋፍ አገልግሎት ለማግኘት በእጅጉ መቸገራቸው፤ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ማእከሉን የተለያዩየክልሉ የመንግሥት ቢሮዎች በተያየ ዘርፍ እንዲመሩት በመደረጉ ብዥታን በመፍጠር ሥራዎችን በማጓተት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ነው። በተመሳሳይ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በአሶሳ ከተማ ለአረጋውያን ማእከል ግንባታ ተብሎ ተሰጥቶ የነበረው ቦታ ከሁለት ዓመታት በፊት በመንግሰት ተመልሶ መወሰዱ እና ይህ ሪፖርት ይፋ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ምትክ ቦታ ያልተሰጠ መሆኑ ታውቋል።

የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ሰብአዊ መብቶች በተመለከተ ያሉ የአመለካከት መሰናክሎች እና የግንዛቤ ክፍተቶች በተጨባጭ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተጎጂ እና ሰለባ የሚያደርጉ መሆኑን ኢሰመኮ በሚያደርጋቸው ክትትሎች እና ምርመራዎች በተደጋጋሚ የሚያመላክተው ነው። ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ባካሄደው ምርመራ በክልሉ የሚገኙ ዓይነ ስውራን ሠራተኞች በተለይም ዓቃቤያነ ሕግ ረዳት የማይቀጠርላቸው በመሆኑ ሥራቸውን ከጉዳት አልባ አቻዎቻቸው እኩል ተወዳዳሪ ሆነው ለመሥራት የሚቸገሩ መሆኑን ተመልክቷል።

ስለሆነም የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብቻ ሳይሆን የመብት ተጠቃሚ የሆኑትን አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ግንዛቤ ማሳደግ እና የሰው ኃይል አቅም መገንባት፣ እንዲሁም የመብቶች ተሟጋች ማኅበራት እንዲቋቋሙ እና ያሉትም እንዲጠናከሩ ማድረግ

የሚመለከታቸውን የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ቅንጅት እና ተጨማሪ ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Yakob Belete

# የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች

# የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች

## የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች

የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ጨምሮ ስደት እና ፍልሰትን በተመለከተ ክትትል በማድረግ መረጃዎችን በየጊዜው በሚያወጣው በዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት (International Organization for Migration) መረጃ መሠረት እስከ ታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር ወደ 3.2 ሚልዮን የሚጠጋ ነው። በተጨማሪም ይህ ቁጥር በአማራ ክልል በሚካሄደው የትጥቅ ግጭት፣ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች (ድርቅ እና የጎርፍ መጥለቅለቅ) እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት በሚያገረሹ የትጥቅ ግጭቶች ሳቢያ በደረሱ መፈናቀሎች ምክንያት እንደጨመረ ወይም እንደሚጨምር የተለያዩ የሰብአዊ ድጋፍ የሚያቀርቡ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይፋ ያደረጓቸው መረጃዎች ያሳያሉ። የሀገሪቱ ሁሉም ክፍሎች በሚባል ደረጃ የተለያየ ብዛት ያላቸው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሚያስተናግዱ ሲሆን፣ እነዚህ ተፈናቃዮች በመጠለያዎች፣ በጊዜያዊ የሰፈራ ቦታዎች ወይም ከማኅበረሰቡ ተቀላቅለው የሚኖሩ ናቸው።

ኢሰመኮ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተመለከተ የሚያደርገው ክትትል የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመፈናቀል ውስጥ ባሉበት ወቅት የመንግሥት ግዴታዎች የሆኑትን የመመዝገብ፣ የግል ሰነድ የመስጠት፣ እንቅስቃሴን የማመቻቸት፣ የደኅንነት ጥበቃ፣ የመጠለያ እና ሌሎች የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት፣ እንዲሁም የማኅበራዊ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሏቸውን መብቶች የሚመለከት ሲሆን በሌላ በኩል ከመፈናቀል ሁኔታ ለመውጣት የሚያስችላቸው እና በዋነኝነት የመንግሥት ግዴታ የሆነው ዘላቂ መፍትሔ የማፈላለግ ተግባር አፈጻጸም ላይ የሚያተኩር ነው። ከዚህ የክትትል ሥራ ጎን ለጎን የሀገር ውስጥ መፈናቀል ሁኔታን ለመከላከል በመንግሥት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት፣ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተገቢውን ጥበቃ የሚያደርጉ የሕግ፣ የፖሊሲ፣ የመዋቅር እና የሀብት ምደባ ተግባራት አፈጻጸምን ይከታተላል፤ ወደ ሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትም ውትወታ ያደርጋል።

ኢሰመኮ የተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ ዓመታዊ የዘርፍ ሪፖርት ይፋ ማድረግ ከጀመረበት ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ ባደረገው ክትትል እንዳመላከተው ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው ክልሎች በተቀባይ ማኅበረሰብ፣ በመንግሥት እንዲሁም መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሰብአዊ ድጋፍ በተለይ የምግብ ድጋፍ ለማቅረብ የሚደረገው ጥረት፣ በተወሰኑ የተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎች በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የተሰባጠረ የተፈናቃዮች የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መኖሩ፣ የኢሰመኮን የክትትል ግኝቶችና ምክረ ሐሳብ ተቀብለው የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጡ የወረዳ፣ የክልል እንዲሁም የፌዴራል አመራርና ተቋማት መኖራቸው በ2016 በጀት ዓመትም ከታዩ መልካም እመርታዎች መካከል ናቸው።

ኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገውን የአፍሪካ ኅብረት ስምምነትን (ካምፓላ ስምምነት) ካጸደቁ 33 የአፍሪካ ሀገራት አንዷ ስትሆን፣ ስምምነቱ ብሔራዊ ሕግ እና ተቋማዊ መዋቅር እንዲኖር ማስቻልን ዋነኛ የመንግሥት ኃላፊነት በማድረግ በደነገገው መሠረት የካምፓላ ስምምነትን ለማስፈጸም የተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ጸድቆ ሥራ ላይ ባለመዋሉ እና የተፈናቃዮችን ጉዳይ በባለቤትነት የሚያስተዳድር ተቋማዊ አደረጃጀት አለመኖሩ፤ መፈናቀልን ለመከላከል፣ ለተፈናቃዮች የሚደረጉ የጥበቃ እና ድጋፍ ሥራዎች እንዲሁም የዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግ ሂደቶች ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች አሁንም አሳሳቢነታቸው እንደቀጠለ ነው።

የተፈናቃዮች ምዝገባ እና ሰነድ የማግኘት መብትን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ የታዩ ጅማሮዎች ቢኖሩም በሀገር አቀፍ ደረጃ በምዝገባ እና በሰነድ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ያለው ክፍተት መቀጠሉ ለተፈናቃዮች የሚደረገው ድጋፍ በአግባቡ እንዳይከናወን አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩ በተጨማሪ ተፈናቃዮች ሌሎች የመንቀሳቀስ እና የማኅበራዊ አገልግሎት የማግኘት መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዳይችሉ እንቅፋት መፍጠሩ እንደቀጠለ ነው።

ወቅቱን የጠበቀ፣ በቂ፣ ያልተቆራረጠ እንዲሁም ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸውን ተፈናቃዮች መሠረት ያደረገ የሰብአዊ ድጋፍ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት አለመኖሩ ተፈናቃዮች ይህንን ክፍተት ለመሙላት እና ያሉበትን ሁኔታ ለመቋቋም አሉታዊ ውጤት ያላቸው አማራጮችን (Negative Coping Mechanisms) እንዲወስዱ መገደዳቸው አሳሳቢ ሲሆን፤ በተጣበበ የመጠለያ ሸራ ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች ወይም የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ሰዎች በጋራ እንዲኖሩ መደረጉ ሴቶችን እና ሕፃናትን ለጾታዊ ጥቃት እና ለጉልበት ብዝበዛ ተጋላጭ የሚያደርግ ነው።

ሆኖም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በአንዳንድ አካባቢዎች የተመዘገቡ መልካም እመርታዎች አሉ። ኢሰመኮ በሐረሪ ክልል በሐኪም ወረዳ በሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ እንዲሁም በሸንኮር ወረዳ በሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ ከየካቲት 17 እስከ 23 ቀን 2016 ዓ.ም. የክትትል ሥራ ካከናወነ በኋላ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሚደረገው የዘላቂ መፍትሔ አተገባበር ከሰብአዊ መብቶች አንጻር የተቃኘ እንዲሆን አድርጓል። በዚህም ኢሰመኮ በክትትሉ ወቅት ሰብአዊ መብቶችን ያማከለ ተፈናቃዮችን በዘላቂነት የማቋቋም ሂደት ምን መመሰል እንዳለበት ግንዛቤ የሚፈጥር ሰነድ አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ተቋማት እንዲደርስ አድርጓል። የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል ለመወትወትም የክትትል ግኝቶችን እና ምክረ-ሐሳቦችን ያየዘ አጭር ሪፖርት በየደረጃው ለሚገኙ የክልል እንዲሁም የፌዴራል የመንግሥት አካላት አቅርቧል፤ በተጨማሪም ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው ቦታዎች ግንቦት 12 ቀን 2016 ዓ.ም. የምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል አከናውኗል። በዚህም ክልሉ ለተፈናቃዮች ዘላቂ መፈትሔ ለማመቻቸት ኮሚቴ በማቋቋም በክትትሉ ግኝቶች እና ምክረ-ሐሳቦች ላይ ለመወያየት ለኢሰመኮ ጥሪ በቀረበው መሠረት ከተቋቋመው ኮሚቴ እንዲሁም ከክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ግንቦት 13 እና 14 ቀን 2016 ዓ.ም. ውይይት ተደርጓል። በዚህም ኢሰመኮ ያቀረባቸውን ምክረ ሐሳቦች ለመፈጸም ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን፤ ይህንንም የክልሉ ፕሬዝዳንት ጽሕፈት ቤት ለኢሰመኮ በደብዳቤ ገልጿል። በተጨማሪ ኢሰመኮ ካደረገው ክትትል በኋላ ተፈናቃዮችን በዘላቂነት ለማቋቋም ለ9 ቤተሰቦች የተሰጡ ቤቶችን ግንቦት 13 እና 14 ቀን 2016 ዓ.ም. ባከናወነው ቀጣይ ክትትል ተመልክቷል፤ ኮሚቴው ያዘጋጀውን ዕቅድ ለመፈጸም የሚያግዝ ዝርዝር ዕቅድ በኢሰመኮ ተዘጋጅቶ ለኮሚቴው ቀርቧል።

በሌላ በኩል ከክትትሉ በኋላ የተቋቋመው ኮሚቴ ያዘጋጀውን ዝርዝር ዕቅድ ተመልክቶ ግብአት የሰጠ ሲሆን በዚህም ዝርዝር ዕቅዱ ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ ሲውል የዘላቂ መፍትሔው አተገባበር ከሰብአዊ መብቶች አንጻር የተቃኘ እንዲሆን ያስችላል። ኢሰመኮ በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት ተፈናቃዮች በዘላቂነት እስኪቋቋሙ ተጠልለው ባሉበት ቦታ ለ3 ዓመታት ተቋርጦ የነበረውን የመብራት እና የውሃ አገልግሎት እንዲያገኙ የክልሉ የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ የምግብ ዋስትና አደጋ መከላከል ጽሕፈት ቤት ለክልሉ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን እንዲሁም ለኢትዮጵያ መብራት ኃይል አገልግሎት የትብብር ደብዳቤ ጽፏል።

የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦትን በተመለከተ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የምግብ እና ሌሎች ሰብአዊ ድጋፍ ፈላጊዎች ቁጥር በበጀት ዓመቱ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ (በመጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. በመንግሥት እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) እርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት በጣምራ በወጣ

መረጃ መሠረት 10.8 ሚልዮን ሰዎች የሰብአዊ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል) ሁኔታውን እጅግ አሳሳቢ አድርጎታል። በትጥቅ ግጭት ባሉ እና በትጥቅ ግጭት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች ያለው ሁኔታ አሳሳቢነት አፋጣኝ ትኩረት የሚሻ ነው። ለምሳሌ በአማራ ክልል አብዛኛዎቹ አካባቢዎች የተፈናቃዮች እና የተመላሾች መጠለያዎች የሚገኙባቸው አልያም ተፈናቃዮች ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩባቸው ናቸው። የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂ እና ወቅቱን የጠበቀ የምግብ ድጋፍ እየቀረበላቸው ባለመሆኑ ለረሀብ አደጋ እየተጋለጡ ናቸው። በተለይ ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ወቅቱን የጠበቀ የምግብ ድጋፍ የማይደረግላቸው በመሆኑ ለከፋ ችግር ተጋልጠዋል። በተለይም በባሕር ዳር ከተማ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቤት ተከራይተው ለመኖር ዐቅም የሌላቸው በመሆኑ ለመጠለያ ችግር ተጋልጠዋል።

በአማራ ክልል ውስጥ በክልሉ አደጋ ሥጋት ሥራ አምራር መረጃ መሠረት ወደ 993 ሺ የሚጠጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች አሉ። በአማራ ክልል ከተወሰኑ አካባቢዎች በስተቀር ሌሎቹ የተፈናቃዮች እና የተመላሾች መጠለያዎች የሚገኙባቸው አልያም ተፈናቃዮች ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩባቸው ናቸው። ተፈናቃዮች በቂ እና ወቅቱን የጠበቀ የምግብ ድጋፍ እየቀረበላቸው ባለመሆኑ ለረሀብ አደጋ እየተጋለጡ ናቸው። በተለይ ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮች ወቅቱን የጠበቀ የምግብ ድጋፍ የማይደረግላቸው በመሆኑ ለከፋ ችግር ተጋልጠዋል። በተለይም በባሕር ዳር ከተማ የሚገኙ ተፈናቃዮች ቤት ተከራይተው ለመኖር አቅም የሌላቸው በመሆኑ ለመጠለያ ችግር ተጋልጠዋል። በአብዛኛው በክልሉ ባለው የትጥቅ ግጭት እና ተያያዥ የጸጥታ ሥጋት እና የእንቅስቃሴ ውስንነት ምክንያት የምግብ ድጋፍ ለማቅረብ አዳጋች ሆኗል። ለአብነት በማእከላዊ ጎንደር ዞን፣ ቀበሮ ሜዳ በሚባለው መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ወቀቱን የጠበቀ ሰብአዊ ድጋፍ ባለተቆራረጠ ሁኔታ እያገኙ ባለመሆኑ፣ ሰዎች በምግብ እጥረት ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠው እንደሚገኙ፣ ተጽዕኖውም በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞች ላይ የበረታ እንደሆነና፣ ተፈናቃዮች በሕብረተሰቡ ከሚደረግ ምግብ እና የገንዘብ መዋጮ ድጋፍ ውጪ ሁኔታውን የሚቋቋሙበት ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው መረዳት ተችሏል። ከኦሮሚያ ክልል ውጭ ማለትም ከቀድሞው ደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተፈናቅለው በአማራ ክልል የተለያዩ ወረዳዎች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮች ምንም ዐይነት የዘላቂ መፍትሔ ሥራ ባልተሠራበት ሁኔታ አሁን ላይ አንጻራዊ ሰላም ያለ በመሆኑ ወደመጡበት ክልል መመለስ ይችላሉ በማለት የክልሉ መንግሥት የሰብአዊ ድጋፍ ያቋረጠ በመሆኑ ተፈናቃዮች ለከፋ ችግር ተዳርገዋል። በተመሳሳይ ከማይካድራ፣ ሁመራ፣ ዳንሻ እና ዲቪዥን በሰሜኑ ጦርነት ሳቢያ ተፈናቅለው በማእከላዊ ጎንደር ቀበሮ ሜዳ ተብሎ በሚታወቅ አካባቢ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ምንም ዐይነት የዘላቂ መፍትሔ ሥራ ባልተሠራበት ሁኔታ ወደመጡበት መመለስ ይችላሉ በማለት መንግሥት የሰብአዊ ድጋፍ በማቋረጡ ለችግር ተጋልጠዋል።

በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን ጃራ መጠለያ ካምፕ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከአፋር ክልል በሚመጡ ታጣቂዎች በተደጋጋሚ ጥቃት የሚደርስባቸው በመሆኑ የደኅንነት ሥጋት አለባቸው። ከኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዞኖች ማለትም ምዕራብ ወለጋ፣ ምሥራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉድሩ ወለጋ እና ምዕራብ ሸዋ ተፈናቅለው በአማራ ክልል የሚገኙ እና የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ያላቸውን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ለመመለስ በሁለቱ ክልሎች የሚመራ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፣ በክልሎቹ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኃላፊዎች እንደተገለጸው ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከ66,000 ተፈናቃዮች መካከል 1,500 መመለስ ተችሏል። ነገር ግን የመመለስ ሂደቱ ተፈናቃዮችን በበቂ ሁኔታ አላሳተፈም የሚል አቤቱታ እየቀረበበት መሆኑ፣ ተፈናቃዮች በሚመለሱባቸው አካባቢዎች አስተማማኝ የጸጥታ ሁኔታ ባለመኖሩ የደኅንነት እና ዳግም የመፈናቀል ሥጋት ያለባቸው መሆኑ እና ተፈናቃዮች/ተወካዮቻቸው ወደቀድሞ መኖሪያቸው እንዲመለሱ በመንግሥት አመራሮች ጫና

የሚደረግባቸው በመሆኑ ተገዶ የመመለስ ሁኔታ መኖሩ አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የትግራይ ታጣቂ ቡድኖች ወደ አላማጣ እና በኮረም ከተማ አስተዳደሮች፣ በራያ አላማጣ፣ ዛታ እና ኦፍላ ወረዳዎች መንቀሳቀሳቸውን ተከትሎ ከሚያዝያ 7 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በርካታ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች በደኅንነት ሥጋት ሳቢያ ከመኖሪያቸው እንደተፈናቀሉ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም ገጠራማ ቀበሌዎች በታጠቁ ኃይሎች የንብረት ዘረፋ እና ውድመት ተፈፅሟል፡፡ በሰሜን ወሎ እና በዋግ ኽምራ ዞኖች በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች የተጠለሉ ተፈናቃዮች አስቸኳይ የሰብአዊ ድጋፍ ለመስጠት በመንግሥት፣ በተራድዖ ደርጅቶች እና በአካባቢው ማኅበረሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ እስከ ሚያዝያ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. በሰሜን ወሎ አደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና 39,000 ተፈናቃዮች እንዲሁም በዋግ ኽምራ ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ከ8,000 በላይ ተፈናቃዮች ተመዝግቦ ነበር፡፡

በኦሮሚያ ክልል በክልሉ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር መረጃ መሠረት በአጠቃላይ ወደ 1.3 ሚሊዮን ሰዎች ከምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ፣ ቦረና፣ ሆሮጉዱሩ እና ምሥራቅ ሸዋ ዞኖች የተፈናቃሉ ሲሆን፣ ተጨማሪ 150,000 ሰዎች በተፈጥሯዊ አደጋዎች ምክንያት ተፈናቅለው 134,000ቹ ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል፡፡ በምዕራብ ወለጋ ዞን በድምሩ 136,181 ተፈናቃዮች ከዞኑ 17 ወረዳዎች እና ከአጎራባች የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አካባቢዎች ተፈናቅለው በዞኑ የተለያዩ የወረዳ ከተሞች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪም፣ በምሥራቅ ሸዋ ዞን 1,257 ቤተሰቦች ከቦራ እና ዱግዳ ወረዳዎች ተፈናቅለዋል፤ በጅማ ከተማ 3,000 እንዲሁም በቡኖ በደሌ ዞን ዴዴሣ ወረዳ 8,000 ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ሁኔታን በተመለከተ በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች የሚስተዋለው የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ተፈናቃዮች ከፍተኛ የመጠለያ፣ ምግብ እና ሕክምናን የመሳሰሉ መሠረታዊ አቅርቦቶችን እንደማያገኙ እና ለከፋ ችግር የተጋለጡ መሆኑ፤ በሁሉም የተፈናቃይ መጠለያ ላሉ ሕፃናት የትምህርት አገልግሎት አቅርቦት አለመኖሩ፤ የጤና አገልገሎት ከተወሰኑት መጠለያ ጣቢያዎች በስተቀር ለሕፃናትም ሆነ ለእናቶች በተገቢው ሁኔታ አለመቅረቡ፤ በየመጠለያ ጣቢያዎቹ ያሉ ሕፃናት በምግብ እጥረት ምክንያት ለሚከሰቱ በሽታዎች መጋለጣቸው፤ የደኅንነት ሁኔታን በተመለከተ በዋናነት በምዕራብ ወለጋ ዞን ቤጊ እና ቆንዳላ ወረዳዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች በአካባቢዎቹ ካለው ከፍተኛ የኢ-መደበኛ ታጣቂዎች እንቅስቃሴ የተነሳ የመንቀሳቀስ መብታቸው የተገደበ እና ለተደጋጋሚ ጥቃቶች እና መፈናቀሎች ሲጋለጡ የቆዩ መሆናቸው እና ተፈናቃዮች በተደጋጋሚ ለእገታ፣ አስገድዶ መሰወር፣ ግድያ እና አካል ማጉደልን ለመሳሰሉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መጋለጣቸው አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በትግራይ ክልል ከሰላም ስምምነቱ አስቀድሞ ከነበሩት ከ2 ሚሊዮን በላይ ተፈናቃዮች ወደ 1.5 ሚሊዮን የሚሆኑት አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አካባቢዎች የተመለሱ ቢሆንም በአካባቢያቸው በተከሰተው ድርቅ ምክንያት አብዛኞቹ ለዳግም መፈናቀል መዳረጋቸውን የትግራይ ክልል ሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ገልጸዋል፡፡ ኢሰመኮ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. እና በኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. በትግራይ ክልል ተፈናቃዮች እና ተመላሾች ባሉበት የተለያዩ አካባቢዎች ክትትሎች አድርጎ ይፋ ባደረገው ሪፖርት እንደተገለጸው በክልሉ አደጋ ሥጋት አመራር ቢሮ፣ በክልሉ የማኅበራዊ እና መልሶ ማቋቋም ጽ/ቤት፣ በመቐሌ ከተማ እና የደቡብ ትግራይ ዞን ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ደረጃ የተፈናቃዮች መረጃ በየጊዜው ወቅታዊ እንደማይደረግ እና መረጃው በተሰባጠረ ሁኔታ ተመዝግቦ ተደራሽ በሆነ መልኩ አለመደራጀቱን ኢሰመኮ መረዳት ችሏል፡፡ በተለይም ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በኋላ ተፈናቃዮች በሚገኙበት አካባቢዎች የሚስተዋል የጸጥታ እና ደኅንነት ሥጋት ባይኖርም የምግብ ድጋፍ አቅርቦት ለተከታታይ ሰባት ወራት ድረስ ተቋርጦ እንደነበረ፤ በወቅቱም ምንም ዓይነት የምግብ ድጋፍ አቅርቦት ሲደርግላቸው እንዳልነበረ፤ የትግራይ ክልል አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ቢሮ ለኢሰመኮ በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም. በሰጠው መረጃ መሠረት በወቅቱ በ5 ከተሞች የሚገኙ 53 የተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎች እንደ ናሙና ተወስደው በተደረገ

ጥናት፣ በዚያን ወቅት በሌሎች ምክንያቶች የሞቱትን ሰዎች ሳይጨምር ቢያንስ 1,329 ተፈናቃዮች በምግብ እጥረት ብቻ መሞታቸውን ጥናቱ እንዳሳየ ዘግቦ የነበረ ሲሆን፤ ኢሰመኮ የዚህን ጥናት ግኝት በራሱ ምርመራ ባያረጋግጥም በወቅቱ ጉዳዩ በከፍተኛ ሁኔታ አሳሳቢ እንደነበረ ያሳያል። በተጨማሪም 970 የሚሆኑ ከ1 እስከ 5 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃይ ሕፃናት ለከፍተኛ የምግብ እጥረት (Malnutrition) መጋለጣቸው እንደለዩ እና በተወሰኑ የጤና ተቋማት እና የረድኤት ድርጅቶች በኩል ተጨማሪ አልሚ ምግቦችን እየወሰዱ እንደነበረ የኢሰመኮ ክትትል አሳይቷል። ኢሰመኮ በኅዳር ወር ባደረገው ቀጣይ ክትትል ከመስከረም ወር ጀምሮ የምግብ ድጋፉ ከፌዴራል አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን መቅረብ የጀመረ መሆኑን ማረጋገጥ ችሏል። ነገር ግን አቅርቦቱ በቂ እንዳልሆነና ለሁሉም ተፈናቃዮች እንደማይዳረስ ኢሰመኮ ያነጋገራቸው ተፈናቃዮች እና የመንግሥት ኃላፊዎች ገልጸዋል። ተፈናቃዮች ከፍተኛ የሆነ የመጠለያ ችግር እንዳለባቸው፣ አብዛኞቹ በተጣበበ ሁኔታ በትምህርት ቤት ውስጥ ተጠልለው የነበረ ሲሆን ቀሪዎቹ በጤና ጣቢያ እና በግለሰብ የብሎኬት ማምረቻ መጋዘን ይገኙ ነበር። ኢሰመኮ ሁለተኛውን ዙር ክትትል ባከናወናበት ወቅት ከክልሉ አደጋና ሥጋት ሥራ አመራር ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት በትግራይ ክልል 110 ትምህርት ቤቶች የተፈናቃይ መጠለያዎች ሆነው ይገኙ ነበር፤ ይህም የመማር ማስተማር ሥራውን አስተጓጉሏል። እንዲሁም በተወሰነ መልኩ በተለያዩ የተራድኦ ድርጅቶች አማካኝነት የወሊድ ክትትል፣ የሕፃናት ክትባት፣ የሥነ-ተዋልዶ ጤና እና ጥቃት ለደረሰባቸው የሥነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ቢሆንም ኢሰመኮ ክትትሉን በሚያከናውንበት ወቅት ትምህርት ሊጀምር ነው በሚል ድርጅቶቹ አገልግሎቱን የሚሰጡበትን የመማሪያ ክፍሎች እንዲለቁ ተደርጎ እንደነበረ፤ በዚህም ምክንያት በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ አገልግሎቱ የሚሰጥ የነበረ ቢሆንም ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች አገልግሎቱ በአደባባይ የሚሰጥ በመሆኑ ለተጎጂዎች ምቹ በሆነ ሁኔታ አገልግሎት ለማግኘት ተቸግረዋል። ኢሰመኮ ያነጋገራቸው የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎች እንዳስረዱት የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተፈረመ በኋላ በክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር ስር በሚገኙ አካባቢዎች ወደ 1.5 ሚሊዮን የሚሆኑ ተፈናቃዮችን የመመለስ ሥራ የተከናወነ ቢሆንም የበጀት ውስንነት በመኖሩ ተፈናቃዮች በሚመለሱበት የቀድሞ መኖሪያ አካባቢዎች መደበኛ ኑሮን ለማስጀመር የሚያስችሉ በጦርነቱ የወደሙ መሠረተ-ልማቶች እና አገልግሎቶች መልሶ ሳይገነቡ እንዲሁም የማቋቋምያ ድጋፍ ሳይደረግላቸው እንዲመለሱ የተደረጉ መሆኑን ገልጸዋል።

በአፋር ክልል በአሁኑ ወቅት አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አካባቢዎች በተወሰነ ደረጃ የሰብአዊ ድጋፍ በመንግሥት በኩል የሚቀርብ ቢሆንም የሚቀርበው የሰብአዊ ድጋፍም ሆነ የሌሎች አገልግሎቶች አቅርቦት የተሻለ አይደለም፣ ድጋፉ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተፈናቃዮችና ተመላሾች፣ በተለይም የሕፃናትን፣ ነብሰጡርንና የሚያጠቡ እናቶችን ልዩ ፍላጎት ያገናዘበ ባለመሆኑ ትኩረት ይሻል። ለምሳሌ ከተለያዩ ምንጮች እስከ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ ያለው መረጃ በአፋር ክልል በበራሃሌ ወረዳ ወደ 3500 የሚጠጉ ተፈናቃዮች እንደሚገኙ ያሳያል። ለተፈናቃዮቹ የሚደረገው የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ተመጣጣኝ ያልሆነ እና የተቆራረጠ ወይም ወቅቱን ያልጠበቀ መሆኑ፣ በአካባቢው በተለይም በበራሃሌ ወረዳ አሳዳ እና ኩስርቱ በሚባሉ አካባቢዎች አሁንም የታጠቁ ኃይሎች በመኖራቸው ተፈናቃዮች የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው መሆኑ እንዲሁም በሰሜኑ ጦርነት ተፈናቃዮች ቤትና ንብረቶቻቸው የወደመባቸው ቢሆንም መቋቋሚያ እና ዘላቂ መፍትሔ ያልተሰጣቸው በመሆኑ ወደ ቀያቸው ለመመለስ አዳጋች እንደሆነባቸው ማወቅ ተችሏል።

በማእከላዊ ኢትዮጵያ በመስቃን እና ማረቆ ግጭት ለተደጋጋሚ መፈናቀል የተዳረጉ ሰዎች ያሉ ቢሆንም ተገቢው ምዝገባ ባለመከናወኑ ቁጥራቸው በትክክል የማይታወቅ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ከካፋ ዞን፣ ዴቻ ወረዳ የተፈናቀሉ እና ቁጥራቸው በትክክል ምዝገባ ያልተደረገ ተፈናቃዮች በሰሜን ጉራጌ ዞን ቡታጅራ ከተማ እና በምሥራቅ መስቃን ወረዳ ኢንሴኖ ከተማ፣ እንዲሁም በካምባታ ጠምባሮ ዞን አንገጫ እና ዶዮ ገና ወረዳ ይገኛሉ። ተፈናቃዮች ምንም

ዐይነት የሰብአዊ ድጋፍ የማያገኙ ሲሆን፣ በርካቶቹ ለዳግም መፈናቀል የተዳረጉ እና የመፈናቀል መንስኤ የሆኑት ግጭቶችን ተገቢው ምርመራ ተካሂዶ የሕግ ተጠያቂነት ባለመረጋገጡ እንዲሁም ተፈናቃዮች የተጠለሉበት አካባቢ ከግጭቱ ስፍራ የራቀ ባለመሆኑ የደኅንነት ሥጋት አለባቸው። ተፈናቃዮቹ ሸሽተው በወጡባቸው አካባቢዎች ያሉ ይዞታዎች ለሌሎች ግለሰቦች መተላለፋቸውን የሚያመላክቱ አቤቱታዎች መኖራቸውም አሳሳቢ እና ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

በሲዳማ ክልል በአብዛኛው ከጉራ ፈርዳ ወርዳ የተፈናቀሉ 884 ቤተሰቦች ወይም 5,872 የሚገመቱ ሰዎች ያሉ ሲሆን፣ በክልሉ 14 ወረዳዎች ተሰባጥረው ይኖራሉ። ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ለተፈናቃዮቹ የሚደረግ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት የለም።

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ በ2012 ዓ.ም. በክረምት ወቅት በዘነበው ኃይለኛ ዝናብ ወንዙ ከሌላው ጊዜ በላይ በመሙላቱ፣ የግልገል ጊቤ 3 የኃይል ማመንጫ ግድብም በመሙላቱ ምክንያት ግድቡን ለማስተንፈስ የተለቀቀው ውሃ የኦሞ ወንዝ በከፍተኛ መጠን እንዲሞላ እና ወንዙ ከዚህ ቀደም በጎርፍ ከሚያጥለቀልቃቸው ቦታዎች በተጨማሪ በሌሎች ቦታዎች ላይ የጎርፍ አደጋ እንዲከሰት አስተዋጽዖ ማድረጉ፤ እንዲሁም የቱርካና ሐይቅ በኅዳር ወር 2013 ዓ.ም. ከመጠን በላይ መሙላቱና ወደ ሐይቁ የሚገባው ውሃ ወደ ኋላ መመለስ መጀመሩ (back flooding) በአካባቢው ያደረሰው ጉዳት 79,828 ሰዎችን (ሴት 42,758 እና ወንድ 37,070) አፈናቅሏል። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በወቅቱ የጥንቃቄ እርምጃዎች ወስጃለሁ ቢልም መፈናቀሉን ለመከላከልም ሆነ ተፈናቃዮቹን በቋሚነት ለማቋቋም አልተቻለም። በዚህም በዳሰነች ወረዳ ከ2012 ዓ.ም. እስከ 2016 ዓ.ም. ድረስ በኦሞ ወንዝ ሙላት ምክንያት በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በሰብል፣ በግል ንብረቶች እና በመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ የተለያዩ ጉዳቶች ደርሰዋል። በተጨማሪ ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ ቤተ-እምነቶች፣ የጤና ኬላዎችና ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በውሃ ተውጠዋል። በወረዳው ካሉ 40 ቀበሌዎች 28ቱ (ከጠቅላላው የወረዳው የቆዳ ስፋት 65%) በውሃ ተውጠው ይገኛሉ። ይህም በአካባቢው የሚኖሩ አርብቶ አደሮችን ለከፍተኛ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዳርጓል። ከጊዜ ወደ ጊዜ በአንዳንድ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ መሻሻሎች ያሉ እና ተፈናቃዮችን በቋሚነት በማቋቋም ረገድ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት በኩል አበረታች ጥረቶች ቢጀመሩም የተፈናቃዮች የመመዝገብ እና ሰነድ የማግኘት መብት፣ ደኅንነቱ እና ጸጥታው በተረጋገጠ ሁኔታ የመኖር መብት፣ በተቻለ መጠንና ፍጥነት የምግብ፣ የውሃ፣ የመጠለያ፣ የሕክምና እና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች፣ የንጽሕና፣ የትምህርት እና ሌሎች አስፈላጊ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያካተተ በቂ የሰብአዊ ድጋፍ የማግኘት መብት፣ እንዲሁም ልዩ ጥበቃ እና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች አያያዝን በተመለከተ ክፍተቶች ታይቷል። የክትትሉ ግኝቶች እና ምክረ ሐሳቦቹን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለማሳወቅ ጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም. በወላይታ ሶዶ ከተማ የምክክር መድረክ ተካሂዷል። በተጨማሪም የጊቤ 3ኛ ኃይል ማመንጫ ግድብን ለማስተንፈስ የተለቀቀው ውሃ የኦሞ ወንዝ እንዲሞላና ሰዎች እንዲፈናቀሉ ተጨማሪ ምክንያት መሆኑ በክትትሉ በተለየው መሠረት ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር 2 የሁለትዮሽ ምክክር ተደርጓል፤ በቀጣይም የውትወታ ሥራዎችን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን፤ ይህንንም ተከትሎ ኢሰመኮ ሚያዚያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም. በወላይታ ሶዶ ከተማ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ጋር ውይይት አድርጓል። በተለያዩ ጊዜያት ኢሰመኮ ባደረገው የሁለትዮሽ እና የጋራ የምክክር መድረኮች ስለተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ በማስያዝ ጉዳዩን የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች በባለቤትነት እንዲይዙት አስችሏል። በቀጣይ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል መሠራት ስላለባቸው ተግባራት ለማሳወቅ፤ በክልሉ አደጋ እና ሥጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት የዕቅድ ማሻሻያ ተደርጎ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ለማቀረብና ውይይት ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ኢሰመኮ ባደረገው ክትትል ተገንዝቧል።

በ2014 ዓ.ም. ከአሪ ዞን የመዋቅር ጥያቄ ጋር በተያያዘ በተከሰተ ግጨት የተፈናቀሉ እና በአብዛኛው በደቡብ አሪ ወረዳ እና በጂንካ ከተማ ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው ለሚኖሩ ተፈናቃዮች የሚደረገው የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ወጥ እና ተመጣጣኝ ያልሆነ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተለይም ከግጦሽ መሬት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከአጎራባች ወረዳዎች እና ከኬንያ አርብቶ አደሮች ጋር በተለያየ ወቅት የሚከሰቱ ውጥረቶች እና ግጭቶች አሉ። በተለይም ከአሪ ዞን ለተፈናቀሉ ሰዎች ግጭት ተከስቶ በነበረባቸው አካባቢዎች የባሕላዊ እርቅ ሥነ ሥርዓቶች በመካሄዳቸው እና አንጻራዊ ሰላም የሰፈነ በመሆኑ ለተፈናቃዮቹ መልሶ ማቋቋሚያ በቀያቸው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታዎች ተጀምረው የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት መቋረጣቸው ለተፈናቃዮቹ የዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግ ሥራውን በእጅጉ ያጓተተው ነው።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል 5 ዞኖች ሥር ባሉ 9 ወረዳዎች በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በመደበኛ መጠለያ እና ከመጠለያ ውጭ የተጠለሉ 1162 ተፈናቃይ ቤተሰቦች በድምሩ 5805 ተፈናቃዮች በቂ ሰብአዊ አቅርቦት አያገኙም። በክልሉ ከፋ ዞን ዴቻ ወረዳ ሻሎ ቀበሌ በ2011 ዓ.ም. በግጭት ምክንያት ከተፈናቀሉ 267 አርሶ አደር ቤተሰቦች መካከል 63 ቤተሰቦች የመሬት ይዞታቸው እና ንብረታቸው በወጣቶች፣ በባለሀብቶች እንዲሁም በክልሉ መንግሥት በመያዙ 63 ተፈናቃይ ቤተሰቦች የካቲት ወር 2013 ዓ.ም. ወደ ቀያቸው ሲመለሱ መግባት እንደተከለከሉ፣ ታስረው የነበሩ ሰዎችም መኖራቸው እና በመፈናቀል ሁኔታም ሆነው የሚቀርብላቸው ሰብአዊ ድጋፍ ባለመኖሩ ለችግር እንደተጋለጡ ለማወቅ ተችሏል። ኢሰመኮ በዚህ ጉዳይ ላይ ክትትል እና ውትወታ በማድረግ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ እና ወደ ቀድሞ የመኖሪያ ስፍራቸው እንዲመለሱ የሚቻልበትን ሁኔታ ከክልሉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ከስምምነት ላይ ደርሷል።

በሶማሊ ክልል የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተመለከተ በተለይም የዘላቂ መፍትሔ በማፈላለግ ረገድ የተከናወኑ አበረታች ተግባራት አሉ። በክልሉ የሚኖሩ ተፈናቃዮች በ11 ዞኖች፣ 93 ወረዳዎች እና 6 የአስተዳደር ምክር ቤቶች ተሰባጥረው የሚገኙ ሲሆን፣ በግጭት፣ በድርቅ እና በጎርፍ ምክንያት የተፈናቀሉ ሰዎች ይገኙበታል። በክልሉ በሚገኙ 607 ተደራሽ ቦታዎች 1,263,155 ተፈናቃዮች (639,469 ወንድ እና 623,686 ሴቶች) አሉ።

በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በአጠቃላይ በ40 ወረዳዎች በተለይም በሸበሌ፣ ሊባን እና አፍዴር ዞኖች በጣለው ከባድ ዝናብ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። በጉዳቱም በቁጥር 66,810 በላይ የሚሆኑ በርካታ ነዋሪዎችን ከቤት ንብረታቸው እንዲሁም ከቀያቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ውስጥ ተጠልለዋል፤ በርካታ እንስሳት አልቀዋል። በርካታ ሰዎች በደረሰው አደጋ ሳቢያ ለምግብ፣ ለውሃ እና ለመድኃኒት አጥረት ተዳርገዋል። የመንግሥት ተቋማት እና ሰብአዊ ድጋፍ ሰጪዎች ለደረሰው አደጋ በወቅቱ ከሞላ ጎደል ድጋፍ ቢያደርጉም የሶማሊ ክልል የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ባወጣው ሪፖርት መሠረት ከ66,810 ተፈናቃዮች ውስጥ 46,109 ብቻ ናቸው ወደነበሩበት ስፍራ መመለስ የቻሉት። ቀሪው 20,701 የሚሆኑት ተፈናቃዮች ወደነበሩበት ቀየ መመለስ ባለመቻላቸው ምክንያት ኅብረተሰቡ ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት አሁንም ቀጥሏል። ቆሎጂ ተብሎ በሚጠራው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ አካባቢ ከቀረጥና ፍተሻ ኬላ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ በሶማሊ እና በኦሮሚያ ክልል የጸጥታ ኃይሎች መካከል ከመስከረም 7 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ለጥቂት ቀናት ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ምክንያት የ5 ወር ሕፃን ጨምሮ 6 በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ የሚኖሩ ተፈናቃዮች የተገደሉ እና በ17 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን በመግለጽ፣ ኢሰመኮ የክልሉ መንግሥት ለተፈናቃዮች በቂ ጥበቃ ማድረግ እንዳለበት እና ተጎጂዎች ፍትሕ ማግኘት እንዳለባቸው ማሳሰቡ ይታወሳል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና በሌሎች አካባቢዎች ተፈጥሮ በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት በክልሉ ከ469,000 በላይ ተፈናቃዮች የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በክልሉ በመጣው አንጻራዊ ሰላም አብዛኛው ተፈናቃይ ወደቀድሞ ቄያቸው ሊመለሱ ችለዋል። በመጠለያ ጣቢያ ተፈናቃዮች ከሚኖሩባቸው የክልሉ አካባቢዎች መካከል በአሶሳ ዞን ባምባሲ ከተማ ኦልድ ካምፕ እና ወርልድ ቪዠን፤ በመተከል ዞን ማንቡክ፤ ገነተ ማርያምና ድባጤ 01 ቀበሌ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ይገኙበታል። በዚህም በጠቅላላው በመጠለያ ጣቢያዎቹ የሚገኙት ተፈናቃዮች 35,000 ያህል ሲሆን በባምባሲ ከተማ ባሉ 2 መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙት ከኦሮሚያ ክልል ተፈናቅለው በ2013 ዓ.ም. የመጡ ናቸው።

ኢሰመኮ በተለያዩ ጊዜያት ባደረጋቸው ክትትሎች የክልሉ መንግሥት በአሁኑ ወቅት ተፈናቃይ የለኝም በሚል አቋም መያዙን ተከትሎ በባምባሲ ከተማ ከኦሮሚያ ክልል ተፈናቅለው ከመጡት ተፈናቃዮች ውጪ በሌሎች መጠለያ ጣቢያዎች ለሚገኙት ተፈናቃዮች የሰብአዊ ድጋፍ ከ 2 ዓመታት በላይ የተቋረጠ ሲሆን፤ የመጠለያ፣ ሕክምናና የምግብ አቅርቦት ችግር መኖሩን ተከትሎ ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተፈናቃዮች ለከፋ ችግር ተዳርገዋል።

በመተከል ዞን ዳንጉር ወረዳ ማንቡክ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ባልተሠሩበት አግባብ በወረዳው መንግሥት በኩል ተገደው ከመጠለያ ጣቢያው እንዲወጡ እየተደረገ የሚገኝ መሆኑና ተፈናቃዮችን ለተጨማሪ ችግር የሚያጋልጥ መሆኑ ታይቷል። የተፈናቃዮች የቀድሞ አካባቢዎች ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም እንዲመለስ እንዲሁም እንደ ትምህርት፣ የሕክምና ተቋማትና መጠለያ የመሳሰሉ አስፈላጊ ሁኔታዎችና ሰብአዊ እርዳታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ ይፈጸሙ የነበሩ ጥቃቶች ጋብ በማለታቸው ብቻ ተፈናቃዮች ተገደው ወደ ነባር ቄያቸው እንዲመለሱ መደረጉ፤ እንዲሁም መጠለያ ውስጥ ያሉትም ቢሆን እንደ ትምህርት፣ ነጻ የሕክምና አገልግሎት፣ በቂ ምግብ፣ መጠለያና አልባሳት የመሳሰሉ መሠረታዊ ሁኔታዎች ባልተሟላበት ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ ኢሰመኮ የለያቸው አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው።

በተጨማሪም የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂ ኃይል በአሶሳ ዞን ብልድግሉ ወረዳ ሥር በሚገኙ የቤልሚሊ፣ አልከሻፊ እና ቤላደሩ ቀበሌ የሚኖሩ ሲቪል ሰዎች ላይ ኅዳር 19 ቀን 2016 ዓ.ም. በሰነዘረው ጥቃት ከሞት፤ አካል ጉዳትና ንብረት ውድመት በተጨማሪ ከጥቃቱ የተረፉ የ3ቱ ቀበሌ ነዋሪዎች ጥቃቱን በመሸሽ ወደ ወረዳው አጎራባች ቀበሌዎችና በአቅራቢያ ወደ ሚገኘው የኦሮሚያ ክልል መነሲቡ ወረዳ አካባቢ ተፈናቅለው የነበሩ መሆኑን ኢሰመኮ ለማወቅ ችሏል። በ2013 ዓ.ም. ከምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ማለትም ጃረሶ ባቦ ጋምበል፣ መንዲ ዙርያ ቀበሌ፣ ነጆ ዙርያ ቀበሌ፣ ቆንዳላ፣ አሹንፋ፣ አርጆጉዳቱ፣ አይራ ጉልሶ አካባቢ ተፈናቅለው አሶሳ ዞን ባምባሲ ወረዳ በጊዜያዊ ማረፍያ የሰፈሩት ቁጥራችው ከ9,951 በላይ የሚሆኑ ተፈናቃዮች የመጡበት ቦታ ጸጥታ ሁኔታ ወደነበረበት ባለመመለሱ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ ይገኛሉ።

## ስደተኞች እና ጥገኝነት ፈላጊዎች

የተ.መ.ድ. የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) የግንቦት ወር 2016 ዓ.ም. መረጃ እንደሚያሳየው 1,051,918 የሚጠጉ እና በአብዛኛው ከደቡብ ሱዳን፣ ከሶማሊያ እና ከኤርትራ የተሰደዱ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በተለይም በጋምቤላ፣ በሶማሊ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ክልሎች የሚገኙ ሲሆን፣ የተወሰኑትም በአዲስ አበባ ከተማ ይኖራሉ። ከባለፈው ዓመት ጀምሮ በሱዳን የተቀሰቀሰውን ግጭት ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ በተለይ በመተማ አማራ

ክልል እና በኩርሙክ ጋምቤላ ክልል የሚገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል፡፡

ኢትዮጵያ የስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶችን በተመለከተ በዓለም እና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ያሉ የሕግ ማዕቀፎችን ያጸደቀች በመሆኗ፤ የስደተኞችን መብቶች በተሻለ ሁኔታ ለመጠበቅ እና ለስደተኞች ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማፈላለግ የሚያስችል አጠቃላይ የሕግ ማዕቀፍ መኖሩ ለሰብአዊ መብቶች ሁኔታው ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው፡፡ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ጥበቃ እና ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም ለማስተባበር የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ተቋም መኖሩ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር እንዲሁም የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ሀገር በቀል የተራድዖ ድርጅቶች፣ መንግሥት ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚያደርገው ጥበቃ እና ድጋፍ የተሟላ እንዲሆን ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑ በመልካም እመርታነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥም ቢሆን በዘንድሮ በጀት ዓመት በተለይም ከሱዳን የፈለሱ ስደተኞችን ተቀብላ ማስተናገድ መቻሏም ለጉዳዩ የምትሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ነው፡፡

በጋምቤላ ክልል 394302 የሚሆኑ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ሲኖሩ ኢሰመኮ በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. በጋምቤላ ክልል በተመረጡ የስደተኛ መጠለያ ካምፖች ባደረገው ክትትል የምግብ እና ምግብ ነክ ድጋፎች በመቋረጣቸው ስደተኞች ለሞት እየተዳረጉ መሆናቸውን እና አሉታዊ ውጤቶች ያሏቸው የመቋቋሚያ ዘዴዎችን (Negative coping mechanism) ለመጠቀም የሚገደዱ መሆኑ ከአሳሳቢ ጉዳዮች መካከል ይጠቀሳል፡፡ ተቋርጠው የነበሩ የምግብ እና ምግብ ነክ ድጋፎች ዳግም ተጀምሮ በባለፉት 2 ወራት መቀጠሉ ጥሩ እመርታ ቢሆንም በአንዳንድ የስደተኛ ካምፖች ለምሳሌ በዲማ ወረዳ የሚገኘው የኦኩጉ የስደተኞች ካምፕ አሁንም ከፍተኛ የምግብ እጥረት መኖሩ፤ እና በጋምቤላ ክልል የሚገኙት ስደተኞች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር በተደጋጋሚ ጊዜ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ውስጥ መግባታቸው፤ በዚህም የተነሳ ለተለያዩ ጥቃቶች ተጋላጭ እየሆኑ መምጣታቸውና ደኅንነታቸው አደጋ ላይ መውደቁ ተጨማሪ አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በስደተኞች እና ተቀባይ ማኅበረሰብ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች እና ግጭቶችን ለመፍታት የክልሉ መንግሥት ከስደተኞች እና ከስደተኞች ተመላሽ አገልግሎት እና ሌሎች አጋር አካላት ጋር በትብብር እየሠራ መሆኑ መልካም ጅማሮ ነው፡፡

ሶማሊ ክልል 346,007 ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ይዛ በሁለተኛነት ትመራለች፡፡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአጠቃላይ 104,094 ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የተ.መ.ድ. የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ባወጣው መረጃ መሠረት 22,305ቱ በጦርነት ምክንያት ከሱዳን ሸሽተው የመጡ እና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚገኙ ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ 78,293 የተመዘገቡ እና በከተማ ለመኖር ፍቃድ ያገኙ ስደተኞች ይገኛሉ፡፡ በአዲስ አበባ የሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች፤ በተለይ ኤርትራዊያን ላይ የሚደረገውን የዘፈቀደ እስር አስመልክቶ በቀረቡ በርካታ አቤቱታዎች መሠረት ኢሰመኮ ለተከታታይ ጊዜ ክትትሎች እና ምርመራዎች ሲያካሂድ ቆይቷል፡፡ በዚህ ረገድ ለኮሚሽኑ የቀረቡ አቤቱታዎችን መሠረት በማድረግ ከኅዳር መጀመሪያ እስከ ታኅሣሥ 26 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ ኢሰመኮ ከስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ጋር በመተባበር ክትትል በማድረግና መረጃ በማሰባሰብ ቀጣይነት ያለው የውትወታ ሥራዎች በማከናወኑ ከሕግ ውጭ የተያዙ ቢያንስ 112 ኤርትራውያን ስደተኞችን በብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕጋጋት መሠረት እንዲለቀቁ ለማድረግ ተችሏል፡፡

በአማራ ክልል የሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ቁጥራቸው 43,178 ሲሆን 22,501 ኤርትራዊያን ስደተኞች በዓለምዋጭ መጠለያ ጣቢያዎች ይገኛሉ። በተጨማሪም በክልሉ ኩመር እና አውላላ የስደተኞች መጠለያዎች ውስጥ የሱዳን እና የኤርትራ ስደተኞች ይገኛሉ። በኩመር መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ስደተኞች በቂና ወቅቱን የጠበቀ የምግብ ድጋፈ፤ የጤና እና የትምህርት አገልግሎት እያገኙ አለመሆ፤ በሱዳን በተከሰተው ጦርነት ሳቢያ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው በክልሉ የተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ተመላሽ ፍልሰተኞች ተገቢውን የሰብአዊ ድጋፍ እያገኙ አለመሆ፤ በኩመር የስደተኞች መጠለያ ካምፕ በቂ የሆነ የጥበቃ አገልግሎት የሌለ በመሆኑ ስደተኞች የደኅንነት ሥጋት እንዳለባቸው፤ ይህ የደኅንነት ሥጋት እየተባባሰ በመምጣቱ በሚያዚያ ወር 2016 ከሱዳን የመጡ ስደተኞች መጠለያውን ለቀው ለመውጣት ተገደዋል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ104,000 በላይ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ይገኛሉ። በክልሉ ወንባ/ባምባሲ፤ ሸርቆሌ እና ጾሬ መጠለያ ጣቢያዎች በጦርነት ምክኒያት ከደቡብ ሱዳን እና ከሰሜን ሱዳን ሸሽተው የመጡ ናቸው። በሱዳን በተቀሰቀሰው ግጭት ከ16,000 በላይ የሱዳን ዜጎች በኩርሙክ የስደተኞች መቀበያ በኩል ወደ ክልሉ በመግባት ጥገኝነት በመጠየቅ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል። ስደተኞች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር በተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ እና በስርቆት ምክንያት አልፎ አልፎ ግጭት እንደሚከሰት፤ በመጠለያ ጣብያዎቹ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ጥቅም ላይ እንደሚውል፣ ለስደተኞች የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንደማይሰጥ እና ስደተኞች ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን እየተነፈጉ ነው። ለስደተኞች የሚቀርበው የምግብ ድጋፍ ለአምስት ወራት ተቋርጦ የነበረ መሆኑን፤ በዚህም ምክንያት ስደተኞች የምግብ እጥረትን ጨምሮ ለከፍተኛ የጤና እና ማኅበራዊ ችግሮች መጋለጣቸውን፣ የተማሪዎች የምገባ አገልግሎት መቋረጡን፣ ተማሪዎች ያለምግብ መማር ስለማይችሉ በርካታ ተማሪዎች ትምህርት ማቋረጣቸውን፣ ስርቆት መበራከቱን፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ሰብል ትሰርቃላችሁ በሚል ለጥቃት እና ለግጭት መዳረጋቸውን፣ ሕጻን ስደተኞች በጉልበት ሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ፣ ሴቶች የእለት ጉርሳቸውን ለመፈለግ ልጆቻቸውን ጥለው ለቀናት ሥራ ፍለጋ ከመጠለያ ወጥተው እንደሚሄዱ ለፆታ ጥቃትም እንደሚጋለጡ፤ ስደተኞች የሚኖሩበት መጠለያ እድሳት ያልተደረገለት መሆኑን እና ከአንድ አመት በፊት በቶንጎ የስደተኞች መጠለያ የደረሰውን ጥቃት ሸሽተው ወደ ፆሬ የስደተኞች መጠለያ የገቡ ስደተኞች መጠለያ እንዳልተሰጣቸውና በሸራ ውስጥ እንደሚኖሩ፤ ለስደተኞች የሚሰጠው የትምህርት አገልግሎት ጥራት እንደሌለው እና የመማሪያ ቁሳቁስ እጥረት ስለመኖሩ፤ ሴቶች፣ ሕጻናት፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች ትኩረት ያላገኙ መሆኑ እና የሚደረግላቸው ድጋፍም እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ለዚህም እንደ ምክንያት የሚቀርበው የበጀት እጥረት መኖሩን እና ወደ ክልሉ የሚያስገቡ ዋና ዋና መንገዶች በጸጥታ ችግር ምክንያት የተዘጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

## ፍልሰተኞች

ኢሰመኮ በ2016 በጀት ዓመት ፍልሰተኞችን በሚመለከት የለያቸው ዋና ዋና አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ዘርፈ ብዙ ናቸው። ኢትዮጵያ የሁለትዮሽ የሥራ ስምምነት ወደ ተፈራረመችባቸው የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት በመደበኛ/ሕጋዊ መንገድ ለመሄድ ፍልሰተኞች በብዛት አገልግሎት የሚያገኙት አዲስ አበባ ብቻ በሚገኙ የግል ሥራ እና አገናኝ ኤጀንሲዎች በኩል ነው። እነዚህም ኤጀንሲዎች በአብዛኛው በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ መገኘታቸው ከተደራሽነት አንጻር ክፍተት መፍጠሩንና ፍልሰተኞች በሕገውጥ ደላላዎች እንዲመዘበሩ ማድረጉን ማወቅ ተችሏል። በመደበኛ መንገድ ለውጭ ሀገር ሥራ የሚሰማሩ ፍልሰተኞች ከ98% በላይ ሴቶች ሲሆኑ፣ ከሚሄዱት 97% በላይ የሚሆኑት ሴቶች በቤት ሠራተኝነት ይሰማራሉ። ለወንዶች ተመሳሳይ የሆነ የሥራ ዕድል በውጭ ሀገር ባለመፈጠሩ

ወንድ ሥራ ፈላጊ ኢትዮጵያውያን መደበኛ ባልሆነ ፍልሰት በብዛት እንደሚሳተፉና ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተጋላጭ እንደሚሆኑ ለመረዳት ተችሏል።

ፍልሰተኞች ከሀገር ከመውጣታቸው በፊት በሚያሰማሯቸው የግል ሥራ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች እንዲሁም በደላላዎች ለተለያዩ ምዝበራዎች የሚጋለጡ መሆናቸው፤ በውጭ ሀገር ለሥራ ከተሰማሩ በኋላም በአሠሪዎቻቸው ለጉልበት ብዝበዛ፣ ለአካላዊና ጾታዊ ጥቃቶች፣ እንዲሁም ለሥራና ፍትሕ የማግኘት መብቶች ጥሰት መዳረጋቸው ፍልሰተኞችን በሚመለከት ከተለዩ አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች መካከል ናቸው። የፍልሰተኛ ሠራተኞችን መብት ለማስከበር የሚሠራ የሌበር አታሼ በመዳረሻ ሀገራት አለመሰማራቱ፣ በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 1226/2020 መሠረት የአዋጁን ተፈጻሚነት ለመከታተል እና ባለድርሻ አካላትን ለማስተባበር ኃላፊነት የተሰጠው የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ቦርድ አለመቋቋሙ ለችግሩ እልባት አለማግኘት አስተዋጽዖ አድርጓል።

ድሬዳዋ ከተማን የሚያካትተው የምሥራቁ የፍልሰት መስመር ዋና የመደበኛ ፍልሰት መስመር ሆኖ የቀጠለ ሲሆን፣ በሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች እና አሳላፊዎች ልዩ ልዩ ወንጀሎች ይፈጸማሉ። ለምሳሌ ዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት በግንቦት ወር 2016 ዓ.ም. ባወጣው መረጃ ከሐምሌ 2015 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ 144,912 ሰዎች (72% ወንዶች) በጂቡቲ በኩል ወደ የመን እና ሳውዲ አረቢያ መደበኛ ባልሆነ መንገድ እንደፈለሱ የዘገበ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 91% ኢትዮጵያኖች ናቸው። ሆኖም በአጥፊዎች ላይ የሚወሰደው የሕግ እርምጃ እና አፈጻጸም አነስተኛ ነው። በሚፈጸሙት ወንጀሎች ውስብስብነት፣ በበጀት እጥረት እና በትኩረት ማነስ ሳቢያ በጉዳዩ ላይ ውጤታማ የምርመራ መዝገቦች አለመኖራቸው፤ የወንጀል ምርመራና ክስን በተመለከተ ከመተላለፊያና መዳረሻ ሀገራት ጋር የትብብር ማዕቀፍ ቢፈረምም በአግባቡ እንደማይፈጸም፤ እንዲሁም ምልመላን፣ መተላለፊያን እና መዳረሻን ያካተተ ሁሉን አቀፍ የምርመራ ሥርዓት አለመኖሩ በመስመሩ የሚከሰቱ የተደራጁ ወንጀሎችን ለመከላከል ክፍተት ፈጥሯል። የዚህ መደበኛ ያልሆነ የፍልሰት መንገድ ዋና መዳረሻ ሳውዲ አረቢያ ስትሆን በተለያየ ጊዜ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያኖችን በግዳጅ ስትመልስ የቆየች ሲሆን ከጥቅምት እስከ ሰኔ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ 70,000 ኢትዮጵያኖች ከሳውዲ አረቢያ ተመልሰዋል። መንግሥት ተመላሾችን በመቀበል የተለያየ ድጋፍ እያደረገ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው እንዲሸኙ ያደረገ ቢሆንም የቅንጅታዊ አሠራሩ ክፍተት ያለው መሆኑ፤ የፍልሰት ተመላሾች በተለያዩ የሥራ መስኮች ለመሰማራት እንዲችሉ የነዋሪነት መታወቂያ ማግኘት አለመቻላቸው ትኩረት የሚሻ ክፍተት ነው።

ሕፃናትን በሚመለከት በዘርፉ ከተለዩ የሰብአዊ መብቶች ክፍተቶች መካከል በሕግ አስከባሪ አካላት በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ የሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ወንጀል ተግባሮች በቂ ትኩረት አለማግኘታቸው፤ የሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ወንጀሎች በብዛት እንደ ሌላ ተራ ወንጀሎች ለምሳሌ የልጆች ጉልበት ብዝበዛ፣ አካላዊ ጥቃት ወዘተ. ተቆጥረው በቂ ቅጣት ሳይሰጥባቸው መቅረታቸው፤ የሚፈልሱ ሕፃናት ለተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የተጋለጡ መሆናቸውና ለሕፃናት ተመላሾች ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በቂ የሕግ፣ የአዕምሮና ሥነ-ልቦናዊ ድጋፍ እንዲሁም መልሶ የማዋሃድ አገልግሎቶች አለመቅረባቸው ይገኙበታል።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አብዛኛውን ተጎጂ ተመላሽ ፍልሰተኞችን ተቀብለው አገልግሎት የሚሰጡ ቢሆንም፣ በሕግ አስከባሪ አካላት እና በተቋማቱ መካከል የመረጃ መለዋወጥን ጨምሮ ቅንጅታዊ አሠራር አለመኖር በተጎጂዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ወደ ሕግ ሳይቀርቡ እንዲቀሩ ያደርጋል። ወደ ሕግ በሚቀርቡበትም ሁኔታ ለተጎጂ ፍልሰተኞች የሚደረገው የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እና የድጋፍ አገልግሎት ዝቅተኛ ነው። የሕግና ፍትሕ ተቋማቱ ለተጎጂዎች የሚሆን ደኅንነቱ የተጠበቀ መጠለያ (safe houses) የሌላቸው መሆኑ፣

ተጎጂዎች የምርመራ እና የክስ ሂደቶች እስኪጠናቀቁ በፖሊስ ጣቢያዎች መታሰራቸው፣ በታሰሩበት የሃይማኖት ነጻነታቸው እንዲሁም የመንቀሳቀስ መብታቸው መገደቡ፣ እንደ ምግብ፣ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ፣ የጤና አገልግሎት ያሉ መሠረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላታቸው፣ እንዲሁም የሥነ-ልቦና ድጋፍ አለመኖሩ ኢሰመኮ በዘርፉ ከለያቸው አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ውስጥ ናቸው።



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/ Amanuel Negeso

# ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

# ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

አንድ ሀገር የሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር ያላትን ቁርጠኝነት ከምታሳይባቸው መንገዶች አንዱ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን መፈረምና ማጽደቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ፈርማ አጽድቃለች፡፡ እነዚህ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በአባል ሀገራት ላይ ግዴታዎችን ይጥላሉ፡፡ ሀገራት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ካጸደቁ በኋላ በስምምነቶቹ ውስጥ የሚገኙ መብቶችን በማረጋገጥ ለስምምነቶቹ መፈጸም ያላቸውን ቁርጠኝነት ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ አብዛኞዎቹ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በአባል ሀገራት ላይ የአፈጻጸም ሪፖርት በስምምነቶቹ ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች የማቅረብ ግዴታ ይጥላሉ፡፡ ይህ ክፍል ኢትዮጵያ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ማጽደቅ አንጻር፣ ባጸደቀቻቸው ስምምነቶች ዙሪያ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ከማቅረብ አንጻር እና በጸደቁ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ አካቶ ከመፈጸም አንጻር ያለችበትን ሁኔታ ይቃኛል፡፡

## የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ከማጽደቅ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ የፈረመችውና ያጸደቀችው አህጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት የለም፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን ኢትዮጵያ በርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን የፈረመች ሲሆን እነዚህ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡

**ሰንጠረዥ አንድ፦ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ከማጽደቅ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ**

| ተ.ቁ | ስምምነቶች | ሁኔታ | የተፈረመበት ወይም የፀደቀበት ቀን |
|---|---|---|---|
| | **የተባበሩት መንግሥታት ስምምነቶች** [1] | | |
| 1. | የማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፤ ኢ-ሰብአዊ የሆነና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት (Convention Against Torture) | ጸድቋል | መጋቢት 5/1986 |
| 2. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Civil and Political Rights) | ጸድቋል | ሰኔ 4/1985 |
| 3. | በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሏዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (Convention on Elimination of All Forms of Discrimination Against Women) | ጸድቋል | ጳጉሜ 5/1973 |
| 4. | አድሏዊ የዘር ልዩነቶችን ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (International Convention on the Elimination of Racial Discrimination) | ጸድቋል | ሰኔ 16/1968 |

[1] https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/TreatyBodyExternal/Treaty.aspx?CountryID=59&Lang=EN

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5. | የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights) | ጸድቋል | ሰኔ 4 /1985 |
| 6. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of the Child) | ጸድቋል | ግንቦት 6/1983 |
| 7. | ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of Persons with Disabilities) | ጸድቋል | ሰኔ 30/2002 |
| 8. | ሁሉንም ሰው ከአስገዳጅ ስወራ ለመጠበቅ የተደረገ ስምምነት (Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) | አልጸደቀም | - |
| 9. | የስደተኛ ሠራተኞችን እና የቤተሰቦቻቸውን መብቶች ለመጠበቅ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (International Convention on the Protection of the Rights of All Migrant Workers and Members of Their Families) | አልጸደቀም | - |
| | **ለተባበሩት መንግሥታት ስምምነቶች አማራጭ ፕሮቶኮሎች** | | |
| 10. | የማሠቃየት ተግባርን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention against Torture) | አልጸደቀም | - |
| 11. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the International Covenant on Civil and Political Rights (CCPR-OP1-IC)) | አልጸደቀም | - |
| 12. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን የሞት ቅጣትን ለማስቀረት ያለመ ሁለተኛ አማራጭ ፕሮቶኮል (Second Optional Protocol to the International Covenant on Civil and Political Rights aiming to the abolition of the death penalty) | አልጸደቀም | - |
| 13. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት በግጭቶች ውስጥ የሕፃናት ተሳትፎ ላይ አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the involvement of children in armed conflict) | ጸድቋል | ግንቦት 6/2006 |
| 14. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት በሕፃናት ሽያጭ፣ ሕፃናትን ለወሲብ ንግድ ማሰማራት እና የወሲብ ፊልም ማራትን ለማስወገድ የተደረገ አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the sale of children, child prostitution and child pornography) | ጸድቋል | መጋቢት 16/2006 |
| 15. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child (CRC-OP-IC)) | አልጸደቀም | - |
| 16. | ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the Rights of Persons with Disabilities) | አልጸደቀም | - |
| 17. | በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሏዊ ልዩነት ላይ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the Convention on the | አልጸደቀም | - |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | Elimination of All forms of Discrimination against Women) | | |
| 18. | የኢኮኖሚ፣ የማኀበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አማራጭ ፕሮቶኮል (Optional Protocol to the International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights) | አልጸደቀም | - |
| | **የአፍሪካ ኅብረት ስምምነቶች**[2] | | |
| 19. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር (African Charter on Human and Peoples' Rights) | ጸድቋል | ሰኔ 8/1990 |
| 20. | የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ቻርተር (African Charter on the Rights and Welfare of the Child) | ጸድቋል | መስከረም 22/1994 |
| 21. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (Maputo Protocol) | ጸድቋል | ሐምሌ11/2010 |
| 22. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Establishment of an African Court on Human and Peoples' Rights) | ተፈርሟል ግን አልጸደቀም | ሰኔ 2 /1990 |
| 23. | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአፍሪካ ስደተኞችን ችግሮች ለመቅረፍ የተደረገው ስምምነት (OAU Convention Governing the Specific Aspects of Refugee Problems in Africa) | ጸድቋል | ጥቅምት 5/1966 |
| 24. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Older Persons in Africa) | ጸድቋል | መጋቢት 4/2012 |
| 25. | በአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና እገዛን አስመልክቶ የተደረገው የአፍካ ኅብረት ስምምነት (ካምፓላ ስምምነት) (African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa (Kampala Convention) | ጸድቋል:: | መጋቢት 4/2012 |
| 26. | የአፍሪካ የሰዎችና ኅዝቦች መብቶች ቻርተር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Persons with Disabilities in Africa) | አልጸደቀም | - |
| 27. | የአፍሪካውያን ዴሞክራሲ፣ ምርጫ እና አስተዳደር ቻርተር (African Charter on Democracy, Elections, and Governance) | ጸድቋል | ታህሳስ 28/2001 |
| 28. | የአፍሪካ ወጣቶች ቻርተር (African Youth Charter) | ጸድቋል | ሚያዚያ 16/2006 |

[2] : https://au.int/en/treaties

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29. | ሙስናን ለመከላከል እና ለመዋጋት የተደረገ የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (African Union Convention on Preventing and Combating Corruption) | ጸድቋል | ጥቅምት 5/2000 |
| 30. | ሽብርን ለመከላከል እና ለመዋጋት የተደረገ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስምምነት (OAU Convention on the Prevention and Combating of Terrorism) | ጸድቋል | የካቲት 26/1995 |
| 31. | የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የዜግነት መብት እና በአፍሪካ ሀገር አልባነትን ማጥፋት ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Specific Aspect of the Right to a Nationality and the Eradication of Statelessness in Africa) | አልጸደቀም | - |
| 32. | የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች የዜጎች ማኅበራዊ ጥበቃ እና ማኅበራዊ ደኅንነት ቻርተር ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Citizens to Social Protection and Social Security) | አልጸደቀም | |

## የሰብአዊ መብቶችን ሪፖርት ከማቅረብ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ

አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች አንዱ የሚጥሉት ግዴታ አባል ሀገራት የስምምነቶቹን አፈጻጸም አስመልክቶ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት የእነዚህን ስምምነቶች አፈጻጸም ለመቆጣጠርና ለመከታተል ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች ማቅረብ ነው። በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን (African Commission on Human and Peoples' Rights) የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር (African Charter on Human and Peoples' Rights)) እንዲሁም የአፍሪካ የሰዎችና ሕህዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (Maputo Protocol) አፈጻጸምን አስመልክቶ በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ሪፖርት አቅርባለች።

የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን በኢትዮጵያ የቀረበውን ሪፖርት አስመልክቶ በሚቀጥሉት ጉባኤዎች ገምግሞ የመደምደሚያ ምልከታውን (concluding observations) ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል። ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያ በርካታ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ለተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች ያቀረበች ሲሆን በኢትዮጵያ የቀረቡ የመጨረሻዎቹ ሪፖርቶች መካከል ከላይ የተጠቀሰው የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር እና የማፑቶ ፕሮቶኮል አፈጻጸምን አስመልክቶ ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የቀረበው ሪፖርት፣ ለተ.መ.ድ. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮሚቴ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ስምምነትን (Convention on the Rights of Persons with Disabilities) አፈጻጸምን አስመልክቶ በጥር 11 ቀን 2015 ዓ.ም. የቀረበው ሪፖርት፣ ለተ.መ.ድ. የሕፃናት መብቶች ኮሚቴ (Committee on the Rights of the Child) የሕፃናት መብቶች ስምምነት (Convention on the Rights of the Child) አፈጻጸምን አስመልክቶ በየካቲት 18 ቀን 2013 ዓ.ም. ያቀረበችው ሪፖርት ናቸው። ለሕፃናት መብቶች ኮሚቴ (Committee on the Rights of the Child) የቀረበውን ሪፖርት አስመልክቶ ኮሚቴው በሚቀጥሉት ጉባኤዎች ሪፖርቱን በመገምገም የመደምደሚያ ምልከታዎችን ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል። ለተ.መ.ድ. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮሚቴ የቀረበው ሪፖርት የቅርብ ጊዜ ሪፖርት እንደ መሆኑ ለወደፊት በኮሚቴው የሚታይ ይሆናል። እስከ አሁን በኢትዮጵያ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ

የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የቀረቡ ሪፖርቶች ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተቀምጧል፡፡

**ሰንጠረዥ ሁለት፦ የሰብአዊ መብቶችን ሪፖርት ከማቅረብ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ**

| የተባበሩት መንግሥታት ስምምነቶች | | | |
|---|---|---|---|
| **ተ.ቁ** | **ስምምነቶች** | **ሁኔታ** | **ምርመራ** |
| 1. | የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Civil and Political Rights) | ኢትዮጵያ ሁለተኛውን ወቅታዊ ሪፖርት በ2007 ዓ.ም. ማቅረብ የነበረባት ቢሆንም ጥምር የ2ኛው እና 3ኛው ወቅታዊ ሪፖርት በ ጥቅምት 11 ቀን 2012 ዓ.ም. አቅርባለች፡፡ ኮሚቴው በሪፖርቱ ላይ ገንቢ የሆነ ውይይት (constructive dialogue) ከመስከረም 30 እስከ ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ.ም. በተካሄደው የኮሚቴው ጉባኤ ላይ ካደረገ በኋላ በጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. ምክረ ሐሳቦችን የያዘ የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል፡፡[3] | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ ሪፖርት የለም |
| 2. | በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሏዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት Convention on the Elimination of All forms of Discrimination against Women (CEDAW) | ኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሏዊ ልዩነትን ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት አፈጻጸምን አስመልክቶ 8ኛው ወቅታዊ ሪፖርትን ኅዳር 12 ቀን 2010 ዓ.ም. ያቀረበች ሲሆን መቅረብ የነበረበት በ2008 ዓ.ም. ነበር፡፡ ኮሚቴው በሪፖርቱ ላይ በመጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም. የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል፡፡ [4] ኮሚቴው ኢትዮጵያ 9ኛውን ወቅታዊ ሪፖርት በመጋቢት 2015 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል፡፡ | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ አንድ ሪፖርት አለ፡፡[5] |
| 3. | የሕፃናት መብቶች ስምምነት Convention on the Rights of the Child (CRC) | ኢትዮጵያ 4ኛውን እና 5ኛውን ጥምር ወቅታዊ ሪፖርት ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. አቅርባለች፡፡ ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ግንቦት 28 | ሪፖርቱ የሚቀርብበት ጊዜ ሰኔ 5 ቀን 2012 ዓ.ም. ነበር፡፡ |

[3] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/SessionDetails1.aspx?SessionID=2575&Lang=en

[4] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/Download.aspx?symbolno=CEDAW/C/ETH/CO/8&Lang=En

[5] ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ይህንን ስምምነት አስመልክቶ ቀለል ያለ የሪፖርት ማቅረቢያ ሂደትን (simplified reporting procedure) ስለተቀበለች እና በዚህም ሂደት መሰረት ሀገራት ሪፖርት የሚያቀርቡት ኮሚቴው ሪፖርት ከመቅረቡ በፊት የጥያቄዎችን መዘርዝር (list of issues prior reporting/LOPR) ከላከ በኋላ ስለሆነ፣ ኮሚቴውም እስከዚህ የሪፖርት አመት ድረስ ለኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሰውን የጥያቄ መዘርዝር ስላልላከ ሪፖርቱ መቅረብ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ቀን 2007 ዓ.ም. ሰጥቷል፡፡[6] ኢትዮጵያ 6ኛውንና 7ኛውን ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶች ሰኔ 5 ቀን 2012 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል፡፡ ኢትዮጵያም ይህን ሪፖርት የካቲት 18 ቀን 2013 ዓ.ም. አቅርባለች፡፡ | |
| 4. | የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights (ICESCR) | ኢትዮጵያ የመጀመሪያ፤ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶችን ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. አቅርባለች፡፡ ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ሰጥቷል፡፡[7] ኮሚቴው ሀገሪቱ 4ኛውን ወቅታዊ ሪፖርት ግንቦት 10 ቀን 2009 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል፡፡ | ሪፖርቱ የሚቀርብበት ጊዜ ግንቦት 10 ቀን 2009 ዓ.ም. ነበር፡፡ ነገር ግን በተባለው ጊዜ አልቀረበም፡፡[8] |
| 5. | ሰዎችን ከመሠቃየት ለመከላከል የተቋቋመው ኮሚቴ Committee against torture | ኢትዮጵያ 2ኛው እና 3ኛው ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶችን ጥር 2012 ዓ.ም. ያቀረበች ቢሆንም መቅረብ የነበረበት ኅዳር 2007 ዓ.ም. ነበር፡፡ ኮሚቴው በሪፖርቱ ላይ ገንቢ የሆነ ውይይት (constructive dialogue) በማድረግ በግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም. የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ሰጥቷል፡፡[9] | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ ሪፖርት የለም፡፡ |
| 6. | አድሏዊ የዘር ልዩነቶች ለማስቀረት የተቋቋመ ኮሚቴ Committee on the Elimination of Racial Discrimination (CERD) | ኢትዮጵያ ከ 7ኛው እስከ 16ኛው ያሉትን ጥምር ወቅታዊ ሪፖርቶች ከ 1980/81 ዓ.ም. እስከ 2001/02 ዓ.ም የሚሸፍን አንድ ሪፖርት በመስከረም 21 ቀን 2001 ዓ.ም. አቅርባለች፡፡ እነዚህ ሪፖርቶች መቅረብ የነበረባቸው ጊዜ 1981/82 ዓ.ም.፤ 1983/84 ዓ.ም.፤ 1985/86 ዓ.ም.፤ 1987/88 ዓ.ም.፤ 1989/90 ዓ.ም.፤ 1991/92 ዓ.ም.፤ 1993/94 ዓ.ም.፤ 1995/96 ዓ.ም.፤ 1997/98 ዓ.ም. እና 1999/2000 ዓ.ም. ነበር፡፡ ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. ሰጥቷል፡፡[10] ኢትዮጲያ ከ 17ኛው እስከ 19ኛው ያሉትን ወቅታዊ ሪፖርቶች ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም. በአንድ ሰነድ እንድታቀርብ ጠይቋል፡፡ | ሪፖርቱ የሚቀርብበት ጊዜ ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም. ነበር፡፡ ነገር ግን በተባለው ጊዜ አልቀረበም፡፡ |

[6] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://digitallibrary.un.org/record/814391?ln=en&v=pdf፡፡

[7] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በማስፈንጠር ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/Download.aspx?symbolno=E/C.12/ETH/CO/1-3&Lang=En።

[8] ይህ ሪፖርት በተባለው ጊዜ ያልቀረበ ቢሆንም ሪፖርቱን ለማቅረብ በሚመለከተው አካል ስራዎች ተጀምረዋል

[9] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በማስፈንጠር ማግኘት ይቻላል https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/treatybodyexternal/SessionDetails1.aspx?SessionID=2627&Lang=en

[10] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በማስፈንጠር ማግኘት ይቻላል https://www.refworld.org/policy/polrec/cerd/2009/en/69552

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7. | ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት<br>Convention on the Rights of Persons with Disabilities (CRPD) | ኢትዮጵያ በዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት ላይ የመጀመሪያ ሪፖርት ታኅሣሥ 30 ቀን 2005 ዓ.ም. ያቀረበች ሲሆን ሪፖርቱ መቅረብ የነበረበት ጊዜ 2004 ዓ.ም. ነበር:: ኮሚቴው የመደምደሚያ ምልከታዎችን (concluding observations) ነሐሴ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ሰጥቷል:: ኮሚቴው ሀገሪቱ 2ኛውን እና 3ኛውን ጥምር ሪፖርቶች በነሐሴ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል:: ይህንንም ሪፖርት ኢትዮጵያ በጥር 11 ቀን 2015 ዓ.ም. አቅርባለች:: | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ ሪፖርት የለም:: |
| **የአፍሪካ ኅብረት ስምምነቶች** | | | |
| 8. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር<br>African Charter on Human and Peoples' Rights | ኢትዮጵያ 7ኛውን ወቅታዊ ሪፖርት 2009 ዓ.ም. ማቅረብ የነበረባት ቢሆንም ከ7ኛው እስከ 10ኛው ከ 2007 እስከ 2015 ዓ.ም. ያሉትን የሚያጠቃልል ጥምር ወቅታዊ ሪፖርት በጥር 2016 ዓ.ም. ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን አቅርባለች:: | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ ሪፖርት የለም:: |
| 9. | የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ኮሚቴ<br>African Charter on the Rights and Welfare of the Child | ኢትዮጵያ 4ኛውን እና 5ኛውን ከ 2006/07 ዓ.ም. እስከ 2011/12 ዓ.ም. ያሉትን የሚያጠቃልል ወቅታዊ ሪፖርት በሐምሌ ወር 2012 ዓ.ም. አቅርባለች:: የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ኮሚቴ የሪፖርቱን መደምደሚያ ምልከታዎች (concluding observations) በየካቲት 2014 ዓ.ም. ሰጥቷል::[11] ኮሚቴውም ኢትዮጵያ ቀጣዩን ወቅታዊ ሪፖርት በየካቲት 2017 ዓ.ም. እንድታቀርብ ጠይቋል:: | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ ሪፖርት የለም:: |
| 10. | የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል)<br>Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (Maputo Protocol) | ኢትዮጵያ የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) ላይ የመጀመሪያ ሪፖርት በጥር 2016 ዓ.ም. አቅርባለች:: :: ይህም ሪፖርት ኢትዮጵያ የሰዎችንና ሕዝቦችን መብቶች ቻርተር አስመልክቶ በጥር 2016 ዓ.ም. ያቀረበችው ሪፖርት ክፍል "ለ" (part b of the Report on the African Charter on Human and Peoples Rights) ሆኖ የቀረበ ነው:: | ጊዜው ደርሶ ያልቀረበ ሪፖርት የለም:: |

[11] ይህንን የመደምደሚያ ምልከታ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል https://www.acerwc.africa/en/member-state/ratifications/66/ethiopia።

## ቁልፍ እመርታዎች

- የአፍሪካ ሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር እንዲሁም የማፑቶ ፕሮቶኮል አፈጻጸምን አስመልክቶ ለአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የሚቀርበው የአፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ መቅረቡ፣
- ለ4ኛው ሁሉን አቀፍ ወቅታዊ ግምገማ (Universal Periodic Review) ኢትዮጵያ ማቅረብ ያለባት መንግሥታዊ ሪፖርት ዝግጅት መጀመሩና ሪፖርቱን አጠናቆ በዚህ ዓመት ለመላክ እየተሠራ መሆኑ፤
- ለዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ኮሚቴ የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ቃል ኪዳን አፈጻጸምን አስመልክቶ በ2009 ዓ.ም. መቅረብ የነበረበትን ሪፖርት ለማቅረብ የዝግጅት ሥራዎች መጀመራቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች

- በጊዜው ያልቀረቡ ሪፖርቶች መኖራቸው፦ ከላይ ካለው ሰንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃል ኪዳን (International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights) አፈጻጸምን አስመልክቶ እና ዘርን መሠረት ያደረገ መድሎን ለማጥፋት የተደረገውን ስምምነት (Convention on the Elimination of Racial Discrimination) አፈጻጸም አስመልክቶ ማቅረብ የነበረባት ሪፖርቶች ሳይቀርቡ ጊዜያቸው አልፏል፡፡ የእነዚህ ሪፖርቶች አለመቅረብና ዘርን መሠረት ያደረገ መድሎን ለማጥፋት የተደረገውን ስምምነት በተመለከተ ሪፖርቱን ለማቅረብ ግልጽ የሆነ ዕቅድ አለመኖሩ፣
- የሚቀርቡ ሪፖርቶች ወቅቱን በጠበቀ መልኩ አለመቅረባቸው፦ ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ በጥቅምት 11/2012 ለተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ ያቀረበችው ሪፖርት መቅረብ የነበረበት ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም. ነበር፡፡ በኅዳር 12 ቀን 2010 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ. ሴቶች ላይ የሚደርሰውን መድሎ ለማስወገድ ለተቋቋመው ኮሚቴ ያቀረበችው 8ኛው ሪፖርት መቅረብ የነበረበት በሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም. ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጥር ወር 2012 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ. ሰዎችን ከመሠቃየት ለመከላከል ለተቋቋመው ኮሚቴ (Committee Against Torture) ያቀረበችው ሪፖርት የቀረበው መቅረብ ከነበረበት ስድስት ዓመት ዘግይቶ ነው፡፡ እንዲሁም በነሐሴ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. ለተ.መ.ድ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ኮሚቴ መቅረብ የነበረበት ሪፖርት የቀረበው ከሁለት ዓመት በላይ ዘግይቶ ነው፡፡ በተጨማሪም በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ለአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ያቀረበችው ወቅታዊ ሪፖርት መቅረብ የነበረበት በነሐሴ ወር 2009 ዓ.ም. ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በጊዜው ማቅረብ ላይ ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ኢትዮጵያ ሪፖርት በማቅረብ የምታገኘውን ጠቃሚ ግብዓት የሚያሳጣና በጊዜ ሂደት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡
- ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት በቂ ትኩረት አለመስጠት፦ የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት በባህሪው በአንድ ተቋም የሚዘጋጅ ሳይሆን የተለያዩ ተቋማትን ተሳትፎ የሚፈልግ ነው፡፡ በተለይም ለሪፖርቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ከአስፈጻሚ አካላት ስለሆነ የእነዚህ አካላት የተቀናጀ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ከዚህ አንጻር ብዙ ክፍተቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም ክፍተቶች በአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ላይ ችግር እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ ግብአት ለመሰብሰብ በሪፖርት አዘጋጅ ተቋም ለሚላኩ ጥያቄዎች በቂ ጊዜ ሰጥቶ ምላሽ ከመላክ አንጻር

እና ግብአቶችን በሚፈለገው ጥራትና ደረጃ አዘጋጅቶ ከመላክ አንጻር ያሉ ችግሮች የሪፖርት ዝግጅትን በማስተጓጎል ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት እንዳይቀርብ እንቅፋት ሆነዋል።

## ተግዳሮቶች

የሰብአዊ መብቶች ስምምነት አፈጻጸም ሪፖርቶችን ከማቅረብ አንጻር ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያሉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:-

- **የተቀናጀ መረጃ እጥረት፦** የሰብአዊ መብቶችን አፈጻጸም ሪፖርት ለማዘጋጀት የተቀናጀ መረጃ አስፈላጊ ነው። የተቀናጀ መረጃ ከሌለ አንድ መብት የተፈጸመበትን ደረጃ ለመለካት፣ ለማወቅም ሆነ ለማስረዳት አስቸጋሪ ይሆናል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በኢትዮጵያ የተቀናጀና የተደራጀ እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ስለሌለ ለእንደነዚህ ዐይነት ሪፖርቶች ግብአት የሚሆን መረጃ ማግኘት አዳጋች ነው። ይህም የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርትን በጊዜው ማቅረብ እንዳይቻል አድርጓል። የተቀናጀ መረጃ እንዲኖር ለማስቻል የፍትሕ ሚኒስቴር ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦች መከታተያ የመረጃ ቋት ማደራጀቱ ከላይ የተጠቀሰውን ተግዳሮት ከማስወገድ አንጻር ትልቅ ሚና የሚኖረው ቢሆንም የመረጃ ቋቱ በቅርብ ሥራ ስለጀመረ ውጤታማነቱን ለመግለጽ ያስቸግራል። ይህ የመረጃ ቋት ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም አስፈጻሚ አካላት መረጃዎችን በሚፈለገው ጥራትና ጊዜ ወደ ቋቱ በማስገባት የመረጃ ቋቱ ሙሉ ለሙሉ ለሚፈለገው ዐላማ እንዲውል ማድረግ አለባቸው።
- **የዐቅም ውስንነት፦** የአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ትልቅ የፋይናንስ ዐቅም የሚጠይቅ ነው። ለሪፖርቱ ግብዓት ለመሰብሰብ፣ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት፣ በሪፖርቱ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን በቂ በጀት ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ይህንን በጀት በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ይህም የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርቶችን ከማቅረብ አንጻር እንደ አንድ ተግዳሮት የሚቀመጥ ነው።
- **ከባለሙያዎች ጋር የሚያያዝ ውስንነት፦** የአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት በዓለም አቀፍ ሪፖርት ዝግጅት ዙሪያ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች የሚከናወን ሥራ ነው። ከዚህ አንጻር የአፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ ተቋማት ተፈላጊውና በቂ የሰው ኃይል እጥረት አለባቸው።
- **ቋሚ የሆነ ኮሚቴ ወይም መሰል መዋቅር አለመኖሩ፦** ኮሚሽኑ የሪፖርት አቅራቢ ተቋም ከሆነው ሚኒስቴር እንደተረዳው ምንም እንኳን ሪፖርት ለማዘጋጀት ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል ቢኖርም፣ የሪፖርት ዝግጅት ሥራው የሚሠራው በጊዜያዊነት በሚዋቀሩ ኮሚቴዎች አማካኝነት ነው። እነዚህ ኮሚቴዎች የሚዋቀሩት ከተለያዩ አስፈጻሚ ተቋማት በተውጣጡ ባለሙያዎች ሲሆን፣ እነዚህ ባለሙያዎች አዲስ ኮሚቴዎች በተዋቀሩ ቁጥር የሚቀያየሩ ናቸው። ይህ ደግሞ በሪፖርት ዝግጅት ላይ ባለሙያዎች በቂ ልምድ እንዳይቀስሙ ምክንያት ሆኗል። በተጨማሪም የሪፖርት አርቃቂ ኮሚቴዎች ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያዎች በተቋማቸው ውስጥ በመደበኛነት የሚሠሩት ሌሎች ሥራዎች ስላላቸው ሙሉ ትኩረታቸውን በሪፖርት ዝግጅቱ ላይ ለማድረግ ይቸገራሉ። ይህም ለሪፖርቱ ግብአቶችን የማሰባሰብ ሥራዎች እና የተሰበሰቡ ግብአቶችን አደራጅቶ ሪፖርቱን የማርቀቅ ሥራዎች በአግባቡ እንዳይሠሩ እንቅፋት ይሆናል። ይህም የሪፖርት ዝግጅቱ በተፈለገው ጥራትና ፍጥነት እንዳይከናወን ያደርጋል።

## ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ ከማካተት (Domestication) አንጻር ያለችበት ሁኔታ

ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ አካቶ ከመፈጸም አንጻር የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሀገሪቷ ሕግ አካል እንደሚሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል። ይህ ደግሞ እነዚህ ስምምነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በቀላሉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያስችላል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸውና ካጸደቀቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚመነጩ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን እንዳላቸው በአንቀጽ 3(1(ሀ)) ይደነግጋል። ይህ አዋጅ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመተግበር አንጻር ፍርድ ቤቶች አካባቢ የሚታየው የአሠራር ክፍተት በመቅረፍ አዎንታዊ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል።

### ቁልፍ እመርታዎች

በጥቅምት 23 ቀን 2016 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንና የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት (Office of the High Commissioner for Human Rights) አዘጋጅነት የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌን (Universal Declaration of Human Rights) 75ኛ ዓመትን ለመዘከር በተካሄደው ሀገር አቀፍ ኮንፍረንስ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፍትሕ ሚኒስቴር የሚስተዋሉ የሕግ ክፍተቶችን ለመሙላት ዓለም አቀፍ የሕግ ልማዶችን (Customary International Law) እና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ሥራ ላይ እንዲያውሉ አስፈላጊ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ቃል ገብቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ የፍትሕ ሚኒስቴር የሚስተዋሉ የሕግ ክፍተቶችን ለመሙላት ዓለም አቀፍ የሕግ ልማዶችን (Customary International Law) እና ኢትዮጵያ ተቀብላ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን በቀጥታ ሥራ ላይ ለማዋል ቃል ገብቷል። በተጨማሪም የፌዴራል ፖሊስ የሕግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን ክብርና ከዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሚመነጩ የሰብአዊ መብቶችን እንዲጠብቁና እንዲያከብሩ ተጨባጭ እርምጃ እንደሚወስድ ቃል ገብቷል። እነዚህ የተገቡ ቃሎች ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን በሕጎች ውስጥ አካቶ ከመፈጸም አንጻር ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል።

### መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች

- ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ ከማካተት አንጻር ያለው ዋናውና አሳሳቢው ጉዳይ እነዚህን ስምምነቶች በሥራ ላይ መዋል መተግበር/መተርጎም ላይ ክፍተት መኖሩ ነው። ለዚህ ማሳያው ፍርድ ቤቶች እና ሌሎች ውሳኔ ሰጪ አካላት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የስምምነቶቹን አንቀጾች ከመጥቀስ በዘለለ እነዚህን ስምምነቶች በሚጠበቀው መጠን ተተርጉመው በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋል ክፍተት፣
- ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እንደ ኢትዮጵያ ሕግ አካል ያለመቀበል ችግር፦ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የኢትዮጵያ ሕግ አካል እንደሆኑ እንደሚቆጠሩ በግልጽ ቢደነግግም፣ ይህንን ሕገ መንግሥታዊ እውነታ ተቀብሎ መተግበር ላይ ክፍተት ይታያል። ይህም ክፍተት በዋናነት የሚገኘው በነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1987 አንቀጽ 2(2 እና 4) ሥር ሁሉም የኢትዮጵያ ሕጎች በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች በነጋሪት ጋዜጣ ላይ መታተም አለባቸው ብሎ

ስለሚደነግግ እና ከእነዚህ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ማጽደቂያ አዋጅ በቀር የስምምነቶቹ ሙሉ ይዘት በአማርኛም ሆነ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ስለማይታተም ነው። የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ሁሉም ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ላይ መታተም እንዳለባቸው ቢደነግግም ይህ ድንጋጌ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የኢትዮጵያ የሕግ አካል ከመሆን ሊያግዳቸው አይችልም። ምክንያቱም እነዚህ ስምምነቶች የኢትዮጵያ ሕግ አካል እንደሚሆኑ የደነገገው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በደረጃ ከነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ስለሚበልጥ እና የሕገ መንግሥት ድንጋጌ በአዋጅ ድንጋጌ ሊሻር ስለማይችል ነው።

- ለሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች አፈጻጸም በቂ የሆነ ትኩረት አለመስጠት፦ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ሲያጸድቅ የስምምነቱን አፈጻጸም የትኛው ተቋም መከታተል እንዳለበት በማጽደቂያ አዋጆቹ ውስጥ በግልጽ ይቀመጣል። ይሁን እንጂ እነዚህ በስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ውስጥ የስምምነቱን አፈጻጸም እንዲከታተሉ ኃላፊነት የሚሰጣቸው ተቋማት ብዙ ጊዜ በቂ ትኩረት ሰጥተው ክትትል በማድረግ ስምምነቱ እንዲፈጸም ተገቢ ሥራዎች አልተከናወኑም። ይህም የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል። የሰብአዊ መብቶች ስምምነት አፈጻጸምን የሚከታተል አካል አለመኖር፣ በማጽደቂያ አዋጆች የስምምነቶቹን አፈጻጸም እንዲከታተሉ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ተቋማት ሥራ የሚከታተለውና የሚቆጣጠረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ስምምነቶች አፈጻጸምን አስመልክቶ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ስለሌለው ተቋማቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዳይወጡ አድርጓል።

## ተግዳሮቶች

ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን መብቶች በሕጎች ውስጥ አካቶ ከመፈጸም አንጻር የሚከተሉት ተግዳሮቶች ተስተውለዋል:-

- **የተደራሽነት ችግር፦** ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በነጋሪት ጋዜጣ ላይ አለመታተም የኢትዮጵያ ሕግ አካል ከመሆን ባያግዳቸውም የስምምነቶቹ ተደራሽነት ላይ ትልቅ እክል ፈጥሯል። ከላይ እንደተጠቀሰው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በኢትዮጵያ ሲጸድቁ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ የሚታተመው የማጽደቂያ አዋጁ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የስምምነቶቹ ይዘት በቀጥታ እንዳይታወቁ አድርጓል። እነዚህ ስምምነቶች በአማርኛ ወይም በሌላ የሀገር ውስጥ ቋንቋ ስለማይተረጎሙ እና እንደሌሎች ሕጎች በእትም ስለማይገኙ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደራሽ ናቸው ማለት አይቻልም። ይህም እነዚህ ስምምነቶች እንደ ኢትዮጵያ ሕጎች ተቆጥረውና ታውቀው በሚፈለገው መጠን በፍርድ ቤቶች ክርክር ቀርቦባቸውና የውሳኔ መሠረት ሆነው እንዳያገለግሉ አድርጓል።

## ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ከመፈጸም አንጻር ያለችበት ሁኔታ

አንድ ሀገር የሰብአዊ መብቶችን ስምምነት ስትቀበልና ስታጸድቅ ስምምነቱን ለመፈጸም ሁሉንም አስፈላጊ የሕግ (legislative)፣ የፍርድ (judicial)፣ የፖሊሲና ሌሎች እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ ይኖርባታል። በተጨማሪም አባል ሀገራት በእነዚህ ስምምነቶች ውስጥ የተካተቱ መብቶችን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የተቋቋሙ የሰብአዊ መብቶች ተቋማትን ምክረ ሳቦች የመቀበልና የመፈጸም ግዴታ አለባቸው። ሌላው የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችን ከመቆጣጠርና ከመከታተል አንጻር የሚነሳው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሁሉን-አቀፍ የግምገማ መድረክ (Universal Periodic Review) ሲሆን ይህም የተቋቋመው በመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም. በተ.መ.ድ. የጠቅላላ ጉባኤ ነው። የተ.መ.ድ. ሁሉን-አቀፍ

የግምገማ መድረክ አሳታፊና ፍላጎት/ትብብር ላይ ተመሥርቶ የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት የሁሉንም የተ.መ.ድ. አባል ሀገራት የሰብአዊ መብቶች አተገባበር ሁኔታ ገምግሞ የሰብአዊ መብቶች አያያዝን ለማሻሻል ምክረ ሐሳብ የሚሰጥበት መድረክ ነው። እስከ አሁን ሁሉን-አቀፍ የግምገማ መድረክ በሦስት ዙር የተከናወነ ሲሆን ኢትዮጵያ በሦስቱም ዙር ተገምግማለች።

የመጨረሻው የኢትዮጵያ ሁሉን-አቀፍ የግምገማ መድረክ ግምገማ በግንቦት ወር 2011 ዓ.ም. የተካሄደ ሲሆን በዚህም ግምገማ 327 ምክረ ሐሳቦች ተሰጥቷት ነበር። ከእነዚህም ምክረ ሐሳቦች ውስጥ ኢትዮጵያ 270 ምክረ ሐሳቦችን ለመፈጸም የተቀበለች ሲሆን 57 ምክረ ሐሳቦችን ሳትቀበል ቀርታለች። ቀጣዩ የኢትዮጵያ ግምገማ በጊዜያዊነት ከጥቅምት እስከ ኅዳር ወር 2017 ዓ.ም. የተያዘ ሲሆን ይህም በ4ኛው ዙር ሁሉን-አቀፍ የግምገማ መድረክ ይሆናል። ከላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንደ ተመለከተው ኢትዮጵያ ሰባቱን የተ.መ.ድ. ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ጨምሮ በርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን አጽድቃለች። ኢትዮጵያ ከሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሚመነጩ ግዴታዎችን በዋናነት የምትፈጽመው በብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር አማካኝነት ሲሆን ይህንን የድርጊት መርኃ ግብር የፍትሕ ሚኒስቴር ከሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመተባበር ያዘጋጀዋል። ኢትዮጵያ በባለፉት ዓመታት ሁለት የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብሮችን አውጥታ የተገበረች ሲሆን በ2013 ዓ.ም. ጸድቆ ሥራ ላይ መዋል የነበረበት 3ኛው የድርጊት መርኃ ግብር ይህ ሪፖርት እስከ ሚዘጋጅበት ጊዜ ድረስ በረቂቅ ደረጃ ላይ ይገኛል።

### ቁልፍ እመርታ

- የፍትሕ ሚኒስቴር ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦች መከታተያ የመረጃ ቋት (National Recommendations Tracking Database) በዚህ የሪፖርት ዓመት ማስጀመሩ አንድ ትልቅ እመርታ ነው። ይህ የመረጃ ቋት አስፈላጊው መረጃ በየጊዜው ቢገባለት ከሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም አንጻር የሚከሰተውን የተቀናጀ መረጃ እጥረት ችግርን በማቃለል አዎንታዊ ሚና ይጫወታል።

### መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች

- የሁለተኛው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር በ2012 ዓ.ም. ከተጠናቀቀ በኋላ 3ኛው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር በተገቢው ጊዜ ጸድቆ ሥራ ላይ ባለመዋሉ የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸምን ከመከታተልና መቆጣጠር አንጻር አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሯል።
- ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ረቂቅ 3ኛው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር አሁን ባለው ሁኔታ የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና የባህላዊ መብቶችን ያላካተተ መሆኑ ነው። ረቂቅ የድርጊት መርኃ ግብሩ ትኩረት ያደረገው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች እንዲሁም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍል መብቶች ላይ ነው። አሁን ባለበት ሁኔታ የድርጊት መርኃ ግብሩ ቢጸድቅ ከኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባሕል መብቶች አንጻር የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች አፈጻጸምን ለመከታተልና ለመቆጣጠር አስቻይ ሁኔታዎች እንዳይኖሩ ያደርጋል። ይህ አካሄድ የሰብአዊ መብቶች አይነጣጠሉም፣ አንዳቸው በሌላቸው ላይ የተደገፉና የተያያዙ ናቸው የሚለውን የዓለም አቀፍ መርሕ የሚጠስ ይሆናል።
- ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ቅድሚያና በቂ ትኩረት ያለመስጠት፦ የሰብአዊ መብቶችን ከመፈጸም አንጻር በፌዴራልና ክልል ደረጃ ከ300 በላይ ተቋማት ያሉ ቢሆንም ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ቅድሚያና በቂ ትኩረት ያለመስጠት ችግር ይታያል።

ይህም ችግር የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦችን በዕቅዳቸው ውስጥ አካቶ ከመፈጸምና ለአፈጻጸማቸው ባለሙያ ከመመደብ ጋር ተያይዞ ጎልቶ ይታያል።

- የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦችን በዕቅዳቸው ውስጥ አካትተው የሚሠሩ ተቋማት ጥቂት በመሆናቸው፣ ለምክረ ሐሳቦቹ መተግበር በቂ ትኩረት አለመስጠት በአብዛኛው ተቋማት ውስጥ የሚታዩ በመሆኑ የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦች በቂ ትኩረት አግኝተው በቅጡ እንዳይፈጸሙ ምክንያት ሆኗል።
- የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም የሚከታተል ባለሙያ በአብዛኛው ተቋማት የሚመድቡ ቢሆንም እስካሁን ድረስ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት ሥራው በሚጠበቀው መጥን አልተከናወነም። በሌላ በኩል እነዚህ ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ብዙ ጊዜ ከሚሠሩበት ተቋም የመልቀቅ ሁኔታ ያለ ሲሆን ይህም ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች በማሳጣት ለአዳዲስ ሰዎች በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ስልጠና እንዲሰጥ ምክንያት ሆኗል። ይህ ዐይነቱ ሁኔታ ደግሞ አብዛኛው ሃብትና ጊዜ ዋናው ሥራ ላይ ሳይሆን ባለሙያዎችን ማሰልጠንና መሰል ሥራዎች ላይ እንዲያልቅ ያደርጋል።
- በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማኅበራት በአህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ ከሰብአዊ መብቶች ሥራ አንጻር ያላቸው ተሳትፎ ውስን መሆኑ፦ የሲቪል ማኅበራት የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም በመከታተልና መቆጣጠር ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማኅበራት በአህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ ከሰብአዊ መብቶች ሥራ አንጻር ያላቸው ተሳትፎ ውስን መሆኑ አሳሳቢ ነው።

### ተግዳሮቶች

ከሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሚመነጩ ግዴታዎችን ከመፈጸም አንጻር በኢትዮጵያ ከተስተዋሉ ችግሮች አንዱና ዋናው የተቀናጀና የተደራጀ የመረጃ አሰባሰብ፣ ማከማቻ (storage) እና አስተዳደር አለመኖሩ ነው። የተቀናጀና የተደራጀ የመረጃ አሰባሰብ፣ ማከማቻ (storage) እና አስተዳደር ሥርዓት ያለመኖር በሁሉም የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር ሥራን በሚሠሩ እንደ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ባሉ ተቋማትና የሲቪል ማኅበራት እንደ ትልቅ ችግር የሚነሳ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ በፍትሕ ሚኒስቴር የተጀመረው ብሔራዊ የምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም መከታተያ የመረጃ ቋት (National Recommendation Tracking Data Base) አበረታች ቢሆንም ይህ የመረጃ ቋት በሚገባ ስላልዳበረ የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸምን አስመልክቶ መረጃ ማግኘት የሚቻለው በቀጥታ የፍትሕ ሚኒስቴርንና ሌሎች በልዩ ልዩ ጉዳይ ላይ የሚሠሩ አስፈጻሚ ተቋማትን በመጠየቅ ብቻ ነው። እነዚህ መረጃዎች በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ ስለማይቀመጡ የሚመለከተውን ተቋም ጠይቆም ማግኘት አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ መንግሥት የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል የመረጃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ አለበት።

### መደምደሚያ

አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ከመፈረምና ከማጽደቅ አንጻር በዚህ የሪፖርት ዓመት ኢትዮጵያ ፈርማ ያጸደቀችው የለም። ይሁን እንጂ አሁንም ኢትዮጵያ ያላጸደቀቻቸው በርካታ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ያሉ ሲሆን እነዚህ ስምምነቶች ቢጸድቁ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶችን ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል ምንም እንኳን በዚህ ዓመት እና ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያ በርካታ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ለተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች አቅርባ የነበረ ቢሆንም እነዚህን ሪፖርቶች በተገቢው ጊዜ ከማቅረብ አንጻር ክፍተቶች ነበሩ። በርካታ የመቅረቢያ ጊዜያቸው የደረሰ ሪፖርቶች መኖራቸው አሳሳቢ ቢሆንም በዚህ ዓመት ኢትዮጵያ አንድ ሪፖርት ማቅረብ ችላለች። ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ

ያሉትን መብቶች በሀገር አቀፍ ሕጎች ውስጥ ከማካተት (domestication) አንጻር የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እነዚህ ስምምነቶች የሀገሪቷ ሕግ አካል እንደሚሆኑ በግልጽ ማስቀመጡ፣ በተጨማሪም በ2013 ዓ.ም. የወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸውና ካጸደቀቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚመነጩ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን እንዳላቸው በግልጽ መደንገጉ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በፍርድ ቤቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያስችላል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን እንደ ኢትዮጵያ ሕግ ቆጥሮ ከመፈጸም አንጻር ያሉትን ክፍተቶች፣ እንዲሁም ከእነዚህ ስምምነቶች ተደራሽነት አንጻር ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ሰፊ ሥራዎች ወደፊት መሠራት ይኖርበታል።

## ምክረ ሐሳቦች

- መንግሥት በተገቢው ጊዜ ውስጥ የሪፖርት ጊዜ ያለፈባቸውን የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርቶችን በመለየት ለሚመለከታቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት ስልቶች/ተቋማት እንዲያቀርብ፣
- አስፈጻሚ ተቋማት ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት ተገቢውንና በቂ የሆነ ትኩረት እንዲሰጡ፣
- መንግሥት ለሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርት ሥራ በቂ የፋይናንስና የሰው ኃይል እንዲመድብ፣
- መንግሥት የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም ሪፖርቶችን በሚያዘጋጁ ተቋማት እነዚህን ሪፖርቶች የማዘጋጀት ሥራን በሚጠበቀው ጊዜ፣ ደረጃና ጥራት፣ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ያካተተ ቋሚ ኮሚቴ እንዲያቋቁም፣
- ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን እንደ ኢትዮጵያ ሕግ አካል ከመቁጠር አንጻር ያለውን የግንዛቤ ችግር ለመቅረፍ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እንዲሠሩ፣
- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ወደ አማርኛና ሌሎች ቋንቋዎች እንዲተረጎም በማስደረግ፣ እንዲሁም እንደሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንዲታተም በማድረግ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰብአዊ መብቶች ስምምነት ማጽደቂያ አዋጆች የስምምነቶቹን አፈጻጸም እንዲከታተሉ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ተቋማት ሥራ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በማበጀት እንዲከታተል፣
- መንግሥት በተቻለ ፍጥነት የ3ኛውን ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች የድርጊት መርኃ ግብር አጽድቆ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ቀጣይነት ባለው፣ በተቀናጀና ስልታዊ በሆነ መልኩ የሚፈጸሙበትን አስቻይ ሁኔታ እንዲፈጥር፣
- መንግሥት የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባሕል መብቶችን በሦስተኛው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርኃ ግብር ውስጥ እንዲካተት እንዲያደርግ፣
- የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦችን በሥራ ዕቅዳቸው ውስጥ በግልጽ በማካተት እንዲተገብሩና የሥራቸው ውጤታማነትም እነዚህን ምክረ ሐሳቦች ከመፈጸም አንጻር እንዲለካ፣
- ሁሉም አስፈጻሚ ተቋማት በፍትሕ ሚኒስቴር ሥር የተደራጀው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳብ መከታተያ የመረጃ ቋት የሚፈልግበትን አገልግሎት እንዲሰጥ በወቅቱ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መረጃ የማስገባቱን ሥራ እንዲያከናውኑ፣
- በጥቅምት 23 ቀን 2016 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንና የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት (Office of the High Commissioner for Human Rights) አዘጋጅነት የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች

ድንጋጌን (Universal Declaration of Human Rights) 75ኛ ዓመትን ለመዘከር በተካሄደው ሀገር አቀፍ ኮንፍረንስ ላይ በመንግሥት አካላት የተገቡ ቃሎች (pledges) እንዲፈጸሙ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በትብብር ሥራዎችን እንዲያከናውኑ፣

- የሲቪል ማኅበራት የሰብአዊ መብቶች አፈጻጸምን በተለያየ መንገድ መደገፍ ይኖርባቸዋል። ለአብነትም ለኢትዮጵያ በተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ዙሪያ የማንቃት (awareness raising) ሥራዎችን በመሥራት፣ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች እንዲፈጸሙ ጉትጎታ በማድረግ እና ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስልቶች/ተቋማት (human rights mechanisms) ሪፖርት በማቅረብና መረጃ በመስጠት እንዲሁም ሌሎች መሰል ተግባራትን በማከናወን ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ፣
- መንግሥት ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስልቶች (Human rights mechanisms) የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅና የሰብአዊ መብቶች ምክረ ሐሳቦች አፈጻጸምን አስመልክቶ ግምገማ ሲያደርግ የሲቪል ማኅበራትን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲያሳትፍ ኮሚሽኑ ያሳስባል።

# ምክረ ሐሳቦች እና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች



Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Ermias Dejene

## ምክረ ሐሳቦች እና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ያለውን ጊዜ በሚሸፍነው በዚህ ዓመታዊ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት የተዳሰሱ የሰብአዊ መብቶች ዘርፎች እና በየርዕሱም የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች እንዲፈጸሙ መከታተል፣ እያንዳንዳቸውን የሚመለከታቸውን አስፈጻሚ አካላት ጋር የውትወታ ሥራ መሥራት እና ግኝቶችን እንደአግባቡ ይፋ የማድረጉ ሥራ ኢሰመኮ በ2017 በጀት ዓመት የሚቀጥል ነው። በተጨማሪም የኮሚሽኑ የዘርፍ ሥራ ክፍሎች የለዩትን ቀዳሚ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በሚቀጥለው በጀት ዓመትም ትኩረት የሚሹ ናቸው።

በዚህ የሪፖርቱ የመጨረሻ ክፍል ዋና ዋና ምክረ ሐሳቦችና በሪፖርት ዘመኑ የተጀመሩ እና በሂደት ላይ ያሉ በመሆናቸው፣ አልያም በሀገራዊ ወይም በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ የሚኖራቸው ክስተቶች፣ ሁነቶች ወይም የተወሰዱ እርምጃዎች ከወዲሁ ለማመላከት እንዲሁም በሚመለከታቸው መንግሥት አካላት ወይም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በሚካሄዱ የትጥቅ ግጭቶች የሚሳተፉ ሁሉም ወገኖች በተለይም ግጭቶቹ በየአካባቢው ነዋሪዎችና በሲቪል ሰዎች ላይ እየደረሰ ያለው ሥቃይ እጅግ እየጨመረ መምጣቱን በማገናዘብ፣ ብቸኛው ዘላቂ መፍትሔ ሰላማዊ ውይይት መሆኑን ተቀብለው በቁርጠኝነት ይተገብሩት ዘንድ ኢሰመኮ በአጽንዖት ጥሪ ከሚያቀርብባቸው ጉዳዮች ዋነኛው ነው። በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የተሟላ ምርመራ ተደርጎ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥና የተበደሉም እንዲካሱ ሁሉም የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት አካላት አስፈላጊውን ሁሉ ሊያደርጉ ይገባል። በተለይም በትጥቅ ግጭት ዐውድ ውስጥ የሚደርሱ ወሲባዊና ጾታዊ ጥቃቶችን በአፋጣኝ ማስቆም የሚገባ ሲሆን፣ ለደረሱ ጥቃቶችም ተጠያቂነት የማስፈን ሥራዎች አሁንም ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው። ተፋላሚ ወገኖች ሲቪል ሰዎችንና ንብረቶችን፣ የሕዝብ አገልግሎቶችን እና መሠረተ ልማቶችን በማናቸውም ሁኔታ ዒላማ እንዳያደርጉ፣ በቁጥጥር ሥር የዋሉ የታጠቁ ኃይሎች አባላትና ሌሎች ተጠርጣሪዎችም ሁኔታ በሕጋዊ አግባብ ብቻ እንዲስተናገድ፤ በተለይም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እና ከሕግ ውጭ የተፈጸመ ግድያ በአስቸኳይ በማጣራት ተጠያቂነት እንዲረጋገጥና የማኅበራዊ አገልግሎቶች በተቻለ ፍጥነት እንዲቀጥሉ እንዲደረግ፤ ተፈናቃዮች አስፈላጊው የሰብአዊ ድጋፍ በአስቸኳይ እንዲደርሳቸው እንዲደረግ፤ ለመፈናቀል የዳረጋቸው ምክንያት እልባት አግኝቶ በዘላቂነት ወደ ቀያቸው የሚመለሱበት ሁኔታ እንዲመቻች ኢሰመኮ ያሳስባል። በግጭት የተጎዱ ሰዎችን እና አካባቢዎችን መልሶ የማቋቋሙ ሥራ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የተጎዱ አካባቢዎችን ሊያካትት የሚገባ ነው።
2. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.) መንግሥት እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህዋሓት) መካከል ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም. የተፈረመው እና የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲፀድቅ የሚደነግገውን የዘላቂ ሰላም እና ግጭት ማቆም ስምምነት (የሰላም ስምምነት) ተከትሎ በፍትሕ ሚኒስቴር አስተባባሪነት ይህንኑ ሂደት የሚያስተባብር እና የሚመራ የባለሞያዎች ቡድን መዋቀሩ የሚታወስ ነው። የሰላም ስምምነቱ በተለይም በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ "የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት እና ከአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማዕቀፍ (African Union Transitional Justice Policy Framework) ጋር በተጣጣመ መልኩ ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ እውነትን ለማውጣት፣ ማኅበረሰባዊ እርቅ

እና ፈውስ ለማምጣት እንዲሁም የተጎጂዎችን መፍትሔ የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ተግባራዊ እንደሚያደርግ" ይገልፃል፡፡ ስምምነቱ አክሎም "የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው የሲቪክ ማኅበራትን ጨምሮ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት በሕዝባዊ ምክክር የሚገኙ ግብአቶችን መሠረት አድርጎ እና መደበኛ ሀገራዊ የፖሊሲ አወጣጥ ሂደቶችን ተከትሎ ሊዘጋጅ እንደሚገባ" ያስቀምጣል፡፡

- በዚህም መሠረት በተጀመረ ሂደት በተለያዩ ደረጃዎች አልፎ በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መጽደቁ የሚታወስ ነው፡፡
- እውነተኛ፣ አሳታፊ፣ አካታች፣ ሀገራዊ ዐውዱን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ እና የዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆችን እና ድንጋጌዎችን ያከበረ የሽግግር ፍትሕ ሂደት ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘላቂ ሰላም፣ ማኅበረሰባዊ ዕርቅ እና ፈውስ ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ ኢሰመኮ ከተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በአፋር፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሱማሌ እና በሐረሪ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከሐምሌ 2014 ዓ.ም. እስከ ታኅሣሥ 2015 ዓ.ም. ድረስ ባካሄዷቸው የማኅበረሰብ ምክክሮች የለዩዋቸውን ቀዳሚ ዋና ዋና ግኝቶች እንዲሁም በአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ እንዲሁም የሽግግር ፍትሕን አስመልክቶየተ.መ.ድ.ን አካሄድ ለመግለጽ በተ.መ.ድ. ዋና ጸሐፊ የወጣው የመመሪያ ማስታወሻ (Guidance note of the United Nations (UN) Secretary General: United Nations Approach to TJ) ላይ የሰፈሩ፤ ሀገራት የሽግግር ፍትሕ ሥርዓትን በሚነድፉበትም ሆነ በሚተገብሩበት ወቅት ሊመሩባቸው የሚገቡ ቁልፍ መርሆችን የያዘ ባለ 90 ገጽ ሪፖርት በታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም. ይፋ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡ ሪፖርቱ ተጠያቂነትን፣ እውነትን መፈለግ፣ ማካካሻ ማድረግ/ካሳ መስጠትን፣ ጥሰቶች እንዳይደገሙ ዋስትና መስጠትን እና ዕርቅን ማስፈን በመሳሰሉት ዋና ዋና የሽግግር ፍትሕ አላባዎች/ክፍሎች እና ግቦች ላይ አጽንዖት በመስጠት የተሳታፊዎችን ዕይታ እና ፍላጎቶችን ያብራራል፡፡ በተጨማሪም የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በመፍታት ረገድ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዐቶች ሊኖራቸው ስለሚችለው ሚና ተጎጂዎች ያላቸውን አመለካከት ያካትታል፡፡ ኢሰመኮ እና የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት በዛሬው ዕለት ይፋ ያደረጉት ይህ ሪፖርት፣ ሁለቱ ተቋማት በታኅሣሥ 6 ቀን 2015 ዓ.ም. ያወጡትን የጋራ ምክረ ሐሳቦችን እና ቁልፍ ግኝቶችን ያካተተ አጠር ያለ መሪ ሰነድ (Advisory Note) የሚያሟላ ነው፡፡ ኢሰመኮ እና የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ጽሕፈት ቤት ለ8 ወራት ያክል ሲካሄዱ የቆዩት የማኅበረሰብ ምክክሮች ባጠቃላይ 805 ሰዎች የተሳተፉበት ሲሆን፣ እነዚህም የተጎጂዎችንና ቤተሰቦቻቸውን፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ ባህላዊና የሃይማኖት መሪዎችን እንዲሁም በሰብአዊ መብቶችና ሰላም ጥረት ላይ የሚሳተፉ ሀገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ያካተቱ ናቸው፡፡ ምክክሮቹ በአፋር፣ በአማራ፣ በሐረሪ፣ በኦሮሚያ፣ በሶማሊ እና በትግራይ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ተካሂደዋል፡፡ ከሃይማኖት መሪዎች ጋር በሀገር አቀፍ ደረጃ ተጨማሪ ምክክር ተካሂዷል፡፡ በሪፖርቱ እና ቀደም ሲል በተሰጡ ምክረ ሐሳቦችና ሌሎች የቴክኒክ ድጋፎች እንደተመለከተው ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በተሟላ መልኩ ተገቢውን ምላሽ መስጠት አስፈላጊነት አጽንዖት የሚሰጠው ነው፡፡ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ማድረግ፣ እውነትን መፈለግ፣ ለተጎጂዎች ካሳ መስጠትን እና ተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ዳግመኛ

እንዳይከሰቱ ዋስትና መስጠትን የሚያጠቃልል ሁሉን አቀፍ የሽግግር ፍትሕ ሂደት መተግበር አስፈላጊነት ላይ አብዛኞዎቹ ተጎጂዎች የሚስማሙበት/የሚጠይቁት እንደሆነ በሪፖርቱ ተመላክቷል። ከተለያዩ አካባቢዎች የተውጣጡ ተጎጂዎችና ማኅበረሰቦች የገለጹትን የፍትሕ ፍላጎት ለማሟላት፣ በኢትዮጵያ ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ምላሽ የሚሰጥ፣ ሁለንተናዊ አሠራርን የተከተለ፣ መጠነ ሰፊ የሽግግር ፍትሕ ሂደት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

- ስለሆነም በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ትግበራና ቀጣይ ሂደቶች ሁሉ ይህንኑ ማስረጽና ማስፈጸም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶቶች ሊከናወን የሚገባ ነው። ኢሰመኮም በዚሁ ሂደት የሰጣቸው ምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸምና ሂደቱ ዓለምአቀፍ መስፈርቶችንና የሰብአዊ መብቶች መርሖችን የተከተለ እንዲሆን ለማስቻል የሚያደርገውን ክትትል የሚቀጥል ይሆናል።

3. በትጥቅ ግጭት ሳቢያ እና ድርቅን ጨምሮ በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጉዳይ ሌላው በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። በተለይም በ2016 ዓ.ም. በጀት ዓመት የምግብ እና ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት እጥረት ወይም በጸጥታ ሁኔታና በሌሎች ምክንያቶች የአቅርቦት ተደራሽ መሆን አለመቻል በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ካደረጉ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ነው። ስለሆነም በተለያየ ቦታዎች ከቂያቸው ለተፈናቀሉ ነዋሪዎች በቂ የሆነ እና አስቸኳይ የሰብአዊ ድጋፍ እንዲቀርብ፣ ሁሉም ተፈናቃዮች ወደ ቄያቸው የሚመለሱበት ሁኔታና ዘላቂ መፍትሔ እንዲመቻች እንዲሁም ለመፈናቀል ምክንያት የሆነው የጸጥታ ሥጋት ሰላማዊና ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ ኢሰመኮ ያሳስባል።
4. ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 አፈጻጸምና ዐውድ ጋር በተያያዘ ከተያዙት ታሳሪዎች ውስጥ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በእስር ላይ የሚገኙት ላይ በአፋጣኝ ማጣራት ተደርጎ እንዲለቀቁ፣ የዋስትና መብታቸው እንዲከበር ማድረግ ያስፈልጋል። ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውሎ ለተራዘመ ቅድመ ክስ እስር መዳረግ የሰብአዊ መብቶች መርሖችን የሚጥስ በመሆኑ ተዓማኒ ክስ ያልቀረበባቸው ታሳሪዎች እንዲሁም በማስገደድ የተሰወሩና ያሉበት ቦታ ሳይታወቅ የታሰሩ ሰዎች ሁሉ ከእስር እንዲለቀቁ፣ የመንግሥት የጸጥታና የአስተዳደር አካላት በቁጥጥር ሥር የሚውሉ ግለሰቦችን በመደበኛ ማቆያዎች ብቻ እንዲይዙና ሁልጊዜም የተያዙ ሰዎች ያሉበት ቦታና ሁኔታ ለቤተሰቦቻቸው እንዲገለጽ እንዲደረግ።
5. በጥበቃ ሥር ወይም የታሠሩ ሰዎችን አያያዝን በተመለከተ ኢሰመኮ ያቀረባቸው ምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም ሲከታተል እና በክልል እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከፖሊስ ጣቢያዎቹ ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም የሲቪክ ማኅበረሰቦች አባላትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት የሚያደርገው የውትወታ ሥራ የሚቀጥል ነው። በተጠርጣሪዎች አያያዝ እና የሰብአዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች መካከል በዋነኝነት ከበጀት ወይም የገንዘብ አቅም እጥረት ጋር የሚያያዙት ናቸው። ይህ ችግር በሁሉም ክልሎች በተጎበኙ የፖሊስ ጣቢያዎች እና ማረሚያ ቤቶች የተስተዋለ ሲሆን፣ በኢሰመኮ የ2014 እና በ2015 በጀት ዓመት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታዊ ሪፖርት የተመላከተ እና ኮሚሽኑ በሚያከናውናቸው የምክክር እና የውትወታ ሥራዎች ሁሉ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጉዳይ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የበጀት እጥረቱ ችግር ተጠርጣሪዎችን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት የሚዳርግ ነው። ሆኖም በፖሊስ ጣቢያዎችም ሆነ በማረሚያ ቤቶች የተስተዋሉ ሌሎች ችግሮች መካከል ከተጠርጣሪዎች መብቶች ጥበቃ/መከበር ጋር የተያያዙና አፋጣኝ መፍትሔ ሊሰጣቸው የሚችሉ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ ተላላፊ ሕመም ያለባቸውን ተጠርጣሪዎችን እና ታራሚዎችን በአፋጣኝ

የመለየት እና ከሌሎች ተጠርጣሪዎች በተለየ ቦታ ማቆየት፣ በተመሳሳይ መልኩ የማኅበረ ሥነልቦና ጉዳት ያለባቸውን ወይም በአካል ጉዳተኝነታቸው፣ በአረጋዊነታቸው ወይም በሌላ ምክንያት ልዩ ፍላጎት /እንክብካቤ/ (special needs) ለሚያስፈልጋቸው ተጠርጣሪዎች ከአቅርቦት ጀምሮ ሌሎች አፋጣኝ መፍትሔዎችን ማፈላለግ አንዱ ተጠቃሽ ችግር ነው። ታራሚዎች ወደ ማረሚያ ቤት ሲዛወሩ ከሌሎች ታራሚዎች ጋር ከመገናኘታቸው በፊት መሠረታዊ ምርመራ በማድረግ እንዲሁም በእራሳቸው ወጪ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ለሚፈልጉ ታራሚዎች ይህ የሚፈቀድበት አሠራር መዘርጋትን ጨምሮ በአሠራር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን መለየት እና አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት ይገባል።

6. በኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ክፍል በዝርዝር እንደተመለከተው በትጥቅ ግጭት እና በጦርነት ሳቢያ በደረሰ ጉዳት፣ በአሁኑ ወቅት ባለው ከፍተኛ የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ ቁጥር፣ ቀደም ሲል ምርታማ የነበሩ አካባቢዎች ምርት በማቋረጣቸው፣ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት በአጠቃላይ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦቱ ላይ ባደረሰው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት በዘንድሮ በጀት ዓመት ሰብአዊ ድጋፍ ፈላጊ የሆነው የማኅበረሰብ ክፍል ብዛት ከእ2015 በጀት ዓመት አንጻርም እጅግ ጨምሯል። በተለይም የትጥቅ ግጭቶች በአማራ ክልልና በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በዘንድሮ በጀት ዓመትም የቀጠሉና ብሎም የተስፋፉ በመሆናቸው ሳቢያ ምርታማ አካባቢዎች መልሶ መቋቋምና ማገገም አልቻሉም። ይህም በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ሁኔታ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ከሌሎች ከፋይናንስና በጀት እጥረት እንዲሁም ከመልሶ ማቋቋም ሥራ መጓተቶችና አለመጀመር ጋር ከመሳሰሉ ችግሮች ጋር ተዳምሮ በጤና አገልግሎት አቅርቦት እንዲሁም በትምህርት የማግኘት መብት ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ በዋነኛነት ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ችግሮች በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች እና በአረጋውያን ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖና ጉዳት በይበልጥ የሚጨምር ነው። በዚህም ሳቢያ የእነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች መብቶች በሚመለከቱት የዚህ ሪፖርት ክፍሎች በዝርዝር እንደተመለከተው የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በዘላቂነት ሊያሻሽሉ ከሚችሉ የሕግ፣ የፖሊሲ፣ የአሠራርና ሂደት መቀረጽና የበጀትና የሰው ኃይል አቅም ሥራዎች እንዳይሠሩ አልያም እንዲጓተቱ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ቀደም ሲል ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራበት በቆዩና እንደጎጂና ልማዳዊ ድርጊቶችና የተለያዩ ወረርሽኞች መከላከል ሥራም እንዲስተጓጎሉ፣ ብሎም የተገኙ ውጤቶች ወደኋላ እንዲመለሱ እያደረገ መሆኑ የሚያመላክቱ መረጃዎች ከተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጭምር እየወጡ ነው። ይህም በእጅጉ አሳሳቢና ሁሉንም የሚመለከታቸውን የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

7. ኢሰመኮ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ይፋ ባደረገው ሁለተኛው ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በማለት ካመላከታቸው አንኳር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች መካከል በሀገር አቀፍ ደረጃ የቅድመ ማስጠንቀቅያና የዝግጁነት መዋቅር፣ አቅምን፣ አሠራርና ሂደቶችን ማጠናከርና ማጎልበት የሚሉትና በተለይም በአዲስ መልኩ በተዋቀሩ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች እልባት ባላገኙ የአስተዳደር ወይም የመዋቀር ጥያቄዎች በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኙና በማናቸውም ሁኔታ ወደ ግጭትና የሰው ሕይወት መጥፋት እንዳያመሩ መከላከል የሚሉት ይገኙበታል። እነዚህ ጉዳዮች አሁንም የሚመለከታቸውን የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው።

8. ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት በሕግ እና በፖሊሲ ቀረጻዎችና እስኪጸድቁ ድረስ ባለው ሂደት ድረስ ሁሉ የመካተት እና ትርጉም ባለው መልኩ የመሳተፍ መብትን የሚያካትት ነው። ባለድርሻ አካላትን (በተለይም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ

የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ የሲቪክ ማኅበራትን እና ሌሎች ስብስቦችና አደረጃጀቶችን) በበቂ ሁኔታና ትርጉም ባለው መልኩ መንግሥት በሚወስዳቸው እርምጃዎችም ሆነ በሚቀርጻቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች ሂደት ማሳተፍ በአስፈጻሚው አካል የተጣለ ግዴታ ከመሆኑም በተጨማሪ በባለድርሻ አካላት ላይ የባለቤትነት ስሜት የሚፈጥርና የተወሰደውን እርምጃ ውጤታማነትን ወይም ተፈጻሚነትን የሚጨምር ነው፡፡ በቂ የምክክርና የምክረ ሐሳብ ማሰባሰቢያ ጊዜ ሳይሰጥ በመቅረቱ ወይም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ባለመካተታቸው፣ አልያም የተዘጋጁ መድረኮች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማድረግ አመቺ ባለመሆናቸው፣ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ያለ በቂ ምክንያት ሳይካተቱ በመቅረታቸው ወይም እጅግ በተፋጠነ ሂደት የሚወሰዱ እርምጃዎች ወይም ሌሎች ሂደቶች በሀገራዊ ጉዳዮች የመሳተፍ መብት እንዲጣስ/እንዲተላለፍ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ስለሆነም በተለይም በሰብአዊ መብቶች ላይ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ የሕግ እና የፖሊሲ ሂደቶች ላይ በቂና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚያካትት የምክክር እና የማሳተፍ አስፈላጊነትን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ እንዲኖርና እንዲተገበር ማድረግ ይገባል፡፡

WWW.EHRC.ORG



# ክፍል ፲

Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Tsegaye Melkamu

# አባሪ 1፡ የሕግ ማዕቀፍ እና አጠቃላይ ማብራሪያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/14 መሠረት ነጻ እና ገለልተኛ የፌዴራል ተቋም ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመ እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ፣ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው፡፡ የተቋቋመባቸውት ዋና ዋና ዓላማዎቹም የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፣ ሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ መጠበቅ/መከታተል እና ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ እንዲሁም ሰብአዊ መብቶቹ ተጥሰው ሲገኙ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ናቸው፡፡

ኢሰመኮ ሥራውን በአግባቡ ለማከናወን እና ተደራሽነቱን ለማስፋት እንዲያስችለው የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች፣ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች እና የፍልሰተኞች መብቶች፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋዊያን መብቶች፣ የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች፣ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት፣ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ፣ የሴቶች እና ሕፃናት መብቶች የሥራ ዘርፎችን የሚመሩ የሥራ ክፍሎች አሉት፡፡ በተጨማሪም የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ፣ የሀብት አስተዳደር፣ የታለንት እና የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የአጋርነት እና የፕሮግራም ዕቅድ፣ የፋይናንስ እና ጠቅላላ አገልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ፣ የሚድያና የኮሙኒኬሽን፣ የሕግና የፖሊሲ ሥራ ክፍሎች እና የዋና ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ኢሰመኮ በአዲስ አበባ ከሚገኘው ዋና ቢሮ በተጨማሪ በባሕር ዳር፣ በሰመራ፣ በጅማ፣ በጅግጅጋ፣ በሃዋሳ፣ በአሶሳ እና በጋምቤላ ከተሞች ጽሕፈት ቤቶች ያሉት ሲሆን፣ በመቀሌ ከተማ ጽሕፈት ቤቱ በአዲስና በተሟላ መልኩ ሥራ እስኪጀምር ድረስ በክልሉ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚከታተሉ በመቀሌ እና በአዲስ አበባ ከተሞች የሚገኙ ባለሞያዎች አሉት፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም. ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ሲሆን፣ በልዩ ልዩ የኢሰመኮ የሥራ ዘርፎች እና ጽ/ቤቶች አማካኝነት በተሰበሰበ መረጃ መሠረት ባለፉት አሥራ አንድ ወራት የነበረውን ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚዳስስ ነው፡፡ ሪፖርቱ ኢሰመኮ በሚንቀሳቀስባቸው የሥራ ዘርፎች የተስተዋሉ ዋና ዋና ቁልፍ እመርታዎችን፣ አሳሳቢ ጉዳዮችን፣ እንዲሁም አንኳር ምክረ-ሐሳቦችን በዝርዝር አቅርቧል፡፡ ሆኖም ይህ ሪፖርት ኢትዮጵያ ባለፉት ወራት የነበረችበትን ጥቅል ሁኔታ የሚያሳይ እንጂ የተከሰቱ የመብት ጥሰቶችን ዝርዝር፣ ብዛት፣ እና ዓይነት ሙሉ በሙሉ የሚያስረዳ አይደለም፡፡

## የሕግ ማዕቀፍ

ይህ ሪፖርት የተዘጋጀው ኢሰመኮን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) መሠረት ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 19/ ንዑስ አንቀጽ 2/ሰ መሠረት ዋና ኮሚሽነሩ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ እና የኮሚሽኑን የሥራ አካሄድ አስመልክቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይጠይቃል፡፡ ኢሰመኮ መደበኛ ሪፖርቶችን ማቅረብ እና አሠራሩን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ እንዳለበት ከላይ የተጠቀሰው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ በአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ይህን ኃላፊነት ከሚያሳካባቸው መንገዶች አንዱ ኢትዮጵያ በበጀት ዓመቱ ከሰብአዊ መብቶች አኳያ የነበረችበትን ሁኔታ የሚዳስስ ዓመታዊ ሪፖርቱን ተጠሪነቱ በቀጥታ ለሕዝብ ለሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ነው፡፡ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ. በ1993 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀው እና የብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት

መርሖች ስብስብ (በአጭሩ የፓሪስ መርሖች ተብሎ የሚጠራው)፣ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ለመንግሥት፣ ለፓርላማ እንዲሁም ለሌሎች አካላት አስተያየቶችን፣ ምክረ ሐሳቦች እና ሪፖርቶችን የማቅረብ አጠቃላይ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡

በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የሰዎች መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች አከባበር ሁኔታ፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የክትትል እና ቁጥጥር ሥራ ከሚያደርግባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑን የምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነምግባር ደንብ ቁጥር 3/2006 በአንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 1/ ለ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 16 እንደተቀመጠው የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ሊያስቆምና ሊቆጣጠር ባልቻለ ክልል ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ የክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎች ሊያከናውን እንደሚችል ከላይ የተጠቀሰው ደንብ ይደነግጋል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እነዚህን የቁጥጥር እና የክትትል ሥራዎች ለማከናወን ያግዘው ዘንድ እንደ ኢሰመኮ ያሉ በሕግ መሠረት በቀጥታ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ ከሚገባቸው መንግሥታዊ አካላት፤ በዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን፣ የተገኙ ውጤቶችን፣ ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን፣ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚያካትት ይዘት ያለው ሪፖርት ይቀበላል፡፡[12]

ስለዚህም ኢሰመኮ ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎችን፣ ደንቦችን እና ዓለም አቀፍ መርሖችን ተከትሎ ይህንን ሪፖርት አዘጋጅቷል፡፡ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች፣ በዋነኛነትም የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫ፣ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (ICCPR)፣ የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊ እና የባህላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (ICESCR)፡ የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር (ACHPR)፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት (CEDAW)፣ የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (Maputo Protocol) አድሎአዊ የዘር ልዩነቶችን ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ የማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፤ ኢ-ሰብአዊ የሆነና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት(CAT)፣ የሕፃናት መብቶች ስምምነት (CRC)፣ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ቻርተር (CRPD)፣ ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት፣ የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል፣ የአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገው የአፍሪካ ሕብረት ስምምነት (ካምፓላ ስምምነት) እና የዓለም-አቀፍ የተለምዶ ሕግ (International Customary Law)፣ እንዲሁም የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥትን ጨምሮ አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች የተደነገጉ የሰብአዊ መብቶችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሪፖርት ነው፡፡ የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ማካተትን በሚመለከት የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የሰብአዊ መብቶች መርኃ-ግብር (World Programme for Human Rights Education, (2005- ongoing)) ፤ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶችን ትምህርት አፈጻጸምን ለመከታተል የተዘጋጀው የመከታተያ ዘዴ (the SDG 4.7 / Human Rights Education Monitoring Tool) ከሚያስቀምጧቸው የትግበራና የመከታተያ አመላካቾች አንጻር በመዳሰስ መረጃዎች ተካትተዋል፡፡

## ሥነ-ዘዴ

ሪፖርቱ ላይ የተካተቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ኢሰመኮ የሚጠቀምባቸው የማስረጃ ማሰባሰብ መሳርያዎችም ከባለመብቶች፣ከተጎጅዎች፣ከዓይን እማኞች፣ከታራሚዎች እና ከተጠርጣሪዎች ወይም አቤቱታ አቅራቢዎች እና ቁልፍ የመረጃ ምንጮች ከሆኑ እንደ ሀገር ሽማግሌዎች፣ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ ሠራተኞች እና ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር

[12] ደንብ ቁጥር 3/2006 አንቀጽ 76 ንዑስ አንቀጽ 1/ሠ እና አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 ይመልከቱ፡፡

ቃለ መጠይቆችን ማካሄድ፣ የአካል ምልከታ ማድረግ፣ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ፣ እንዲሁም ከሚመለከታቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ ከመንግሥት ባለድርሻ አካላት ጋር የቡድን ውይይቶችን ማካሄድ፤ ሰነዶችን መሰብሰብና መመርመር፣ በፍርድ ቤት እና መሰል የፍትሕ ተቋማት የተሰጡ ውሳኔዎችን መመርመርና እንደ አስፈላጊነቱ ጥናቶች ማካሄድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ከተለያዩ ሀገራት ተሰደው ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ተጠልለው የሚገኙ ስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች፣ ከፍተኛ ድርቅ የተከሰተባቸው አካባቢዎች እና ፖሊስ ጣቢያዎች፣ ማረሚያ ቤቶችን እና ሌሎች ማቆያ ስፍራዎችን የመስክ ምልከታ እና ክትትል ከሚደረገባቸው ሥፍራዎች መካከል ናቸው።

ኢሰመኮ ምርመራውን ባካሄደበት እንዲሁም ማስረጃዎችን በሰበሰበበት እና በመዘነበት ወቅት በገለልተኝነት፣ ግልጽነት፣ ታማኝነት መርሖች እና በስትራቴጂ እቅዱ 2014_2018 ዓ.ም. በተዘረዘሩት እሴቶች እና መመሪያዎች በመመራት ሲሆን፣ ለኮሚሽኑ የመረጃ ምንጭ የነበሩትን ምስክሮች እና ተጎጂዎች በመለየት እና መረጃ በመሰብሰብ ሂደት ሚስጥራዊነትን፣ የምስክሮች ደኅንነት ጥበቃን እና ለተጨማሪ ጉዳት አለማጋለጥ መርሕን ተከትሏል።

ኢሰመኮ በዚህ ሪፖርት ያካተታቸው መረጃዎችና ግኝቶች የማስረጃ ምዘና ደረጃቸው በተመሳሳይ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና በዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራዎች እንዲሁም በዓለም አቀፍ አጣሪ ኮሚሽኖች ወይም እውነት አፈላላጊ አካላት ጥቅም ላይ የሚውለውን “ምክንያታዊ አሳማኝነት” (reasonable grounds to believe) ተብሎ የሚታወቀውን የማስረጃ ምዘና መስፈርት ነው። ሪፖርቱ ያካተታቸው መረጃዎች ቢያንስ አንድ ተዓማኒነት ካለው የመጀመርያ ደረጃ መረጃ ምንጭ እና ተጨማሪ ገለልተኛ እና ተዓማኒነት ካላቸው ምንጮች የተረጋገጡ ናቸው።

## የመረጃ አሰባሰብ ሥነ-ዘዴ ውስንነቶች

በተገባደደው በጀት ዓመት ካጋጠሙ ተግዳሮቶች መካከል በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ የትጥቅ ግጭቶች እና የጸጥታ መደፍረሶች ሳቢያ ኢሰመኮ እንደአስፈላጊነቱ ተንቀሳቅሶ ሥራውን ማከናወን ባለመቻሉ በሁሉም የሀገሪቷ ክፍሎች ያሉትን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ መመርመርና መከታተል እንዳይችል ማድረጉ ነው። ከሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ተፈጻሚ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ቁጥር 6/2015 የኢሰመኮ መደበኛ በሆኑና መደበኛ ያልሆኑ የተጠርጣሪዎች እና የታራሚዎች ማቆያ ቦታዎችን ክትትል ሥራውን አዳጋች አድርጎት ቆይቷል። በዚህ ረገድ መንግሥታዊ አካላት የኮሚሽኑን ተደራሽነት የሚያቀላጥፍ በቂ ትብብር አለማድረጋቸው የኮሚሽኑ የምርመራና ክትትል ሥራ ላይ ተጽዕኖ ካመጡ ምክኒያቶች ውስጥ ይጠቀሳል።

በተጨማሪም ኢሰመኮ በተጣለበት ኃላፊነት ልክ ሥራዎቹን ለመከወን የሰው ኃይል እና የፋይናንስ ውስንነቶች በ2016 በጀት ዓመት በተወሰነ መልኩ ቀጥሏል። ኢሰመኮ ጽሕፈት ቤቶች በሌለው ወይም በሌላ ምክንያት በአካል ተደራች መሆን ባልቻለባቸው አካባቢዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው አሠራር መሠረት በርቀት የሚከታተል እና የሚመረምር መሆኑን የቀጠለ ቢሆንም፣ ከእነዚህ አካባቢዎች የሚሰበሰውን መረጃና ማስረጃ ውሱን እንዲሆን አስገድዷል።

# አባሪ 2፡

## ኢሰመኮ ከ 2012 እስከ 2016 ዓ.ም. ያስመዘገባቸው ውጤቶች አጭር ገለጻ

**ራዕይ**

- ሰብአዊ መብቶች ባሕል የሆኑባት ኢትዮጵያ

**ተልዕኮ**

- ሰብአዊ መብቶች ለሁሉም ሰዎች እንዲስፋፉ እና እንዲጠበቁ ማስቻል

**እሴቶች**

- በእኩልነት፣ በሰብአዊ ክብር እና በፍትሕ ላይ በመመሥረት የኮሚሽኑ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው ፡-
    - ተቋማዊ ነጻነት፣ አካታችነት፣ ከተጎጂዎች/ለጉዳት ተጋላጭ ከሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር የቆመ፣ እውነትን የያዘ እና በሥነ-ምግባር የታነጸ፣
    - በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ሰብአዊ መብቶች ሰነዶች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግጋት መመራት፤
    - ብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና ሰብአዊ መብቶች ላይ በተለይ የሚሠሩ ተቋማትን የአጋር ደረጃ ለመስጠት እ.ኤ.አ. በ2017 በአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የወጣ የአቋም መግለጫ (ACHPR/Res.370(LX)2017) እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ሁኔታን በሚመለከቱ መርሖች (የፓሪስ መርሖች) ማዕቀፎች ውስጥ መንቀሳቀስ።

**ተቋማዊ ነጻነትን እና ዐቅምን ማረጋገጥ**

- ሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም. የዶ/ር ዳንኤል በቀለ በኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነርነት መሾም፣
- ኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶችን ግንዛቤ የማስፋፋት፣ የማስጠበቅ እና የማስከበር ሥራ በተሟላ መንገድ እንዲያከናውን እና የማስፈጸም ዐቅሙን ለማሳደግ እንዲያስችለው የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 201/1992 ማሻሻል (አዋጅ ቁጥር 1224/ 2012) እና ኢሰመኮ ዓለም አቀፍ የብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት መስፈርቶች (Paris Principles for Human Rights) ሊያሟሏቸው የሚገቡትን መስፈርቶች ያካተተ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው አድርጓል። ዋና ዋና ይዘቶች፡-
    - በምርጫ ወቅት የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅን ክትትል የማድረግ፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መርማሪ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ስለሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ሁኔታ ክትትል እንዲያደርግ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውንም ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች ወይም በቁጥጥር ወይም በእገታ ሥር የሚገኙ ሰዎች ያሉበትን ስፍራ እንዲሁም እንደ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መጠለያ ጣቢያ፣ የገበያ ማዕከል የመሳሰሉ እና የሕዝባዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ያለ ቅድመ ማስታወቂያ እንዲጎበኝ እና ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን እንዲያከናውን፤
    - ኮሚሽነሮች በክልል ጽሕፈት ቤት ሳይሆን በዘርፍ እንዲሆኑና፣ ቀደም ሲል ከነበሩት ሦስት ኮሚሽነሮች (1 ዋና ኮሚሽነር፣ 1 ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና 1

የሕፃናት እና የሴቶች መብቶች ኮሚሽነር ) በተጨማሪ ሌሎች ከአራት ያላነሱ የልዩ ልዩ ሰብአዊ መብቶች ዘርፍ ጉዳዮችን የሚመሩ ኮሚሽነሮች እንዲኖሩት፤

- ካሉት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በተጨማሪ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ወይም እንደሁኔታው መለስተኛ የኮሚሽኑ ማዕከሎች ሊኖሩት እንዲችል፤
- ገለልተኛነታቸውና ብቃታቸው የተረጋገጠ፣ እንደ አግባብነቱ በአዋጁ አንቀጽ 12 ሥር የተዘረዘሩትን ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ እንዲሁም ግልጽና አሳታፊ የኮሚሽነሮች ሹመት ሂደት መዘርጋት፤
- ብቃትና የትምህርት ዝግጅት ላይ መሠረት ያደረገ ነጻ የባለሙያዎች ቅጥር እንዲፈጽም፣ የውስጥ አደረጃጀትና መዋቅር እንዲሠራና ኃላፊዎችን እንዲመድብ፣ የሰው ሀብት፣ የንብረትና የፋይናንስ አስተዳደር ዝርዝር መመሪያ የማውጣት ሥራ እንዲሠራ እንዲሁም ከመንግሥት በየዓመቱ ከሚመደብለት በተጨማሪ ከሌሎች ምንጮች ሀብት ማሰባሰብ እንዲችል፣

- በዚህም የሕግ ማዕቀፍ መሠረት ኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች አያያዝን ከመከታተል፣ ከመመርመርና ከማስፋፋት ተልዕኮው ጎን ለጎን የተቋማዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ፡-

  - ሁሉንም የኢሰመኮን ሠራተኞች ያሳተፈ ተቋማዊ የዐቅም እና የሰው ሀብት ዳሰሳ እና ጥናት ማድረግ፣ በዚህም 17 የሚሆኑ ዋና ዋና ክፍተቶች የተለዩ ሲሆን እነዚህን ክፍተቶች ለመቅረፍ በጥናቱ የተካተቱ ምክረ ሐሳቦችን መፈጸም፣
  - ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- አዲስ ተቋማዊ መዋቅር መቅረጽ እና በዚሁም መዋቅር መሠረት የሰው ሀብት ፖሊሲና የአሠራር መመሪያ፣ አዲስ የሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም አስተዳደር እና ሥርዓት ዘርግቶ መተግበር፣
  - የተቋሙን የበጀት ነጻነት ማረጋገጥ የሚያስችል የፋይናንስ እና አስተዳደር ማጽደቅ እና መተግበር፣ በዚሁም መሠረት ለተቋማዊ ለውጡም ሆነ የኢሰመኮን ተልዕኮ ማሳካት የሚያስችል ሀብት ማሰባሰብ እና ቀልጣፋ አሠራር መዘርጋት፣

- በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም. የምክትል ዋና ኮሚሽነር እንዲሁም የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ኮሚሽነር፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ደግሞ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ኮሚሽነር እና የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ኮሚሽነሮች መሾም፤
- ከሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገውን የኢሰመኮን የ5 ዓመት የስትራቴጂ እቅድ አሳታፊ በሆነ መልኩ መቅረጽ፣ ማወያየት እና ማጽደቅ፤
- የተሻለ ተደራሽነት፡-

  - የኢሰመኮን ዋና ቢሮ በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትም ሆነ በሌሎች አማራጮች በቀላሉ መድረስ በሚቻልበት፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለአረጋውያን ተደራሽ በሆነ እና በቀላሉ ለሕዝብ ሊታይ በሚቻልበት ቦታ እንዲሆን ማስቻል፣
  - በነጻ የስልክ መስመር (7307) ወይም በማንኛውም መንገድ ኢሰመኮን ማግኘት እንዲቻል የዲጂታል ተደራሽነቱን ማሻሻል (የተሟላ የድረገጽ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች እና የስልክ አገልግሎት እንዲኖሩት ማስቻል፣
  - በአሶሳ፣ በጋምቤላ፣ በጅግጅጋ፣ በጅማ፣ በሃዋሳ እና በሰመራ የሚገኙ የከተማ ጽሕፈት ቤቶቹን ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል፣
  - የሚዲያ እና የኮሙኒኬሽን አገልግሎቱን ለመገናኛ ብዙኃን እና ለማንኛውም ተደራሽ እንዲሆን የሚያስችል የሥራ ክፍል በአዲስ መልኩ ማዋቀር እና ግልጽ የሆነ አሠራር እንዲኖረው ማድረግ፣ እንዲሁም ኢሰመኮ ለሕዝብ ይፋ

የሚያደርጋቸው ሪፖርቶች እና ሰነዶች ለማንኛውም ሰው በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል፣

## ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ ዕውቅና

- በታኅሣሥ ወር 2014 ዓ.ም. ኢሰመኮ ከጠንካራ የግምገማ ሂደት በኋላ የሚሰጠውን የዓለም አቀፉ የብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጥምረት (Global Alliance of National Human Rights Institutions (GANHRI)) የደረጃ "A" Status Accreditation (አንደኛ ደረጃ) ዕውቅና ማግኘቱ ኮሚሽኑ የፓሪስ መርሖችን ሙሉ በሙሉ ማሟላቱን የሚያረጋግጥ ሲሆን ጥምረቱ ኮሚሽኑ በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም የሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ እና ለማስፋፋት እየተጫወተ ያለውን ሚና አድንቆ፣ በተለይም ኢሰመኮ በ2006 ዓ.ም. ተመሳሳይ ግምገማ በተደረገበት ወቅት በጥምረቱ ተለይተው የነበሩ ጉድለቶችን ለማስተካከል ያደረገውን ጥረት አመስግኗል። ኢሰመኮ ወደዚህ ደረጃ መሸጋገሩ በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት እና በሥሩ በሚገኙ ተቋማት ውስጥ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት የጠቅላላ ጉባኤ አካላት ውስጥ ነጻ ተሳትፎ እንዲኖረው ያስቻለ ከመሆኑም ባሻገር፣ በዓለም አቀፉ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ጥምረት (GANHRI) ውስጥ አባል ለመሆን፣ ድምጽ ለመስጠት እና የአመራር ቦታዎችን ለመያዝ ብቁ ያደርገዋል።
- ይህንን ተከትሎ በሚያዝያ ወር 2014 ዓ.ም. ኢሰመኮ በአፍሪካ የሴቶች እና ሕፃናት መብቶች ሙያዊ ኮሚቴ የተባባሪ አባልነት ደረጃ (affiliate status) የተሰጠው ሲሆን፣ ይህ ደረጃ ኢሰመኮ በኮሜቴው ውስጥ የሚያደርገውን እና ከኮሚቴው ጋር የሚሠራውን ሥራ የሚያጠናክር ነው።

## የኢሰመኮ ተደራሽነት

አዲስ አበባ፣ አሶሳ፣ ጋምቤላ፣ ሃዋሳ፣ ጅግጅጋ፣ ጅማ፣ መቀሌ፣ ሰመራ በሚገኙ የከተማ ጽሕፈት ቤቶቹ አማካኝነት ለሕዝብ አገልግሎቶቹን እየሰጠ ሲሆን፣ በነጻ የስልክ መስመር 7307 በተጨማሪ ተንቀሳቃሽ የአቤቱታ አገልግሎት በመዘርጋት ተደራሽ ያልሆኑ አካባቢዎችን ጋር ባለሙያዎቹን በማጓጓዝ አገልግሎት ይሰጣል።

የኢሰመኮን ተደራሽነት በማስፋት ረገድ አስተዋጽዖ ከሚያደርጉት የኮሚሽነሮች እና የተቋሙ ባለሞያዎች ከመቶ ሺህ በላይ ተከታዮች ያሏቸው የማኅበራዊ ገጾች በተጨማሪ፣ የኢሰመኮ ድረገጽ በዓመት በአማካይ 179,280 ጎብኚዎች፣ በፌስቡክ ገጽ 151,000፣ በኤክስ/ትዊተር ገጽ 156,763፣ በሊንክድኢን ገጽ 17,000 እና በዩቲዩብ 1,110 ተከታዮች አሉት።

## የኢሰመኮ የፕሮግራም መስኮች

1. የሰብአዊ መብቶች ትምህርት
2. የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ
3. የሴቶችና የሕፃናት መብቶች
4. የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን መብቶች
5. የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ፍልሰተኞች መብቶች
6. የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች
7. የኢኮኖሚያዊ እና የማኅበራዊ መብቶች
8. የኮሙኒኬሽን፣ የመረጃና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና አጋርነት
9. ተቋማዊ ሪፎርም እና ዘላቂ ዐቅም ግንባታ ናቸው።

## ቁልፍ ክንዋኔዎች

- **የሰብአዊ መብቶች ትምህርት**
  - ከ2014 ዓ.ም. ጀምሮ በአማካይ በዓመት ለ1306 ሰዎች የሚደርስ እና በየዓመቱ ለተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጥ የሰብአዊ መብቶች የአሰልጣኞች ስልጠና፣
  - ለፖሊስ፣ ለማረሚያ ቤት አስተዳደሮች፣ ለወጣቶች እና ከወጣቶች ጋር ለሚሠሩ ተቋማት፣ ለሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት መሪዎች፤ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶች፣ በስደተኞች መብቶች፣ በአካል ጉዳተኞች መብቶች፣ በሴቶች እና ሕፃናት መብቶች ዙርያ ከሚሰጡ ሥልጠናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ በሆኑ እንደ ሽግግር ፍትሕ ላይ ባሉ ጉዳዮች ላይ ለሲቪክ ማኅበራት ድርጅቶች እና ለኪነጥበብ ባለሙያዎች ጨምሮ ለተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚሰጡ ስልጠናዎች፣
  - የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ ለማካተት የሚከናወኑ ተግባራት እና የውትወታ ሥራ፣ የመማሪያ ሰነዶች ጥናት እና ክለሳ፣ የአስተማሪዎች ስልጠና፣ የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ሥርዓቶች ውስጥ በአግባቡ ለማካተት እና ለማጠናከር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈረሙ፣
  - ለብዙኃኑ ተደራሽ በሆነ መልኩ ወቅታዊ በሆኑ እና ትኩረት በሚሹ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ተሰናድተው ይፋ የተደረጉ 220 ገደማ ማብራሪያዎች፣ የባለሙያ አስተያየቶች፣ አጫጭር ቪድዮዎች እና ሌሎች ሰነዶች፣
  - ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡና ከ80 ያላነሱ ትምህርት ቤቶች የተሳተፉበት ዓመታዊ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰብአዊ መብቶች የምስለ ችሎት (Human Rights Moot Court) ውድድር፣ 4 ዙር ዓመታዊ ውድድሮች በተሳካ መልኩ መካሄዱ፣
  - “ሁሉም ሰብአዊ መብቶች በማናቸውም ጊዜ ለሁሉም” በሚለው የኢሰመኮ መሪ ቃል መሠረት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቀን ለየት ባለ መልኩ እና ታዳጊዎችን እና ወጣቶችን፣ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን እና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር በዕለት ተዕለት ሥራቸው እምብዛም ቀረቤታ ባለመኖራቸው ወይም በሌላ ምክንያት የሰብአዊ መብቶች መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳብ ማወቅ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርግላቸዋል ተብለው የተለዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በልዩ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ እና ትርጉም ባለው መልኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲከበር መደረጉ፣ በዚህም ከ30 በላይ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን ያሳተፈ እና በአጠቃላይ አካላዊ እና የድረገጽ ተደራሽነቱን በየጊዜው በማሻሻል ሦስት ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫሎች በሁሉም የኢሰመኮ ጽሕፈት ቤት በሚገኙባቸው የክልል ከተሞች መዘጋጀት መቻሉ::

- **የሰብአዊ መብቶች ክትትል**
  - በየዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በአማካይ 250 ፖሊስ ጣቢያዎች እና 40 ማረሚያ ቤቶች መጎብኘታቸው፣ በአምስት ዓመት ውስጥ የ1,100 ፖሊስ ጣቢያዎች እና የ230 ገደማ ማረሚያ ቤቶች ሁኔታ እና በተጠርጣሪዎች እና ታራሚዎች አያያዝ ላይ ክትትል ተደርጎ የተገኙ ውጤቶች፣

- ወደ 30 የሚጠጉ የክትትል ሥራ ውጤቶች/ሰነዶች ይፋ መደረጋቸው፤ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች፣ የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶች፣ የስደተኞች መብቶች እና የፖሊስ ጣቢያዎች እና የማረሚያ ቤቶች ሁኔታ ሪፖርቶች፣
- ኢሰመኮ በተሻሻለው መቋቋሚያ አዋጁ ቁጥር 210/2012 አንቀጽ 6(11) መሠረት በ2013 ዓ.ም. የተካሄደውን ጠቅላላ ምርጫ፣ በሲዳማ ክልል እና በቀድሞው ደቡብ ክልል የተደረጉት ሕዝበ ውሳኔዎችን፣ እንዲሁም ጠቅላላ ምርጫ ባልተካሄደባቸው አካባቢዎች የተደረገውን ምርጫ የሰብአዊ መብቶች ክትትል፣
- በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ክትትል ሥራው ኢሰመኮ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚሰጣቸው ምክረ ሐሳቦች እና ከሚያደርገው የውትወታ ሥራ በተጨማሪ የተከናወኑ የማቆያ ቤቶችን ጨምሮ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ሥራዎች፣

- **የሰብአዊ መብቶች ምርመራ**

  - ወደ 8000 የሚጠጉ አቤቱታዎች ተስተናግደው 46% የሚሆኑ በኮሚሽኑ የምርመራ እና የውትወታ ሥራ እልባት የተሰጣቸው፣ 47% የሚጠጉ ከሕግ ምክር እና አስፈላጊ ሲሆን ከድጋፍ ደብዳቤ ጋር ወደሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የተመሩ፣
  - የነጻነት መብታቸውን ያለአግባብ በተነፈጉ ሰዎች ዙሪያ ያሉትን ስልታዊ እና ተደጋጋሚ የመብት ጥሰቶችን ለመለየትና ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ የሆነውን ብሔራዊ ምርመራ /National Inquiry/ ማከናወንና ሪፖርት ማድረግ፣
  - ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች እንዲሁም በተለያዩ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች፣ በስደተኞች፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና በአካል ጉዳተኞች መብቶች ላይ የተከናወኑ 60 የምርመራ ሥራ ውጤቶች/ሰነዶች እና ሪፖርቶች፣ ከእነዚህም መካከል፡-

    - የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል *ምርመራ ሪፖርት*፣
    - ከተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር የምሥራቅ አፍሪካ ጽሕፈት ቤት (UNOHCHR — EARO) ጋር በመሆን ያከናወነው የጣምራ ምርመራ እና ይፋ የተደረገ *ሪፖርት*፣
    - በአፋር እና አማራ ክልሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ የተደረገ ምርመራ *ሪፖርት*።

- **ውትወታ**

  - ኢሰመኮ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ዓመታዊ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ እንዲሁም ለሕዝብ ይፋ መደረግ መጀመሩ፣ በዚህም 2 ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ፣ እንዲሁም 7 በተመረጡ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች (ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ) ላይ ወይም በማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ (በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ በስደተኞች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋውያን) ያተኮሩ ዓመታዊ ሪፖርቶች ይፋ ተደርገዋል፣

- ወቅታዊ በሆኑ እና የረዥም ጊዜ ዕቅድ እና ከፍተኛ ትኩረት ይሻሉ ተብለው በተመረጡ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ በተከናወኑ ጥናቶች ወይም ይፋዊ ምርመራዎች ላይ የተመሠረቱና ይፋ የተደረጉ ከ20 በላይ ሰነዶች እና ሪፖርቶች፣
- ኢሰመኮ በተለያዩ በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ በሚወጡ ሕጎች እና ፖሊሲዎች ላይ፣ ኢትዮጵያ ያላጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እንዲጸድቁ፣ እንዲሁም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ፣ የፍትሕ ሚኒስቴር እና የተለያዩ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ወይም በእራስ ተነሳሽነት በየጊዜው የሚሰጡ የባለሙያ እና የሕግ አስተያየቶች፣
- የክትትል እና የምርመራ ሥራዎች የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች እንዲፈጸሙ ተጨማሪ ግፊት እና ድጋፍ ለማድረግ፣ እንዲሁም የምክረ ሐሳቦችን አፈጻጸም ለመከታተል የተካሄዱ 200 የሚሆኑ መድረኮች፣ በውትወታ ሥራዎቹ አማካኝነት ከተገኙ ውጤቶች መካከል በዋናነት:-

    - ኢሰመኮ ከተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር የምሥራቅ አፍሪካ ጽሕፈት ቤት (UNOHCHR — EARO) ጋር በመሆን ባከናወነው ምርመራ ጣምራ ሪፖርት በተሰጠ ምክረ ሐሳብ መሠረት የሽግግር ፍትሕ ሂደት መጠነ ሰፊ በሆነ መልኩ ለደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ የሚያገረሹ ግጭቶችን በዘላቂነት ለማስቆም እና እልባት ለመስጠት የሚኖረው ከፍተኛ አስተዋጽዖ ተቀባይነት አግኝቶ ይህንኑ በተመለከተ ባለፉት 2 ዓመታት መንግሥት ያከናወናቸው ተግባራት እና የተጀመሩ ሌሎች ሥራዎች፣

- አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች እንዲጸድቁ እና በሀገራዊ የሕግ ማእቀፎች ውስጥ እንዲካተቱ (Domestication) ለማድረግ በተከናወኑ የውትወታ ሥራዎች:-

    - የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1187/2012 የአፍሪካ ሕብረት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍ ስምምነት ወይም የካምፓላ ስምምነት (African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa (Kampala Convention) አህጉራዊ ስምምነት እንዲጸድቅ መደረጉ፤
    - እንደዚሁም የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል (Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Older Persons in Africa) እንዲጸድቅ የተሠሩ ሥራዎች፤

- **ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች**

ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት በሀገር ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ እንዲሁም በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ደረጃ በሰብአዊ መብቶች እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በሚሠሩ የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ ኮሚቴዎች፣ ኮሚሽኖች እና መሰል ተቋማት ጋር የመሥራት፣ አጋርነት የመፍጠር፣ ሪፖርቶች የማቅረብ እና ሌሎች ትብብሮችን የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው:: ይህም በኢሰመኮ መቋቋሚያ አዋጅ ከተዘረዘሩ ተግባራት እና ኃላፊነቶች መካከል የተደነገገ ሲሆን፣ በተለይም ተቋሙ የአንደኛ ደረጃ ዕውቅና ያለው በመሆኑ ይህንን ዓለም አቀፍ ትስስር የመፍጠር ኃላፊነቱን የሚያጠናክረው ነው:: በዚህ ረገድ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ዋነኞቹ፦

- ኢሰመኮን በሀገር አቀፍ ደረጃ በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚሠሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ጋር በየወቅቱ የሚያገናኝ እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይት

የሚያደርግ መድረክ መፈጠሩ፣ ተቋሙ በሚያስተባብራቸው ወይም በሚያዘጋጃቸው የክትትል ሥራዎች ውጤቶችን ማጋሪያ፣ የውትወታ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና መሰል መድረኮች ላይ የድርጅቶች ተወካዮች እንዳግባቡ መሳተፋቸው እና መካተታቸው፣ በተለይም በሰብአዊ መብቶች ትምህርት ረገድ የአሰልጣኞች ስልጠና እና መሰል ስልጠናዎች ተሳታፊዎች እና ተጠቃሚዎች የሲቪክ ማኅበረሰብ እና ሌሎች የማኅበረሰብ አደረጃጀቶች ተወካዮች እንዲሆኑ መደረጋቸው፣

- በአህጉር ደረጃ ኢሰመኮ የአፍሪካ የብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ኅብረት (NANHRI) አባል፣ ንቁ ተሳታፊ መሆኑ እና ዓመታዊ መዋጮውንም በየወቅቱ የሚከፍል እንዲሆን መቻሉ እና ከሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የዋና አስተባባሪ ኮሚቴ (Steering Committee) አባል ሆኖ መመረጡ፣ የአፍሪካ ብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ኅብረቱ በአዲስ አበባ ቢሮ እንዲከፍት ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ ቢሮው በቅርቡ ሥራ የሚጀምር ይሆናል፣ በሌሎች የአፍሪካ ሕብረት የብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎችና መድረኮች መገኘት እና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ ከሌሎች የአህጉሩ ብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ እና የትብብር ግንኙነቶች መፈጠራቸው እና መጠናከራቸው፣
- ኢሰመኮ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ባለሥልጣን (IGAD) አስተባባሪነት የተዋቀረውና የበይነ መንግሥታቱ አባል ሀገራት ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት አባል የሆኑበት ጥምረት ዋና ሰብሳቢ ሆኖ መመረጡ፣
- በአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን (ACHPR) የሚቀርቡ የሰብአዊ መብቶች ሪፖርቶችን በማቅረብ እና የኢሰመኮ ተሳትፎ የሚጠበቅባቸው ስብሰባዎች ሁሉ በመሳተፍ ለሀገራዊ ጉዳዮች እና ለተቋሙ ዕይታና ቅቡልነት አስተዋጽዖ ማድረግ መቻሉ፣
- በዓለም አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማትን የሚያስተባብረው እና የተቋማቱን ሁኔታ ገምግሞ ደረጃ የሚያወጣው ጥምረት (GANHRI) ሙሉ አባል መሆን መቻሉ እና ጥምረቱ በሚያስተባብራቸው መድረኮች እና ጉዳዮች ላይ የተሟላ ተሳትፎ ማድረግ መቻሉ፣ በዚህም በበርካታ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ በተለያየ ወቅት በአቅራቢነት እና በመድረክ አስተባባሪነት መጋበዙ፣
- ኢሰመኮ ደረጃ አንድ ያገኘ ብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋም በመሆኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (UNHRC) ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና ሪፖርት ማቅረብ መቻሉ፣ ኢትዮጵያን የተመለከተ ጉዳዮች ለውይይት በቀረቡበት የተ.መ.ድ. ጉባዔም ሆነ ሌሎች መሰል የተ.መ.ድ. መድረኮች ሪፖርት ማቅረብ እና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ መቻሉ፣
- በተለያዩ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በጽሑፍ እና ሪፖርት አቅራቢነት፣ በአባልነት፣ በአዘጋጅነት፣ በአስተባባሪነት እና በተጋባዥነት ከተሳተፈባቸው በርካታ መድረኮች በተጨማሪ፣ ከ2012 እስከ 2016 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ውስጥ ኢሰመኮ በተለያዩ ዋና ዋና የአፍሪካ እና የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች፣ ኮሚሽኖች እና መሰል መድረኮች 38 የሰብአዊ መብቶች ሪፖርቶች አቅርቧል።

## ዘላቂነትን ማረጋገጥ

- ተቋማዊ ዐቅምን ማጠናከር፡ የኢሰመኮን ወቅታዊ የሀብት፣ የሰው ኃይል፣ የአሠራር እና የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ተደራሽነት የማሻሻሉ ሥራ ቀጣይነት ሊኖረው የሚገባ ነው። ይህንን ለማስቻል በዋነኝነት በየደረጃው ያሉ ኮሚሽነሮች፣ የሥራ ክፍል ዳይሬክተሮች እና የጽሕፈት ቤት ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች እንዳግባቡ ብቁ የሆኑ ተተኪ ባለሞያዎችን በማፍራት እና በማሰልጠን ከፍተኛ

አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። የገንዘብ እና ሌሎች ለተቋሙ ሥራ ውጤታማነት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና አሠራሮችን በተመለከተ፣ ቀዳሚው በተለይም በመንግሥት የሚመደበውን ዓመታዊ በጀት በየጊዜው እንዲሻሻል ማስቻል፣ ሌሎች የገንዘብ ምንጮችን ማስፋት እና ኢሰመኮ የእራሱ የገቢ ምንጮች እንዲኖሩት ማድረግ በቀጣይነት የሚደረጉ ጥረቶች ይሆናሉ። ኢሰመኮ በሁሉም ክልሎች እና አካባቢዎች አካላዊ እና ዲጂታል ተደራሽነት እንዲኖረው የሚከናወኑ ሥራዎችም ተጠናክረው የሚቀጥሉ ናቸው።

- የኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች ሥራዎች ለሀገራዊው ወቅታዊ ሁኔታ ተመጣጣኝ የሆነ፣ አስፈላጊና አዎንታዊ አስተዋጽዖ ሆኖ እንዲቀጥል የሚደረገው ጥረት የማያቋርጥ ነው። በተለይም በ2016 ዓ.ም. በጸደቀው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መሠረት ትግበራው የሚጀመረው እና እንዲሁም የብሔራዊ ምክክር ሂደት በሀገር አቀፍ ደረጃ እና ለበርካታ ዓመታት የሚካሄዱ ሂደቶች እንደመሆናቸው እና ብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ሂደቶቹን በመከታተልና በሌሎች ተግባራት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ እንደመሆኑ፣ ኢሰመኮ እስካሁን ካከናወናቸው ተግባራት በተጨማሪ ይህንኑ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለውን ዝግጅት በማድረግ ላይ ነው።

# አባሪ 3፡ የምስል ምንጮች

በየዓመቱ ታኅሣሥ 1 ቀን የሚውለውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቀን ለማሰብ እና የዕለቱ ዓላማ በተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች የሰብአዊ መብቶችን ለተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ማስፋፋት እንደመሆኑ፣ ኢሰመኮ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት እና በሁሉም የከተማ ጽሕፈት ቤቶች በሚገኙበት ቦታ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል አዘጋጅቷል፡፡

ታኅሣሥ 1 ቀን 2016 ዓ.ም. በተካሄደው የሰብአዊ መብቶች ፌስቲቫል ቀደም ሲል ከተካሄዱት ለየት ባለ መልኩ የፎቶግራፍ እና የአጫጭር ፊልሞች ውድድር በማካተት አሸናፊ ሥራዎችን በፊልም ፌስቲቫሉ እለት ተሸልመዋል፡፡ የፎቶግራፍ ውድድሩ በ2015 በጀት ዓመት አሳሳቢ ጉዳይ ተብሎ ከተለዩ የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች መካከል በሆነው በቂ የሆነ መኖሪያ ቤት ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ የአጫጭር ፊልሞች ውድድሩ ደግሞ በሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዘርፍ አሁንም አሳሳቢ ሆነው ከቀጠለው በሕይወት የመኖር መብት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

እነዚህ በዘንድሮ በጀት ዓመት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ላይ የሽፋን እና የክፍል መለያ ገጾች ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ ምስሎች ለ3ተኛው የኢሰመኮ ፊልም ፌስቲቫል የፎቶግራፍ ውድድር ከቀረቡ ምስሎች የተውጣጡ ሲሆን፣ ሥራዎቹን ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት እንዲውሉ ፈቃዳቸውን ለሰጡ ተወዳዳሪዎች በሙሉ ኢሰመኮ ምስጋና ያቀርባል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የዋና ገጽ ሽፋን ምስል፦ ውበት ጌታቸው | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Wubet Getachew |
| 2. | የክፍል አንድ ምስል፦ ገመቹ ፍቃዱ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Gemechu Fikadu |
| 3. | የክፍል ሁለት ምስል፦ በረከት ብርሃኑ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Bereket Berhanu |
| 4. | በሕይወት የመኖር መብት ክፍል ምስል፡ ቅዱስ ኤርሚያስ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Kidus Ermias |
| 5. | ከአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 6/2015 ጋር አተገባበር ጋር የተያያዘ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክፍል ምስል፦ መቅደላዊት አሰፋ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Meqdelawit Assefa |
| 6. | የነጻነት እና የፖለቲካ መብቶች ክፍል ምስል፦ ሰአዳ ሙሳ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Sa'ada Mussa |
| 7. | በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች አያያዝ ክፍል ምስል፦ ሙሴ ተወልደ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Mussie Tewolde |
| 8. | ለኢሰመኮ የቀረቡ አቤቱታዎች ክፍል ምስል፦ ኤርሚያስ ጌታሁን | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Erimias Getahun |
| 9. | ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ክፍል ምስል፦ ሕይወት ታደሰ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Hiwot Taddesse |
| 10. | የሴቶች እና ሕፃናት መብቶች ክፍል ምስል፦ ፍሬሕይወት ግዛው | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Firehiwot Gizaw |
| 11. | አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ክፍል ምስል፦ ናሆም ግርማ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Nahom Girma |
| 12. | የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች፦ ያቆብ በለጠ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Yakob Belete |
| 13. | ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች ከመወጣት አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ክፍል ምስል፦ አማኑኤል ነገሶ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Amanuel Negeso |
| 14. | ምክረ ሐሳቦች እና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ክፍል ምስል፦ ኤርሚያስ ደጀኔ | Photo credit: EHRC/AHRFF submission/2016/Ermias Dejene |